# የመጽሐፍ ፤ ቅዱስ ፤ ትርጓሜ።

# ሮሜ።

## መግቢያ

ክፍል 1- ፍርዱ - ሮሜ 1:1 - 3:20
ክፍል 2 - ጽድቅ - ሮሜ 3:21 - 5:21
ክፍል 3 - ቅድስና - ሮሜ 6:1 - 8:39
ክፍል 4 - የእስራኤል አለመውረስ - ሮሜ 9:1 - 11:36
ክፍል 5 - የክርስቲያን ኑሮ - ሮሜ 12: 1 - 14:23
ክፍል 6 - ሰላምታ፥ ተግሣጽና ቡራኬ - ሮሜ 15:1 - 16:27

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## ትርጓሜ።

ይህ ትርጓሜ የተመሠረተው

በ1948 ዓ.ም. በታተመ አዲስ ኪዳን ላይ ነው።

እንዲሁ ደግሞ መዝሙረ ዳዊት ተጠቅሶ በሚገኝበት ጊዜ ትርጉሙ በ1947 ዓ.ም. ከታረመው መጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ነውና የምዕራፉ (የመዝሙሩ) ቁጥር ከግዕዙ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ ነው። ይህ ሲሆን፥ የዱሮ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ሰው ከመዝ. 10 አንሥቶ እስከ መዝ.. 146 ድረስ በተጠቀሰው የምዕራፉ ተራ ቁጥር ላይ አንድ መጨመር ያስፈልገዋል።

ዳ.እ

ጎንደር

1949 ዓ.ም.

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## መግቢያ

1. «የሐዋርያው ...............................................
2. .............የጳውሎስ .......................................
3. ............................................ መልእክት ......................
4. ........................................................................ ወደ ሮሜ ሰዎች»

## 1. የጸሐፊው ሐዋርያነት

ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያነትን የተቀበለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 12ቱን ሐዋርያት በመረጠ ጊዜ አይደለም። ከ12ቱ አይደለም። (ማር.3፡13-19)። ሐዋርያነትን የተቀበለው ጌታ ካረገ በኋላ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብም ተመረጠ እንጂ በሰው አልተመረጠም። (የሐዋ.9፡6፤ 15፤ 20፤ 21፥ ገላ.1፡1-2፤ 1ኛቆሮ.9፡1-2)።

## 2. የጳውሎስ የሕይወት ታሪክ።

በጌታችን ዘመን ጳውሎስ ገና ልጅ ነበር፥ ለምን? ዲያቆኑ እስጢፋኖስ በተወገረ ጊዜ ጳውሎስ ገና «ጎበዝ» ተብሎአልና። (የሐዋ.7፡58) በዚያን ጊዜ ደግሞ ገና ተማሪ ይሆን ይሆናል፥ ለምን? በኢየሩሳሌም የተገኘው ለትምህርት ነውና። (የሐዋ.22፡3)። ኢየሩሳሌም የትምህርት አገሩ ነው እንጂ የትውልድ አገሩ አይደለም። የተወለደው ዛሬ ቱርክ አገር በሚባለው በዚያን ጊዜ በሮማ ግዛት ውስጥ በነበረው በኪልቅያ አውራጃ በሚገኘው በጠርሴስ ከተማ ነው። (የሐዋ. 22፡3)። ወላጆቹ ዕብራውያን (አይሁድ) ነበሩ፤ ነገር ግን ጳውሎስ የተወለደው በሮማ ግዛት ውስጥ ስለነበረ ሁለት ዜግነት ነበረው፥ 1ኛ ዕብራዊ፤ 2ኛ ሮማዊ። (ፊልጵ.3፡5፥ የሐዋ.22፡25-28)። በሕፃንነቱ፥ ከብንያም ወገን የነበረው፥ ከብንያም ወገን ስለ ነበረ የእስራኤል መጀመርያ ንጉሥ የሆነውን የሳውል ስም ተሰጠው። ሐዋርያ በሆነ ጊዜ ግን ስሙ ተለውጦ ጳውሎስ ተባለ። (የሐዋ.7፡58፤ 9፡4፤ 13፡9)። የአይሁድን ልጆች ለትምህርት ወደ ዋና ከተማቸው ወደ ኢየሩሳሌም መላክ ልማድ ነበርና ዕድሜው ሲፈቅድለት ሳውል ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም ተልኮ ገማልያል

በሚባል ስመ ጥሩ የሕግ መምህር ትምህርቱን ተማረ፥ (የሐዋ.5፡34፤ 22፡3)። ገና በኢየሩሳሌም ሳለ እስጢፋኖስ ወንጌልን ለመስበክ መጣ።

ሲሰብክ ሕዝቡ ተቃወሙት። ሳውልም ከሕዝቡ ጋር ተባብሮ በሚወግሩት መካከል ተገኘ። በመካከላቸው የተገኘበት ምክንያት ግን እርሱ የተማረው ትምህርት ሕግ ወይም ኦሪት ነበርና እስጢፋኖስም ያስተማረው ሕግን የሚነካ ስለ መሰለው ለእግዚርብሔር ሕግ ቀንቶ ነው እንጂ በክፉ አሳብ ተይዞ አይደለም፥ (ገላ.1፡14፤ 1ኛጢሞ. 1፡13)። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በሽተኛ ስለነበረ ድንጋይ አንሥቶ ለመጣል ስላልቻለ የወጋሪዎችን ልብስ መጠበቅን መረጠ፥ (2ኛቆሮ.12፡7፤ ገላ.4፡13-15፤ የሐዋ.7፡58)። ይህን ልብስ ግን እየጠበቀ ሲመለከት የተደረገውን ለማየት የተነገረውንም ለመስማት ስለተመቸው እስጢፋኖስ የሞተበትን ቅን መንፈስ አስተዋለ፤ ስለ ኢየሱስ የተናገረውንም ቃል ሰማ። ይህ የክርስቲያኖች ነገር እንዴት ከሰይጣን ይሆናል? ብሎ ተጠራጥሮ በጥርጥር ተነድፎ በሕሊናው ታውኮ ሰነበተ። ቢሆንም፥ «የክርስቶስ ነገር እንደምን እውነት ይሆናል?» ብሎ ልቡን አጽንቶ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መስሎት፥ ቤተ ክርስቲያንን በማሳደድ በረታ፥ (የሐዋ.8፡3፤ 1ኛጢሞ.1፡13፤ የሐዋ.9፡5፤ 26፡9-11)። ከዕለታት አንድ ቀን ግን ክርስቲያኖችን ለማስያዝ ፈልጎ ደማስቆ ወደሚባል የሶርያ አገር ዋና ከተማ ሲሄድ፥ ገና በመንገድ ላይ ሳለ ጌታ ተገለጠለት። በዚያን ጊዜ ጌታ በእውነት ሕያው መሆኑን ከማስተዋሉ የተነሣ የክርስቲያኖች ስብከት እውነት እንደሆነ ተረዳና በጌታ አመነ። ወደ ከተማም በደረሰ ጊዜ ተጠመቀ፥ (የሐዋ. 9፡1-19)። አሳቡ ሁሉ ስለተመሳቀለበት ይህ ነገር እንዴት አድርጎ እውነት እንደሚሆን ለመመርመር፥ ብሉያትን ከክርስቲያኖች ትምህርት ጋር ለማመዛዘን ብሎ፥ በደማስቆ ከተማ ዙሪያ ወደምትገኝ ወደ አረብ አገር ሄዶ ብቻውን ሶስት ዓመት ተቀመጠ፥ (ገላ.1፡17)። የነገሩን እውነተኝነት ተረድቶ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ በበርናባስ አማካይነት ከሐዋርያት ጋር ተቀላቀለ። አይሁድ ግን ሊገድሉት ስለ ፈለጉ ሐዋርያት ወደ ተወለደበት አገር ወደ ጠርሴስ ሰደዱት፥ (የሐዋ.9፡26-30)።

በእስጢፋኖስ ምክንያት በተነሣው ስደት ምእመናን ወደየአገሩ ተሰደዱ። አንዳንዶችም ወደ ሶርያ ደርሰው አንጾኪያ በሚባል ከተማ ቤተ ክርስቲያንን ተከሉ። ቁጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች ቢጨመሩላቸው መምህራን አስፈላጊ ስለሆኑ ባርናባስ ወደ ጠርሴስ ሄዶ ሳውልን አመጣ፥ (የሐዋ.11፡19-26)። ሳውል በአንጾኪያ ሲያስተምር ሳለ መንፈስ ቅዱስ በውጭ አገር እንዲሰብክ ስለጠራው፥ አንድ ጊዜ ከባርናባስ ጋር፥ አንድ ጊዜ ከሲላስ፥ አንድ ጊዜም ከልዩ ልዩ ወንድሞች ጋር፥ 3 ጊዜ ወጥቶ አስተምሮ ወንጌልን እስከ ግሪክ አገር አደረሰው፥ (የሐዋ.13፡1-14፥28፤ የሐዋ.15፡36-18፤22፤ የሐዋ. 18፡23-21፡17፤ ሮሜ 15፡19)። ከ3ኛው ጉዞ ሲመለስ ምንም በኢየሩሳሌም እሥራትና መከራ እንደሚቆየው ቢያውቅም፥ የመንፈስ ቅዱስ አስገዳጅነት በልቡ ስለ ተሰማው ጨክኖ

ሄደ። ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ሁከት እንዳይነሣ ብለው ሽማግሌዎች በብልሃት ወደ ቤተ መቅደስ እንዲገባ አደረጉ፤ ሕዝቡ ግን አወቁት ከተማውም በሞላ ተሸበረ። ወሬውም ወደ ሮሜ መንግሥት የጭፍራው ሻለቃ ስለ ደረሰ እርሱ ከወታደሮቹ ጋር እየሮጠ ደረሰና ጳውሎስን ከአይሁድ እጅ ነጥቆ አዳነው፥ (የሐዋ.21፡1-36)። ጳውሎስ ቂሣርያ በሚባል ከተማ ሁለት ዓመት ታሥሮ ተቀመጠ፥ (የሐዋ.24፡27)። በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ወደ ቄሣር ይግባኝ አለ። በይግባኙም መሠረት በመርከብ ወደ ሮሜ ተላከ። ከመንገድ መርከቡ አደጋ አግኝቶት ተሰበረ። ነገር ግን ሁሉም ሳይጎዱ ወደ ሮሜ በደኅና ደረሱ፥ (የሐዋ.27፡1-28፥16)። ሁለት ጊዜ በንጉሠ ነገሥት ፊት ቀረበ፥ (2ኛጢሞ.4፡16-17)። አንድ ጊዜ ተፈትቶ ወደ እስጳንያ አገር እንደ ሄደ ይናገራል፤ ይህ አልታወቀም እንጂ እንደገናም ተይዞ ሁለት ዓመት ደግሞ ታሥሮ እንደተቀመጠ ታውቆአል። በዚያን ጊዜም ወደ ኤፌሶን፥ ወደ ፊልጵስዩስ፥ ወደ ቆላስይስ፥ ወደ ፊልሞናም መልእክቶቹን ጻፈ። ሁለተኛ በቄሣር ፊት በቆመ ጊዜ ግን የሞት ፍርድ ተፈረደበት፥ (2ኛጢሞ.4፡5-11)። ስለ አሟሟቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ነገር የለም። ነገር ግን በ65 ዓ.ም. ወይም በ66 ዓ.ም. ከሮሜ ከተማ ወደ ውጭ ተወስዶ «ቪያ አስቲያ» በሚባል መንገድ ላይ ራሱ እንደ ተቆረጠ ይነገራል።

## 3. የመልእክቱ አጻጻፍ

ሀ) ሁኔታው
ለ) አሳቡ
ሐ) ክፍሎቹ
መ) አሳሳቡ
ሠ) ጥቅሙ

ሀ) መልእክቱ የተጻፈው በቆሮንቶስ ከተማ ነው። ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ለድሆች ክርስቲያኖች የሚሆን የገንዘብ መዋጮ በውጭ አሁጉር ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተቀብሎ ያን ሁሉ የገንዘብ እርዳታ ይዞ ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሥቶአል፥ (ሮሜ 15፡25-26)። ጊዜው በ56 ዓ.ም. እና በ58 ዓ.ም. መካከል ነው። ለ3 ጊዜ ነው መንገድ የሄደው በቆሮንቶስም 3 ወር ተቀምጦአል፥ (1ኛቆሮ.16፡1-4፤ 2ኛቆሮ.8፡1-7፤ የሐዋ.22፡2-3)። አሳቡ ጥቂት ቀን በኢየሩሳሌም ከተቀመጠ በኋላ ወደ እስጳንያ ለመሄድ ነበርና፥ ወደዚያም ሲሄድ መንገዱ የግድ በሮሜ በኩል ነውና፥ ከመድረሱ በፊት እርሱ በተለይ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖ ሳለ እስከ አሁን ድረስ ወደ ሮሜ አለመሄዱን ለማስረዳት፥ መምጣቱንም ለማስታወቅና በአፍ ለማስተማር ያልቻለውንም በጽሑፍ ለማስተማር ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክቱን ጻፈ፥ (ሮሜ 1፡9-13፤ 15፡22-29)። መልእክቱን (ወረቀቱን) ተቀብላ ወደ ሮሜ ያደረሰችው

በቆሮንቶስ አቅራቢያ የሚገኝ የክንክራኦስ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነች ፌበን የምትባል ሴት ናት፥ (ሮሜ 16፥1-2)።

ለ) የመልእክቱ አሳብ ጽድቅ ነው፤
አስፈላጊነቱ - (ምዕ.1-3፡20)፥
መገኘቱ - (ምዕ.3፡21-ምዕ.5)፥
ፍሬው - (ምዕ.6-8)፥
አለመቀበሉ - (ምዕ.9-11)፥
ሥራውም - (ምዕ.12-15)።
መጨረሻው ምዕራፍ - (ምዕ. 16) በተለይ ሰላምታ ነው።

የጽድቅን አስፈላጊነት ለማስረዳት ሐዋርያው የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመለክታል፥ (1፡18)። አስፈላጊነቱ፥ ያውም ለዓለም ሰው ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ስለሚገለጥ ነው። ይህ ቁጣ በአሕዛብ ላይ እንደሚመጣ (በምዕ. 1)፥ በአይሁድ ላይም እንደሚመጣ (በምዕ. 2) ስለተነገረን በዓለም ሰው ሁሉ ላይ ቁጣ ይመጣበታል ማለት ነው፥ (ምዕ.3፡1-20)። ስለዚህ ጽድቅ ለዓለም ሰው ሁሉ አስፈላጊ ነው።

ጽድቅ ለሁሉ አስፈላጊ እንደሆነ እንዲሁ ለሚያምኑ ሁሉ ጽድቅ ተገኘ፤ መገኘቱም የእግዚአብሔር ጽድቅ በመገለጡ ነው፤ የምንቀበለውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፥ (3፡21-31)። ይህ ነገር እውነት መሆኑን ለማስረዳት ሐዋርያው የአይሁድ አባት የሆነውን የአብርሃምን ነገር ያነሣል፥ (ምዕ.4)። አብርሃም በእምነቱ እንደጸደቀ እኛም እንዲሁ በእምነት እንጸድቃለን። ይህን በእምነት የምናገኘውን ጽድቅ ስፍሩንና ስፋቱን በምዕ.5 ላይ እናገኛለን። የአዳም አለመታዘዝ ታላቅ የቁጣን ሥራ ከሠራ ይልቅ የክርስቶስ መታዘዝ የበለጠ ሠርቶአል፥ ኃጢአትም ከበዛበት መጠን ይልቅ የጸጋ መጠኑ በልጦአል። እንግዲህ ጽድቅ ተገኘ፥ «ከኃጢአትም ሁሉ የክርስቶስ ጸጋ በለጠ» ተባለ። ታዲያ፥ ሰው አሁን ኃጢአትን ቢሠራ ምን አለበት? ከምዕ.6 እስከ ምዕ.8 ድረስ ይህን ነገር ይመረምራል።

ጽድቅ የደኅንነት መጀመሪያ ነው እንጂ ፍጻሜ አይደለም። ከጽድቅ የቅድስና ፍሬ ይመነጫል። የጸደቅንበት ምክንያት እንድንቀደስ እንድንከበርም ነው። እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ባሰበ ጊዜ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከደረሰበት ጉዳትና ጉድለት ሁሉ አድኖ ወደ ተፈጠረበት መልክና ምሳሌ ሊመልሰው ቆርጦአል። አሳቡ ሰውን ሁለመናውን ከኃጢአት ለማዳን ነው፥ ይኸውም «ከኃጢአት ማዳን ማለት ከኩነኔው ከግዛቱና ከመኖሩ ነፃ ማውጣት ማለት ነው። ይህም ስለሆነ የጸደቀ ሰው ገና በኃጢአት እንዲኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ ከቶ

አይደለም። «በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?» ለሚለው ጥያቄ ጳውሎስ በምዕ.6 «ሉረ ከቶ አይደለም!» ብሎ የጸናውን መልስ ከሰጠ በኋላ፥ በጥምቀት የተመለከተውን ከክርስቶስ ጋር የሆነውን የምእመንን መሞት በማስረዳት ከኃጢአት ፍጹም መለየቱን ገልጦአል። ይህም ለጻደቀ ሰው የሚቻል ነገር ነው። ለምን? ቢባል፥ በመሞቱ ከኃጢአት ግዛት ወጥቶአልና። በሕግ ያላገኘውን ኃይል በጸጋ ይገኛልና። በዱሮ ኑሮአችን የኃጢአት ባሪያዎች ሆነን የኃፍረትን ፍሬ እንደ አፈራን፥ እንዲሁ አሁን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆነን የቅድስናን ፍሬ እናፈራለን። ይህም ተገቢአችን ነው።

በምዕ.6፡14 ላይ «ከሕግ በታች አይደላችሁም» ብሎ ነበርና ጳውሎስ በምዕ.7 የሕግን ነገር ያስረዳል። በባልና ሚስት ምሳሌ አድርጎ ከሕግ ፍጹም መፈታታችንን አስረድቶ ሲያበቃ ሕግ መንፈሳዊ ሲሆን እኛ ሥጋውያን በመሆናችን ሕግ ሊቀድሰን አለመቻሉን አመልክቶአል። ሕግ ያልቻለውን ግን እግዚአብሔር አድርጎአል፥ (ምዕ.8)። የቅድስና መሠረት ክርስቶስ ሲሆን፥ ቅድስናን የምናገኘው እኛ ራሳችን በመንፈስ በመመላለስ፥ በመንፈስ ቅዱስም ሥራ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የክብሩም ወራሾች ያደርገናል። ወደዚያም እንዳንደርስ ሊከለክለን የሚችል የለም።

ሐዋርያው አሁን የጽድቅን ዶክትሪን ትቶ ለጊዜው፥ ከምዕ.9 እስከ ምዕ.11 ድረስ፥ እሥራኤል የተስፋ ቃልን ስለ አለመውረሳቸው ነገር ያነሣል። እነዚህ በምዕ.8 ላይ የተጻፉት ተስፋዎች አስቀድመው ለእስራኤል ተሰጥተው ነበር። የእግዚአብሔር ልጆች እነርሱ ነበሩ፥ የተመረጡትም እነርሱ ነበሩ፥ ርስትን የመውረስ ተስፋ የተሰጣቸው ለእነርሱ ነበረ። አሁን ምን ሆነ? በእነርሱ ፈንታ አሕዛብ የተተኩ ይመስላል። የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአልን? ተስፋውም ቀርቶአልን? የለም! አልተሻረም፥ አልቀረምም! ተስፋው ለጥቂቶች ለተወሰኑት ነው እንጂ ለእስራኤል ሁሉ አልተሰጠም ነበር። ተስፋው የሚሄድበትን መስመር እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ጀምሮ መርጦት ነበር። (ምዕ.9።) እርሱ ለማዳን ሲመርጥ እስራኤል ይወቅሱታልን? ይልቁንም፥ እግዚአብሔር በፍቅር ተከትሎአቸው በማይነገር ዋጋ፥ እርሱም በልጁ ደም፥ ጽድቅን ከገዛ በኋላ ልኮ መገኘቱንም ስላስታወቃቸው፤ እነርሱ ባለመቀበላቸው ይወቀሳሉ! ለምን? ቢባል፥ ጽድቅ የሚገኘው በሥራቸው ሳይሆን በእምነት ስለ ነበረና እነርሱ አናምንም ብለው ሊቀበሉት ስላልወደዱ ነው። ተጠንቅቆ ቢጠራቸው በፍጹም እምቢ አሉ (ምዕ.10።) ጥንት የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ግን ከቶ የሚቀር አይደለምና፥ አሕዛብ እስኪገቡ ድረስ እስራኤል ካለማመናቸው የተነሣ በአንድ ዳር ምንም ቢቀሩ፥ በመጨረሻ ላይ «እስራኤል ሁሉ ይድናል»። (ምዕ.11)

ሐዋርያው ጽድቅ የሚገኘው በእምነት መሆኑን፥ በእስራኤል ዘንድ የእግዚአብሔር ሥራም ቅን መሆኑን በማረጋገጥ የእስራኤል የአለመቀበልን ክፍል ጭርሶ፥ ተመልሶ የጽድቅን ሥራ በማስረዳት ትምህርቱን ቀጥሎአል። ከእምነት

ቀጥሎ ምግባር (መልካም ሥራ) እንዲገባ ታስቦአልና፥ የጸደቀ ሰው እንዴት አድርጎ መመላለስ እንደሚገባ ያስረዳል። ኑሮው በእግዚአብሔር ዘንድ የክርስቶስን መንፈስ የሚመስል (ም. 12)፥ በመንግሥት ዘንድ የፍጹም ታማኝነት (ም. 13)፥ በክርስቲያን ወንድሞችም ዘንድ የፍቅርና የአንድነት (ም. 14) እንዲሆን ያስፈልጋል ይላል። ይህም የፍቅርና የአንድነት አሳብ ወደ ም. 15 ይገባል፥ በዚህ ምዕራፍ ግን የሥራውን አሳብ ደግሞ ከገለጠ በኋላ መልእክቱን ወደ መጨረስ ያደርሰዋል። በም.16 በሮሜ ለነበሩት ሁሉ የእርሱንና ከእርሱ ጋር በቆሮንቶስ የነበሩትን የክርስቲያኖች ሰላምታ እያቀረበ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የፍጹም ደኅንነት መግለጫ የሆነውን መልእክቱን አቁሞአል።

ሐ/ መልዕክቱ በ5 ክፍል ይከፈላል።

1ኛ/ ም.1-3፡20:- የፍርድ ክፍል።

የጽድቅን አስፈላጊነት የሚያስረዳ የእግዚአብሔር አብ ክፍል ነው።

2ኛ/ ም.3፡21-ም.5:- የጽድቅ ክፍል።

የጽድቅን መገኘት የሚያስረዳ የእግዚአብሔር ወልድ ክፍልነው።

3ኛ/ ም.6-8:- የቅድስና ክፍል።
የጽድቅን ፍሬ የሚያስረዳ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስክፍል ነው።

4ኛ/ ም.9-11:- <u>የእስራኤል አለመውረስ ክፍል።</u>
የጽድቅን አለመቀበል የሚያስረዳ የእስራኤል ክፍል ነው።

5ኛ/ ም.12-14:- የክርስትና ኑሮ ክፍል።
የጽድቅን ሥራ የሚያስረዳ የቤተ ክርስቲያን ክፍል ነው።
ም.15 የጳውሎስ የሥራው አሳብ፥
ም.16 ሰላምታ ነው።

ማስገንዘቢያ:- የመልዕክቱ አከፋፈል አብዛኛው 3 3 ምዕራፍ በመሆኑ፥ ሦስቱ ሥላሴዎች በደኅንነታችን ነገር እንዴት በአንድነት እንዳደረጉ ያስታውሰናል።

መ/ የመልዕክት አሳሳብ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ነው :-

1ኛ ክፍል- <u>ፍርድ</u>:-
ም.1 በአሕዛብ ላይ፥
ም.2 በአይሁድ ላይ፥

ምዕ.3፡ 1-20 በዓለም ሁሉ ላይ ይሆናል።

2ኛ ክፍል- ጽድቅ፡-
ምዕ.3 ከ21 መገለጡ፡
ምዕ.4 መቆጠሩ፡
ምዕ.5 መስፋቱ ሲሆን።

3ኛ ክፍል- ቅድስና፡-
ምዕ.6 ተመደበ
ምዕ.7 ታጣ
ምዕ.8 ተገኘ

4ኛ ክፍል- የእስራኤል አለመውረስ፡-
ምዕ. 9 የእግዚአብሔር ምርጫ፥
ምዕ.10 የእስራኤል እምቢታ፥
ምዕ.11 የአሕዛብ መተከል ነው።

5ኛ ክፍል- የክርስቲያን ኑሮ፡-
ምዕ.12 በእግዚአብሔር ዘንድ፥
ምዕ.13 በመንግሥት ዘንድ፥
ምዕ.14 በወንድሞች ዘንድ።
ምዕ.15 የጳውሎስ የሥራው አሳብ ሲሆን
ምዕ.16 ሰላምታ።

ሠ/ የመልዕክቱ ጥቅም ልዩ ልዩ ነው

አንደኛ፥ ከሁሉ አስቀድሞ ለአእምሮና ለመንፈስም ማጎልመሻ ይሆናል። ይህ መልዕክት «ሥጋ» ነው፥ (1ኛቆሮ.3፡ 2፤ ዕብ.5፡ 12-14)። መንፈሳዊ እድገትንም የግድ ያስጨምራል። አሳቡም ክርክሩም ጭፍቅ ያለ (ብዙ ትርጉም ያለው) ነውና እያንዳንዱ ቁጥር ሁሉ ቢመረመር ከሁሉም ጥቅም ይገኝበታል።

ሁለተኛ፥ ቴዎሎጂን (ትምህርተ መለኮት) ለመማር ለሚፈልግ ሰው ዋና ማስተማሪያ ይሆንለታል። ሰው ሁሉ ያመነውን ለምን እንደሚያምንበት፥ ምክንያቱን፥ ማወቅ ይገባዋል። በዚህ መልዕክት ክርስቲያን የሃይማኖቱን መሠረቶች ተገልጠውና ተዘርዝረው ያገኛቸዋል፥ (1ኛጴጥ.3፡ 15)።

ሦስተኛ፥ መልዕክቱ ሰው የሚድንበትን መንገድ አጉልቶ ያሳያል። የኃጢአትን ርኩሰት፥ ኃጢአትም የሚያመጣውን ፍዳ ይገልጥና ኃጢአተኛ ከአምላኩ ጋር ታርቆ ሰላም የሚያገኝበትን መንገድ ያስተምራል። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ የታረቀ ሰው

ተመልሶ ኃጢአትን ሳያዘወትር በቅድስና ለመኖር የሚችልበትን ዘዴ ያስረዳል። ይህ ለሁላችን አስፈላጊ ነው።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ክርስቲያንነቱን የሚገልጥበትን አኳኋን ያሳያል። «ክርስቲያን» መባል ብቻ አይበቃም፥ ለክርስቲያን ሁሉ የተገባ አገባብ አለው። ስለመንግሥት አከባበር፥ ስለ ቀረጥና ግብር አከፋፈል፥ በክርስቲያንና በክርስቲያን መካከል ስላለው ትንንሽ ልዩነት መተጋገሥ፥ ስለ በዓል ቀን አከባበር፥ ስለ መብል ዓይነት፥ ስለዚህ ሁሉ ነገር እናነባለንና ለዛሬ ዘመናችን የሚሆን የመልዕክቱን ጠቃሚነት ሳንገነዘብ አንቀርም።

## 4 መልዕክቱ የተጻፈላቸው ሰዎች

የሮሜ ቤተ ክርስቲያን መቼ እንደ ተተከለ እንዴትም እንደ ተተከለ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ማስረጃ የለም። በጳውሎስ የተተከለ አልነበረም፥ (ሮሜ 15፡20-22)። ሌላም ሐዋርያ የተከለው አይመስልም። ቅዱስ ጴጥሮስ ተከለው የሚሉ ሰዎች አሉ። ነገር ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሮሜ እንደሄደ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተናገረም። ጳውሎስ ይህን የሮሜን መልዕክት በጻፈ ጊዜ ጴጥሮስ በሮሜ አልነበረም። ቢኖር ኖሮ ጳውሎስ በመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ በተናገረ ነበር፥ ወይም ቢያንስ በመጨረሻ ላይ ሰላምታውን ሁሉ ሲያቀርብ ለቅዱስ ጴጥሮስ ባቀረበ ነበር። በኋላ ደግሞ በሮሜ ሆኖ ወደ ኤፌሶን፥ ወደ ፊልጵስዩስና ወደ ቆላስይስ ሲጽፍ ጴጥሮስ እዚያ ቢኖር ኖሮ የጴጥሮስን ሰላምታ ባቀረበላቸው ነበር። አላቀረበምና ከዚያ የነበረ አይመስልም። ጴጥሮስ ግን በበዓለ ኀምሳ ስብከትን በኢየሩሳሌም ባደረገ ጊዜ የሮሜ ሰዎች እዚያ ነበሩና እነርሱ ምናልባት ወንጌልን ወደ ሮሜ አድርሰው ይሆናል፥ (የሐዋ.2፡10)። ወይም ደግሞ አቂላና ጵርስቅላ ተመልሰው ወደ ሮሜ በሄዱ ጊዜ እነርሱ አድርሰውት ይሆናል። ምክንያቱም፥ በቤታቸው የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን አስፋፍታ ይሆናልና፥ (የሐዋ.18፡2-3፤ ሮሜ 16፡3-5)። የሆነ ሆኖ፥ በዚህ መልዕክት የሚገኘውን ከባድ ትምህርት ለመቀበል የቻሉ በመሆናቸው ጳውሎስ መልዕክቱን በጻፈ ጊዜ የሮሜ ክርስቲያኖች በሃይማኖት የጸኑ እንደነበሩ እንረዳለን። ጳውሎስም እሥረኛ ሆኖ በደረሰ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ሊቀበሉት ወጥተዋል፥ (የሐዋ.28፡14-15)።

በቤተ ክርስቲያን ከነበሩት የሚበዙት የአሕዛብ ወገን የነበሩ ይመስላል፥ (ሮሜ 1፡5-6፤13-15፤ 11፡13፤ 15፡16)። በምዕ. 16ም ላይ ከተጻፉት ሰሞች የሚበዙት የአሕዛብ ወገን ናቸው። ነገር ግን ደግሞ በመካከላቸው ኦሪትንና ብሉይ ኪዳንን ያወቁት አይሁዶች ወይም ከአሕዛብ ወገን ወደ ይሁዲነት የገቡት እንደነበሩ ግልጥ ነው፥ (ሮሜ 7፡1)። የብሉይ ኪዳን ጥቅስም በብዙ ተጥቅሶአል። ስለዚህ

በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሕዛብና አይሁድ ተቀላቅለው እንደተገኙ ታውቆአል።

* * *

# ትርጓሜው

## የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች

## ምዕራፍ 1

1.2. ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። 3.4. ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ ስለ ልጁ ነው፤ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 5. በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤ 6. በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ። 7. በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

8. እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ። 9.10. በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና፥ ምናልባት ብዙ ቆይቼ ወደ እናንተ አሁን እንድመጣ በእግዚአብሔር ፈቃድ መንገዱን እንዲያቀናልኝ እየለምንሁ ሁል ጊዜ ስጸልይ ስለ እናንተ ሳላቋርጥ አሳስባለሁ። 11. ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና፤ 12. ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው። 13. ወንድሞች ሆይ፥ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። 14. ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤ 15. ስለዚ ህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።

16. በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና። 17. ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።

18. እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ 19. እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። 20.21. የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ

መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። 22.23. ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፡ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መሰለው ለወጡ።

24. ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው፤ 25. ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።

26. ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ 27. እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።

28. እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ 29. ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ 30. የሚያሾከሹኩ፥ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ 31. ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ 32. እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።

* * *

# 1ኛ ክፍል፦ ፍርድ (ምዕ.1፡ 1-3፡ 20)

## ምዕራፍ አንድ

ጳውሎስ ወንጌልን ለማስተማር በእግዚአብሔር የተለየ ሐዋርያ ነውና በወንጌል ተመክቶ፥ ሰውን ከጥፋት ለማዳን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፥ ብሎ የሰውን ጥፋት በማስረዳት መልዕክቱን ይጀምራል። «ወንጌል አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው (ለአሕዛብ ወገን) የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው» ብሎ ሲያበቃ በዚህ በምዕራፍ 1 ላይ ወንጌል ለተናቁት ለአሕዛብ ወገን፥ በምዕራፍ 2ትም ላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆኑት ለአይሁድ፥ ለሁለቱም፥ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጣል።

ቍ.1-7፦ ሐዋርያው እንዴት ባለ ጥንቃቄ ይጽፋል! ይህ መልዕክት በቀላል ወይም በችኮላ የተጻፈ አይደለም። ጸሐፊው ሊቅ ሆኖ ቃሎችን ሁሉ በጥንቃቄ መርጦአል። እያንዳንዱ ቃል ከበድ ያለ ነው፥ ሁሉም ቃላት ተፈላጊ ሙያ ይዘዋል፥ ለእያንዳንዱም ቃል ትርጓሜ አለው። እንደ ብልሃተኛ የአናጢ አለቃ ሆኖ መሠረቱን አሁን ቃል በቃል ሊመሠርት ነው፥ (1ኛቆር.3፡10) በሥልጣን ሊናገር ነውና አስቀድሞ ስለ ራሱ ይናገራል፦

ሀ/ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ እንደሆነ፥ (የሐዋ.9፡6፤ ገላ. 6፡17)።
ለ/ ሐዋርያ ሊሆን እንደተጠራ፥ (የሐዋ.9፡15፤ 11፡26)።
ሐ/ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደተለየ፥ (የሐዋ.13፡2)።

ሁለተኛ፥ ስለሚያስተምረው ወንጌል ይናገራል፦

ሀ/ የራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር እንደሆነ፥ (ገላ.1፡11-12)።
ለ/ አዲስ ነገር ሳይሆን በነቢያት አፍና በቅዱሳን መጻሕፍት ተስፋ የተሰጠበት እንደሆነ፥ (ዘፍጥ.3፡15፤ ዘዳግ. 18፡15-19፤ ኢሳ. 53።)
ሐ/ ስለ ሌላ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ፥ (ሉቃ.2፡10-11)።

ሦስተኛ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገራል፤ ሲናገርም ሙሉ ስሙን ይሰጠዋል፥ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ይላል። መጀመሪያ የማዕረጉ ስም፥ «ጌታችን»፥ ጌታችን ነውና (የሐዋ.2፡36)። ሁለተኛ የሰው ወገን ስም፥ «ኢየሱስ»፥ የእግዚአብሔር መድኅን ነውና፥ (ማቴ.1፡21)። ሦስተኛ የእግዚአብሔር ወገን ስም፥ «ክርስቶስ»፥ ለደኅንነት ሥራ በእግዚአብሔር የተቀባ «መሢሕ» ነውና፥

(የሐዋ.4፡26፥28፤ 10፡38)። ይህም «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ትውልዱ ከዳዊት ነውና በሥጋው «የሰው ልጅ»፤ ከሙታን ከመነሣቱም ኃይል የተነሣ «የእግዚአብሔር ልጅ» መሆኑ ተገልጦአልና ትስብእቱና መለኮቱ ተረጋግጦአል፥ (ማቴ. 1፡1-16፤ መዝ.15፡10።) በአንድ አካሉ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ሆኖ ተገኘ ማለት ነው።

አራተኛ፥ ከአሕዛብ ጋር ጉዳዩን ያመለክታል። ጳውሎስና የቀሩት ሐዋርያትም ለዓለም ሰው ሁሉ የሚሆን ጸጋን ሐዋርያነትንም ከክርስቶስ ዘንድ ተቀብለው ነበር፥ ምንጩ ጸጋ ነው። የያዙትም ቃል ጸጋ ነው። (2ቆሮ.5፡18-20)። አሳባቸውም ሕዝቦች ሁሉ በክርስቶስ እንዲያምኑ ለክርስቶስም እንዲታዘዙ ነበረ። በእነዚህ በተባሉት ሕዝቦች መካከል የሮሜ ሰዎች ደግሞ አሉና ጳውሎስ አሁን፥ አምስተኛ፥ ስለ እነርሱ ይናገራል፡-

ሀ/ በዚያ በተናገረው የጸጋ ቃል የሮሜ ሰዎች ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ሊሆኑ ተጠርተዋል።

ለ/ የተጠሩትም ተወዳጆች የሆኑት የእስራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆኑ በአሕዛብ መካከል የእግዚአብሔር ተወዳጆችም የሆኑት ጭምር ናቸው፥ (ሮሜ 11፡28)።

ሐ/ የተጠሩበትም ምክንያት ቅዱሳን እንዲሆኑ እንጂ እንዲያምኑ ብቻ አይደለም። ለእነዚህ ከአብና ከወልድ ዘንድ የአባትንና የጌታን ጸጋና ሰላም ይመኝላቸዋል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ፤» ሰው እንደ ሆነና «በቅድስና መንፈስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ፤» አምላክ እንደ ሆነ ከክርስቲያን ሃይማኖት ዋና ትምህርቶች አንዱ ነው። ከሰው የሚወለድ ሰው፥ ከአምላክም የሚወለድ አምላክ እንደ ሆነ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነገር ነው። ጌታችን በአንድ በኩል ከዳዊት ዘር፥ ከሴት፥ ከድንግል ማርያም፥ በመወለዱ ሰው ነው። በሌላ በኩል ግን የጌታችን የኢየሱስ እናት ንጽሕት ድንግል ስትሆን መድኃኒታችን ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር በመወለዱ፥ አምላክ ነው፥ (ማቴ.1፡20-23፤ ሉቃ.1፡30-35።)

በሁለት ሰዎች መካከል ጥል ሲኖር ያ በመካከላቸው ገብቶ ሊያስታርቃቸው የሚፈልገው ሰው የሁለቱን ጥለኞች ነገር እንዲያውቅ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ፥ እንዲሁ ጥሉ በአምላክና በሰው መካከል ሲሆን በመካከላቸው ገብቶ የሚያስታርቃቸው በአንድ ሰውነቱ አምላክና ሰው እንዲሆን ያስፈልጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና ሰው ባይሆን ኖሮ አስታራቂ ለመሆን አይበቃም ነበር።

የኢየሱስ እናት ማርያም ፍጹም ድንግል መሆንዋን የግድ አስፈላጊ የሚያደርግ ይህ ነው። ድንግል ባትሆን ኖሮ ከእርስዋ የተወለደው ሕፃን ሰው ብቻ በሆነ ነበርና

ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት ለመሆን ባልበቃም ነበር። እርስዋ ግን ቅድስት ንጽሕት ድንግል በመሆንዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርስዋ በመወለዱ፥ በአንድ ሰውነቱ አምላክና ሰው ነበረና አስታራቂ መድኃኒትም ለመሆን በቃ።

ሌላ አስታራቂ የሌለው በዚህ ምክንያት ነው። አምላክነት የተሰጣቸው ሌሎች አሉ ቢባል 1ኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ነገር አይመሰክርም፤ 2ኛ፥ «ሌሎች አማልክት አይሁንልህ» ብለው አሥርቱ ቃላት ይከለክላሉ። (ዘፀ.20፡3)። የሚያማልዱ (የሚጸልዩ) ብዙ ይሁኑ እንጂ አስታራቂው እርሱ አንዱ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ብቻ ነው። እነመሐመድ፥ እነቡድሃም፥ ሌሎች ብዙ አስተማሪዎች ሆነዋል፤ ከድንግል የተወለደ ግን ከኢየሱስ በቀር ሌላ ከቶ ስለሌለ፥ ሰውን ከአምላኩ ጋር ለማስታረቅ የበቃ ሌላ በፍጹም የለም፥ (የሐዋ.4፡12)። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሎ እላይ የተጻፈውን ያረጋግጣል:-

«አንድ እዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፥» (1ኛጢሞ.2፡5)።

ይህም የሆነበት ምክንያቱ ከድንግል የተወለደ፥ አባቱ አምላክ የሆነ ማለት፥ ሌላ ስለሌለ ነው። ከድንግልም የተወለደ ሌላ ከሌለ፥ በአንድ ሰውነቱ አምላክና ሰው የሆነ ሌላ የለምና አስታራቂ አንድ ብቻ መሆኑ ነው።

የጌታችን የኢየሱስ እናት ማርያም ፍጹም ድንግልና በምናምንበትና በምናስተምረውም መጠን በዚያ ልክ ከእርስዋ የተወለደው (ኢየሱስ) ብቻ አስታራቂ መሆኑን ማረጋገጣችን ነው።

ቊ.8-17:- አሁን ደግሞ በእነርሱ ዘንድ ያለ አሳቡን ይገልጥላቸዋል። የሮሜ ሰዎች ምናልባት «በእኛ ዘንድ ያለው ጉዳይ ምንድር ነው?» ቢሉ፥ መልሱ እንደሚከተለው ነው:- የእምነታቸው ነገር በዓለም ሁሉ ተወርቶአል። ወደ ጳውሎስም ዘንድ ደርሶ እጅግ ደስ አሰኝቶታል። በዚህ ነገር እግዚአብሔርን ያመሰግናል፤ ከሰማ ግን ይጸኑ ዘንድ የግድ ይጸልይላቸዋል። ከሰማም ደግሞ ሊያያቸው በብርቱ ይፈልጋል። የሮሜ ሰዎች ከአሕዛብ ወገን ናቸው፤ እርሱም ሮማዊ ነው፤ ከተማቸው ሮሜ ነው። ይህም ከተማ በዚያ ዘመን ታውቆ የነበረው የዓለም ሁሉ ዋና ከተማ ነው። ወንጌል በዚያ ቢሰበክ ቃሉ ወደ ዓለም ሁሉ ተሰራጭቶ ይወጣ የለምን? መንፈሳዊ ስጦታንም ደግሞ ሊያካፍላቸው ይፈልጋል፤ ምክንያቱም አሳቡ ዘወትር ይህ ነውና። ምነው ጥቂት ጊዜ በአንድነት በተቀመጡ፤ ኅብረታቸው እንደምን የሞቀ፤ የሁለታቸውም ጥቅም እንደምን ከፍ ያለ በሆነ ነበር! መቼም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ወደ ሮሜ ለመሄድ አስቦ ነበር፥ ነገር ግን ተከለከለ፥ (ም. 15፡20፥22)። ሆኖም አሳብና ናፍቆት አልቀረም ነበር። ለተማሩት ለግሪክ ሰዎች እና ለመሐይሞችም ዕዳ እንዳለበት ይሰማዋል። መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶታልና ወንጌልን ለሁሉ ማካፈል ግዴታ አለበት፥ (1ኛቆሮ.9፡16-17)።

በወንጌልም የሚያፍር አይደለም። ከተማው ሮሜ ነው፥ ጠቅላይ ከተማ፥ የሥልጣን የኃይልና የጥበብ ሁሉ ምንጭ፤ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና የዓለም ሁሉ ሊቃውንት እዚያ ናቸው። ሮማዊ መባል ብቻ ካኮራ በሮሜ መኖርስ እንደምን ይበልጥ ያኮራ! የሚመጣላቸው ግን ከባላገር (ከገጠር) ነው፥ የያዘውም የተሰቀለ ሰው ትምህርት ነው! ወንጌል በእውነት የስንፍና ነገር አይመስልምን? ትምህርቱስ ዝቅተኛ አይደለምን? በሮሜ የነበሩ ጥበበኞች አሳባቸው ሁሉ ከፍ ባለ ትምህርት ላይ ሲሆን ወንጌልን አይንቁምን? በአስተማሪውስ አይስቁበትምን? ነገሩ የድካም ድካም ነገር ነው። የተነገረለቱ ክርስቶስ በድካም ተወልዶ በድካም የሞተ ሲሆን ነገሩ ኃይል በሞላበት በዚያ በሮማ ከተማ እንደምን ሆኖ ይታይ ይሆን? «አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፥ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» የተባለው ሲሆን ወንጌል የክርስቶስም ነገር፥ ይልቁን በሮሜ ሲሰበክ፥ ማሰናከያ ሞኝነትም አይሆንምን? (1ኛቆሮ.1፡22-25)። ጳውሎስ ግን «አላፍርም» ይላል።

ምክንያቱም ምንም ስንፍናና ድካም ቢመስል በእውነት የጥበብ ጥበብ የኃይልም ኃይል ነገር ነውና። ያውም ለእግዚአብሔር ሰዎች ለአይሁድና ለተናቁም ለአሕዛብ። (ለግሪኮች።) በወንጌል ኃይል፥ የጠፉት ወደ መዳን፥ ኃጢአተኞች ወደ ቅዱሳን፥ ርኩሳን ወደ ንጹሓን፥ የሰይጣን ልጆች ወደ እግዚአብሔር ልጅነት የሚለወጡበት ኃይል፥ አለና በእርሱ በዓለም ከሚገኝ ኃይል ሁሉ የበለጠ የእግዚአብሔር ኃይል አለበት። ላመኑት የሚሆን ወንጌል ነው። ምክንያቱም «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» እንደ ተባለም ሁሉ ከእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሚያምኑት በእርሱ ይገለጣል። መጠኑም «ከእምነት ወደ እምነት» ነው፥ ምክንያቱም በመሸፈኛ እንደ ተሸፈነ ሥዕል ነውና። መሸፈኛው ቀስ በቀስ እየተወገደ ሲሄድ ሥዕሉ የበለጠ እንደሚታይ እንዲሁ ከእምነት ወደ እምነት የሚጓዝ ሰው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ከበለጠ ወደ በለጠ ለመገንዘብ ይደርሳል።

በቍ.14 እና በቁ.16 ላይ፥ እንዲሁም በሌሎች ብዙዎች ሥፍራዎች (2፡9-10፤ 3፡9፤ 10፡12) ላይ ስለ «ግሪክ» ሰዎች እናነባለን። እነዚህ እነማን ናቸው? ከዛሬው ከግሪክ አገር የመጡ ናቸውን? አይደሉም። መልዕክቱ በተጻፈበት ዘመን እንደ አይሁድ አሳብ የዓለም ሰው ሁሉ በሁለት ወገን ብቻ ይከፈል ነበረ፤ በአይሁድ፥ ወይም አይሁድ ባልሆኑት በአሕዛብ። በዚያን ጊዜ ደግሞ የግሪክ ሥልጣኔ ታውቆ በነበረው ዓለም በሞላ ተስፋፍቶ ስለነበር፥ ጠቅላላም ቋንቋ የግሪክ ቋንቋ ስለነበር፥ የሠለጠነና አይሁድ ያልሆነ ሁሉ «ግሪክ» ይባል ነበር። በዚህ ምክንያት፥ አሕዛብ ለተባለው ቃል ደግሞ ነጠላ ቃል ስለሌለ፥ ከአሕዛብ ወገን ስለ አንድ ሰው ብቻ መናገር ሲፈለግ መጽሐፍ ቅዱስ «ግሪክ» ይለዋል። እንደዚሁም ከአሕዛብ ስለ አንዳንዶች ሲናገር «ግሪኮች» ይላቸዋል። ስለ አሕዛብ ግን በጠቅላላው ሲናገር በዚያን ጊዜ «አሕዛብ» ይላል። እንግዲያስ ጳውሎስ «ግሪክ»

ወይም «ግሪኮች» ሲል አሕዛብን ሲያመለክት ነው፥ (የሐዋ.14፡1-2 ደግሞ ተመልከቱ።)

ማስገንዘቢያ፦ እላይ ከተባለው ማስረጃ ሁለት ነገሮችን እንማር፥

1ኛ፤ በወንጌል ማፈር አያስፈልግም። ስለምን እናፍር ይሆን? በዓለም ሰዎች ዘንድ ወንጌል እስከ ዛሬ ድረስ የስንፍናና የድካም ነገር ሆኖ ስለሚታይ አይደለምን? የዓለም ሰዎች ከፍ ያለ፥ ጥበብ የሞላበትን ነገር ሲፈልጉ የምናስተምረው ወንጌል ዝቅተኛ ነገር ይመስላቸዋል። ሳይንስ፥ ሳይኮሎጂ፥ ፍልስፍናና ፊዚኦሎጂ፥ ይኸው ነው፤ ዛሬ የዓለም ሰዎች የሚፈልጉት! እኛም በእምነት የሚቀበሉት እና ቀላል ትምህርት የሚመስለውን ወንጌልን እንሰጣቸዋለን፥ የወንጌልንም ነገር አይፈልጉም። በዚህ በአቶሚክ ዘመን ሰዎች የሚፈልጉት ኃይልን ሲሆን፥ ወንጌላችን የድካም ነገር ይመስላል። የሰው ሁሉ አሳብ ከፍ ባለ ነገር ሲውል ታናሽ ለሚመስል ነገር ጊዜውን የሚያባክን ሰው የለም። በአገር ቤትም ዝቅ ያለ የድካም ነገር ሆኖ ሲታይ በታላቁ በአዲስ አበባ ከተማ እንደምን ይታይ ይሆን? ስሙ፤ ጳውሎስ «አላፍርም» ይላል፤ እኛስ? እናፍራለንን? አንፈር።

2ኛ፤ የሰው ጽድቅ አለ፤ የእግዚአብሔርም ጽድቅ አለ። ሐዋርያው የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ነው። የሰው ጽድቅ በሰውና በሰው መካከል ያለ ጽድቅ ነው። ለምሳሌ፥ በሰው ዓይን እገሌ ጻድቅ ሰው ነው። በቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓይን ግን ያ ሰው ኃጢአተኛ እንደ ሆነ ይታያል። በሰው ዘንድ የሰው የጽድቁ ሥራ እውነተኛ ምግባር ሆኖ ይታይ ይሆናል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን «ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፥» (ኢሳ.64፡6)። የሰው ጽድቅና የእግዚአብሔር ጽድቅ ለየብቻው ነው። ሰው በሥራው የሚያገኘው የራሱ ጽድቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ አይቆጠርም። ግምታቸውም ለየብቻው ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና አሳቡ አንድ ነው፤ የእኛ የርኩሳን አሳብ ሌላ ነው። የሰው ጽድቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የማይረባ ስለሆነ እግዚአብሔር በእውነት የምንጸድቅበትን የራሱን ጽድቅ ሰጥቶናል። ይህም ጽድቅ በወንጌል ይገለጣል።

ቍ.18-32፦ ይህ በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰው ሁሉ፥ በሮሜ ስንኳ ላሉት፥ አስፈላጊ የሆነበት በምን ምክንያት ነው? አስፈላጊ የሆነበት ምክንያቱ የእግዚአብሔር ቁጣ በሰው ሁሉ ላይ፥ በሮሜ ስንኳ ባሉት፥ ከሰማይ ስለሚገለጥ ነው። እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣባቸዋል። ኃጢአትና ዓመጽ ከምን መጣ? እውነትን እያወቀ ያ እውነት እንዳይወጣ ብሎ በመጋፋትና በመከልከል ነው። ኃጢአት ማለት የተገባውን እያወቀ ማመፅ ማለት ነው። በእነዚህ ቍጥሮች ደጋግመን

የምናገኛቸው ቃሎች «እውነትን ዐወቁ፡ እውነትን ግን ተጋፍተው ከለከሉ፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣል፡» የሚሉ ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ የሚናገረው ስለማናቸውም ሰው ሁሉ ሲሆን ዕውቀት የላቸውም የተባሉት ጣዖታትንም ያመለኩት፡ አይሁድ ሳይሆኑ የአሕዛብ ወገን ናቸውና ምዕራፉ በተለይ ስለ አሕዛብ እንደሚናገር ግልጥ ነው። «ዕውቀት የላቸውምና የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ እንደምን ይገለጣል?» ቢባል፡ ሐዋርያው «ዕውቀት እኮ አላቸው፥ እውነትንም ዐውቀዋል፥ እውነትን ግን ተጋፍተው ከልክለው እውነትን በውሸት ለውጠዋል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ ፍርድም ይመጣባቸዋል» ይላል። ዕውቀት የላቸውም ይባላልን? ሉረ! አላቸው እንጂ! እግዚአብሔር ራሱ ስለገለጠላቸው የሚያመካኙት የላቸውም። የማይታየው ነገር በሚታየው፥ የማይታወቀው ነገር በሚታወቀው፥ ይታወቃልና እግዚአብሔርን፥ ኃይሉንም፥ አምላክነቱንም፥ በፈጠረው ፍጥረት ዐውቀዋል። «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል፤» እንደ ተባለው ነው፥ (መዝ.18፡1)። ሰው ሁሉ ዐውቆአል ማለት ነው። (ቁ.19-21) ዐውቆም እውነትን ተጋፍቶ ከልክሎአል። አሕዛብ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብርና ምስጋና እያወቁ ክብርንና ምስጋናን አንሰጥም ብለው በፈጣሪ ፈንታ የተፈጠረውን አመለኩ፥ አገለገሉትም። እውነትን በውሸት በመለወጥ እውነትን ተጋፍተው ጣዖታትን አመለኩ፥ (ቁ.21-23) ስለዚህ ከቁጥር 24 እስከ 32 ድረስ ሦስት ነገሮች እንደደረሰባቸው እናገኛለን። «ስለዚህ» እግዚአብሔር «አሳልፎ ሰጣቸው።» ሦስት ጊዜ ይህን አሳዛኝ ቃል እናገኛለን፥ (ቁ.24፤26፤28)።

1ኛ/ አዋርደውት ነበርና ስለዚህ እግዚአብሔር ራሳቸውን እንዲያዋርዱ አሳልፎ ሰጣቸው፥ (24)

2ኛ/ የተገባውን እውነትን በውሸት ለውጠው ነበርና ስለዚህ እግዚአብሔር ለማይገባ፥ ለነውር ልውጫ አሳልፎ ሰጣቸው፥ (26፤27።)

3ኛ/ እግዚአብሔርን ለማወቅ አልወደዱም ነበርና ስለዚህ እግዚአብሔር ላላዋቂ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፥ (28)

አትክልተኛው አትክልቱን አሳልፎ ሲሰጥ በማሳው (በቅብቅቡ) ላይ በየዓይነቱ የሆነው አረም እንደሚበቅልበት ሁሉ፥ እንዲሁም እግዚአብሔር ሰውን አሳልፎ ሲሰጥ በዚያ ሰው ልብ ውስጥ እስከዚያ ድረስ ተደብቆ ተጠብቆም የነበረው ኃጢአት ሁሉ ነፃነትን አግኝቶ ሕያው ይሆናል፥ ይገዛውማል፥ ይወርሰዋልም።

አሕዛብ ተዋረዱ፥ ተነወሩ፥ ኃጢአት የሞላባቸው ሆኑ። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ የሞት ፍርድ የሚገባቸው መሆኑን እያወቁ እውነትን ገና ተጋፍተው ከልክለው ዐመፅ ማድረግን ሳያቋርጡ ጎሽ! ጎሽ! እያሉ ይህን ሁሉ የሚያደርጉትን እያደፋፈሩ

ከእነርሱ ጋር ይስማማሉ። «ለእነዚህ ሰዎች ሞት ይገባቸዋል» ብሎ የእግዚአብሔር ሕግ ፍርዱን ሰጥቶአል።

ማስገንዘቢያ፡- አሁን የምንገነዘባቸው አራት ነገሮች አሉ።

መጀመሪያ፥

ኃጢአት እንዴት የሚያስጸይፍ የሚያስፈራም ነገር ነው! በውኑ ኃጢአት እስከዚህ ድረስ ያደርሳልን? የእግዚአብሔር ቃል «አዎን፥ ያደርሳል» ይላል። ይህስ ከሆነ ምናልባት እኛ በዚህ በኃጢአት መንገድ እንገኛለንን? እውነትን እያወቅን እምቢ ብለን፥ እውነት እንዳይወጣ እንዳይገዛንም ተጋፍተን እንከለክለው ይሆንን? ኡረ! ይህ አይሁን! እንዴት የሚያስፈራ ነገር ነው! እንዲህ ማድረግ ወዴት እንደሚያደርሰን በዚህ ምዕራፍ አይተናልና እጅጉን እንጠንቀቅ እንፍራም።

ሁለተኛ፥

እግዚአብሔር በእውነት ሰውን «አሳልፎ ይሰጣል»? አሳልፎ እንደሚሰጣቸው በዚህ ምዕራፍ ላይ ብቻ ሳይሆን በመዝ:80፡8-12 እና በሐዋ.7፡41 እና 42 ላይ ተጽፎአል። አዎን፥ ሰው የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ ልቡን እልከኛ ቢያደርግና ለመታዘዝ ባይፈቅድ፥ በወደደው መንገድ ይሄድ ዘንድ እግዚአብሔር ይተወዋል። ሰውን ይከለክል ነበር፤ ሰው ግን አልከለከል ቢል፥ እግዚአብሔር ልጓሙን ለቆ ይተወዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ የደነደነውን ልብ አብዝቶ ያደነድነዋል፥ (ዘፀ.7፡13፤14፤22)። ይህም ከሆነ፥ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» (ዕብ.4፡7) የተባለውን ቃል እንስማ።

ሦስተኛ፥

ሰውን ወደተባለው ቆሻሻ ሁሉ የሚጥል እግዚአብሔር ነውን? «ወደ ርኩሰት» (ቁ.24)፥ «ለሚያስነውር ምኞት» (ቁ.26)፥ «ለማይረባ አእምሮ» (ቁ.28)፥ አሳልፎ ሰጣቸው ሲባል፥ እግዚአብሔር ወደዚያ ሁሉ ዘንድ ይመራል ማለት ነውን? ከቶ አይደለም! ወደ ኃጢአት የሚያደርስ ኃጢአት ነው እንጂ! ሰው ኃጢአትን ሲሠራ ኃጢአት በላዩ ግዛቱን እያጸና ይሄዳል። አንዱ ኃጢአት ወደ ሌላ ኃጢአት ያደርሳል፤ ያም ሁለተኛ ኃጢአት የባሰ ኃጢአት ይሆናል። ኃጢአትን የሚሠራ ሰው ቀስ በቀስ ወደ ነውር ረግረግ የሚገዝ ነውና ከኃጢአት አጥብቀን እንሽሽ።

አራተኛ፥

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኃጢአትን በሠሩት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል፤ ፍርዱም ይደርሳል፤ የተባለውን አንብበናልና ወንጌልን ያልሰሙትን ሕዝቦች እናስባቸው። አንዳንዶች ሰዎች እንደሚሉ፥ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ነገር ትእዛዙንም አልሰሙምና አይፈረድባቸውም። አይፈርድባቸውምና በደኅና ተቀምጠዋል። ባይሰሙ ስንኳ ይሻላቸዋል ይላሉ፤ ምክንያቱም የሰሙ እንደሆነ ዕውቀታቸው ወደ ፍርድ ያገባቸዋል። ስለዚህ ባታስረዱአቸው ይሻላል ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ አይልም። መጽሐፍ ቅዱስ በዚሁ ምዕራፍ ላይ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ነገር ሰምተዋል፤ ዐውቀዋልም፥ ዐውቀውም በድለዋል ይላል። የእግዚአብሔርን ፍጥረት በማየት ወደ ዕውቀት፥ ሕሊናቸውም ስለሚነግራቸው ትእዛዙን ወደ መስማት፥ እንደደረሱ ይናገራል። በምዕ.2፡12 ላይ ደግሞ «ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ... ይጠፋሉ» ተብሎ የተጻፈውን እናያለን። ኢየሱስም «ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁም ትጠፋላችሁ» ብሎአል፥ (ሉቃ.13፡3፤5)። የለም! በደኅና አልተቀመጡም፤ የተቀመጡት በሞትና በፍርድ ጥላ ነው። ሰው ሄዶ ካላስተማራቸውና ወደ ክርስቶስ ካልመራቸው ለዘላለም ይጠፋሉ። እንዲድኑ ከታሰበ መስማት የግድ ያስፈልጋቸዋል፤ (ሮሜ 10፡11-15)። እንግዲያስ እኛ ወንጌልን የሰማን ሰዎች ለእነዚህ ሁሉ ኃላፊነት የለብንምን? ካልነገርናቸውስ ደማቸው ከእጃችን ይፈለግ የለምን? (ሕዝቅ.33፡1-9)። እኛ ብርሃንን የተቀበልንበት ሌሎች ደግሞ ብርሃኑን እንዲያዩ አይደለምን? (ማቴ.5፡14-16)። እንከያስ ፍርድ እንዳይፈረድብን እነርሱም ደግሞ ለዘላለም እንዳይጠፉ ወገባችንን ታጥቀን ወንጌልን ላልሰሙት ሁሉ ተግተን እናካፍላቸው።

* * *

# ምዕራፍ 2

1. ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና። 2. እንደ ዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን። 3. አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፥ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታ መልጥ ይመስልሃልን? 4. ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? 5. ነገር ግን እንደጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአ ብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። 6. እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ 7. በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ 8. ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። 9. ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ 10. ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው። 11. እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና።

12. ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ 13. በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና። 14. ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ 15. እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። 16. ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል።

17. አንተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ፥ 18. ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ፤ 19.20. በሕግም የዕውቀትና የእውነት መልክ ስላለህ፥ የዕውሮች መሪ፥ በጨለማም ላሉ ብርሃን፥ የሰነፎችም አስተማሪ፥ የሕፃናትም መምህር እንደሆንህ በራስህ ብትታመን፤ 21. እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? 22. አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? 23. በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን? 24. በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።

25. ሕግን ብታደርግ መገረዝስ ይጠቅማል ሕግን ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ አለመገረዝ ሆኖአል። 26. እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርዓት ቢጠብቅ አለመገረዙ እንደ መገረዝ ሆኖ አይቈጠርለትምን? 27. ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው

የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ሕግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሃል። 28. በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ 29. ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።

* * *

# ምዕራፍ ሁለት።

ዕውቀት የላቸውም በተባሉ አሕዛብ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ቢገለጥና ፍርዳቸው የተገባ ቢሆን በዕውቀታቸው ብዛት በተመኩ በአይሁድ ላይ ቁጣው እንደሚገለጥ ፍርድም እንደሚመጣ ጥርጥር የሌለበት ነገር ነው። ቢሆንም፥ አይሁድ ከዚያ ከሰማይ ከሚገለጠው ቁጣ የሚድኑበትና ከፍርድ የሚያመልጡበት እንደ ዣንጥላ ቁጥረው ይጠጉበትና በጥላው ይመኩ የነበር 3 ነገሮች እንደ አሉአቸው አሰበዋል።

1ኛ፤ የእግዚአብሔር ልዩ ወገን (አይሁድ) በመሆናቸው፤

2ኛ፤ ሕግን (ኦሪትን) በመቀበላቸው፤

3ኛ፤ የኪዳኑን ምልክት (መገረዝን) በመሸከማቸው።

## ቁጥ. 1-11፦ የእግዚአብሔር ልዩ ወገን (አይሁድ) በመሆናቸው

ምዕራፍ 1 በተለይ ስለ አሕዛብ እንደ ተናገረው እንዲሁ አሁን ምዕራፍ 2 በተለይ ስለ አይሁድ እንደሚናገር ቁ.17 ያሳስበናል። አሕዛብና አላዋቂዎች እንኳ የሚያመካኙት ሲያጡ (1፡20-21) እንዴት ይልቅ አይሁድና በሌሎች ላይ ለመፍረድ የበቃ ዕውቀት ያላቸው ሁሉ የሚያመካኙት ያጡ! «እነርሱ የሚያመካኙት አጥተዋልና ስለዚህ አንተ የምታመካኘው የለህም» ይላል፥ (ቁ.1።) ምክንያቱም፥ ሰው ሁሉ፥ አይሁዳዊው ደግሞ፥ እነዚያን ነገሮች (እውነትን በዓመፃ መከልከልና እውነትን በውሸት መለወጥ ማለት) ስላደረጉ ነው። አይሁድ ግን የእግዚአብሔር ፍርድ እየበቃው፥ አንዱ ለአይሁድ አንዱም ለአሕዛብ፥ እንደ ሆነ ስለ መሰላቸው ከፍርድ ለማምለጥ አሰበዋል። «እኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነንና እግዚአብሔር አይፈርድብንም» አሉ። ጳውሎስ ግን በዚህ አንቀጽ «እግዚአብሔር በሰው ሁሉ ላይ የሚፈርድበት ፍርድ እኩል ነው» ብሎ ይህን መጠጊያቸውን አፈረሰ። እግዚአብሔር ልዩነትን ሳያደርግ በአይሁድና በአሕዛብ ላይ በአንድ እውነተኛ ፍርድ ይፈርዳል። ቸርነቱና ትዕግሥቱ አዘገየው እንጂ ከአሁን በፊት ፍርዱ በአይሁድ ላይ በመጣ ነበር፤ አሁንም ደግሞ ልባቸውን አጽንተው ንስሐ ያልገቡ እንደሆነ ያ የሚገለጠው ቁጣ፥ የእግዚአብሔርም ቅን ፍርድ፥ በአይሁድ ስንኳ ቢሆን ተከማችቶ ይመጣል። እግዚአብሔር በእኩል ፍርድ ይፈርዳልና መልካም ላደረገው ሁሉ፥ አይሁዳዊ ወይም የአሕዛብ ወገን መሆኑን ሳያጣርጥ፥ መልካምን ይመልስለታል። እንደዚሁም ደግሞ ክፉ ለሠራው ሁሉ ክፉን ይመልስበታል። ለሁሉ ፍርዱ እኩል ነው፤ ነገር ግን አይሁዳዊ የበለጠ መብት ስለ ተሰጠው የበለጠም ዕውቀት ስላለው፥ በሁለቱ ነገሮች፥ በሕይወቱና በቁጣው፥ ቀዳሚነት አለው። «እግዚአብሔር ለአይሁዳዊ አያዳላምና አይሁዳዊ

(የእግዚአብሔር ልዩ ወገን) በመሆን ሰው ከዚያ ቁጣ አይድንም ከፍርድም አያመልጥም» ብሉ ሐዋርያው መጀመሪያ የአይሁድን ጥላ አፍርሶአል።

## ቍ.12-24፡- ሕግን (ኦሪትን) በመቀበላቸው

በኃጢአተኛ ሁሉ ላይ ፍርድ ይመጣል። ልዩ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ (እንደ ምዕ.1) ልዩ ሕግም ያላቸው አይሁድ (እንደ ምዕ. 2) ኃጢአትን ያደረጉ እንደሆነ ፍርዳቸው የተረጋገጠ ነው። «ይጠፋሉ»፥ «ይፈረድባቸዋል»፥ ይላል፥ (ቁ.12።) ምክንያቱም፥ ሰው የሚጸድቅበት ሕግን በመፈጸም ነው እንጂ ሕግን በመቀበል ብቻ አይደለም። ልዩ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ሕሊናቸው ያልተገባውን ወይንም ደግሞ የተገባውን አስረድቶ ሲያበቃ ስለሚከስሳቸው ወይም ስለሚያመካኛቸው በባሕርያቸው ሕግ እንዳላቸው ይገልጣሉ። በዚያም ሕግ ይፈረድባቸዋል። አይሁድ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚገልጥ ልዩ ሕግን የተቀበሉ፥ ያንም ሕግ ያወቁ ያስተማሩትም ስንኳ፥ በአይሁዳዊነታቸውና በዕውቀታቸው የተመኩ፥ የተቀበሉትን ሕግ አልጠበቁምና በዚያ ሕጋቸው ይፈረድባቸዋል። የማናቸውም ሕግ ሁሉ ዓይነተኛ ሥራው ለመፍረድ ነውና በዚህ መልእክት ላይ ይህን ነገር ብዙ ጊዜ እናገኛለን። ሕግ የተሰጠበት ለፍርድ ነው እንጂ ለደኅንነት አይደለም። ሕግ ተቀባይ ዐዋቂም አብዝቶ ይፍራ እንጂ አይኵራበት። አይሁድ ሕግን (ኦሪትን) ተቀብለው ነበር! ነገር ግን አልጠበቁትም። ሌሎችን ሲያስተምሩ ያስተማሩትን እነርሱ ራሳቸው አልፈጸሙም። የተቀበሉትን ሕግ በመጠበቅ እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ አሳፈሩት። እነርሱ አይሁዶች ሆነው፥ እንደሚገባቸው ሁሉ ስሙን በአሕዛብ መካከል እንዲከበር በማድረግ ፈንታ ያ የተቀደሰ ስሙ እንዲሰደብ አደረጉ። «አልጠበቃችሁትምና ሕግን በመቀበላችሁ ምክንያት ከቁጣ የምትድኑና ከፍርድ የምታመልጡ ሳይሆን የተቀበላችሁት ሕግ እርሱ ራሱ ይፈርድባችኋል! ስለምን ብትሉ፥ ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ የሚሰሙ ብቻ ጻድቃን አይደሉም» ብሉ ሐዋርያው ሁለተኛ የአይሁድን ጥላ አፍርሶአል።

## ቍ.25-29፡- የኪዳኑን ምልክት (መገረዝን) በመሸከማቸው

እግዚአብሔር የወዳጁን የአብርሃምን ዘር በልዩ ምርጫ መርጦ ለራሱ የተለዩ ሕዝብ ሲያደርጋቸው በእርሱና በእነርሱ መካከል ኪዳን አድርጎ የኪዳኑን ምልክት የሚሆን መገረዝን ሰጣቸው። መገረዝ የእርሱ ሕዝብ እንደ ሆኑ ምልክትና እርሱ ላደረገላቸው ኪዳን ማኅተም ነበረ። ይህ ሲሆን፥ አይሁድ ልዩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲሆኑ፥ በመካከላቸውም ኪዳን ሲኖር፥ ከቶ የሚፈረድባቸው አልመሰላቸውም። «የኪዳኑን ምልክት በተሸከመው ሰው ፍርድ የለበትም» ብለው አይሁድ ይመኩ ነበር።

ነገር ግን የኪዳኑን ቃል ስንመለከት ኪዳኑ በሁለት ወገኖች (በእግዚአብሔርና በሰው) በኩል እንደነበረ እናያለን። «በፊቴ ሂድ ፍጹምም ሁን፥ ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ ...» ይላል፥ (ዘፍጥ.17፡1-2)። ደግሞ «አንተ ደግሞ ኪዳኔን ትጠብቃለህ። አንተ ዘርህም ከአንተ በኋላ በትውልዳቸው» ተባለ፥ (ቁ.9።) ደግሞ «ይህ ነው የምትጠብቁት ኪዳኔ» ይላል፥ (ቁ.10።) ዘፀ.29፡3-8ን ደግሞ ተመልከት። ማለት፥ እግዚአብሔር ያለው «ብታደርገው እኔ አደርገዋለሁ! ብትጠብቁት እኔ አጸናዋለሁ» ነበረ እንጂ እንዲያው አደርገዋለሁ» አላለም። ሕጉን የጠበቁ እንደሆነ በእውነት ምልክቱ (መገረዛቸው) በጠቀመ ነበር! ሕጉን ግን ካልጠበቁ ኪዳኑ አይጸናም ነበርና ምልክቱ ምን ይጠቅማል? ሕግን ከሚያፈርስ ከተገረዘ አይሁዳዊ ይልቅ ሕግን የሚጠብቅ አሕዛብ ይሻላል።

ምልክቱ አይሁዳዊን (የእግዚአብሔርን ሰው) ከአመለከተ፥ ሰውዬው የእግዚአብሔር ሰው ካልሆነ ምልክቱ ውሸታም ሆነ! ጥቅምም የለውም ማለት ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ምልክት የልቡ መገረዝ ነው እንጂ የሥጋው መገረዝ አይደለም። በሰውር፥ በልቡ ለእግዚአብሔርም ማለት፥ አይሁዳዊ የሆነ እርሱ እውነተኛ አይሁዳዊ ነው። እውነተኛም መገረዝ በሚዳዊነት ያለውና በሰው የሚመሰገን ሳይሆን በልቡ ያለውና በእግዚአብሔር የሚመሰገን ነው። «የኪዳኑን ሕግ ካልጠበቃችሁ ኪዳኑ አይጸናም! የተመለከተውንም ካልሆናችሁ ምልክቱ ዝም ብሎ ነው» በማለት ሐዋርያው ሦስተኛ የአይሁድን ጥላ አፍርሶአል።

አይሁድ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጡበት ያሰቡአቸው ሦስቱ ጥላዎች ተወግደዋልና አይሁዳዊ ደግሞ እንደ ቀረው የዓለም ሰው ሁሉ ሆኖ ለሚገለጠው ቁጣ ክፍት (ግልጥ) እንደ ሆነ ታይቶአል። እንደ አሕዛብ ወገን ሰው እንዲሁ አይሁዳዊ ደግሞ ከኃጢአት በታች ነውና ፍርድ ይቆየዋል፥ (ቁ.9።) ጽድቅ አስፈላጊ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጽድቅ በቀር የሚጠጋበት ጥላ የለውም።

እንግዲያስ በምዕ.1 እና በምዕ.2 ላይ ያገኘነው ነገር ባላወቁት አሕዛብ እና ባወቁት አይሁድ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣባቸው ነው። «እግዚአብሔር የሚመለከተው ኃጢአተኛውን ሳይሆን ኃጢአትን ነው። አድራጊው ማንኛውም ቢሆን የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአተኝነቱና በዓመፃው ላይ ይገለጣል። በሐዋርያው ዘመን እንደነበረ ዛሬም እንደዚያው ነው። «አልተማርሁም» በማለት አመካኝቶ (1፡20-21) ከፍርድ ለማምለጥ አይቻልም! «ተምሬአለሁ» በማለትም እንዲሁ አመካኝቶ ከፍርድ ለማምለጥ አይቻልም፥ (2፡1፥3)። ሁሉቱም ኃጢአት አድርገዋል! በሁለቱም ላይ ፍርድ ይመጣባቸዋል።

ማስገንዘቢያ፡- አሁን ግን ስለዚህ ስለ ምዕራፉ ነገር እናስብ። አይሁድ የያዙአቸውን ሦስቱን ጥላዎች ብዙዎቹ የዛሬ ክርስቲያኖች የያዙአቸው አሉ። አይሁድ «አይሁዳዊ በመሆኔ እድናለሁ እንጂ አይፈረድብኝም» እንዳሉ፥ እንዲሁ

ዛሬ «ክርስቲያን ነኝና ክርስቲያን በመሆኔ እድናለሁ» የሚሉ ብዙ አሉ። ለዚህ ለአይሁዳዊው አሳብ ግን የሐዋርያው መልስ ምን እንደ ሆነ እናስተውል። «እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና አይሁዳዊ በመሆን ሰው አይድንም» አላለምን? ብሎአል! ታዲያስ፥ ዛሬ እንዴት ነው? «ክርስቲያን በመሆን ሰው አይድንም፥ ከፍርድም አያመልጥም» የግድ ይባል የለምን? በእውነት ይባላል። የለም፥ ያ «ክርስቲያን» የተባለ ሰው ኃጢአትን አድርጎአልና ፍርድ ይፈረድበታል እንጂ ክርስቲያን በመባሉ አይድንም።

እንዲሁም ደግሞ ሁለተኛውን ጥላ ብናስብ፤ አይሁዳዊ የተማረ በመሆኑና የእግዚአብሔርን ነገር በተሻለ በማወቁ፥ በሥልጣኔውና በከፍተኛ አኗኗሩ ምክንያት እንደሚድን ለሚያስብ ሰው ሐዋርያው ምን አለው? «ሕግን የሚያደርጉ ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም» አላለምን? (2:13) ብሎአል! እኛስ? ከብዙዎች ሰዎች የበለጠ ዕውቀት ስላለን፥ ከፍ ባለም የሥልጣኔ ደረጃ ስለምንኖር፥ ኬሌቦችና ከነፍሰ ገዳዮች የተሻልን በመሆናችን፥ ወይም ደግሞ ኃጢአታችን ከኃጢአታቸው ይልቅ ጨዋ በመሆኑ፥ እንድናለንን? አንድንም! ሕግን፥ እርሱም የእግዚአብሔርን ሕግ፥ ጠብቀናልን? «እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል» ተብሎአልና የለም፥ የሠለጠንን በመሆናችን አንድንም።

ታዲያ፥ ያ ሦስተኛ ጥላ አያድነንም ይሆን? አይሁዶች ምን አሉ? «የእግዚአብሔር ወገኖች ነን፥ የኪዳኑንም ምልክት ተሸክመናል» አላሉምን? ለዚሁስ ሐዋርያው ምን ብሎ መለሰላቸው? «ካልሆንህ ምልክቱ ምን ያደርጋል? የተመለከተውን (አይሁዳዊን) ካልሆንህ ምልክቱ አይረባም» አላለምን? ብሎአል! ታዲያ መገረዝ ለአይሁዳዊ የነበረው ሁሉ ጥምቀት ለክርስቲያን ያው ሲሆን፤ ጥምቀትም ደግሞ መገረዝን መስሎ ሰው የክርስቶስ ወገን መሆኑን ሲያመለክትና ከክርስቲያኖች ጋር የተደረገው የኪዳኑ ምልክት ሲሆን፥ ስለ እኛ ክርስቲያኖች ምን ይባላል? «የእግዚአብሔር ወገኖች ነን፥ የአዲስ ከዳኑንም ምልክት ተሸክመናል» ስንል ጥምቀታችን ያድነናልን? «ተጠምቄአለሁ፥ ክርስቲያንም ነኝ» እላለሁ። ክርስቲያን ካልሆንሁሳ? መገረዝ ሰውዬው አይሁዳዊ እንደሆነ ምልክት ብቻ ነው እንጂ ሰውዬውን አይሁዳዊ ለማድረግ (ለመፍጠር) አይችልም። እንደዚሁም ጥምቀት ክርስቲያን ሊያደርግ (ሊፈጥር) ይችላልን? ይልቁንስ ሰው ክርስቲያን ስለሆነ የክርስቲያን ምልክት (ጥምቀትን) ይቀበል የለምን? መገረዙ ያ የተገረዘው ሰው አይሁዳዊ እንደሆነ አመልክቶአል፤ ሰውዬው ግን በእውነት አይሁዳዊ ያልሆነ እንደሆነሳ? ሚዳዊ (ውጫዊ) ምልክቱን ተቀብሎ በልቡ አይሁዳዊ ስላልሆነ ሰው «መገረዙ መገረዝ አይደለም» ተብሎ የለምን? (ቁ.28) ሉረ ለመሆኑ፥ በእኛ «ክርስቲያኖች በተባልነው ዘንድስ እንዲሁ አይደለምን? እውነተኞች የልብ ክርስቲያኖች ካልሆንን መጠመቃችን ብቻ ያድነናልን? በሐዋ. ምዕ.8 ላይ ሲሞን

በተባለው ሰው ዘንድ ነገሩ እንደምን ሆነ? «አመነ፥ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር» ተባለ፥ (ቁ.13) ነገር ግን ክርስቲያን አልሆነም፥ አለመሆኑም ግልጥ ነው። «እንደ ምን?» ትላላችሁን? ቁ.21-23 ተመልከቱ። መጀመሪያ ሐዋርያ የሆነው ቅዱስ ጴጥሮስ ለዚህ ለተጠመቀ ሰው ምን አለው? «ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ» (ምነው፥ ሲሞን የሚጠፋ ነውን? የተጠመቀ ሆኖ?) « ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም።» (በደኅንነት ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለውም ማለት ነው) «እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ፥ ምናልባት የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን፤ በመራራ መርዝና በዓመፃ እሥራት (ገና) እንዳለህ አይሃለሁና» ብሎት የለምን? በግልጥ ክርስቲያን ሆኖ ይሆን ይሆናል፥ በስውር ( በልቡ) ግን ክርስቲያን አልነበረም። ምልክቱንስ ተቀብሎአል፥ ምልክቱ የተመለከተውን ግን አልሆነም ነበርና ገና ለጥፋት የሚሆንና በደኅንነት ነገር ፈንታ የሌለው፥ ገና ንስሐ ገብቶ ይቅርታን ለምኖ ከታሠረበቱ እሥራት መፈታትን ከፍርድ መዳንንም መለመን ሆኖበታል።

ሌላ ማስረጃ ደግሞ አለ። በየወኅኒ ቤቱ ከሚገኙት ሌቦችና ነፍስ ገዳዮች የሚበዙት የተጠመቁ ናቸው። በመጠመቃቸው ይድናሉን? 1ኛቆሮ.6፥9 እና 10ን ደግሞ 1ኛዮሐ.3፥15ን ተመልከቱ። አይድኑምና በመጠመቃችን ብቻ አንድንም ማለት ነው።

የለም፥ በሁሉ፥ በተማሩትም ባልተማሩትም፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል ፍርድም ይመጣል። ለሁሉ፥ ለአሕዛብ ወገንና ለአይሁድም፥ ለእኛም ለክርስቲያኖች ደግሞ፥ ጽድቅ አስፈላጊ ነውና የእግዚአብሔር ወገን (አይሁድ) ወይም የክርስቶስ ወገን በመሆናችን፥ ሕግን በማወቃችን፥ ወይም የኪዳኑን ምልክት በመሸከማችን ሳንተማመን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ከሚገኝበቱ ከአንዱ ቦታ ብቻ (ከክርስቶስ) እንፈልግ።

* * *

# ምዕራፍ 3

1. እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? 2. በሁሉ ነገር ብዙ ነው። አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። 3. ታዲያ ምንድር ነው? የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? እንዲህ አይሁን፤

4. በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ

ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆን እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን። 5. ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያስረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። 6. እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል? 7. በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ካለቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል? 8. ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።

9. እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከስሰናቸዋልና፤ 10. እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ :-

11. ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ 12. ሁሉ ተሳስተዋል፥ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም። 13. ጕሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በምላሳቸውም ሸንግለዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤ 14. አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤ 15. እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤ 16. ጥፋትና ጕስቍልና በመንገዳቸው ይገኛል፥ የሰላምንም መንገድ አያውቁም። 17.18. በዓይኖቻ ቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም።

19. አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ 20. ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።

21. አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ 22. እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ 23. ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ 24. በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል

እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። 25. እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስረያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥ 26. ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው። ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። 27. በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። 28. ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና። 29.30. ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፥ የተገረዘን ስለ እምነት ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው። 31. እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።

* * *

# ምዕራፍ ሦስት

ሐዋርያው በሁለቱም ክፍሎች የዓለም ሰዎች፥ በአሕዛብና በአይሁድ፥ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣባቸው በም.1 እና በምዕ.2 አስረድቶአል። አሁን በምዕ.3 አይሁድ ለሚያነሡ ክርክር አስቀድሞ መልስ ከሰጠና የዓለም ሰው ሁሉ ከፍርድ በታች በመሆኑ ጽድቅ ፈላጊ መሆኑን ካስረዳቸው በኋላ፥ ከቁ.21 ጀምሮ በምዕ.1፡17 ላይ «ይገለጣል» የተባለው የእግዚአብሔር ጽድቅ መገለጡን ይናገራል።

ቍ.1-4:- ጳውሎስ በምዕ.2፡28 ላይ «በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለም» ደግሞ «በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝ መገረዝ አይደለም» ብሎ ነበርና አይሁድ ምናልባት «እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው?» ብለው በተከራከሩት ነበርና ለእነዚህ ለሁለቱ ጥያቄዎች መልሱን አሁን ይሰጣል።

«የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው?» ለተባለው ጥያቄ «በሁሉ ነገር ብዙ ነው» ብሎ መጀመሪያውን ነገር ብቻ ይጠቅሳል። ያም መጀመሪያ ነገር ምንኛ ታላቅ ነው! እግዚአብሔርንና ፈቃዱንም ለማወቅ፥ ዓለምንም ለማስተማር፥ ለአይሁድ ተሰጥቶአል። ብልጫውን ለማወቅ ይህን አንዱን ነገር ብቻ ማሰብ ይበቃል። አይሁዳዊ የሆነ ሕፃን የእግዚአብሔር ዕውቀት በሚገኝበት አገር ተወልዶ በፈቀደበት ሰዓት ሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ ሲችል ያ በአሕዛብ አገር የተወለደው ቢናፍቅ ስንኳ ለማወቅ አይቻለውም። ያ መጀመሪያ ብልጫ ብዙ ነው፥ እርሱንም የሚመስለሉ በምዕ.9፡4፤5 ላይ ተጽፈዋል። አይሁዳዊ መሆን ታላቅ ዕድል ነው።

«የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው?» ለተባለው ጥያቄ ደግሞ፥ መልሱ እንደዚሁ ነው። «በሁሉ ነገር ብዙ ነው።» ምክንያቱም፥ የእግዚአብሔር ታማኝነት ለዘላለም ነውና። መገረዝ የኪዳን ምልክት ነበረ፤ በዚያም ኪዳን ታላቅ ነገር ለእስራኤል ተሰጥቶ ነበር፥ (ዘፍጥ.17፡1-11)። የኪዳኑ ተስፋ ለጊዜው እንዳይፈጸም ሰው ባለማመኑ ሊያስቀረው ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን በመጨረሻ ላይ «ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ ቃሌ አያልፍም» እንደ ተባለ ለተገረዙት ከዕለታት አንድ ቀን ኪዳኑ ይፈጸምላቸዋል። እስራኤልም ሁሉ ይድናል፥ (ሮሜ 11፡26፤29)።

ቍ.5-6:- አሁን ደግሞ ሌላ ክርክር መጥቶአል። የእግዚአብሔርን ጽድቅ እንዲገለጥ ያደረገው የእኛ ዓመፃ ነበረ፥ (1፡17-18)። የህማ ከሆነ፥ ዓመፃችን መልካም አላደረገም ወይ? መልካምንስ ካደረገ እግዚአብሔር ቁጣን ለምን ይገልጣል? ይልቅስ ደስ አይሰኝበትም ኖሮአልን? በኃጢአታችን ተጠቅሞአል

ማለት ነው። «እንዲህ አይሁን!» (ወይም «ሎረ ከቶ አይደለም!») ብሎ ሐዋርያው በአሳቡ ብቻ ተጻይፎ «የፍርድ አፈራረድ እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርድበታል?» ብሎ በማረጋገጥ ጥያቄውን መልሶታል። «ይፈረድበታል» ተብሎ ተጽፎአልና አለጥርጥር ቁጣውን በኃጢአት ሁሉ ላይ ይገልጣል ማለት ነው።

ቍ.7-8:- ሦስተኛ ክርክር የሚነሣው በዚህ ምዕራፍ በቁ.3 እና 4 ላይ ስለተባለው ነገር ነው። «አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን» ተባለ። የእኔ ውሸት የእግዚአብሔርን እውነት አልቆታል፤ ደግፎታልም። ታዲያ፥ ከሚፈርድብኝ ይልቅ ለምን አያመሰግነኝም? እንዲህም ማለት እኔ ባደረግሁት ክፋት መልካም ወጥቶአልና መልካም ነገር አይደለምን? ማለት ነው። አንዳንዶች ሰዎች «ትምህርታቸው እንደዚህ ነው» ብለው ክርስቲያኖችን ይሰድቡ ነበር። ጳውሎስ ግን እንዲህ ያለውን አሳብ ጠልቶ መልሶ «እንደዚህ የሚሉ ፍርዳቸው (እግዚአብሔር ሲፈርድባቸው) ቅን ነው» ይላል።

ቍ.9-20:- አራተኛ ክርክር ደግሞ ተነሥቶአል። እርሱም «እንግዲህ፥ እንደዚህ በቁ.2 ላይ እንደተባለው ከሆነ፥ እኛ አይሁዶች ከእነርሱ (ከአሕዛብ) በእውነት እንበልጣለንን?» የሚል ነው። ጳውሎስ ግን «ከቶ አይደለም። በመብትና በስጦታ እንበልጣቸዋለን እንጂ (ቁ.2) በኃጢአት ረገድ በምዕ.2 እንዳየን ሁሉ ከእነርሱ ጋር እኩል ነንና ከእነርሱ ጋር ከኃጢአት በታች ሆነናል። ይህም ከሞላ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ ነው» ብሎ ጥቅስ ጠቅሶ መልስ ሰጥቶአል። ይህ ግን ከዳዊት ከሰሎሞን ከነቢያትም ሁሉ ዘንድ ተጠራቅሞ የተጠቀሰ ጥቅስ ከምን መጽሐፍ ነው የተገኘ? ከሕግ መጽሐፍ ነዋ! ታዲያ፥ የሕግ መጽሐፍ የሚናገረው ከሕግ በታች ላሉት ለአይሁድ፥ አይደለምን? ይህ የሕግ መጽሐፍ ደግሞ ያጸድቃቸዋልን? ሎረ አያጸድቃቸውም! ኃጢአታቸውን ገልጦ አስታውቆ ፍርድን ይፈርድባቸዋል እንጂ ከቶ አያጸድቃቸውም። እንግዲያስ ያገኘነው ነገር ይህ ነው፤ አሕዛብ ሆነ አይሁድም፥ ዓለም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ተጠቃልሎአል። ፍርድ በሁሉም ላይ የሚሆን ከሆነ ጽድቅ ለሁሉ አስፈላጊ ነው።

ማስገንዘቢያ

ሀ) ከቁ.5 እስከ ቁ.8 በተገለጠው ክርክር ሐዋርያው ወደ ነገሩ ገብቶ ሳይከራከር የእግዚአብሔርን እውነተኛነት ብቻ በማስረዳት የተመለከተውን አጉል አሳብ እንደ መለሰው እንመልከት። እነዚህን የሚመሳሰሉ በጣም የሚያስቸግሩ የዐዋቂዎች ጥያቄዎች አሉ። ጳውሎስ ራሱ ዐዋቂ ነበረ፤ ቢሆንም፥ በእንዲህ ያለ ዓይነት ክርክር

ለመግባት ጠልቶ ቂም የሆነ የእግዚአብሔርን ታላቅ ነገር ለማረጋገጥ ራሱን ወስኖአል።

ለ) «መልካም እንዲመጣ ክፉ እናድርግ» የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ፥ መጽሐፍ ቅዱስ «የእነርሱ ፍርድ ቅን ነው» ብሎ መፍረዱን እናስተውል። ፍርድ ሲፈርድባቸው ቅን ነው፥ ይገባቸዋል፥ ማለት ነው። መልካም እንዲመጣ ክፉ ማድረግ ተፈቅዶአልን? ከቶ አልተፈቀደም! ክፉ ምን ጊዜም ቢሆን ክፉ ነው። በአድራጊውም ላይ ፍርድን ያመጣል።

ሐ) የዓለም ሰው ሁሉ ከኃጢአት በታች ነው። (ቁ.9) የዓለም ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ነው። (ቁ.19) ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል፤ በሁሉም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ አርፎአል፥ (1፡18፤ ዮሐ.3፡36)። በሁሉም ፍርድ ተመደበ፥ (ዕብ.9፡27) «አልተማርሁም፥ አላወቅሁም» ብሎ ማመካኘት የለም፥ (ም.1) «ክርስቲያን ነኝ፥ የሠለጠንሁ ዐዋቂ ነኝ፥ ሕግን ተቀባይ ነኝ፥ ተጠምቄአለሁ» ብሎ ማመካኘት የለም፥ (ምዕ. 2) ሁሉ ከፍርድ በታች ሆነዋል፤ ማንም አያመልጥም። ከዚህ ፍርድ የሚያድን አንድ መንገድ ብቻ አለ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማግኘት ነው። ያለ እርሱ መዳን የለም።

* * *

## 2ኛ ክፍል- ጽድቅ:- (ከምዕ.3፡21 እስከ ም.5 መጨረሻ)

ቁ.21-26:- አሁን ግን በጳውሎስ ዘመን፥ እርሱም በሚሰብከው ወንጌል (1፡17)፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ የሚታየው ጽድቅ (እግዚአብሔር የሚሰጠው ጽድቅ) ተገለጠ። ከሕግ ውጭ ነው፥ በሕግም የማይደገፍ ነው፥ ነገር ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት ነው። ሕግ ለሰው ኃጢአተኝነት መስክሮ እንደነበር (3፡11-18) እንዲሁ ለእግዚአብሔር ጽድቅ ይመሰክራል። ይህ ጽድቅ በምዕ.1፡16 እንደተነገረው ለሚያምኑ ሁሉ ነው፥ ለአይሁድም ለአሕዛብም፥ የሚገኘውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው። በአሕዛብና በአይሁድ፥ በዓለም ሰው ሁሉ ዘንድ፥ ልዩነት የለምና፤ ለምን? ቢባል፥ ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና። በኃጢአት አንድ እንደነበሩ ሁሉ አሁን ደግሞ በጽድቅ አንድ ይሆናሉ። ኃጢአት በሁሉ ነበረ፥ አሁን ጽድቅ ለሁሉ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል ሁሉ እንዲያው፥ ያለ ዋጋ፥ በጸጋ ይጸድቃሉ። ኢየሱስን ማስተስሪያ እንዲሆን ያቆመው እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ማስተስሪያ የሆነ በደሙ ነው፥ መስተስሪያው የሚገኝበት በእምነት ነው። መሠረቱ የእርሱ ደም፥ መንገዱ የእኛ እምነት ነው። ሐዋርያው «እግዚአብሔር ይህን ያደረገው በሁለት ምክንያት ነው» ይላል፤ 1ኛ፤ በፊት፥ በዱሮ ዘመን፥ የተደረገውን ኃጢአት ሲያሳልፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው። 2ኛ፤ በአሁኑ ዘመን የሚያምኑትን ለማጽደቅ እንዲችልና ይህን ሲያደርግ ጽድቁን ለማሳየት ነው። ኢየሱስ ማስተስሪያ ሆኖ ደሙን ባያፈስ ኖሮ በእውነተኛ ፍርድ የሚፈርደው እግዚአብሔር የሰውን ኃጢአት ለማሳለፍና ለመተው፥ ሰውንም ለማጽደቅ፥ ባልቻለም ነበር፤ ለምን? ቢባል፥ ለማጽደቁ መሠረት፥ እርሱም ከሕግ ጋር የሚስማማ መሠረት፥ ይኖር ዘንድ የግድ አስፈላጊ ነውና። ይህስ ባይሆን የዳኛው ታማኝነት በተነካ (በተነቀፈ) ነበር። ኢየሱስ ግን መጥቶ ስለ ዓለም ኃጢአት ሲል ደሙን ካፈሰሰ፥ እንደ ሕጉ ትዕዛዝ የኃጢአት ደመወዝ ተከፍሎ ነበርና፥ እግዚአብሔር ሰውን ለማጽደቅ ችሎአል። ኢየሱስም ለዚህ ሥራ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ተመድቦ፥ ተቀብቶ፥ ማስተስሪያ ተደርጎ፥ ቆሞ ነበርና (1ኛጴጥ.1፡20-21። ራእይ 13፡8)። እግዚአብሔር ወደ ዓለም መምጣቱን ደም ማፍሰሱንም አይቶ፥ በዚያ መሠረት:- 1ኛ፤ የድሮ ቅዱሳንን ኃጢአት አሳልፎ ትቶ ነበር፤ 2ኛ፤ በዚያ ደም አምኖ ማስተስሪያውን የተቀበሉትን ሰዎች ኃጢአት ዛሬ ደግሞ አሳልፎ ሊያጸድቃቸው ይችላል። ይህንንም ሲያደርግ ጻድቅ ሆኖ ይታያል እንጂ ሊወቅሰው የሚችል የለም።

ቊ.27-31፡- እንግዲያስ፥ ሕግ ሰውን በማጽደቅ ፈንታ ከፈረደበት፥ ጽድቅም የሚገኝበት ያለ ሕግ ሥራ፥ በእምነት፥ ከሆነ ሰው የሚመካበት ነገር የለም። እፍ ሁሉ ተዘጋ፥ (ቁ.19።) አይሁድ የእግዚአብሔር ወገን በመሆናቸው፥ አሪትን በመቀበላቸውና የኪዳኑን ምልክት በመሸከማቸው ተመክተው ነበር። አሁን ግን ይህ ሁሉ ተወግዶአል። አይሁድ እግዚአብሔር የእነርሱ እንደሆነ፥ የአሕዛብም አምላክ ሌላ እንደሆነ፥ ወደ ማሰብ ደርሰው ነበር። የለም፥ እግዚአብሔር የሁሉም አምላክ ነው። ሰውንም ሁሉ፥ የተገረዘን ያልተገረዘንም፥ የሚያጸድቅበት በአንድ መንገድ ነው፤ እርሱም በእምነት። ይህንስ ስንል ሕግን እንሽራለንን? ሉረ አይሁን! ሕግ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆነና ጽድቅ ለሁሉ፥ አስፈላጊ እንደ ሆነ ገልጦአል። ያንም የሕግ ቃል እናጸናለን። ወይም ደግሞ «ሻራችሁት፤ የሕግ ትእዛዝ እንዳይፈጸም አደረጋችሁ» ቢባል፤ የለም፥ አንሽረውም! ሰው ሊፈጽም ያልቻለውን እናስፈጽማለን እንጂ! (8፡3-4።)

ማስገንዘቢያ፡- ከእነዚህ ከአለፉት ቁጥሮች 3 ነገሮችን መገንዘብ ይገባናል።

1ኛ፤ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከሕግ ሥራ ውጭ የሆነ ጽድቅ ነው። ይህንም ነገር ግልጥ ለማድረግ ጳውሎስ በዚህ አንቀጽ ላይ ደጋግሞ ጽፎታል። ቁ.21፡- «ያለ ሕግ» ቁ.22፡- «በማመን የሚገኝ»፤ ቁ.25፡- «እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ»፤ ቁ.25 ደግሞ፡- «በእምነት የሚገኝ»፤ ቁ.28፡- ያለ ሕግ ሥራ በእምነት» ብሎ ነገሩን አረጋግጦአል። የእግዚአብሔር ጽድቅ ከሕግ ሥራ ውጭ ነው (ቲቶ 3፡5)፤ ደግሞ፥ ያለ ዋጋ በነፃ የምናገኝ የጸጋ ስጦታ ነው። ቁ.25፡- «እንዲያው በጸጋው»፤ ምዕ.5፡16-18፡- «ስጦታው... ስጦታው... የጽድቅ ስጦታ ... ስጦታው...» ይላል። ምዕ.6፡23፡- «የጸጋ ስጦታ»፤ ኤፌ.2፡8፡- «የእግዚአብሔር ስጦታ» ይላል። እንግዲያስ እኛ ደግሞ የእግዚአብሔር ጽድቅ በታላቅ ዋጋ ተገዝቶ (1ኛጴጥ.1፡18-19) በነፃ፥ በእምነት፥ የሚገኝ ስጦታ እንደ ሆነ እርግጠኞች እንሁን።

2ኛ፤ የተገረዘ ስለ እምነት ያልተገረዘም በእምነት፥ ሁለቱም በእምነት ይጸድቃሉ እንጂ አይሁዳዊ በመገረዙ አይድንም፥ የአሕዛብ ወገንም ባለመገረዙ አይጠፋም፥ (ቁ.29 እና 30።) ይህም እላይ በምዕ.2፥ ቁ.25-29 ላይ ከተባለው ትርጉም ጋር የሚስማማ ነው። ምልክቱ ያለው ሰው በእምነት እንጂ በምልክቱ አይድንም፤ ምልክቱም የሌለው ሰው ምንም ምልክቱ ባይኖረው ስንኳ፥ በእምነት ይድናል። መገረዝም የጥምቀት ምሳሌ ነው። ጥምቀት ምልክት ነው እንጂ ማዳኛስ አይደለም። ማዳኛ እምነት ነው። «እንግዲህ የጥምቀት ጥቅሙ ምንድር ነው?» ቢባል (3፡1) መልሱ እላይ እንደ ነበረ «በሁሉ ነገር ብዙ ነው» ይባላል። አስቀድሞ እንደ መገረዝ ሆኖ፥ በኪዳኑ ያገባል፤ ሁለተኛም፥ የጌታን ትዕዛዝ ይፈጽማል፥ (ማቴ. 28፡19 እና 20)። እነዚህም ቀላሎች ነገሮች አይደሉም።

3ኛ፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በኢየሱስ በኩል ሁለት ነገሮች እንዳሉ እናገኛለን፤ 1ኛ «ቤዛነት» (ቁ.24)፥ 2ኛ «ማስተስሪያ»፥ (ቁ.25።)

በአማርኛችን «ቤዛነት» የተባለው ቃል፥ ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈበት በግሪክ ቋንቋ «አፖሉትሮውስስ» ይባላል። ይህ ቃል ደግሞ በቈላ. 1፡13፤ 14፤ በ1ኛጢሞ.1፡18 እና በኤፌ. 1፡7 ላይ ተጽፎ ይገኛል። «አፖሉትሮውስስ» የተባለው ቃል ፍቺ «መዋጀት» ወይም ደግሞ «መልሶ መግዛት» ነው። በመፈጠራችን የእግዚአብሔር ነበርን፥ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጠፋን (ተለየን)፥ እግዚአብሔርም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መልሶ ገዛን።

በአማርኛ ደግሞ «ማስተስሪያ» የተባለው ቃል በግሪክ ቋንቋ «ህላስሞስ» ይባላል። ይህ ቃል ደግሞ በ1ኛዮሐ. 2፡2 እና በ9.4፡10 ላይ ተጽፎ ይገኛል። በዘፀአ. 25፡17-25 እና በዘሌዋ. 16፡13-17 ላይ የተጻፈለት የ«ማስተስሪያ መከደኛ» አሳብ ይዞ «ህላስሞስ» ማለት «መከደኛ» ማለት ነው። ኃጢአታችን እግዚአብሔርን አስቀይሞ ነበር። ኢየሱስ ባደረገው ሥራ ያ ቅያሜ ተወግዶአልና እግዚአብሔር እንደገና በአባትነት ዓይን አይቶን ከተለያየንበት ወደ ኅብረት ይቀበለናል።

* * *

# ምዕራፍ 4

1. እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን? 2. አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም። 3. መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። 4. ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ 5. ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል። 6. እንደ ዚሁ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቈጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል፦

7. ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤
8. ጌታ ኃጢአቱን የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።

9. እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረ? ወይስ ደግሞ ስለ አለመገረዝ? እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት እንላለንና። 10. እንዴት ተቈጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም፥ ሳይገረዝ ነበር እንጂ። 11. ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቈጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው፥ 12. ለተገረዙ ትም አባት እንዲሆን ነው፤ ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው።

13. የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም። 14. ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተስፋውም ቃል ተሽሮአል፤ 15. ሕጉ መቅሠፍትን ያደርጋልና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም።

16.17. ስለዚህ ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተስፋው ቃል እንዲጸና እንደ ጸጋ ይሆን ዘንድ በእምነት ነው፤ እርሱም፦ ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ ተብሎ እንደተጻፈ፥ ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው። 18. ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፥ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ። 19. የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑ በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ 20.21. ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም። 22. ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት። 23. ነገር ግን፦ ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ፤ 24.25. ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው።

# ምዕራፍ አራት

በዚህ ምዕራፍ ታላቅ የ«መቈጠር» ትምህርት አለን። አብርሃምን ማስረጃ አድርጎ እርሱ ስንኳ በሥራው እንዳልጸደቀ፥ ነገር ግን በእምነቱ ምክንያት ጽድቅ እንደ «ተቈጠረለት» ይነግረናል። ለእርሱ (ለአብርሃም) እንደ ተቈጠረ እንዲሁ ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን ለሆኑት፥ ለልጆቹ ሁሉ «ለምናምነው ለእኛ»፥ ይቈጠራል።

ቊ.1-8፦ ጳውሎስ በምዕ. 3፡27-30 ላይ «ትምክህት ቀርቶአል፤ ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቈጥራለን እግዚአብሔር የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው፤ የተገረዘን ስለ እምነት፥ ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ነው» ብሎ ነበር። ይህ ከቶ እውነት ይሆን ይሆንን? ጽድቅ ለአሕዛብ ደግሞ ይሰጣልን? ሰው ሳይገረዝ ሊጸድቅ ይችላልን? ሰውስ የሚጸድቅበት በሥራ ሳይሆን በእውነት በእምነት ነውን? ይህ ሁሉ ከሆነማ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ? አብርሃምም ተገቢ ማስረጃችን ነው። የአይሁድ አባት ነው፤ የመገረዝ መጀመሪያ ነው በሥራም «የእግዚአብሔር ወዳጅ» እስኪባል ድረስ ከሁሉ ብልጫ ያለው ነው። አብርሃም በሥራ ሳይሆን በእምነት የጸደቀ ከሆነ ሌላም የአብርሃም ልጅ የሆነ ሁሉ በእምነት እንደሚጸድቅ ግልጥ ነው። ነገር ግን ከቶ እውነት ይሆን ይሆንን? «ትምክህት ቀረ» ሲባል እንደ አብርሃም የመሰለ ሰው የሚመካበት እንደሌለው ማለቱ ነውን? «አፍ ሁሉ ተዘጋ» ሲባል ከቶ የአብርሃም አፍ ጭምር ተዘግቶአልን? ቃሉን አጽንቶ «አዎን» ብሎ ሐዋርያው በዚሁ ምዕራፍ በሙሉ በምዕ. 2 እና በምዕ. 3 ላይ የተባለው ነገር ሁሉ ለአብርሃም ስንኳ እንደተጻፈ እያረጋገጠ ፍርድ በሁሉ እንደ ሆነ፥ እንዲሁ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሚያምኑ ሁሉ እንደሚቈጠር ያስረዳል።

የለም፥ በሰው ፊት እንደሆነ እንጂ በእግዚአብሔር ፊት አብርሃም ስንኳ የሚመካበት ነገር የለውም። ጳውሎስ ቃሉን ይደግፍ ዘንድ የሕግ (የኦሪት) መጽሐፍን ያስመሰክራል። «መጽሐፍ ምን አለ?» መጽሐፍማ «አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆና ተቈጠረለት» ይላል፥ (ዘፍጥ.15፡6)። ይኸው ጽድቅ «ተቈጠረለት» እንጂ የለውም ነበር! ለሠራው ሥራ የሚሆን ተገቢ ደመወዝ ቢሆን ኖሮ «ተከፈለለት» በተባለ ነበር እንጂ «ተቈጠረለት» ባልተባለም ነበር። ሥራ ላልሠራ ሰው ግን በጸጋ ከተሰጠ መጽሐፉ «ተቈጠረለት» ሲል ከነገሩ ጋር የሚስማማውን ቃል ተናግሮአል። መጽሐፉ «የተቈጠረለት እግዚአብሔርን ስላመነ፥ ስለ እምነቱ፥ ነበረ» ይላል። ይህም የመቈጠር ነገር ስለ አብርሃም ብቻ አልተጻፈም። ስለ ዳዊት ደግሞ፥ ስለዚያ ሁለተኛው ታላቅ የአይሁድ መሪ፥ ስለ

እርሱ ደግሞ ተጽፎአል። ስለምን ቢባል፥ በመዝ. 31፡1 እና 2 ላይ የተናገረው ስለ ራሱ ነውና። ዳዊት «ብፅዕና ያለው ኃጢአቱ ያልተቈጠረበት ኃጢአተኛ ነው» ብሎ ይህን የጽድቅን አቈጣጠር ነገር ያወቀው ራሱ ዳዊት አስረድቶአል።

ቍ.9-25፡- ለአብርሃም በእምነቱ ምክንያት ጽድቅ እንደ ተቈጠረ እንጂ በሥራው እንዳልጸደቀ ተረጋግጦአል። አሁንም፥ «ይህ ለሰው ሁሉ ነውን? ወይስ ለተገረዙ ብቻ ነውን?» የሚል ጥያቄ ይነሣል። እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ እንደ ተቈጠረለት ተብሎአል። ይሁን እንጂ ይህ ቃል ለሁሉ ሊባል ይቻላልን? በቁ.9 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልሱ በቁ.23 ላይ ይገኛል። ቁ.9፡- «እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረ? ወይስ ደግሞ ስለ አለመገረዝ? ለአብርሃም እንደተቈጠረለት ተባለ» ሲል፥ ቁ.23 «ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ» ብሎ መልስን ይሰጣል።

ጳውሎስ የእግዚአብሔር ጽድቅ «ለሚያምኑ ሁሉ» እንደ ሆነ ጽፎአል (3፡21፤22)፥ «ያለ ሕግ ሥራ በእምነት ነው» ብሎአል፥ (3፡28) «ያልተገረዘ በእምነት ይጸድቃል» ብሎአል፥(3፡29፤30)። አብርሃም በእምነት እንደ ጸደቀ ከቁ.1-8 አይተናል፤ አሁን ከቁ.9-25 ይህ የተቈጠረለት ጽድቅ በእውነት ለሚያምኑ ሁሉ፥ ለአይሁድም ለአሕዛብም፥ ለተገረዘም ላልተገረዘም፥ እንደ ሆነ እናያለን።

«ጽድቅ ተቈጠረለት» የተባለለት ለመገረዝ መጀመሪያ ለአብርሃም ምንም ቢሆን፥ የተቈጠረለት ገና ሳይገረዝ በፊት ነው። ጽድቅ የተቈጠረለት እግዚአብሔርን ባመነ ጊዜ ነው፥ (ዘፍ.15፡5፤6)። በዚያን ጊዜ እስማኤልም ይስሐቅም አልተወለዱም ነበር። ጽድቅ ከተቈጠረለት በኋላ የሚስቱን ባሪያ አገባና ከ1 ዓመት በኋላ እስማኤል ተወለደ። ይህ ሲሆን አብርሃም የ86 ዓመት ሰው ነበረ፥ (ዘፍ.16፡1-4፤15፤16)። አብርሃም የ99 ዓመት ሰው ሲሆን፥ እርሱም ማለት ጽድቅ ከተቈጠረለት 14 ዓመት በኋላ፥ እግዚአብሔር ኪዳን ገባና በመካከላቸው የነበረው የኪዳኑ ምልክት የሚሆን የመገረዝን ሥርዓት ሰጠው፥ (ዘፍ.17፡1-14)። ከዚያም በኋላ አብርሃም ተገረዘ፥ (ዘፍ.17፡25፤26)። ስለዚህ፥ ጽድቅ የተቈጠረለት ሳይገረዝ በፊት እንደ ሆነ ግልጥ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ላልተገረዙት ደግሞ ጽድቅ በመቈጠሩ አባታችን አብርሃም ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው፥ (ገላ.3፡7)። ይህም የብፅዕና ወይም የጽድቅ መቈጠር ምሳሌ የሆነ የተስፋ ቃል (ዘፍ.17፡1-8) የተሰጠበት መሠረት «ያለ ሕግ» በእምነት ያገኘው ጽድቅ ነው እንጂ ሕጉ (አሪት) አይደለም። ይህ ሁሉ የሆነ፥ ሕግ (አሪት) ሳይሰጥ ብዙ ዓመት በፊት ነበረና (ገላ.3፡16-18) በዚያ የተስፋ ቃል «ዘርህ» ሲባል የእምነት ዘር፥ ከአይሁድም ከአሕዛብም የሚያምኑት፥ ማለቱ ነው እንጂ የሕግ ዘር፥ አይሁድ ብቻ፥ ማለት አይደለም። የተስፋ ቃል «ለብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ» ብሎት ነበር (ዘፍ.17፡4፤5፤6)፤ ስለዚህ «አባታችን አብርሃም» የተባለው (ቁ.1)

«የሁላችን አባት» ሆኖአል፥ (ቁ.16፤17)። ይህም የሆነ ስለ አመነ ነው። መቶ ዓመት በመኖሩ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋ ተመልክቶ እግዚአብሔር ሕይወት እንደሚሰጥ፥ ልጅም በሌለው ጊዜ እግዚአብሔር እንዳለ እንደሚያደርግ፥ አምኖ «ሆኖአል» ብሎ «ተመስገን!» አለ። ስለዚህ፥ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት። «ተቈጠረለት» የሚለው ቃል ግን ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፤ ነገር ግን እላይ እንዳየን ለእኛ ለምናምነው ደግሞ ይቈጠራል። አብርሃም ያመነበት ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ በእግዚአብሔር ነበረ፤ (ዘፍ.15፡5፤6። ሮሜ 4፡16፤17።) እኛም እንደዚሁ ሁሉ የሞተውን ኢየሱስን ባስነሣው በእግዚአብሔር ማመን አለብን፥ (ቁ.24፤25)።

ማስገንዘቢያ:-ዋና የዚህ ምዕራፍ ትምህርት የጽድቅ መቈጠር ትምህርት ነው። እኛ «ሰው ጻደቀ» ስንል ምን ማለታችን ነው? «ጽድቅ» የተባለው ቃል የፍርድ ቤት ቃል ሆኖ «ማጽደቅ» ዳኛው የሚያደርገው ነገር ነው፥ (መዝ.142፡2)። ዳኛው የከሳሽንና የተከሳሽን የሁለቱን ወገኖች ቃል አድምጦ በሁለቱ አመዛዝኖ ብያኔውን ይሰጣል። ተከሳሹን ወይም ያጸድቃል ወይም ይፈርድበታል። ሰው ስንኳ ቃሉን (ብያኔውን) ለእግዚአብሔር በመስጠት እግዚአብሔርን ለማጽደቅ ይችላል! (መዝ.50፡4። ሉቃ.7፡29)። እንደዚሁ ነው እግዚአብሔር፥ ቃሉን (ብያኔውን) ለእኛ በመስጠት፥ የሚያጸድቀን። እኛ ግን በእውነት ጻድቃን አይደለንም፥ ኃጢአተኞች ነን እንጂ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ሲል፥ እርሱም ስለ አደረገልን ሥራ፥ ለሚያምኑ ሁሉ ጽድቅን ይቈጥራል። በራሳችን ጻድቃን አይደለንም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ሲል ይበይንልናል እንደ ጻድቃንም ይቈጥረናል፥ (2ኛቆሮ.5፡21)። ሁላችን የምንጸድቅበት በዚህ በተቈጠረልን ጽድቅ ነው።

ሐዋርያው የአብርሃምን ታሪክ ጠቅሶአል፤ እኛም ያን ታሪክ ብንገነዘብ መልካም ነበረ።

በአብርሃም ዘንድ የሃይማኖቱ ታሪክ ቅደም ተከተሉ እንደዚህ ነበረ:- 1፤ ጻደቀ። 2፤ ተገረዘ። 3፤ ሥራን ሠራ።

ከሁሉ አስቀድሞ ጻደቀ፤ ማለት፥ እግዚአብሔርን ስለ አመነ ጽድቅ ተቆጠረለት፥ (ዘፍ.15፡6)። ከጻደቀ 14 ዓመት በኋላ «ሳይገረዝ በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ» (ዘፍ.17፡25፤26፤ ሮሜ 1፡11)። ከተገረዘም 13 ዓመት ያህል*በኋላ ታላቅ ሥራውን ሠራ፥ (ዘፍ.22፡1-19)።

* «13 ዓመት ያህል» የተባለበት ምክንያቱ:-

ይስሐቅ የተወለደው አብርሃም ከተገረዘ 1 ዓመት በኋላ ነው (ዘፍ.17፡24፤ 21፡5)። ይስሐቅ ደግሞ መሥዋዕት የሚነድድበቱን እንጨት «ከሩቅ» ለመሸከም በመቻሉ (ዘፍ.22፡4፤6) በዚያን ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ የ12 ዓመት ልጅ እንደሆነ ያሰኛል። ከመገረዙ እስከ ሥራው ድረስ 13 ዓመት አለፈ ማለት ነው።

እንግዲህ ሥራውን የሠራ ከጸደቀ ከ27 ዓመት በኋላ ነው። ይህ የአብርሃም የታሪኩ ቅደም ተከተል ለሁላችን የሚሆን ማስረጃ ነው። ጽድቅን የምናገኘው (የሚቈጠርልን) በእምነት ነው፤ ባመንንም ጊዜ ነው። ካመንን በኋላ ያገኘነውን የጽድቅ ማኅተም የሆነ የጥምቀትን ምልክት መቀበል ይገባናል። ከዚያም በኋላ ደግሞ እምነታችን እውነተኛና ሕያው እምነት ከሆነ መልካም ሥራን (ምግባርን) እንሠራለን። መልካም ሥራን የማንሠራ ከሆነ እምነታችን እውነተኛና ሕያው ሳይሆን የሐሰትና የሞተ ነው፥ (ያዕ.2፥14-26።) እምነታችን ከሥራ ተለይቶ ሳይሆን አብሮ ያደገ እንደሆነ፥ እምነታችን ይፈጸማል ጽድቃችንም ይታተምልናል። ሥራ እምነትን እንዲከተል የግድ አስፈላጊ ነው፤ ይህ ካልሆነ፥ የሚያድነንና እውነተኛ እምነት አይደለም። እምነታችን ግን እውነተኛና ሕያው ከሆነ እኛ ሳናስብ ሳንጨነቅበትም፥ እምነታችን እንደ መልካምና ሕያው ዛፍ ሆኖ የሥራን ፍሬ አውቆ ያፈራል። በብሉይ ኪዳን ዘመን መገረዝ፥ ወይም በአሁኑ ዘመን መጠመቅ፥ ላገኘነው ጽድቅ የእግዚአብሔር ማኅተም እንደሆነ እንዲሁ ሥራ የእምነታችን ማኅተምና ምልክት ነው። ሥራችን ከብዙ ዓመት በፊት ምናልባት የኖረን የእምነታችን ማኅተምና ምልክት ነው።

መገረዝ፥ ስለዚህም ደግሞ ጥምቀት፥ በእውነት ምን እንደሆነ በቁ.11 እናያለን። «ሳይገረዝ በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ» ይላል። ማኅተም ነው፥ ምልክትም ነው።

ከዚህ በፊት አግኝቶ በነበረው ጽድቅ ላይ የእግዚአብሔር ማኅተም ነው። ውል በማኅተም እንደሚጸና እንዲሁ መገረዝ ለተገኘው ጽድቅ የእግዚአብሔር ማኅተም ነው። አብርሃም በእምነት ጽድቅን ተቀብሎ ነበር፤ በተገረዘም ጊዜ እግዚአብሔር አተመለት። እምነት መቼም ባይቀድም ኖሮ ጽድቅ ባልተገኘም ነበርና እግዚአብሔር ያትምለት ዘንድ ባልቻለም ነበር። እምነት ካልቀደመ መገረዙ ከንቱ በሆነ ነበር ማለት ነው። እምነት ግን ሲቀድምና አብርሃም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ በኋላ ቢገረዝ እግዚአብሔር ስጦታውን አተመለት። በመገረዙ ጸድቆ አይደለም፤ በመገረዙ ግን በእምነት አግኝቶት የነበረው ጽድቅ ታተመለት። በብሉይ ኪዳን ዘመን መገረዝ የነበረው ሁሉ በአዲስ ኪዳን ዘመን ጥምቀት ሆኖአልና ጥምቀት ዛሬ የሚያደርግልንን ሥራ ልናስተውል እንችላለን። ያለ እምነት ማኅተሙ ከንቱ ነው፤ እምነት ካለ ግን ማኅተሙ ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጣል።

አብርሃም ባይገረዝ ኖሮሳ? ጽድቅ የተቈጠረለት ስለ እምነት እንደ ሆነ እናውቃለን። ከመገረዙ በፊት እንደ ተቈጠረለት እናውቃለን። ይህም ከሆነ፥ «የተቀበለው እንደ ምን አድርጎ ይጠፋበታል?» ይባል ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ በሌላ ወገን ደግሞ የአብርሃም ልጆች ሁሉ እንዲገረዙ ታዝዘው እንደነበረ እናያለን። ደግሞ፥ «ያልተገረዘው ወንድ ሁሉ... ያች ነፍስ ከወገኖችዋ ተለይታ ትጠፋለች፥ ኪዳኔን አፍርሳለችና» ተባለ፥ (ዘፍጥ.17፥13፤14)። ስለዚህ፥ ሰው በዚያ ዘመን

አልገረዙ፥ ወይም በዛሬ ዘመን አልጠመቀ፥ቢል አኳኋኑ በጣም አስጊ እንደ ሆነ እንረዳለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን አዝዞአል (ማቴ.28፡19-20)፤ ሐዋርያትም አዝዘውታል፥ (የሐዋ.2፡38፤ 10፥48)። ከጌታችን ጋር አብሮ የተሰቀለው አንደኛው «ከፉ አድራጊ» አመነ፥ እንደተጠመቀ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም፥ የተጠመቀም አይመስልም (ሉቃ.23፡39-43)። ሌሎችም ደግሞ በስደት ምክንያት፥ ወይም ጤና በማጣት፥ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ሳይጠመቁ ይሞቱ ይሆናል። ይሁንና፥ ሰው የሚጸድቅበት በእምነት እንጂ ሰው በመገረዝ ወይም በመጠመቅ እንደማይድን አይተናልና እነርሱ ይድናሉ። ነገር ግን መጠመቅ ሲችል ሳለ ሳይጠመቅ የቀረ ክርስቲያን በጣም እንደሚጎዳ እውነተኛ ነገር ነው።

እንግዲያስ መገረዝ ማኅተም ነው፥ ጥምቀትም ማኅተም ነው። ነገር ግን ማኅተም ብቻ አይደለም፤ ደግሞ ምልክት ነው። በእግዚአብሔር ወገን (በኩል) ማኅተም ሲሆን በሰው ወገን በኩል ምልክት ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር ኪዳን ገባ፥ (ዘፍጥ.17፡2-11)። ኪዳኑንም ካስታወቀው በኋላ «የቁልፈታችሁን ሥጋ ትገርዛላችሁ፥ ምልክትም ይሆናል። በእናንተና በእኔ መካከል ላለው ኪዳን» አለ፥ (ዘፍጥ.17፡11)። እንግዲህ ሰው በተገረዘ ጊዜ በዚያ ኪዳን ውስጥ መግባቱን ያመለክት ነበር። እንደዚሁ ዛሬ እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን-ገብቶ እንድንጠመቅ አዝዞአል። እንግዲህ የተጠመቀ ሰው በኪዳኑ እንደ ገባ ያመለክታል። የክርስቶስ መሆኑን፥ ከሌሎችም ሰዎች ልዩ መሆኑን፥ ያመለክታል።

ስለዚህ፥ መገረዝና ጥምቀት አንድ ዓይነት ናቸው። በእግዚአብሔር ወገን (በኩል) ሥርዓቱ ማኅተም ነው፤ በሰው በኩል ደግሞ ምልክት ነው። ምልክት ብቻ አይደለም፤ ከምልክት እጅግ የበለጠ ነገር ነው። እንግዲያስ ጥምቀትን እናክብረው።

ጽድቅ ይቈጠርልን ዘንድ ማመን ያስፈልጋል። ባልተገባ ነገር ብናምን ግን እምነታችን አይጠቅምምና በምን ነገር ማመን እንደሚገባን ብናውቅ መልካም ነው። በሌላ ሃይማኖት የሚተዳደር ሰው ሁሉ ያምናል፤ ነገር ግን በሚገባ ነገር አያምንምና እምነቱ አያጸድቀውም። እንደዚሁ ደግሞ አጋንንት ያምናሉ፤ እምነታቸው ግን ከገሃነመ እሳት አያድናቸውም፥ (ያዕ.2፡19)። በዚህ ምዕራፍ ግን (ሮሜ 4፡24-25) ጽድቅ ይቈጠርልን ዘንድ በምን ማመን እንደሚገባን ተጽፎአል። «ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን፥ እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን፥ ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን፥ ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው» ይላል።

አብርሃም ጽድቅን ያገኘበቱን እምነት ሲያምን «ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ፥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ፤ ... የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም በሚችል አምኖአልና (4፡17፤18፤21) ጽድቅ ተቈጠረለት። ለእኛ ደግሞ የሚቈጠርልን ከሆነ እኛ እንደዚሁ «ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው»፥ ጻድቃንም ያልሆኑትን እንደ ጻድቃን በሚቈጥር፥ የሰጠውንም ተስፋ በፈጸመው፥

ማመን ያስፈልገናል። አሳልፎ እንደ ሰጠው፤ ከሙታንም እንዳስነሣው፤ በእነዚህ በሁለቱ ነገሮች ማመን ያስፈልገናል። አሳልፎ ለምን ሰጠው? «ስለ በደላችን» ይላል። የኃጢአትን ዋጋ ለመክፈል፤ ኃጢአታችንም ተሸክሞ በእኛ ፈንታ ለመሞት፥ (ኢሳ.53፡4-6)። ይህ አንድ ነገር ነው። ደግሞ ሌላ አለ። በሁለተኛው ነገር ደግሞ ማመን ያስፈልገናል፤ እርሱም እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው። ለምን አስነሣው? «እኛን ለማጽደቅ» ይላል። ማለት፥ መቀበሉን ለማስረዳት። ጌታችን ኢየሱስ ዕዳችንን ከፍሎ ነበር፤ እግዚአብሔር ኢየሱስን በማስነሣት ደረሰኙን አሳየን። ሁሉ ተከፈለ፤ እግዚአብሔርም «በቃ! ነፃ ውጡ!» ብሎ አጽድቆናል። መጠራጠር አያስፈልግም፥ እግዚአብሔር ታርቆናል፥ (2ኛቆሮ.5፡19)።

እግዚአብሔር ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን፥ እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን፥ ጌታችን ኢየሱስን አስነሥቶአል። በዚሁም እንመን።

በእነዚህ በሁለቱ ነገሮች ለሚያምን ሰው ጽድቅ ይቆጠርለታል።

* * *

# ምዕራፍ 5

1. እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ 2. በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። 3.4. ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤ 5. በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።

6. ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። 7. ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። 8. ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። 9. ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን። 10. ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ 11. ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።

12. ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ 13. ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤ 14. ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።

15. ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። 16. አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። 17. በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።

18. እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። 19. በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ 20.21. ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።

# ምዕራፍ አምስት

በምዕራፍ 3 ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ መገለጥና በምዕራፍ 4 ስለዚያ ጽድቅ «መቈጠር» ካነበብን በኋላ፥ አሁን በምዕራፍ 5 አስቀድሞ በጸደቀ ሰው ሕይወት፥ ከዚያም በኋላ በዓለም ዘንድ፥ ስለ ጽድቁ ስፋት እናነባለን። ይህ ምዕራፍ ትልቁ የአዳምና የክርስቶስ ማመዛዘኛ ምዕራፍ ነው።

ቍ.1-11፦ ጽድቅን ማግኘትንም ማወቅ፤ እንደምን ያለ ታላቅ ነገር ነው! «ከጸደቅን»! ከጸደቅን እንዴት ያለ በር ተከፈተልን! «ከጸደቅን»! አሳቡን ጥቂት እንያዝ። እኛ ጸድቀናልን? ፍርድ በሁሉ ነበረ፥ ስለዚህም በእኛ ሆነ። እንዲሁ አሁን ጽድቅ ለሁሉ ሆነ፥ ስለዚህም ደግሞ ለእኛ ነው። መገለጡን መቈጠሩንም አይተናል። ተቀብለነዋልን? «ከጸደቅን»! ትልቅ ነገር ነው።

ከጸደቅን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰላምን እንያዝ። እግዚአብሔር ማሰናከያን አስወግዶ ታርቆናልና እኛም እንታረቀው፥ (2ኛቆሮ.5፡18-20)። የተገኘልንን ሰላም እንያዝ። በእግዚአብሔር ዘንድ ሰላምን እንያዝ እንጨብጥም እንጂ ገና እንደ ተጣላን መሆናችንን አናስብ፤ የሚያስታርቀንን አንፈላልግ፤ ሌላ ጽድቅን ለማግኘት አንጣጣር። «እርይ!» ብለን እንረፍ።

ጥንዳንድ ትርጉም ደግሞ ይህ ቁ.1 «ሰላም አለን» ተብሎ ይተረጎማል። ይህም የሆነ እንደሆን በቁ.1 እና 2 ላይ ያለፈው፥ ያሁኑና፥ የወደፊቱም ነገር ታጽፎ ይገኛል። ባለፈው፥ ሰላምን አገኘን፥ ጥሉ ተወገደ፥ ትግሉ አለፈ፥ ከቁጣ ወደ ጸጋ ከሞትም ወደ ሕይወት አለፍን፥ «ሰላም አለልን»። ባሁኑ መግባትን አግኝተናልና የቆምንበት በእግዚአብሔር በጸጋው ጮራ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ራሱ ወዳለበት ወደ ቤተ መቅደሱ ወደ ውስጡ ክፍል፥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን፥ ገብተን በእግዚአብሔር ፊት ቆምን፥ (ዕብራ.9፡2-12፤10፥19-20)። በወደፊቱም፥ በእግዚአብሔር ክብር ተካፋዮች በመሆናችን «እንመካለን»። «እንመካለን» እንጂ «ተስፋን እናደርጋለን» አይልም። የክብርን ተስፋ የሰጠን እግዚአብሔር ራሱ ነውና ክብሩን እንድንካፈል የተቈረጠ ነገር ነው። ነገሩ እንደ አብርሃም ነገር ነው። «አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ» እንደተባለ ነው፥ (ዮሐ.8፡56)። ወይም ደግሞ «የሰጠውንም ተስፋ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ... ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ» እንደተባለ ነው፥ (ሮሜ 4፡19-21)። አብርሃም «ተስፋ ማድረግን» ብቻ አላደረገም፤ ነገር ግን «በእርግጥ ይፈጽምልኛል» ብሎ፥ በዚያን ጊዜ ተቀብሎት እንደነበር ቈጥሮ በመቀበሉ ተመካ። እንደዚሁ ለእኛም፥ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶናልና፥ የክብሩ ተካፋዮች በእርግጥ እንሆናለን» ብለን

ተስፋን ማድረግ ብቻ ሳይሆን በእውነት አሁን ስንኳ በዚያ ክብር እንደገባን ቈጥረን እንመካለን፥ (ሮሜ 8፡18-21፤30)።

ይህ የጸደቀ ሰው የሰላም የደስታና የአለኝታ ሕይወት በመከራ ስንኳ እንድንደሰት ያደርገናል። ከመከራ ተስፋ ይፈጠራል! መከራም ያን ክብር ያስታውሰንና ያስመኘናል። በመከራ ስንሆን ሳለን ያ የክብር ተስፋ የተመሠረተበት በጽኑ መሠረት፥ እርሱም በእግዚአብሔር ፍቅር ነውና ተስፋችን እንደማያሳፍረን እናውቃለን። እንደሚወደንና እስከ መጨረሻ፥ ክብሩን እስከ መቀበል እንደሚያደርሰን እናውቃለን። እንደሚወደን የምናውቀው ክርስቶስ ስለ እኛ በመሞቱ ነው። በዚያ ዘመን ከወደደንና እስከ መስቀል ድረስ ከሄደልን፥ ዛሬስ ከጸደቅን በኋላ እንደምን ይበልጥ ከቁጣው ያድነን! «ምናልባት ይጥለን ይሆን?» ማለት፥ ወይም «እንደርስም፥ የክብር ተካፋዮች እኛ እንደምን እንሆናለን?» ብሎ መጠራጠር አያስፈልገንም። ኃጢአተኞች ስንሆን ሳለን ወደደን ሞተልንም! ከጸደቅንና ከታረቅን በኋላ እስከ መጨረሻ ድረስ በሕይወቱ ጠብቆ አድኖ ወደ ክብሩ እንድንገባ ያደርግ የለምን? ያደርጋል! ይህም ብቻ አይደለም። የንጉሥ ልጅ በአባቱ ተመክቶ «አባቴ ናቸው እኮ!» እንደሚል እንዲሁ እኛ የሚደርስብንን ስድብ ሆነ መከራ ሆነ ንቀን «ግድ የለም! እግዚአብሔር አባቴ ነው! አባቴ እግዚአብሔር ነው!» ብለን በእግዚአብሔር ተመክተን ምን ጊዜም ቢሆን እንደ አሸናፊዎች ሆነን እንኖራለን። የማግኘቱ ጥቅም የሚያደርሰን እስከዚህ ድረስ ነው።

<u>ቍ.12-21</u>፡- ሐዋርያው በጸደቀ ሰው ሕይወት ውስጥ የጽድቅን ስፋት ካስረዳ በኋላ! አሁን በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የጽድቅን ስፋት በዓለም ዘንድ ያሳየናል። በሰው ሁሉና በኃጢአት ሁሉ ላይ እንደሚደርስ እናገኛለን። በአንድ ኃጢአት ምክንያት ብቻ ኃጢአትና ሞት በሰው ሁሉ እንደተዛመተ፥ እንዲሁ የጸጋ ብዛትና የጽድቅ ስጦታ ብዛት፥ እንደተደረሰ ለሰው ሁሉ እናያለን።

«ስለዚህ ምክንያት» እስከዚህ ድረስ የጻፈውን ነገር ሁሉ በአንድ ጥቅልል ጠቅልሎ ሊጨርሰው ይፈልጋልና። ከምዕ.1 ጀምሮ እስከ ምዕ.3፡20 ድረስ ሰው ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆነ አመልክቶ ነበር፥ (3፡9)። ይህንም አሳብ እዚህ ላይ ደግሞ በትንሹ ይቀጥለዋል። እንደዚሁም ደግሞ ከምዕ. 3፡21 ጀምሮ እስከ ምዕ. 5፡11 ድረስ ለሚያምን ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሚቈጠርለት ጽፎአል፥ (3፡22፤ 4፡24-25)። ስለዚህም ነገር ደግሞ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ትንሽ ይጨምራል። እንግዲህ ሁለቱን አሳብ አንሥቶ፥ ማለት የኃጢአትን ስፋትና የጽድቅን ስፋት፥ በአጭር ቃል አገናኝቶ የጽድቁን ክፍል ይጨርሳል።

ኃጢአት በአንድ ሰው ምክንያት ወደ ዓለም ሁሉ ተላልፎ እንደ ገባና ሞት የገባበት ምክንያት በኃጢአት እንደሆነ አስቀድሞ ያስረዳል። ሞት የኃጢአት ማስረጃ፥ ወይም ደግሞ ምልክት ነው። ኃጢአት በሰው ሁሉ እንዳለፈ የምንረዳበት

ሞት በሰው ሁሉ በማለፉ ነው። ሰው እንደ አዳም ሕግን በመተላለፍ ማለት ሕግን እያወቀ በመበደል፥ የድፍረት ኃጢአት ባያደርግ እንኳ ይሞት ነበር። ነገር ግን ሕግ (ኦሪት) ገና አልመጣም ነበርና ሕግን አውቆ ተላልፎ ኃጢአትን ለማድረግ አይቻልም ነበር። ቢሆንም፥ በዚያ ዘመን ሁሉ፥ ማለት አዳም ኃጢአትን ካደረገ ጀምሮ ኦሪት እስከትሰጥ ድረስ፥ ሰው ሁሉ ይሞት ነበር። ሞት የመጣው በኃጢአት ምክንያት ነውና፥ ሰውም ሁሉ የሚሞት ሲሆን፥ ኃጢአት በሰው ሁሉ እንዳለፈ ተገለጠ፥ (ቁ.12-14።)

በመልእክቱ መጀመሪያ ክፍል፥ እንደዚሁም በዚህ ምዕራፍ ከቁ.12 እስከ 15 ድረስ፥ ኃጢአት በሰው ሁሉ እንዳለፈ ተነግሮአል። አሁን ደግሞ፥ እንደ መልእክቱ ሁለተኛ ክፍል ሆኖ፥ ከቁ.15 እስከ 21 ድረስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሚያምኑ ሁሉ እንደተረፈ እናገኛለን። ስለዚህ ከኃጢአት ይልቅ የክርስቶስ የጽድቅ መጠን እጅግ እንደ በለጠ እናያለን። የአዳም የኃጢአቱ ጠንቅ ቢሰፋ የክርስቶስ የጽድቁ ትሩፋት ከዚያ እጅግ በለጠ። አዳም ለክርስቶስ አምሳል ሆኖአል፥ ነገር ግን በተፃራሪው! ማለት፥ በአዳም የተበላሸ ሁሉ በክርስቶስ ተበጅቶአል፥ ያውም በበለጠ መጠን። አዳም የአንድ ወገን አባት ወይም አለቃ እንደሆነ እንዲሁ ክርስቶስ የአንድ ወገን አባት ወይም አለቃ ሆኖአል። አዳም ለልጆቹ አንድ እርስትን እንዳወረሰ ክርስቶስም ለልጆቹ አንድ እርስትን አወርሶአል። በሁሉ በኩል ግን የክርስቶስ ውርስ እንደሚበልጥ እናገኛለን።

አዳምና ክርስቶስ በሦስት መንገዶች ይመሳሰላሉ:-

1ኛ. ቁ.15:-በአዳም በደል ብዙዎቹ ሞተዋል።

በክርስቶስ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።

2ኛ. ቁ.16:-ከአዳም ዘንድ ፍርድ ለኩነኔ መጥቶአል።

በክርስቶስ የሆነው ስጦታ በብዙ በደል ለማጽደቅ መጥቶአል።

3ኛ. ቁ.17:-በአዳም በኩል ሞት ነገሠ።

በክርስቶስ በኩል የጽድቅን ስጦታ የሚቀበሉ ይልቁን በሕይወት ይነግሣሉ።

እንደዚሁ ደግሞ የአዳም ሥራና የክርስቶስ ሥራ በሁለት መንገዶች ይመሳሰላሉ:-

1ኛ. ቁ.18:-በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ

ለኩነኔ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።

በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።

2ኛ. ቁ.19፡-በአንድ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች ሆኑ።

በአንድ ሰው መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

ሕግ (ኦሪት) በአዳምና በክርስቶስ ዘመናት መካከል በደልን ለማብዛት ሾልኮ ገባ። ሕግ ሲበዛ በደል የግድ ይበዛል፤ በደልም የበዛበት ምክንያቱ ሰውን የበለጠ ቅዱስ ለማድረግ ነው፥ ደግሞም ኃጢአተኝነቱን በማስረዳት ሰውን ወደ መድኅኑ ለመምራት ነው፥ (ገላ.3፡24)። ሕግ ግን በመግባቱ ምክንያት፡-

ቍ.20፡21፡- ኃጢአት በበዛበት ዘንድ፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ።

እዚያ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ፥ ጸጋ ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ።

በአዳም የደረሰብንን ጉዳት አይተናል። ገና በእርሱ ብንሆን ከእርሱ እርስት እንሳተፋለን። ክርስቶስ ግን የአዳምን ጥፋት በሰራው ስላበጀ በእርሱ ብንሆን ከጸጋውና ከጽድቅ ስጦታው እርስት እንሳተፋለን። ኃጢአት ምንም ቢበዛ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በልጦ ሁሉን ሸፍኖአል። ከኃጢአት ስፋት ይልቅ የጽድቅ ስፋት ተንሰራፍቶአልና በክርስቶስ ላሉት ኩነኔ የለባቸውም።

<u>ማስገንዘቢያ</u>

ሀ) ሰው የሚሠራውና ሰው የሚወርሰው፥ ሁለት ዓይነት ኃጢአት እንዳለ እናያለን፥ (ቁ.12-14።) ኃጢአተኞች የሆንን ኃጢአትን ስላደረግን ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ስለ ተወለድን ነው። «ኃጢአተኞች ነንና ኃጢአትን እናደርጋለን» ነው እንጂ፥ «ኃጢአትን ስላደረግን ኃጢአተኞች ሆነን» አይደለም። «ከርኩስ ንጽሕናን የሚያወጣ ማን ነው? አንድም የለም» ሲል ኢዮብ እርግጡን ተናግሮአል፥ (14፡4)። እንዲሁም ደግሞ ጌታ «ከእሾህ ወይን፥ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም» ብሎ መስክሮአል፥ (ማቴ.7፡16-18) እኛ የአዳም ልጆች ነንና ኃጢአተኞች ሆነን እንወለዳለን ማለት ነው። ይህንም የሚያስረዳ የቅዱስ ዳዊት ታሪክ ነው። ዳዊት ፈጽሞ ቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ሰው፥ እንደነበረ እግዚአብሔር ራሱ መስክሮአል፥ (የሐዋ. 13፡22) ዳዊትም ቅዱስ ነበረና ኃጢአትን ለማድረግ ልማዱ ከቶ አልነበረም። ቢሆንም፥

በልቡ የኖረው ከአዳም የወረሰው ኃጢአት ወደ ኃጢአት አደረሰው። ዳዊት ባደረገው ኃጢአት ተጸጽቶ ይህን ያልለመደውን ያልወደደውንም ኃጢአት በምን ምክንያት እንዳደረገው ለማወቅ ሲጨነቅ «እነሆ በዓመፃ ተወለድሁ፥ እናቴም በኃጢአት አረገዘችኝ» በማለቱ ምክንያቱን ተረዳ፥ (መዝ. 50፡5) ቅዱስ ነበረና ኃጢአትን ማድረግ ምንም ባይወድ የአዳም ልጅ ነበረና ኃጢአትን አፈራ። በዚህ ምክንያት ነው ዕውቀት ወይም እእምሮ የሌላቸው አሕዛብ፥ እብዶችም፥ ሕፃናትም፥ ኃጢአተኞች ሆነው ተገኝተው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ካላገኙ በስተቀር የሚፈረድባቸው። በዚህ ምክንያት ደግሞ ቅዱሳን የተባሉት ሁሉ ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ እንረዳለን። ኢዮብ «ሰው ምንድር ነው ይጸራ ዘንድ ወይስ ከሴት የተወለደ ጻድቅ ይሆን ዘንድ? እነሆ በቅዱሳኑ ስንኳ አይታመንም፥ ሰማይም በፊቱ ንጹሕ አይደለም» ብሎአል፣ (ኢዮብ15፡14-15)። ዳዊትም «ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ» ብሎአል፣ (መዝ.13፡2-3)። ጳውሎስም «ልዩነት የለም፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» አለ፣ (ሮሜ 3፡23)። ይህ ነው ደግሞ ከዚህ በፊት ያገኘነው ነገር፤ ማለት፣ ለሰው ሁሉ ጽድቅ እንደሚያስፈልግ። በአዳም ኃጢአት ምክንያት ኃጢአት በሁሉ ላይ እንዳለፈ አይተናልና ከአዳም የተወለደ ሁሉ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ካላገኘ በስተቀር ከኃጢአትና ከፍርድ በታች እንደሚሆን እናውቃለን።

ለ) በቁ.15፡16፣17 እና 18 ላይ ከበደሉ ጋር የሚመዛዘን አንድ «ስጦታ» የተባለውን ነገር እናገኛለን። ይህ «ስጦታ» ምንድር ነው?

በቁ.15 ላይ «በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነ ስጦታ» እንደ ሆነ ተነግሮአልና ስጦታው ከክርስቶስ ዘንድ እንደ መነጨ እንረዳለን። በዚያ ቁጥር ደግሞ ስጦታው ከበደሉ ይልቅ «ለብዙዎች እንደ በዛ» ተባለ።

በቁ.16 ላይ ስጦታው «በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ» ተባለ። ስለዚህ ብዙዎች የሚበዛ በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነ፣ ለማጽደቅ የመጣ፣ ስጦታ እንደሆነ ተገለጠ።

በቁ.17 ደግሞ «የጽድቅ ስጦታ» ተባለ። ይህንም ስጦታ የሚቀበሉ በሕይወት ይነግሣሉ ተባለ።

በቁ.18ትም ደግሞ ስጦታው «ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ» ይላል።

ከዚህ ሁሉ የተነሣ «ስጦታው» ጽድቅ እንደሆነ እንረዳለን።

ይህ በእውነት በጣም የሚያሳስብ ነገር ነው። እንግዲህ ጽድቅ ለብዙዎች የሚሆን፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመነጨ (ቁ.15)፥ ሕይወትን ለማጽደቅ የመጣ

(ቁ.16)፥ በሕይወት የሚያነግሥ፥ ሰውም የሚቀበለው (ቁ.17)፥ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን እንደ ስጦታ ይሰጣል ማለት ነው። የሚሰጠውም በጸጋ ነው (ቁ.15)፥ ይህም «ጸጋ» ማለት አንዳች የግዴታ ነገር ሳይኖር እንዲሁ እንደስጦታ የተሰጠ ወይም የተደረገ ነገር ማለት ነው።

ጽድቅ የጸጋ ስጦታ እንደ ሆነ ማወቅና ማስተዋል ትልቅ ነገር ነው! ከማወቅና ከማስተዋል ይልቅ ግን መቀበል ይሻላል! ለምን ቢሉ፥ «የሚቀበሉ በሕይወት ይነግሣሉ» ተብሎአልና። ይህን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነ የእግዚአብሔር የጸጋን ስጦታ ለመቀበል እያንዳንዳችን እንትጋ። (ስለ «ስጦታው» የሚናገሩ ሌሎች ጥቅሶች:- ዮሐ.4፡10። ሮሚ 6፡23። ኤፌ.2፡8)።

ሐ) በቁ.20፣21 ላይ የተጻፈውን ነገር ስናስተምር ኃጢአትን ለመሥራት ተማሪዎቻችንን እናደፋፍር የለምን? «ኃጢአት በበዛበት ዘንድ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ሲል፥ ኃጢአት ምንም ቢበዛ ጸጋ ይሸፍነዋል ማለቱ አይደለምን? ይህስ ከሆነ ኃጢአትን ብንሠራ ምን አለበት? እንኩነንም ተብሎ የለምን?

ይህ ግን የሐዋርያውን ቃል ማጣመም ነው። ሐዋርያው የሚያደርገው ለኃጢአተኛ ተስፋ መስጠት ነው። ሰው ምንም ክፉ ቢሆን ኃጢአቱም ምንም ቢበዛ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ጽኑ ተስፋ አለለት። ኃጢአቱ ምንም ቢበዛ «ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ይላል። በ1ኛዮሐ.1፡7 «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» ተብሎ እንደተጻፈ ነው። ኃጢአትን ለመሥራት ይህ ያደፋፍራልን?

ሐዋርያው የተናገረው ቃል መቼም ፈጽሞ እውነት ነው። ከቁ.15 ጀምሮ ከአዳም መጠን የክርስቶስ፥ ከበደሉ መጠን የስጦታው፥ ከኃጢአት መጠን የጸጋ፥ እንደሚበልጥ ተናግሮአል። «ኃጢአት በበዛበት ዘንድ ጸጋ በለጠ» መባሉ እውነት ነው! ነገር ግን «ይህማ ከሆነ ኃጢአትን እንሥራ! ጸጋ እንዲበዛ እኮ በኃጢአት ጸንተን እንኑር!» ማለት ነውን? «ኃጢአትን ምንም ብናበዛ ጸጋ ተርፎአልና ምን ያስፈራል?» ለማለት አያደፋፍርምን? አያደፋፍረን! ጽድቅን የሚከተለው ቅድስና ነውና በምዕ.6 ጳውሎስ «ሉረ አይሁን!» ብሎ (6፡2፤16) «ኃጢአትን እንሥራ» ከተባለው አሳብ ጋር በጭራሽ አለመስማማቱን ይገልጣል። ክርስቲያ የሆነ ሰው የሐዋርያውን ቃል አጣምሞ ኃጢአትን ለማሥራት አይድፈር!

* * *

# ምዕራፍ 6

1. እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። 2. ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? 3. ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4. እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።

5. ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ 6. ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቆአልና። 7.8. ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤ 9. ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። 10. መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል። 11. እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ።

12. እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤ 13. ብልቶ ቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅረቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ። 14. ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።

15. እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላይደለን ኃጢአትን እንሥራን? አይደለም። 16. ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ። 17.18. ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ፥ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ፥ ከኃጢአትም አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለ ተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። 19. ስለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኩስነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ።

20. የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና። 21. እንግዲህ ዛሬከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? 22. የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና። አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ

አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው። 23. የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።

* * *

# 3ኛ ክፍል- ቅድስና፡- (ከም.6 እስከ ም.8)

## ምዕራፍ ስድስት

ምዕራፍ 6 በም.5 መጨረሻ ላይ ከተባለው ነገር የተነሣ በብዙዎች ሰዎች ልብ ውስጥ የተገኘው የጥያቄው መልስ ነው። በምዕ.5 መጨረሻ ላይ «ኃጢአት በበዛበት ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ተብሎአልና ሰው ምናልባት «እንግዲህ ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑር» ብሎ ኃጢአትን ለመሥራት ነፃነት ያለው ይመስለው ይሆናል። ከቁ.1 እስከ ቁ.14 ድረስ ሐዋርያው የቅድስናን መሠረት ሲገልጥ ከቁ.15 እስከ ቁ.23 ድረስ በቅድስና እንድንኖር ማድረግ የሚገባንን ነገር ይነግረናል።

ለጸደቀ ሰው ኃጢአትን መሥራት በፍጹም ያልተገባ ነገር እንደ ሆነ በዚህ ምዕራፍ ላይ ሲገለጥ ሳለ ያ ሰው ደግሞ ኃጢአትን ሳይሠራ መኖር እንዴት እንደሚቻለው ይገልጣል። ሰው በእምነት እንደሚድን፥ ማለት፥ ጽድቅ እንደሚቈጠርለት ባለፉት ምዕራፎች ላይ ተጽፎአል። ክርስቲያን ኃጢአትን ቢሠራ ኩነኔ የለበትም፤ ይህም እውነት ነው፤ ነገር ግን ለጸደቀ ሰው ኃጢአትን መሥራት ከቶ አይሆንም! ለእውነተኛ ክርስቲያን ደግሞ የማይቻል ነው።

ቅድስና ማለት ሳይፈተን ቀርቶ ኃጢአትን በጭራሽ አለማወቅ ማለት ሳይሆን፥ ተፈትኖ አሸንፎ ኃጢአትን ሳይሠራ መኖር ማለት ነው። ሰው ኃጢአትን ከቶ እንደማይሠራ ወይም የኃጢአት ንክኪት በፍጹም እንደማይገኝበት ማለት አይደለም፥ (1ኛዮሐ.1፡8፤ ያዕ.3፡2)። ነገር ግን ኃጢአትን አያዘወትርም፥ በልማድም አያደርግም ማለት ነው፥ (1ኛዮሐ.3፡6-10)። የጸደቀ ሰው ኃጢአትን በድንገት ይሠራ ይሆናል፤ ነገር ግን የኃጢአት ልማድ የለውም። ቅዱስ ነውና ኃጢአትን ይጠላል፥ ነገር ግን የለበሰው ሥጋ ደካማ ነውና አንዳንድ ጊዜ በፈተና ተሸንፎ ይወድቅ ይሆናል። ተሸንፎ ቢወድቅ ግን እንደምን ያዝናል! ለዚህ ሁሉ ነገር ዋና ማስረጃ ቅዱስ ዳዊት ነው። ዳዊት ቅዱስ ነበረ፥ ኃጢአትንም መሥራት አልለመደም ነበር፥ ነገር ግን በድንገት በክፉ ፈተና ተጸመደ ተሸንፎም ወደቀ፤ አመንዝራም ነፍሰ ገዳይም ሆነ፥ (2ኛሳሙ.11፡1 እስከ ም.12፡15)። በኋላ ግን ቅዱስ ነበረና እንደ ምን አዘነ! (መዝ.50)። እንደዚሁም ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ በድንገት ቢፈተን ወደቀ፤ በኋላም መራራ ልቅሶ አለቀሰ፥ (ማቴ.27፡69-75)። ከአንዱ፥ እርሱም ከኢየሱስ፥ በቀር ኃጢአትን ያልሠራ የለም፥ (ሮሜ 3፡23)። የጸደቀ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ኃይል ያገኛልና ፈተናን ለማሸነፍና

ኃጢአትን እንዳይሠራ ችሎታ አለው፤ ያልጸደቀ ግን ኃይል የለውምና የግድ የኃጢአት ባሪያ ሆኖ ይኖራል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የቅድስና መጽሐፍ የሆነ «ኦሪት ዘሌዋውያን» የእስራኤልን ከባርነት መውጣት የሚናገረውን «ኦሪት ዘፀአትን» ተከትሎ፥ የዳነ ሰው በቅድስና እንዲኖር አስፈላጊነቱን እንደሚያመለከት፥ እንዲሁ አሁን በዚህ በሮሜ መልእክት ከጽድቅ ክፍል ተከትሎ የቅድስና ክፍል ይገባል። ከጸደቅን ከዳንንም በኋላ በቅድስና እንድንኖር ታስቦአል ማለት ነው፥ (1ኛዮሐ.2፡6)። የጸደቀ ሰው ጽድቅን ካላደረገ፥ ማለት በቅድስና ካልኖረ፥ በእውነት ጻድቁ ይሆንን? አሰኝቶ ያጠራጥራል። (1ኛዮሐ.2፡29፤ 3፡7)። ስለዚህ ጳውሎስ «በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?» ለተባለው ጥያቄ «ሉረ አይሁን!» ወይም ደግሞ «ሉረ ከቶ አይደለም!» ብሎ ይመልሳል።

ይህ የቅድስና ክፍል ነው። ጥያቄው «በእምነት የጸደቀ ሰው በዚያ በድሮ ኃጢአቱ ጸንቶ መኖር ይችላልን? የሚል ነው። መልሱ «እንዲህ አይሁን!» ወይም «ሉረ ከቶ አይደለም» የሚል ነው።

በዚህ ምዕራፍ ለዳነ ሰው ቅድስና እንደ ተመደበ እናያለን። ነገር ግን ይህ ብቻ አይደለም። ክርስቶስ የመጣ ፈጽሞ ሊያድነን ነው፤ እርሱም ማለት ከኃጢአት ፍርድ፥ ከኃጢአት ኃይል፥ በመጨረሻም ላይ ከኃጢአት መኖር ስንኳ፥ ሊያድነን መጣ ማለት ነው። ክርስቶስ ግማሽ መድኀን ሳይሆን ፍጹም መድኀን ነው። በሞቱ በውጭ ከምንሠራቸው ከኃጢአት ሥራዎችና በውስጥ ከአዳም ከወረስነው ኃጢአት እንዳዳነን ከዚህ በፊት አይተናል፥ (3፡24፤ 5፡19)። አሁን በትንሣኤ ሕይወቱ ከኃጢአት ኃይልና ግዛት እንዴት ደግሞ እንደሚያድነን እናገኛለን፤ በኋላ ደግሞ በምዕ.8 ከኃጢአት መኖር ስንኳ እንደሚያድነን እናያለን።

ክርስቶስ የመጣው «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን ነበረ እንጂ (ማቴ.1፡21) ሕዝቡ በኃጢአታቸው ለማዳን አልነበረምና ቅዱሳን እንጂ ኃጢአትን የምንሠራ ጻድቃን እንድንሆን አይፈቅድም። ለዚህም ነገር እስራኤል ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ከምስር ምድር ብቻ አላወጣቸውም፥ ነገር ግን ወደ ከነዓን ደግሞ አስገባቸው፥ (ዘፀ.6፡6-8)። እንደዚሁ እኛ ነፃነት ያለን ልጆቹ እንድንሆን እንጂ ገና የኃጢአት ባሪያዎች ሆነን እንድንኖር አላዳነንም። በክርስቶስ ሞት ከፍርድ መዳን አለ፤ በሕይወቱም ደግሞ ከመውደቅ እንኳ መዳን አለ።

ምዕራፉ በ2 ክፍል ይከፈላል። በመጀመሪያ ክፍል (ቁ. 1-14) ያለ ኃጢአት መኖር የሚቻል እንደሆነ፥ በሁለተኛም ክፍል (ቁ.15-23) ያለ ኃጢአት መኖር የግድ አስፈላጊ እንደሆነ እናያለን። ሁለቱ ክፍሎች በጥያቄ ይጀምራሉ፤ በሁለቱም «ባታውቅ ይሆናል» ተብሎ መልስ ተሰጥቶአል።

ቁ.1-14:- «እንግዲህ ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን?» «ሉረ አይሁን! እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ አታውቁምን ...?» ማለት፥ ባታውቅ ኖሮ እንዲህ ያለ ጥያቄ ባልጠየቅህም ነበርና ይህን ያልህበት ባለማወቅህ ይሆናል ማለት ነው። ጥያቄ አቅራቢው ያላወቀው ምን ነገር ኖሮአል? መሞቱን ነዋ! ሞቶ ነበርና «እንዴት አድርገህ ትኖርበታለህ?» ብሎ ሐዋርያው ሲጠይቅ ጥያቄው በእውነት የተገባ ጥያቄ ነው። የሞተ ሰው እንዴት አድርጎ በኃጢአቱ ጸንቶ ይኖራል? ነገር ግን ምዕራፉን ከመጀመሪያ እንጀምረው:-

ጥምቀትን በተጠመቅን ጊዜ ከክርስቶስ አንድ እንሆን ዘንድ ተጠመቅን፥ (ቁ.3)። እርሱም ማለት፥ ጥምቀታችን ከጌታ ጋር አዋሐደን ማለት ነው። ከክርስቶስ ጋር ከተዋሐድን ከተባበርንም በሞቱ፥ በመቀበሩ፥ በመነሣቱ፥ በመቀመጡ፥ በመክበሩ፥ በሁሉ፥ ተዋሐድን ተባበርንም፥ (ኤፌ.2፡5-7)። በዚህ ክፍል ግን በተለይ ስለ መሞታችንና ስለ መነሣታችን ይናገራል። «ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ ሆንን... ክርስቶስም ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንመላለሳለን» ይላል፥ (ቁ.3፤4።) ለዚህ ነገር ጥምቀት ምሳሌአችንና ማስረጃችን ነው። በዚያ ዘመን እንደ ሆነ፥ ገናም ዛሬ በብዙዎች ዘንድ እንደሚደረግ፥ ሰው የተጠመቀበት በውኃ (በወንዝ) ገብቶ በመጥለቅ ነበረ፥ (የሐዋ.8፡36-38)። ሰውዬው ወደ ውኃው ገብቶ በውኃው ይጠልቅና ከመታየት ይጠፋል፤ ይህም ለዓለምና ለዱሮ ሕይወቱ መሞቱን መቀበሩንም ያስረዳል። ከዚያ በኋላ ደግሞ ተመልሶ ብቅ ይላል፤ ይህም ለአዲስ ሕይወት መነሣቱን ያስረዳል። አረመኔ ሆኖ ገባ፥ ክርስቲያን ሆኖ በክርስቲያንነት ለመመላለስ ከውኃው ወጣ። ሁለቱ ሥራዎች አሉ ከእርሱ ጋር እንደ ሞትን ብቻ አይደለም፥ነገር ግን ከእርሱ ጋር የተባበርን እንደሆነ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንድንኖር ነው፥ (ቁ.5።) ይህም ማለት፥ በአሉታ ኃጢአትን አለመሥራት ብቻ ሳይሆን በአዎንታ በቅድስና ደግሞ መኖር ያስፈልገናል፤ የጨለማን ሥራ ማውጣት ብቻ በቂ ሳይሆን የብርሃንን ጋሻ ጦር ደግሞ መልበስ አለብን ማለት ነው። (ሮሜ 13፡12)። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ለራሱ ወይም ስለ ራሱ ሳይሆን ለእኛ ወይም ስለ እኛ ነው። በተሰቀለም ጊዜ «የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ» የሚል ስም በራሱ ላይ ተጽፎ ይሆናል፤ ነገር ግን የተሰቀለበት ለእኛ ብሎ ነበረና (ኢሳ. 53፡5) እኛ እያንዳንዳችን የራስ የራሳችንን ስም ጠርተን «እገሌ ተሰቅሎአል» ለማለት እንችላለን። ነገር ግን በእውነት «እኛ» እንደተሰቀልን አይደለም፥ «እኛ ገና ሕያዋን ነንና (ገላ.2፡20)፥ ነገር ግን በክርስቶስ ሆነን «አሮጌው ሰዋችን»፥ እርሱም ማለት የአዳም ባሕርያችን፥ ተሰቅሎአል፤ ይኸውም ያደረበቱ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ እንዲሁም ለኃጢአት እንዳንገዛ ነው። ከክርስቶስ ጋር ሳንሰቀል በፊት በአሮጌው ሰዋችን የነበረው «የኃጢአት ሥጋ» እርሱም ማለት ኃጢአት የሚደበቅበትና የሚሠለጥንበት ሥጋችን፥ ለኃጢአት ያስገዛን ነበር፤ ዛሬ ግን ያ ሰዋችን ተሰቅሎ ሞቶአልና የኃጢአት ሥጋ ለኃጢአት ሊያስገዛንና ባሪያዎች ሊያደርገን አይችልም። ምክንያቱም፥ የሞተ ሰው ከኃጢአቱ ነፃ ስለ ሆነ (ስለ ጸደቀ) ነው፤ እርሱም ማለት፥

የሞተውን ሰው ሊያስገዛ (እንዲያገለግል ለማድረግ) የሚችል የለምና። የሞተ ባሪያ ከባርነቱ አርነት ወጥቶአል ማለት ነው፥ (ኢዮብ 3፡17-19)። (ቁ.6)

እውነት ነው፥ በክርስቶስ ሆነን ሞተናል፤ በዚህም ምክንያት ከኃጢአት ጸድቀናል ነፃ ሆነንም ተለቅቀናል፥ ነገር ግን በመዋሐዳችን ምክንያት ደግሞ ከእርሱ ጋር እንኖራለንና አሁን እርሱ እንደተመላለሰ እኛ ደግሞ ልንመላለስ ይገባናል፥ (1ኛዮሐ.2፡6) (ቁ.7፡8) ክርስቶስ ተመልሶ ወደ ሞት እንደማይሄድ ደግሞ ተመልሰን ወደ ኃጢአት መግባት ከቶ አይገባንም። እርሱ አንድ ጊዜ፥ አንድ ጊዜም ብቻ፥ ለኃጢአት ሞቶአል የኃጢአትንም ጉዳይ ጨርሶአል፥ ከዚያም ወዲህ ለእግዚአብሔር ለዘላለም ይኖራል። (ቁ.9፤ 10።) እንዲሁ እኛ በእርሱ ሆነን፥ ከእርሱ ጋር ተባብረን፥ አንድ ጊዜ ለሁልጊዜ ለኃጢአት እንደ ሞትን ከእኛ ጋር የኃጢአት ጉዳይ እንደ አለቀ፤ ስለዚህም ደግሞ ወደ ኃጢአት መመለስ ከቶ እንደማንችል፤ ለእግዚአብሔርና ለቅድስና ሁሉ ሕያዋን እንደ ሆንን፤ ራሳችንን መቁጠር ነው። ወደ ኃጢአት መመለስና በኃጢአት ጸንተን መኖር በፍጹም የለም፥ (ቁ.11)። ነገሩ እስራኤላውያን ከግብፅ እንደ ወጡና ወደ ከነዓን እንደገቡ ነው፥ (ዘፀ.14፡13፥ 14፤ ዘኍል.11፡5)። ለግብፅ፥ ለባርነቱም ለሽንኩርቱም፥ ሞቱ አልተመለሱበትም። የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ወደ ከነዓን ገቡ፥ ለከነዓንም ኖሩ። ለግብፅ ሞቱ፥ ለከነዓን ኖሩ። እንዲሁ ደግሞ እኛ የጥምቀትን ባሕር ተሻግረን ለኃጢአት እንሞታለን ለእግዚአብሔርም በቅድስና እንኖራለን።

እንግዲህ በዚህ ከክርስቶስ ጋር በመዋሐዳችሁ መሠረት ላይ ቁሙ! አስቀድሞ ለማመን በኋላም ለማድረግ ተጠርታችኋል። ቁጠሩ፥ ከዚያም በኋላ አድርጉ። እንደ ሞተ የሚትቈጥሩትንና ወደ ሞት የሚጓዘውን ሥጋችሁን ኃጢአት አይግዛው አይንገሥበትም! እየከለከላችሁት ሂዱ እንጂ ከቶ እሺ አትበሉት። በመጀመሪያ ላይ በፈቃዳችሁ ተቃወሙት፥ ሁለተኛም ብልቶቻችሁን ለኃጢአት እያቀረባችሁ ሳትኖሩ ራሳችሁንና ብልቶቻችሁን በተቈረጠ አኳኋን አንድ ጊዜ ለሁልጊዜ ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ (ሮሜ 12፡1)። በመቻላችሁ ደግሞ እንዳትጠራጠሩ፥ «ኃጢአት አይገዛችሁም» ተብሎአልና። ኃጢአት አይገዛችሁምና ይቻላችኋል ማለት ነው። የአርነት አዋጅ እነሆ! ነገር ግን ኃጢአት የማይገዛን በምን ምክንያት ነው? «ከጸጋ በታች እንጂ (እርሱም ማለት፥ በጸጋ ግዛት እንጂ) ከሕግ በታች (እርሱም ማለት፥ በሕግ ግዛት) ስላልሆንን» ነው። ገዥን ለወጥን ማለት ነው። ዱሮ፥ ማለት ከመሞታችን በፊት፥ ሕግ ይገዛን ነበር። ሕግ ያዝዛል እንጂ ትእዛዙን የምንፈጽምበትን ኃይል አይሰጥምና ሕግ ኃጢአት እንዲገዛን አደረገ፥ (8፡3፤ 4)። አሁን ግን በመሞታችን ምክንያት ከሕግ ገዥነት ወጣንና ለጸጋ ተገዛን። ሕግን መጠበቅ አለመቻላችንን አይቶ እግዚአብሔር በጸጋው እንዲሁ ወድዶናልና የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ በነገሩ ገብቶ ከኃጢአት ሊያድነን ብሎ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ በክርስቶስ ሆኖ ስለ እኛ ሲል እስከ ጎልጎታ ድረስ ሄደ፥ (ዮሐ.3፡16፤

2ኛቆሮ.5፡19፤ ገላ.4፡4-6)። የእግዚአብሔር ጸጋ ከኃጢአት ሊያድነን ቈርጦአልና ኃጢአት እንዳይገዛን እርሱ ራሱ ይጠብቃል፥ (1ኛተሰ.5፡23፤24)። የባሪያዎች የነፃነት አዋጅ እነሆ! (ቁ.14)።

የለም! በኃጢአት ጸንተን አንኑር! ለኃጢአት ሞተናልና ከኃጢአት አርነት ወጥተናል። እንቃወመው፥ እንከላከለው፥ ከኃጢአት ተለይተን በቅድስና እንኑር። ይህንም ማድረግ እንችላለን፤ ለምን ብትሉ፥ «ከጸጋ በታች ናችሁና ኃጢአት አይገዛችሁምና!»

<u>ማስገንዘቢያ</u>፦ ይህ ክፍል ስለ ፈተናና ስለ ኃጢአት ማሸነፍ መሠረታዊ ክፍል ነው። ከሁሉ አስቀድሞ ክፍሉ የሚመጣበትን ቅደም ተከተል መረዳት ያስፈልገናል። የሚመጣው ከጽድቅ ክፍል ቀጥሎ ነው። ጽድቅ ይቀድማል ማለት ነው። ይህም ማለት፥ ጽድቅን ያልተቀበለ ሰው ኃጢአትን በማሸነፍ ነገር (በቅድስና) ፈንታ የለውም ማለት ነው። የክርስቶስ የማዳኑ ተካፋይ አይደለምና በዚያ ማዳን ሊካፈል አይችልም። ቅድስና ለጻድቃን ብቻ ነው።

ጽድቅን ማግኘት አንድ ነገር ሲሆን ኃጢአትን ማሸነፍና በቅድስና መኖር ሌላ ነገር ነው። «ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው» እንደ ተባለ ሁሉ (ዮሐ. 8፡34) በባርነት የሚኖሩ ስንትና ስንት ጻድቃን (ክርስቲያኖች) አሉ! ከኃጢአት ፍርድ በእውነት ድነዋል፥ የዘላለምን ሕይወት እንደ ተቀበሉ ዐውቀዋል፥ ወደ መንግሥተ ሰማያትም ለመሄድ ተስፋ አላቸው፤ ነገር ግን ዛሬ በኃጢአት ይኖራሉ፥ በባርነቱም መሆናቸውን ያውቃሉ። ጻድቃን ናቸው፤ ነገር ግን ባሪያዎች ናቸው! አኳኋናቸው ምንኛ አሳዛኝ ነው!

ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከቶ አይደለም። ሰውን ፈጽሞ ለማዳን አስቦአል እንጂ ከኃጢአት አድኖ ገና በኃጢአት መተው አሳቡ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የሠራው ሥራ ግማሽ ሥራ ብቻ ሳይሆን ፍጹም ሥራ ነው፤ ግማሽም መድኃኒት ሳይሆን ፍጹም መድኃኒት ነው። ፍጹም መድኃኒት ነውና ከሁሉ ያድናል፤ እርሱም ማለት፥ ከኃጢአት ሁሉ ለሰው ሁሉና ከማንኛውም ኃጢአት ሁሉ ፍጹም መዳን አለ።

ክርስቲያን ኃጢአትን የማያሸንፍበት መጀመሪያ ምክንያቱ ድል መንሣት ለሰው ልጅ ሁሉ እንደ ተመደበ ባለማወቁ ነው። «ወይስ አታውቁምን?» ተባለ፥ (ቁ.3) ለአንዳንድ ሰው ብቻ፥ ልዩ መንፈስ ላለው ሰው፥ እንደ ተሰጠ እንጂ ለእርሱ ለራሱ እንደተሰጠ አላወቀም። በዚህ ሥጋ ባለበት ጊዜ ሁሉ ኃጢአትን መሥራት የግዴታ ነገር እንደሆነ ሲመስለው ለወደፊት እንጂ ዛሬውኑ ከኃጢአት ለመዳን ተስፋ የለውም። ዳሩ ግን እያንዳንዳችን ያለ ኃጢአት እንድንኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ፥ ያለ ኃጢአትም እንድንኖር ደግሞ አስፈላጊው ሁሉ እንደተደረገ

እንመን። በኃጢአት እየተሸነፍን መኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን ክርስቲያን ሁሉ ይወቅ። ለሁሉ፥ ከሁሉም፥ ፍጹም መዳንን ነፃነትም እንዳለ ይወቅ።

እንግዲህ የድል በር ምንድር ነው? ከሁሉ አስቀድሞ መዳን ሁሉ ከእኛ ሳይሆን ከእግዚአብሔር፥ በሥራ ሳይሆን በእምነት፥ እንደ ሆነ እርግጠኞች እንሁን። በመታገልና በሥራ የተገኘ ማነኛውም ዓይነት መዳን የለም፥ (ኤፌ.2፡8፥9)። ከዚያም በኋላ ማነኛውም ዓይነት መዳን ሁሉ «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» እንደሆነ እናስተውል። ከኃጢአት ፍርድ ለመዳን፥ ወይም ከኃጢአት ኃይልና ግዛት ለመዳን፥ መንገዱ አንድ ነው፤ እርሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሆነው እምነት ነው፥ (የሐ.3፡16፤ 4፡12)። ብዙዎች ክርስቲያኖች ጽድቅ እንዲቈጠርላቸው የራሳቸውን ሥራ ትተው በኢየሱስ ሥራ ብቻ ካመኑ በኋላ የሚቀደሱበት በራሳቸው ሥራ እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ይህ ፈጽሞ ስሕተት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን የሚንድንበት በእምነት ነው እንጂ በሥራችን አይደለምና በራሳችን ወይም በሥራችን ተስፋ ቈርጠን፥ መታገላችንን ሁሉ ትተን፥ በእምነት ብቻ ለመዳን እናስብ እንጠባበቅም። ኃጢአትን የምናሸንፍበት በእምነት ነው። የድል በር ይህ ነው።

ከኃጢአት ባርነት እንድንወጣ በምን እንመን? ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ከቁ.1 እስከ 14 ድረስ መልሱን ይሰጠናል። ከክርስቶስ ጋር፥ በሞቱና በመነሣቱ፥ በመተባበራችንና በመዋሐዳችን በማመን ነው። ምሥጢሩ ይህ ነው። የትግል ነገር አይደለም፥ የሚሰማንም ነገር አይደለም፥ ከክርስቶስ ጋር እንደ ሞትን ከእርሱም ጋር እንደተነሣን በመቁጠር (በማመን) ብቻ ነው። ነገሩ እውነት እንደሆነ እንቈጥራለን፤ ደግሞም እውነት ነው፤ እንደ መቁጠራችንም እንራመዳለን። እኛ ራሳችንን ከነድካማችን ለእግዚአብሔር ኃይል እንሰጣለን። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በነገሩ ገብቶ ያድነናል፤ እኛም ያን ኃጢአት እናሸንፋለን። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምዕራፍ ከክርስቶስ ጋር መሞታችንን አስተምሮናል፤ «ቁጠሩ!» ብሎናል፤ «ኃጢአት አይገዛችሁም» ብሎ ቃሉን ሰጥቶናል። መዳን የእግዚአብሔርን ቃል በማመን ነው። ሰይጣን ፈተናን ይዞ ሲመጣ እኛ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ላይ ቆመን «ሙቼአለሁና ልትገዛኝ አትችልም፤ ይህን ነገር ማድረግ አልፈቅድም፤ ሂድ!» ብለን ብንቃወመው ሰይጣን ይሸሻል፥ (ያዕ.4፡7)። በዚያ ጊዜም በእውነት በእኛ ላይ ኃይል እንደሌለው እንረዳለን፥ እንደዚህም ማድረግ ልማዳችን ዘወትር ሲሆን ሁልጊዜ በድል ተራምደን በቅድስና እንኖራለን።

እንግዲያስ ኃጢአትን (ፈተናን) ወደ ማሸነፍና ወደ ቅድስና የሚመራ የድል በር ከዚህ እንደሚከተለው ነው:-

1ኛ፥ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤው ጋር በመተባበራችን እግዚአብሔር «ኃጢአት አይገዛችሁም» ብሎ ቃሉን እንደሰጠን ማወቅ፥

2ኛ፥ በየቀኑ በየሰዓቱና በየደቂቃው ይህን ነገር መቁጠር ( ማመን)።

3ኛ፥ ራሳችንን ብልቶቻችንንም አንድ ጊዜ ለሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ማቅረብ።

«መሞቴ አይሰማኝም፥ ምነው በእውነት በሞትሁ!» ትላለህን? «ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? (9፡20)። በቃሉ ልትጠራጠር ነህን? «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» መባሉን ዕወቅ! (እንባ.2፡4፤ ሮሜ 1፡17፤ ዕብራ.10፡38)። ብሎአልና ያለ እምነት የሚድን የለም። «ባታምኑ አትጸኑም»፥ (ኢሳ.7፡9) ንጉሡ ነገሥት «አርነት ወጥተሃል!» ሲልህ አታምንምን? የባሪያዎች ነፃነት አዋጅ እነሆ ተነገረልህ!

የባሪያዎች ነፃነት አዋጅ በአንድ አገር ሲነገር በሩቁ አውራጃዎች የተቀመጡት አንዳንዶች ባሪያዎች አልሰሙትም ይሆናል፤ በዚህም ባለማወቃቸው ምክንያት ለጌቶቻቸው ገና ሲገዙ ኖረው ይሆናል። አንዳንዶችም ደግሞ ነገሩ እውነት አልመሰላቸውምና አላመኑትም ይሆናል። እነዚህም ደግሞ ካለማመናቸው የተነሣ ገና ሲገዙ ተገኙ። ይህ ሁሉ ግን ከቶ አስፈላጊ አልነበረም። ንጉሡ ነገሥት ቃሉን ሰጥቶ ነበርና ጌታው ምንም ጨካኝ ብርቱም ቢሆን አዋጁን አውቆ፥ አዋጁን አምኖ፥ በአዋጁ ቃል መሠረት ነፃነትን የጠየቀ ባሪያ ሁሉ አርነት ይወጣ ነበር። ሊከለክለው የሚችል ከቶ አንድም አልነበረም። መንግሥት ቃሉ ሰጥቶ ነበርና በቃ! ነገሩ አለቀ! ነፃ ባሪያዎቹም ወጡ።

እንደዚህ ነው ጳውሎስ «ወይስ አታውቁምን?» ብሎ የሚጽፈው። ከኃጢአት ተገዥነት የባሪያዎች ነፃነት አዋጅ ተነግሮአል፤ በአርነትም እንድንሳተፍ ማወቅና ማመን ብቻ ነው። «አንችልም» እንዳንል ይኸው «አይገዛችሁም» ብሎ አምላክ ቃሉን ሰጥቶአል! እውነት እንደሆነ ቢሰማንም ባይሰማንም ያለብን ማመን ነው። «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ!» (ማቴ.9፡29)።

የሞትን እኛ መሆናችንን እንጂ ኃጢአት፥ ያ የዱሮ ጌታ፥ አለመሆኑን ማስተዋል ያስፈልገናል። ሰይጣን ገና አልሞተም፥ ኃጢአትም ገና አልጠፋም፥ ፈተናም ከቀድሞው ስንኳ ምናልባት ለክርስቲያን የከፋ የበረታም ይሆናል። እኛ ግን ለኃጢአት ሞትን። ዲያብሎስ እንደሚያገሣ አንበሳ ገና ይዞራል (1ኛጴጥ.5፡8) ፈተናም ይገነፍላል፤ ነገር ግን በእውነት ከክርስቶስ ጋር እንደሞትን በእምነት ስንቆም ሰይጣንና ፈተና ይደክማሉ፥ ዱሮም እንወድቅበት በነበረው ቦታ አሁን እንቆማለን። የዱሮ ጌታ የሞተ ባሪያውን ለማሠራት እንደማይችል፥ ያም የሞተ

ባሪያ ከባርነቱ እንደወጣ፤ እንዲሁ ኃጢአት የሞተን ሰው ሊነካ አይችልም። ምንም ቢጮኽ ቢያስፈራራ ያ ሬሳ አይገደድም።

ክርስቲያን ሆይ! ራስህን ለማዳን መሞከርህን መታገልህንም ትተህ በእምነት ዳን። መታገልህን ስታቆም ያ «ኃጢአት አይገዛችሁም» የተባለው ቃል እውነት እንደ ሆነ ታገኛለህ፥ ከባርነትም ግሩም ወደ ሆነ አርነት ትወጣለህ። እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር ቃል ነው እኮ!

<u>ቁ.15-23</u>፦ በቁ.14 ላይ «ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁም» ተባለ። እንኪያስ ጸጋ ያድነናል፥ ሕግ አይፈርድብንም፥ ስለዚህ ኃጢአት ልንሠራ እንችላለን ማለት ነውን? ሉረ አይሁን! በቁ.3 እንደ ሆነ እንዲሁም እዚህ ደግሞ «አታውቁምን?» ተባለ። ይህም ማለት ባወቃችሁ ኖሮ ባልጠየቃችሁም ማለት ነው። ማወቅ ይገባቸው የነበር ምን ነገር ኖሮአል? «ለመታዘዝ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ» ነው። ከሁለቱ ነገሮች አንዱን ልንሆን እንችላለን፤ ወይም የኃጢአት ባሪያዎች ወይም የመታዘዝ ባሪያዎች፥ (ቁ.15፤16)።

ለውጥ ተደርጎአል። ዱሮ የኃጢአት ባሪያዎች ነበራችሁ፤ ዛሬ ግን የተሰጣችሁለትን ቃልም (አምሳል) ልትመስሉ ከልባችሁ ታዛዦች ስለሆናችሁ ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ተገዛችሁ (ተለወጣችሁ)። የታዘዛችሁለት ጌታ ተለወጠ ማለት ነው። (ቁ.17፤18)።

የኃጢአት ባሪያዎች በነበራችሁ ጊዜ የኃጢአትን ሥራ ለመሥራት ብልቶቻችሁን ለርኩሰት ሁሉ ታቀርቡ እንደነበራችሁ፥ እንዲሁ ዛሬ የጽድቅ ባሪያዎች ስትሆኑ ብልቶቻችሁን ሊቀደሱ ለጽድቅ አቅርቡ። እውነት ነው፥ ጳውሎስ ምሳሌውን አይወድም፥ በምዕራፍ 7ትም ይለውጠዋል፥ ስለምን ቢሉ፥ እግዚአብሔር የሚፈልገው ነፃነት ያላቸው ልጆች ነው እንጂ በባርነት የታሠሩትን አይፈልግም። ነገር ግን በማስተዋል ደካሞች ነንና ጳውሎስ በምንችለው ምሳሌ ያስተምረናል፥ (ቁ.19።)

አሁንም ደግሞ ሁለቱን ነገሮች ሁለቱንም ሥራዎች አመዛዝኑ። ዱሮ የኃጢአት ባሪያዎች በነበራችሁ ጊዜ ከጽድቅ ጋር ጉዳይ አልነበራችሁም። አንድ ሰው የሌላውን ባሪያ ሊያዝዝ አይችልምና በዚያ ጊዜ የኃጢአት ስትሆኑ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁ ማለት ነው። እስኪ አሁን ደግሞ ጥቅሙን አስቡ። ዛሬ ስታስቡበት የምታፍሩበት የዚያ ነገር ጥቅሙ ምን ኖሮአል? ምንስ አግኝታችሁበታል? የሚጠብቃችሁ ሞት ነበረ እንጂ ምንም አላገኛችሁበትም። አሁን ግን ጌታን ለውጣችሁ ለእግዚአብሔር ከተገዛችሁ፥ አንድ ሰው የሌላውን ባሪያ ሊያዝዝ አይችልምና፥ ከዱሮ ጌታችሁ (ከኃጢአት) አርነት ወጥታችኋል። ከዛሬው ሥራሳ? ፍሬ ጥቅምም አለን? አለ! የቅድስና ፍሬ መልካም ፍሬ፥ አለ፤ በመጨረሻውም የዘላለም ሕይወት አለ!

ኃጢአት የተባለው ጌታ ለባሪያዎቹ የሚከፍለው ደመወዝ ሞት ነውና፥ እግዚአብሔር ግን ለልጆቹ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ የዘላለም ሕይወት ነው፥ እርሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ። (ቁ.20-23።)

እንግዲያስ ጌትየው አጉል፥ ሥራውም ጥቅም የማይሰጥ ከሆነ፥ አስፈላጊነትና ተገዳጅነት ከሌለ፥ ለምን ብለን ኃጢአትን እንሠራለን? ፈጽሞ የማይገባ ነው።

ማስገንዘቢያ

ሀ) «ሕግ አይፈርድብንምና ኃጢአት እንሥራ!» ለምን ብለን? የዚህ ክፍል ዋና አሳቡ ይህ ነው። ለምን ብለን ኃጢአት እንሥራ?

ሁለት ጌቶች አሉ፤ ከሁለት ለአንዱ ልንገዛ የምንችል ስንሆን ለምን ብለን ለኃጢአት እንገዛለን? በመሞታችን ምክንያት ከኃጢአት ጋር አሥራቱ ተበጠሰ፤ አሁንም በመነሣታችን ከክርስቶስ ጋር በሕይወት ተባበርን ተሣሠርንም። (ቁ.1-14።) በዚህ በምዕ. 6 ላይ እንደምናገኘ ክርስቶስን እንደ ጌታ እናስበዋለን፤ በምዕ. 7 ደግሞ እንደተወደደ ባል እናስበዋለን። እርሱ ጌታችን ወይም ንጉሣችን ከሆነ ለሌላ ጌታ ወይም ንጉሥ ተገዝተን ብንሠራ ከዳተኞች መሆናችን አይደለንም? መሪያችን ወደ ሌላ አገር ሄዶ ሳለ (ሉቃስ 19፡12) ባዕድን ተቀብለን ለመሪያችን የሆነውን ለእርሱ ለባዕዱ መስጠት፥ ለእርሱም እሺ ብሎ መገዛትና መታዘዝ፥ ይገባናልን? ከቶ አይገባም! ወይም ደግሞ እርሱ የተወደደ ባላችን ከሆነ፥ ከጌታ ጋር የሚተባበር አንድ መንፈስ ሲሆን (1ኛቆሮ.6፡17)፥ የክርስቶስ ብልቶች የሆኑት ብልቶቻችንን ወስደን የጋለሞታ (የሰይጣን) ብልቶች እናደርጋቸውን? (1ኛቆሮ.6፡15)። ሉረ ከቶ አይሆንም! ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእንደዚህ ያለ አሳብ አጥብቀን እንራቅ! «ኃጢአት እንሥራን?» ሉረ! ለምን ብለን? የለም የለም፥ ከቶ አንድም ኃጢአት አንሥራ! «ከሕግ በታች አይደላችሁም» መባሉ እርግጥ ነው፤ ነገሩም ፈጽሞ እውነት ነው፤ ነገር ግን ማንኛውም ጥቅም ከቶ ከሌለ፥ በደሙ ለዋጀን ከደት ምንዝርናም ሲሆን (1ኛጴጥ.1፡18፤19)፥ ኃጢአትም ለመሥራት ደግሞ ግዴታ በጭራሽ ከሌለ፥ ኃጢአትን መሥራት እንዴት ያለ ዕብደት ነው!

«ኃጢአት እንሥራን?» ለምን ብለን? ይህ ቃል በጆሮአችን በቀንና በሌሊት ሳያቋርጥ ዘወትር ይሰማንና ኃጢአትን ከቶ ከቶ አንሥራ።

ለ) በቁ.23 ላይ እንደተነገረ የዘላለም ሕይወት በሥራ የሚገኝ «ደመወዝ» ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን በኩል የሚሰጠን «የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ መሆኑን መገንዘብ ትልቅ ነገር ነው። ደመወዝን የምናገኝ ከሥራችን ነው፤ ኃጢአትም የሚከፍለው ደመወዝ ሞት ነው። የዘላለም ሕይወት ግን «ደመወዝ» ሳይባል «የጸጋ ስጦታ» ታባለ፤ እርሱም ማለት፥ « ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል» ማለት ነው፥

(4፡5።) የዘላለም ሕይወት፥ ወይም ጽድቅ ወይም ደኅንነት (ይህ ሁሉ አንድ ነገር ነውና)፥ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታን የምናገኝበት በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን በማመን ነው እንጂ ደመወዝ አይደለም፥ የሚገኝበትም በሥራ አይደለም። በአንዱ ወገን ሥራና ደመወዝ አሉ፤ በሌላም ደግሞ እምነትና ስጦታ አሉ። እነዚህም አይደበላለቁም።

* * *

# ምዕራፍ 7

1. ወንድሞች ሆይ፥ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን? 2. ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች። 3. ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።

4. እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ። 5. በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ 6. አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥ ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።

7. እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ፦ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። 8. ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና። 9. እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤ 10. ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤ 11. ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታልሎኛልና። 12. በእርስዋም ገድሎኛል። ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።

13. እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር። 14. ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። 15. የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም። 16. የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ። 17. እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ። 18. በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። 19. የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። 20. የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ።

21. እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ። 22. በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ 23. ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ። 24. እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን

ያድነኛል? 25. በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ።

* * *

# ምዕራፍ ሰባት

በዚህ ምዕራፍ የምናገኘው የሕግ ነገር ነው። ሕግ የተሰጠበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊገልጥና ኃጢአት ከተባለ ሁሉ ጠብቆ በቅድስና ሊያስኬድ ነበረ። ያን ሁለተኛ ነገር ለማድረግ ግን ሕግ አልቻለምና በሕግ ቅድስና ታጣ። ምዕ.1 እስከ ም.3 ድረስ ስለ ተሠራ ኃጢአት፥ ምዕ.5 ስለ ተወረሰ ኃጢአት፥ ምዕ.7 ስለሚገዛን ኃጢአት ይናገራል። ኃጢአትም የገዛን በሕግ ምክንያት ነው።

ቁ. 1-6፡- በእነዚህ ቁጥሮች ሐዋርያው ገና የምዕ. 6ትን አሳብ ይዞአል። ኃጢአትን የምናሸንፍበት ከክርስቶስ ጋር መዋሐዳችንን በመቁጠር እንደ ሆነ በዚያ ምዕራፍ ተረድተናል። ከክርስቶስ ጋር እንዴት እንደሞትን፥ እንዴትም እንደተነሣን፥ ከተናገረ በኋላ ከቁ. 15 እስከ 23 ድረስ የጌታና የባሪያ ምሳሌን አንሥቶ ለዱር ጌታ ተገዝተን የኃጢአትን ሥራ ሳንሠራ አሁን ለአዲስ ጌታ፥ እርሱም ለጽድቅ ወይም ለእግዚአብሔር፥ ተገዝተን የጽድቅን ፍሬ እንድናፈራ አመልክቶን ነበር። ያ የጌታና የባሪያ ምሳሌ ግን ደስ አላሰኘውም፥ አለመውደዱንም በምዕ.6፡19 ገልጦአል። ስለዚህ አሁን ያንኑን ትምህርት ለማስተማር ብሎ ምሳሌውን ይለውጥና የባልና የሚስት ምሳሌ ያቀርባል።

በምዕ.6፡15-23 እና በምዕ.7፡1-6 የምናገኛቸው ምሳሌዎች አንድን ነገር ያስረዳሉ፥ እርሱም ከክርስቶስ ጋር በሕይወቱ መተባበራችንንና መዋሐዳችንን ነው። መተባበራችን በጌታና በባሪያው መካከል እንዳለ ነው! ነገር ግን በእውነት ከዚያ በበለጠ ይቀርባልና በባልና በሚስት መካከል እንዳለ መዋሐድ ነው። ስለ ባልና ሚስት «አንድ ሥጋ ናቸው» እንደተባለ (ዘፍ.2፡24) እንዲሁ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ተዋሕዶአል። «በክርስቶስ ሥጋ» ለኃጢአት ብቻ ሳይሆን (6፡16) ለሕግ ደግሞ ሞተናልና (7፡4) ከእሥራቱ ስለተፈታን፥ ፈቃዳችን ቢሆን፥ የፈቃድ ነገር ነውና! «ከሙታን ለተነሣ» ለክርስቶስ ልንታሰር (ልንተባበር፥ ልንዋሐድ) እንችላለን። ሚስቶች ነንና ለባላችን እንገዛለን (ቁ.6) ነገር ግን ለዱሮ ባላችን፥ ለሕግ፥ እንደተገዛን! ወይም ደግሞ ባሪያ ለጌታው እንደሚገዛ! በፈደል ግዴታ ተገኝንት ሳይሆን አሁን በመንፈስ አርነት እንገዛለን። እውነት ነው፥ ለክርስቶስ ታስረናል ተባብረናልም! ነገር ግን በምዕ.6፡15-23 እንደ ሆነ የባርነት ነገር ሳይሆን የፈቃድና የፍቅር ነገር ነው። ደስ የምናሰኝበቱ ባሪያዎቹ ስለሆንን አይደለም! እፍቃሪ (ወዳጅ) ሚስቱ ስለሆንን ነው እንጂ። በመጀመሪያው፥ በጌታና በባሪያ፥ ምሳሌ ደግሞ አስቀድመን የኃጢአትን በኋላም የጽድቅን ሥራ እንደ ሠራን! እንዲሁ በዚህ በሁለተኛው ምሳሌ አስቀድመን «ኃጢአት» እና «ሞት» የተባሉትን ልጆች ለሕግ እንወልዳለን፥ በኋላም «ቅድስና» እና «ሕይወት» የተባሉትን ልጆች

ለክርስቶስ እንወልዳለን፥ (ቁ.4፤5።) ይህም ሁሉ ማለት፥ ከክርስቶስ ጋር ተዋሕደናልና ኃጢአትን ማፍራት አንችልም ማለት ነው። ኃጢአትን እናፈራ እንደሆነ የክርስቶስ ወገኖች አይደለንም ማለት ነው።

ጳውሎስ በምዕ.6፡14 ላይ «ከሕግ በታች አይደላችሁም» ብሎ ነበርና ያን ነገር አሁን ሊያስረዳ ይፈልጋል። የባልና የሚስት ነገር ጠቅሶ ሕግ ሰውን በሕይወት ሳለ እንጂ ከሞተ በኋላ ሊገዛው አይችልምና በባልና በሚስት መካከል ያለው ሕግ (እስራት፥ መተባበር) ሁለቱ ገና ሳሉ እንጂ አንዳቸው ከሞተ በኋላ ሊጸና አይችልም ይላል። እንግዲያስ ባልዮው ሳለ ሕጉ (ማር.10፡6-9) ይጸናልና ሚስቲቱ ለሌላ ልትሆን አትችልም። ባልዋ ግን ቢሞት ከጋብቻ እስራት ተፈትታለችና ለሌላ ልትሆን ትችላለች፥ (ቁ.1-3።) ምሳሌው ይህ ነው፤ አሁንም በቁ.4-6 ላይ ፍቹን እናገኛለን።

በምሳሌው እንደተባለው ሁሉ እናንተ «በክርስቶስ ሥጋ ተሰቅላችኋልና (6፡6) «ሕግ» ለተባለ ባላችሁ ሞታችኋል፥ በመካከላችሁም የነበረው እስራት ተበጥሶአል። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ደግሞ ተነሥታችኋል እንጂ ሞታችሁ አልቀራችሁምና (6፡8) «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥» ቈላስይስ 3፡9። ገና በሥጋ ሳለን፥ እርሱም ማለት ከክርስቶስ ጋር ሳንሞት በፊት፥ በሕግ ምክንያት የፈለቀ የኃጢአት መሻት በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና እርግዘን ለሞት የሚሆኑትን ልጆች ወለድን፥ (ያዕ.1፡15)። «(በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።» መገዛታችን መቼም አልቀረም- ሚስት ለባልዋ እንደምትገዛ ዓይነት ይኸውም በመንፈስ (በጸጋ) ነው እንጂ በዱሮው ዓይነት፥ እርሱም በፊደል (በሕግ) አይደለም።

እንግዲያስ የክርስቶስ የሆኑት፥ ከክርስቶስ ጋር መዋሐዳቸውን አጽንተው ሲቆጥሩ ሳሉ፥ ኃጢአትን ሊሠሩ እንደማይችሉ እናያለን፥ (1ኛዮሐ.3፡9)። መዋሐዳቸውን ግን ቢረሱ ይሠሩት ይሆናል፥ (1ኛዮሐ.1፡3፥8፤ 2፡1)። «እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና»፥ 2ኛቆሮ.11፡2።
ደግሞ፡- (ዮሐ.8፡31-34፥ 1ኛዮሐ.3፡8፤10)።

ቁ. 7-24፡- የድል በር ተነግሮአል፤ ነገር ግን የጳውሎስን መልእክት እስከዚህ ድረስ ያነበበ ሰው «እንግዲህ በባርነት የያዘን ሕግ ነውን ወይስ ኃጢአት?» ብሎ ይጠራጠር ይሆናል። ለምን ቢባል፥ ሐዋርያው አንድ ጊዜ «ሕግ ነው»፥ አንድ ጊዜም ኃጢአት ነው»፥ ያለ ይመስላልና። የገዛንና በኃጢአት የያዘን ሕግ ነውን? ጳውሎስ ግን በዚያው «ሉረ አይሁን!» ወይም «ሉረ ከቶ አይደለም!» በሚል ቃል እንደ ወትሮው ሁሉ እየተጸየፈ በጽኑ ቃሉ ይመልሳል። «ሉረ አይሁን! አሳቡ እንኳ

የማይቻል ነው!» ይላልና ከዚህ ቃል ጀምሮ እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ድረስ በባርነት የያዘን ያ ኃጢአት እንደ ሆነ ያስረዳናል።

ሕግ ገና ሳይመጣ በፊት ኃጢአት ነበረ፤ ነገር ግን አልተገለጠም ነበርና መኖሩ አልታወቀም። ሕግ የመጣው ኃጢአትን ለመግለጥ ነው። ለምሳሌ፥ ሕግ ሳይመጣ በፊት ምኞት አድሮብኛል፤ ነገር ግን ኃጢአት መሆኑ አልታወቀም ነበርና በንጹሕ ሕሊና ኖርሁ። ከዚያ በኋላ ሕግ መጣ፤ አትመኝ ተባልና ያ ያደረብኝ ምኞት ኃጢአት መሆኑ ታወቀ። ኃጢአት መሆኑን አሁን ዐወቅሁኝ፥ ነገር ግን ምኞቴን ለማስቀረት አልቻልሁም! አልቻልሁምና ሕግ ለሞት አሳልፎ ሰጠኝ። ሕግ ማለፊያ ነው፥ የተገባም ነው፥ እኔ ግን ከኃጢአት ግዛት በታች የተሸጥሁ ነኝና ልፈጽመው አልቻልሁም። ክርስቲያን ሆኛለሁና ልፈጽመው በወደድሁ ነበር፤ ነገር ግን አልቻልሁም። በሥጋዬ መቅደስ ውስጥ ከእኔ የበረታ ሌላ አለ፥ እርሱም የሰይጣን ወኪል፤ እርሱም ወደ ኃጢአት መርቶ ይግርከኛል። በብልቶቼ ውስጥ ነውና ዱትም ብሄድ፥ ምንም ባደርግ፥ እርሱ አብሮኝ አለና ነፃ መውጣት አልችልም። «እኔ ምንኛ ጕስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» (ቁ.24።) «ማን» እንደ ተባለ አስተውሉ፤ ለምን ቢሉ፥ ከእኛ ውጭ የሆነ መድኃኒት እንዲሆን ያስፈልጋልና።

«ማን ያድነኛል!» ተብሎአልን? «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» የተባለለት ማን ነው? ኢየሱስ አይደለምን? «ማቴ.1፡21)። «መዳን በሌላ በማንም የለም» ተብሎ የለምን? (የሐዋ.4፡12)። እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር ፈቅዶ የለምን? (ቈላ.1፡19-20)። አዎን፥ እውነት ነው፥ መዳን የሚገኘው «በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን» ነው፥ (ቁ.25፤ ም.6፡23)። ጽድቅ በእርሱ እንደ ሆነ እንዲሁ፥ እግዚአብሔር ለዘላለሙ ይመስገን፥ ቅድስናና ነፃነት ደግሞ በእርሱ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ሙሉ መዳን አለ!

(ቁ.7-12)፡- «ሕግ ኃጢአት ነውን?» ሎረ ከቶ አይደለም! ሎረ አይሁን! ሕግ ግን ለኃጢአት መነሻ ሆነ። ምክንያቱም፥ ሕግ ከመምጣቱ በፊት ለኃጢአት ኃይል አልነበረውም። ሕግ ከመጣ በኋላ ግን ኃጢአት ኃይልን አገኘ፥ (1ኛቆሮ.15፡56)። ደግሞ፥ ሕግ በበዛበት መጠን ኃጢአት አብሮ እየበዛ እንደሚሄድ የታወቀ ነው። ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነው፤ ኃጢአት መሆኑ አይቈጠርም፤ የሚነሣበትም መሠረት የለውም። ዱሮ፥ ሕግ ከመምጣቱ በፊት፥ ከኃጢአት ነፃ ነበርን፤ ሕግ አልነበረምና ኃጢአት አይቈጠርብንም ነበር፥ ፍርድም አይፈረድብንም ነበር። ስለዚህ ሕያዋን ነበርን። ከዚያ በኋላ ግን ሕግ በመኖሩ ምክንያት ኃጢአት ሕያው ሆነ፤ እኔም በሕጉ ምክንያት ደግሞ ሞትሁ! ለሕይወት ተሰጥቶ የነበረው ሕግ ፈራጅ ሆነብኝና የግድ ገደለኝ! ሕጉ ቅዱስ ነው፥ መልካምም ነው፤ ነገር ግን ፈራጅ ሆኖብኛልና ከሕግ በታች ባልሆን ይሻላል!

ቁ, 13-20፡- እንግዲያስ የገደለኝ ሕግ ነውን? ወይስ ኃጢአት? ኃጢአት ነው እንጂ ሕግ ከቶ አይደለም። ሕግ መልካም ነው፥ የተሰጠበትም ምክንያት ኃጢአት ምንና ምን እንደ ሆነ ለመግለጥና የኃጢአትን ክፉነት ለማስታወቅ ነው። በዚህ በመልካሙ ነገር ለእኔ ሞትን የሠራ ኃጢአት ነው። ችግሩ ሕግ መንፈሳዊ ሲሆን እኔ ሥጋዊ በመሆኔ ነው። አንስማማም ማለት ነው። እኔ መንፈሳዊ ብሆን ኖሮ የሕግ ትእዛዝ በእኔ ይፈጸም ነበር፤ ነገር ግን ከሥጋ ድካም የተነሣ፥ እኔ ሥጋዊ በመሆኔ ማለት፥ ለሕግ አልተቻለም፥ (8፡3-6) የማደርገው እንኳ ለእኔ ምሥጢር ነው፥ ነገሩ አይገባኝም። ማለት፥ የምጠላውን አደርጋለሁ እንጂ የምወደውን አላደርግም። ይገርማል! ያን ክፉ ነገር ለማድረግ ምንም ባልወድ አደርገዋለሁ! ክፉን አልወድምና ሕጉ መልካም እንደሆነ እኔ ራሴ ምስክር ነኝ። ልመስክር እንጂ ሕግን ገና አፈርሰዋለሁ! ነገር ግን በእውነት ኃጢአትን የማደርገው እኔ አይደለሁም፤ በሌላ ተገድጄ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። የማይታዘዝልኝ ሥጋዬ ነው። መልካሙን አደርግ ዘንድ ፈቃድ አለኝ፤ ሲኖረኝ ሳለም መልካሙን ለማድረግ ችሎታ የለኝም። ፈቃድ አለኝ፤ ችሎታን ግን አጣሁ።

<u>ቁ. 21-25</u>፡- አሁንም በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ስለ ሌላ ሕግ ደግሞ እናነባለን። በሰው ወይም በእግዚአብሔር የተደነገገ ሕግ ሳይሆን ሁልጊዜ፥ ዘወትር፥ የሚደረግ እና የሚሆን ነገር ስለሆነ «ሕግ» ይባላል። የተለማመደ ነገር ነው ማለት ነው።

ይህ ሌላ «ሕግ» ምንድር ነው? መልካምን አደርግ ዘንድ ስወድ ክፉ እንዲያድርብኝ ነው። በውስጡ ሰውነቴ፥ በልቤ፥ እኔ የእግዚአብሔርን ሕግ ሸወድ በብልቶቼ ውስጥ ይህ «ሌላ ሕግ» አለ፤ ሌላ ኃይል፥ ሌላ ሰው፥ ሌላ ጌታ፥ ሌላ መንፈስ፥ ማለት ነው። በአእምሮዬ መልካሙን ለይቼ መልካሙን ለማድረግ አስባለሁ፤ ነገር ግን ይህ «ሌላ ሕግ» ከአእምሮዬ ሕግ ነጥሎኝ ከብልቶቼ ወዳለው የኃጢአት ሕግ ይማርከኛል። «የኃጢአት ሕግ» ተባለ፤ ለምን ቢባል፥ ኃጢአትን መሥራት ደግሞ የተለማመደ ነገር ይሆናልና። የአእምሮዬ ሕግ አለ፤ በብልቶቼ የኃጢአት ሕግ አለ፤ ያም «ሌላ ሕግ» አለ፤ ይህም መጨረሻው ከፍ ካለ ከአእምሮዬ ሕግ ነጥሎኝ ወደ ታችኛው ወደ ኃጢአት ሕግ ሁልጊዜ አሳልፎ ይሰጠኛል። የምወደውን ለማድረግ አልቻልሁም። «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነቴ (ስለምን በእውነት በዚህ ባርነት መኖር የሞት ያህል ነውና) ማን ያድነኛል?» ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን! ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሔር አድርጎአል። ነፃነት የቅድስና አረማመድም አለልኝ፥ እርሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ!

ማስገንዘቢያ

1. ከቁ.1 እስከ 3 ድረስ የባልና የሚስት ሕግ እናገኛለንና ብንመረምረው ለዛሬ ዘመናችን የሚሆን ትምህርት እናገኝበታለን።

ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ እንደታሰረች ተነግሮአል። ሕግ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በቁ. 3 እናያለን፤ የጋብቻ ሕግ ነው። በዚህ ሕግ ባልዋ በሕይወት ሳለ ያች ያገባች ሴት ለእርሱ ታሥራለችና ለሌላ ወንድ መሆን አይፈቀድላትም። ባልዋ ቢሞት ግን ከዚያ ከጋብቻ ሕግ ተፈትታለችና ሌላን ልታገባ ትችላለች።

ሕጉ ሴትዮዋ አንድ ጊዜ ካገባች ያ ባልዋ በሕይወቱ እስካለበት ዘመን ድረስ ለእርሱ ታስራለችና ለሌላ ብትሆን አመንዝራ እንጂ ሚስት አይደለችም ይላል። ይህም ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕግ እንደ ሆነ ከዘፍጥ.2፡24 እናያለን። ሰው ይህን ሕግ ለመጠበቅ ተቸግሮ ሌላ ሕግ፥ እርሱም የመፋታትን ሕግ፥ አወጣ። ጌታ ግን ወደ ጥንቱ ሕግ ተመልሶ «መፋታት አይገባም» ብሎ ቃሉን ሰጠ፥ (ማቴ.19፡3-9)። እንደዚህም ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛቆሮ.7፡39 አስተምሮአል። በእግዚአብሔር ዓይን ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸውና ከሞት ሌላ ይህን እስራት የሚበጥስ የለም። ከዚያ «አንድ ሥጋ» ከሆኑት ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ከሌላ ሥጋ ጋር ቢገናኝ ብቻ ነው። «ያለ ዝሙት ምክንያት» አይለያዩ ተባለ፥ (ማቴ.5፡31-32፤ 19፡9)። ይህን ሕግ ማፍረስ ከዐሥርቱ ቃላት 7ኛውን ቃል ማፍረስ ነውና፥ የሚፈረድብንም በሰው ልማድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ሕግ ነውና፥ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ በጣም ይጠንቀቅበት።

2. ከቁ.14 እስከ 24 ድረስ የሚገኘው ነገር የብዙዎቻችን ነገር ነው። ነገር ግን «የብዙዎቻችን» ሲባል የእውነተኛ ክርስቲያን ነገር ብቻ ነው። በእምነት ያልጸደቀ ሰው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ከተጻፈው ትግል ምንም አያውቅም። ቅድስና ለዓለም ሰው ሳይሆን አስቀድሞ ጸድቅ ለተቀበለ ሰው ብቻ እንደ ሆነ ታውቆአል። ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት አቀማመጣችንን ይለውጣል እንጂ ኃይል አይሰጠንም። «እንደ ጻድቃን» ያደርገናል፥ ጽድቅም ይቈጥርልናል እንጂ፥ ጽድቅ ከራሳችን የለንም፤ ጻድቃንም ወደ መሆን አያደርሰንም። ነገር ግን በእምነት ጻድቃን ስለሆንን የምንወደውና የምንጠላው ነገር ሁሉ ተለወጠ። አሁን ኃጢአትን እንጠላለንና ኃጢአት መሥራትን አንወድም። የጸደቀ ሰው ቅዱስ ለመሆን የዘወትር ምኞቱ ነው። በውስጥ ሰውነቱ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋልና ሊጠብቀው ይጥራል። ነገር ግን የወደዱትን ለማድረግ የማይችሉ ስንትና ስንቶች ክርስቲያኖች አሉ! መቆም፥ ኃጢአትን ሳያደርጉ በኃጢአት ሳይሸነፉ መኖር ማለት፥ ይታገላሉ። ብዙ ጊዜ በተለይ አንድ ኃጢአት ነው የሚይዛቸው። ያን ኃጢአት መሥራትን አይፈቅዱም አይፈልጉምም፤ ነገር ግን ምንም ቢታገሉ ይወድቃሉ ይሸነፋሉም። እውነተኞች፥

አዲስ የተወለዱ፥ አማኞች ክርስቲያኖች ናቸው፥ በቅድስናም ለመኖርና ቅዱሳን ለመሆን ይናፍቃሉ ይታገላሉም። አንዳንድ ጊዜ እስከ ጥቂት ቀን ድረስ ያሸንፉሉ ደስም ይላቸዋል፤ በመጨረሻ ግን በብልቶቻቸው ያለ ያ «ሌላ ሕግ» ሁልጊዜ ያሸንፋቸዋልና ይወድቃሉ። እውነተኛ ክርስቲያኖች የሆንን ሁሉ ይህን ትግል እናውቅ የለምን? እንፈልጋለን፤ ነገር ግን አንችልም። ፈቃድ አለን፤ ኃይል ግን አጣን። የምናደርገውን አናውቅም፤ ዕብዶች የሆንን ይመስለናል። ለማሸነፍ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን፥ ያልሞከርነው ብልሃት የለም። መሐላ እንምላለን፥ ሰውነታችንን እንቀጣለን፥ እንጸልያለን፥ እንጦማለን፥ እንመነኩሳለንም፥ ያላሰብነው ነገር የለም፤ ነገር ግን በመጨረሻው ላይ ትግላችን ሁሉ ዋጋ የሌለው፥ ተስፋችንም ከንቱ፥ ነገሩ የማይቻል ሆኖ ተገኝቶአል። ተስፋ ቈርጠን ከዚህ ከም.7፡24 ከሚገኘው ሰው ጋር «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነቴ ማን ያድነኛል?» ብለን ወደ መጮኽ ደርሰን የለምን? አንዳንዶቻችንም መውደቅ ከቶ የማናመልጥበት ነገር እንደ ሆነ አሰበናል! ባሪያዎች ነንና አርነት ልንወጣ አንችልም እንላለን።

በዚህ በሚያሳዝን ባርነት የሚይዘን ምንድር ነው? በሽታውን ካወቅን መድኃኒትን ምናልባት እናገኛለንና።

ጥፋቱ መቸም/የተጀመረው በአዳም ጊዜ ነው። አዳም ለእግዚአብሔር ቃል ሳይታዘዝ ለሰይጣን ስለታዘዘ (ዘፍጥ.3፡3-6) እጁን ለሰይጣን ሰጥቶ የሰይጣን ተገዥ (ባሪያ) ሆነ፤ እኛም በእርሱ ባሪያዎች ሆንን፥ ዘፍጥ.1፡26። ሥጋውያን የሆንን በዚያ ጊዜ ነው፥ (ሮሜ 7፡14፤ 8፡3)። ለመግዛት የተፈጠርን (ዘፍጥ.2፡28-30፥ መዝ.8፡4-8) በኃጢአት ምክንያት የምንገዛ ባሪያዎች ሆነን ተገኘን። አዳም፥ ሰውም፥ የሰይጣን ተገዥ በሆነ ጊዜ ሰይጣን ወኪሉን በሥጋው ውስጥ አኖረ። «ሌላ ሕግ» የተባለው ይህ የሰይጣን ወኪል ነው። እርሱም በውስጣችን ነው፥ ከእኛም የበረታ ነው፥ በሥጋችን ነው፥ ስለዚህ በሥጋ እስካለንበት ጊዜ ሁሉ ድረስ ከእኛ ጋር ይሆናል፤ ፈቃዱንም የግድ ያስፈጽመናል። እኔ እውነተኛ ክርስቲያን ስሆን ያ የሰይጣን ወኪል በበለጠ ይፈትነኝ ይሆናል እንጂ ከቶ አይተወኝም፤ ወደ ገዳም መንኵሼ ብሄድ ከንቱ ነው፤ አብሮኝ ይመጣልና፤ መታገልም ከንቱ ነው፥ ከእኔ ይበረታልና! ጳውሎስ «እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ» ሲል ይህን ማለቱ ነው፥ (7፡17፤8)።

እውነተኛ ክርስቲያን ሆይ! ይህን ነገር ዕወቅ አስተውልም! በውስጥህ፥ እርሱም ማለት በሥጋህ፥ የሰይጣን ወኪል አለ። ክፉ የሆነው ሥጋህ አይምሰልህ። ሥጋህ ቅዱስ ነው፥ የእግዚአብሔርም ነው፥ (1ኛቆሮ.6፡19-20)። በሥጋህ ውስጥ ግን ወንበዴ ገብቶአል፥ ይገዛልም፥ አይወጣምም። ሊያወጣው የሚችል ከእርሱ የበረታ ነው እንጂ አንተ ልታወጣው ከቶ አትችልም፥ (ማቴ.12፡29)። «ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል?

ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል» (1ኛቆሮ.15፡57) «... ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።»

እንግዲያስ ማን ያድነኛል?» ትላለህን? ይህ ነው መልካሙ ጥያቄ! አሁንስ ተስፋ አለ! ተስፋ በራስህ ስታደርግ ተስፋ የለም። ሌላን መድኃኒት ለማግኘት በዙሪያህ ስትመለከት መልካም ነው! የሚያድንህ አለና። አንተ እጅህን ከነገሩ ብታነሣ እርሱ ትዳዩን ያደርግልሃል። እንዳች መዳን በራስህ ያለ መስሎሃልን? መዳን ሁሉ በኢየሱስ እንደ ሆነ ረስተሃልን? (የሐዋ.4፡12)። በል! መዳን ወዳለበት ዘንድ ተመልከት። ከዚህ በፊት መቆም አልቻልህም አሁን ግን መድኃኒትህ ጽኑ ነውና መውደቅ ወዳለመቻል ስንኳ ትደርሳለህ! አሁን «የኃጢአት ሕግ» ወደ «ቅድስና ሕግ» ይዛወራል! ቅድስና የተለማመደ ነገር ሊሆን ነውና!

መንገዱ ምንድር ነው? መጀመሪያ፥ ከዚህ በፊት እንዳየን ሁሉ፥ በእምነት ነው እንጂ በሥራ፥ በራስህ ትግል፥ ከቶ አይደለም። መንገዱ በምዕ.6 ላይ ባገኘነው ነገር፥ እርሱም ማለት ከክርስቶስ ጋር መዋሐዳችንን በመቁጠር ነው፥ (6፡11።) ይህ የድል <u>በር</u> ነው። በዚህ በመዋሐዳችን ስንቈጥር በምዕ.8ትም ላይ ይህ መቁጠር «በመንፈስ መመላለስ» ይባላል! ያደረብን መንፈስ ቅዱስ ያን «ሌላ ሕግ» አድክሞ ለመቆምና በማያቋርጥ ቅድስና ለመመላለስ ያስችለናል። እኛ ስናምን መንፈስ ቅዱስ ለማሸነፍ ይሰጠናል። የድል ጎዳና ይህ ነው። በሩ በምዕ.6! ጎዳናውም በምዕ.8 ነው።

አሁን የመውደቅ ሕግ ቀርቶአል፥ የመቆምም ሕግ ገብቶአል። ከክርስቶስ ጋር መዋሐዴን ከቈጠርሁ ኃጢአትን መሥራት ግዴታ የለም፥ ለእርሱም መታዘዝ የለብኝም። ከኃጢአት ሕግ እርነት ወጣሁ ማለት ነው። ኃጢአትን መሥራት መቼም ገና የሚቻል ነገር ነው፥ መቁጠሬንም ቸል ያልሁት እንደሆነ ኃጢአትን እሠራለሁ። ነገር ግን በፈቃዴ ነው እንጂ ግዴታው ቀርቶአል። ኃጢአትን መሥራት አሁን አይገድደኝም፥ ባሪያ የነበርሁ አሁን ጌታ ሆንሁ። ጎዳናውን በም.8 እናያለን! ነገር ግን አሳቡን አሁን እንገንዘበው፦ ያለብኝ ማመን ነው እንጂ መታገልስ የለብኝም። ከክርስቶስ ጋር መዋሐዴን በምቈጥርበት ጊዜ ሁሉ በውስጤ ያለው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በውስጤ ባለው በሰይጣን ወኪል ላይ የማያቋርጥ ድል ይሰጠኛል።

* * *

# ምዕራፍ 8

1. እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። 2. በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። 3.4. ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። 5. እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። 6. ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። 7. ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ 8. በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።

9. እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። 10. ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። 11. ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።

12. እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። 13. እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። 14. በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። 15. አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደ ገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። 16. የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። 17. ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።

18. ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። 19. የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ 20. በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ 21. ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት መጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። 22. ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። 23. እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኩራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነትን እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። 24. በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? 25. የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።

26. እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ 27. ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

28. እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። 29. ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፤ 30. አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።

31. እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? 32. ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? 33. እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከስሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው? 34. የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። 35. ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?

36. ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን

ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

37. በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። 38. ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ 39. ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

* * *

# ምዕራፍ ስምንት

ይህ የሙሉ መዳን ምዕራፍ ነው። ስለ ሰውነታችን መዳን፥ በፊታችን ስለሚቈየን ክብር፥ ስለ መዳናችን ጽናት፥ እናነባለን። የእግዚአብሔር ፈቃድ ነፍሳችን ብቻ እንዲድን ሳይሆን ሰውነታችንም ደግሞ እንዲድንና እኛ ልጆቹና ወራሾቹ ሆነን የክብሩ ተካፋዮች እንድንሆን ነው። ይህም ፈቃዱ ከመፈጸሙ ሊከለክል የሚችል ከቶ አንድም ነገር የለም። በምዕራፉም መጨረሻ ላይ ደግሞ፥ በምዕ.6 እና በምዕ.7 መጨረሻ ላይ እንዳገኘነው፥ ይህ ሙሉ መዳን የሚገኝበት «በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን» እንደ ሆነ እናያለን። በእርሱ ሙሉ፥ የተፈጸመ፥ የዘላለምም መዳን አለ።

ክርስቶስን በማመን ምክንያት ጽድቅ ከተቈጠረልን በኃጢአታችን ሁሉ ኩነኔ እንደሌለብን በምዕ.3 መጨረሻና በምዕ.4 መጨረሻ ላይ አይተናል። ከዚያ በኋላ በምዕ.5 ላይ ስለተወረሰ ኃጢአት ደግሞ ቢናገር «ኃጢአት በበዛበት ዘንድ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ» ብሎአልና ከእርሱ ደግሞ ኩነኔ እንደሌለብን ተረዳን። አሁንም ደግሞ በምዕ.7 ስለሚገዛን ኃጢአት አንብበናል። በዚያም ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ያ ከኃጢአት ኃይል በታች የተጠቃ ክርስቲያን «እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ብሎ ጮኾ ነበር። ክርስቲያን ነውና ነፍሱ እንደ ዳነ ያውቃል፤ አሁን የተቸገረበት በሰውነቱ ነው። ጻድቅ ሰው ቅዱስ ደግሞ ሊሆን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ለጽድቁ እንዳሰበ እንዲሁ ደግሞ ለቅድስናው እንዳሰበ በዚያ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ተስፋ ተሰጥቶአል። «በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» ተብሎ ነበር። ማለት፥ ከዚያ በሰውነቱ ካለ የኃጢአት ኃይልና በሰውነቱ ካለ ሞት፥ በእግዚአብሔር ዘንድ መዳን አለ፥ ያም መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ነው፥ ማለት ነው። ስለዚህ አሁን በምዕ.8 ሰውነታችን ደግሞ እንዴት እንደሚድን ይነግረናል። ሰውነታችን ካደረበት የኃጢአት ኃይል ዛሬ የሚድንበት እና ከዚህ በኋላ ከኃጢአት መኖር ስንኳ የሚድንበት፥ በክርስቶስ ካመንንና ከእርሱ ጋር ከተዋሐድን በኋላ በተሰጠንና አሁን በሰውነታችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ለሰውነታችን ፍጹም ድል የሚሰጥ እርሱ ነው። «ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነታችን» የሚያድነን መንፈስ ቅዱስ ነው።

ትልቁ የዚህ ምዕራፍ ችግር «መንፈስ» የተባለውን ቃል መተርጎም ነው። ከዚህ በፊት በመልእክቱ ይህን ቃል ብዙ ጊዜ አላገኘነውም። በዚህ ምዕ.8 ላይ ግን 21 ጊዜ እናገኘዋለን! «መንፈስ» ሲባል አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ማለት እንደሆነ ግልጽ ሲሆን፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ወይም የሰው መንፈስ ወይም ደግሞ መንፈሳዊ ነገር እንደ ሆነ በእርግጥ አይታወቅም። የመጽሐፍ ቅዱስ

ሊቃውንት አልተስማሙበትም፤ አንዱም እንደዚህ አንዱም እንደዚያ አድርጎ ተርጉሞታል።

ሁለተኛ ችግር ደግሞ አለ። ሐዋርያው በቁ.2 ስለ ኃጢአት እና ስለ ሞት ሕግ ሲናገር ስለ የትኛው ሕግ ነው የሚናገረው? ስለ እግዚአብሔር ሕግ ነውን? እርሱ ኃጢአትን ገልጦ ወደ ሞት ያደርሳልና፤ ደግሞ በሚከተለው ቁጥር ስለዚያ ሕግ በግልጥ ይናገራልና። ወይም በምዕ.7፡23ና 24 ላይ የተባለለት ወደዚህ ሞት የሚያደርስ የኃጢአት ሕግ ነው? ይህ ነው ብሎ ነገሩን መቍረጥ ያስቸግራል።

ቢሆንም፥ መሠረታዊው አሳብ፥ እርሱም የድል ጎዳና፥ ፈቃዳችን ለመንፈስ ቅዱስ ሲያደላ ሲያዘነብልም መንፈስ ቅዱስ ራሱ ድሉን እንደሚሰጠን ነው። እኛ በክርስቶስ ለኃጢአት እንደሞትን፥ በእርሱም ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆንን፥ ስንቈጥር እርሱ መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ሰጥቶ የእግዚአብሔርን ሕግ እንድንፈጽም ያደርጋል። «እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚመላለስ ሰው»፥ እርሱም ማለት በክርስቶስ ያላመነና መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት ፍጥረታዊ ሰው (1ኛቆሮ.2፡14)፥ ብቻውን ነውና ያ በውስጡ ያለው የሰይጣን ወኪል የግድ ይገዛዋል። በክርስቶስ አምኖ ከእርሱ ጋር እንደሞተና እንደተነሣ የሚቈጥረው ሰው ግን በውስጡ፥ ከሰይጣን ወኪል ሌላ፤ ሌላ እርሱም የእግዚአብሔር ወኪል የሆነ መንፈስ ቅዱስ፥ አለ። መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ነውና፥ ከተፈጠረም ከሰይጣን ፈጣሪ አምላክ ይበረታልና፥ እኛ ለመንፈስ ቅዱስ አድልተን «እንደ መንፈስ ፈቃድ» ብንመላለስ ያደረብን መንፈስ ቅዱስ የማያቋርጥ ድል ይሰጠናል። የድል ጎዳና ይህ ነው።

ቁ.1-11፡- በም.7 ላይ የተናገረለት ሰው በውስጡ ካለው ኃጢአት የተነሣ ተቸግሮ «ማን ያድነኛል?» ብሎ ጮኾ ነበር። ሐዋርያው መልስ ለመስጠት ሲጀምር፥ እስከ አሁን ድረስ የጻፈውን ሁሉ አስተውሎ «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ማንኛውም ዓይነት ኵነኔ የለባቸውም» ብሎ ለመልሱ የሚሆን መሠረታዊ ነገር አስቀድሞ ይመሠርታል። በተሠራ ኃጢአት ምክንያት በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑትና ለተዋሐዱት ኵነኔ የለም፥ (3፡22-25፤ 4፡23-25)። በተወረሰ ኃጢአት ምክንያት ደግሞ እንደዚሁ ኵነኔ የለም፥ (5፡18-21)። አሁን ደግሞ በሰውነታችን ላለው ኃጢአት እንዳንገዛ በክርስቶስ ኢየሱስ ኵነኔ የለም ተባለ፥ (8፡1።) ቁ.2 ደግሞ ምክንያቱን ያስረዳል። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሕግ ከዚያ በም.7፡23ና 24 ላይ ካየነው፥ ሰውነታችንን ወደ ሞት ከሚያደርስ የኃጢአት «ሕግ» አውጥቶናል። ኃጢአትን መሥራት ሕግ ሆኖ ነበር፥ እኔም ባሪያ ሆኜ ነበር። ከዚያ ሕግና ከዚያ ባርነት ሌላ «ሕግ»፥ እርሱም የመንፈስ ቅዱስ ሕግ፥ አርነት አውጥቶኛል። ይህ እውነት ነው፥ ነገር ግን ከዚህ በሚቀጥሉት ቍጥሮች ሐዋርያው ይህ ነገር ለመንፈሳውያን፥ እርሱም ማለት «በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ብቻ እንደሆነ ይጽፋል። መንፈስ ቅዱስ «የሕይወት መንፈስ» የተባለበት ምክንያት እርሱ ሕይወት ሰጪ ሆኖ ለሞት የተሰጠ ሰውነታችንን (7፡24) ሕያው የሚያደርግ

እርሱ ስለ ሆነ ነው። መንፈስ ቅዱስ ይህን አርነት ሊያወጣን የሚችልበት እግዚአብሔር የገዛ ልጁን ልኮ ኃጢአትን በሥጋ ስለ ኰነነ ነው። በልጁ ላይ ሆኖአልና አሁን «በእርሱ ላለን ኵነኔ የለብንም። እግዚአብሔር የገዛ ልጁን ልኮ ኃጢአትን በሥጋ ኰንኖአልና ኃጢአት በእኛ ዛሬ ሊሠለጥን አይችልም። ልጁ የተላከ «በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ» ነው እንጂ የእርሱ ሥጋ ኃጢአተኛ አልነበረም። ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለተወለደ በኃጢአተኛ ሥጋ አልነበረም፤ ነገር ግን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ መጥቶአል፥ (ዮሐ.1፡14፤ 2ኛቆሮ.5፡21፤ ዕብ.4፡15)። በእርሱ ሥጋ፥ በዚያም እኛን በሚያስቸግረን ዓይነት ሥጋ፥ እግዚአብሔር ኃጢአትን ኰነነ። ኢየሱስም ለኃጢአት ሁሉ መሥዋዕትን አቀረበ። እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት የኃጢአት ነገር አልቆላቸዋል። በምዕ. 7 እንዳነበብን፥ ሕግ የተሰጠበት ምክንያት ከኃጢአት ጠብቆ በቅድስና ሊያራምደን ነበር። እኛ ግን የሥጋ በመሆናችን (7፡14) ይህን ለማድረግ ሕጉ አልቻለም። ሕግ መንፈሳዊ ሆኖ ለመንፈሳውያን ነበረ። ሕጉ የሚፈጸም ከሆነ እኛ መንፈሳውያን እንድንሆን ያስፈልጋል፤ እግዚአብሔርም ያደረገው ይህንኑ ነው። መንፈሱን በውስጣችን በማኖር መንፈሳዊያን አደረገንና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ፥ በእኛ፥ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸማል፤ እኛም ከኃጢአት ተጠብቀን በቅድስና ልንኖር እንችላለን። እንደ መንፈስ ፈቃድ ብንመላለስ፥ ቅድስና ሕግ ይሆንልናል ማለት ነው። እንደ ሥጋ ፈቃድና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚመላለሱ በዮሐ.3፡6 ላይ እንደተነገረባቸውና እንደ ተነገረላቸው ናቸው። እንደ ሥጋ የሚመላለሱ ሥጋውያን ናቸው፤ እንደ መንፈስ የሚመላለሱ መንፈሳውያን ናቸው። መንፈሳዊ ሰውና ሥጋዊ ሰው ፈጽሞ በልዩ ሕይወት ውስጥ ሥጋ ከቶ አይችልም፤ ነገር ግን በእኛ፥ በመንፈሳውያን፥ «በክርስቶስ» በሆንን፥ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አለ፥ እርሱም ለሕግ እንድንታዘዝ ያደርጋል፥ (ሕዝ.36፡27)።

እንደ ሥጋ ፈቃድ በሚመላለስ በፍጥረታዊ ሰው (2ኛቆሮ.2፡14) እና እንደ መንፈስ ፈቃድ በሚመላለስ በመንፈሳዊ ሰው መካከል ታላቅ ልዩነት አለ። እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ (ኤፌ.2፡3) የሥጋን ነገር ያስባሉ፤ እንደዚህም ማሰብ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፥ እንደዚህም የሚሄዱ ለሕግ መገዛት አይችሉምና፥ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ አይችሉም። «አይቻልም!» የተባለው ቃል በሥጋ በሆኑት ላይ ለዘላለሙ ተጽፎአል። ነገር ግን እንደ መንፈስ ፈቃድ ብንመላለስ፥ ከመንፈስ የተወለድን ስንሆን ማለት፥ የመንፈስን ነገር እናስባለንና ለእግዚአብሔር ሕግ ልንገዛና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንችላለን። ለእኛ መቻል አለ ማለት ነው። አለመቻሉ ለሥጋውያን ነው እንጂ ለእኛ ለመንፈሳውያን አይደለም፥ (ቍ.1-8)።

በምዕ.7፡24 ላይ የተገኘው ሰው «ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነቴ ማን ያድነኛል?» ብሎ ሲጮኽ የተመኘው ሰውነቱን ከገዛው ከኃጢአት ኃይልና ከሞት የሚያድን

ከበረና፥ በዚህ በምዕ.8፡1-8 ድረስ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ በመኖርና በመሥራት ሰውነቱ ከዚያ ከሠለጠነበት ኃጢአት እንዴት እንደዳነ ተናግሮናል። አሁን ደግሞ ከቊ.9-11 ድረስ ሰውነቱ ባደረበት መንፈስ ቅዱስ ከሞት ደግሞ እንዴት እንደሚድን ያሳያል። በመንፈሳዊ ሰው፥ ማለት፥ «በክርስቶስ» በሆነ ሰው መንፈስ ቅዱስ ገብቶ ሰውነቱን ቤተ መቅደሱ ያደርግና (1ኛቆሮ.6፡19-20) ከኃጢአት ኃይል ከሞትም ያድነዋል። ስለዚህ በቊ. 9 የኢየሱስ ክርስቶስና ቅዱሳን ሊሆኑ ለተጠሩት በሮሜ ላሉት ሲጽፍ (1፡6-7) ሐዋርያው በድፍረት ቃል «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም» ይላል። ጥርጥር ያለበት እንደ መሆኑ «ያለ እንደሆነ» ሳይል «ከሆነ» ይላቸዋል። አለና፥ «ከሆነ»፥ በሥጋ ተይዛችሁ ሳይሆን መንፈሳውያን ናችሁ ይላል። ማለት፥ ነገሩ አለቀ! መንፈሳውያን ናችሁና መንፈስ ቅዱስ ሰውነታችሁን ከኃጢአት ኃይል ከሞትም ያድናል ማለት ነው። ምናልባት ግን የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ሰው ቢኖር፥ ያ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን አይደለም። የክርስቶስን ስም ይሸከምና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄድ ይሆናል እንጂ በእውነት የክርስቶስ ወገን አይደለም። ክርስቶስ ግን በመንፈሱ በእኛ ውስጥ ከሆነ! እውነት ነው፥ ሰውነታችን መቸም ከአዳም በወረስነው በኃጢአት ጠንቅ ምክንያት ሟች ነው (5፡12)፥ መንፈሳችን ግን ክርስቶስ ባደረገልን ሥራና ከክርስቶስ ዘንድ በተቀበልነው ጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። ሰውነታችን ይሞታል! ነገር ግን ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው መንፈስ ቅዱስ እኛን ደግሞ ያስነሣል። ማለት፥ «ለሚሞተው ሰውነታችን ሕይወትን ይሰጣል» ማለት ነው። በም.7፡24 ላይ የነበረውም ሰው የተመኘው ይኸው ነገር ነው! የሰውነቱን መዳን ተመኝቶ «ማን ያድነኛል?» ብሎ ቢጮኽ ሐዋርያው «መንፈስ ቅዱስ ያድንሃል!» ብሎ መልስ ሰጥቶአል። እግዚአብሔር አብ የሙሉ መዳናችንን አሳብ አስቦአል! እግዚአብሔር ወልድ ለሙሉ መዳናችን የሚሆነን መሠረት ጥሎአል! እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚህ አሳብና መሠረት ላይ ሠርቶ ሙሉ መዳናችንን ይፈጽማል። ስለዚህ ነው በቊ.9 ላይ «የእግዚአብሔር መንፈስ» ከተባለ በኋላ «የክርስቶስ መንፈስ» የተባለው። በቊ.11ም ደግሞ «መንፈሱ» ሲል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው። በውስጣችን በሚኖር መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት ኃይል ከሞትም መዳንን እናገኛለን።

<u>ቊ.12-17</u>፡- አሁንም ደግሞ ሐዋርያው እንደ መንፈስ ፈቃድ እንኖር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስም እንመራ ዘንድ ያለብንን ዕዳ ያመለክተናል። ሥጋ የዋለልን ውለታ ከቶ የለምና ለሥጋ ምንም ዕዳ የለብንም። እንደ ሥጋ ፈቃድ እሺ ብለን ብንኖር የግድ «ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ብለን እንደገና እንጮኻለን። በውስጣችን ባለው መንፈስ ቅዱስ ግን በየጊዜው ሁሉ ከሥጋችን የሚመነጭ የኃጢአት መሻት (7፡5) ተንኰልንም ብንገድል በሕይወት፥ በነፃነትና በአርነት፥ በኃይልና በደስታ፥ በዚያም በበዛ ሕይወት (ዮሐ.10፡10) እንኖራለን። እንደዚህ ስንኖር ግን፥ ማለት እንደ መንፈስ ፈቃድ ኖረን ምን ጊዜም ቢሆን

በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ነን እንጂ ተመልሰን ባሪያዎች መሆናችን አይደለም። (ጳውሎስ በምዕ.6፡19 ላይ የተሰጠውን ምሳሌ ያልወደደበት ምክንያት ይህ ነው።) ለዚህም ነገር የሚመሰክር መንፈሳችን ነው፤ ለምን ቢሉ፥ አሁን እንደገና የባርነትን መንፈስ ተቀብለን በፍርሃት አንገዛም፤ ነገር ግን ከልባችን የልጅነት መንፈስ ፈልቆ እግዚአብሔርን «አባት» እንለው ዘንድ ያሰኘናልና። የሚመሰክርም የራሳችን መንፈስ ብቻ አይደለም፤ ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ «በእውነት ልጆችህ ናቸው» ብሎ ለልጅነታችን ይመሰክራል (ኢሳ.63፡16)። እንግዲያስ መንፈስ ቅዱስ መስክሮአልና በእውነት ልጆች መሆናችን ነው። ልጆችም ከሆንን እንደ ሌሎች ልጆች ሁሉ ሆነን ወራሾች፥ ያውም የእግዚአብሔር ወራሾች፥ ነን፤ ከክርስቶስም ጋር መከራ ዛሬ ተቀብለን አንድነታችንን ብናስረዳ በኋላ ከእርሱ ጋር ደግሞ የክብር ተካፋዮች እንሆናለን።

ቅድስና ዕዳ ነው! እንደዚህ የሚያዩት እንዴት ጥቂቶች ናቸው! በብዙ ሰዎች ዘንድ ቅድስና ለአንዳንዶች ለቅዱሳንም እንጂ ለእነርሱና ለሰው ሁሉ እንደሆነ ከቶ አይመስላቸውም። ጳውሎስ ግን በቅድስና መኖር መቻሉን አረጋግጦ ሲያበቃ ለክርስቲያን ሁሉ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ይነግረናል። ቅድስና ዕዳ ነው! «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነው» (1ኛተሰ.4፡3)። «ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።» (ዕብ.12፡14)። «የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛጴጥ.1፡13-19) ተብሎአል። አዎን፥ ቅድስና ለክርስቲያን ሁሉ የሚሆን ዕዳ ነው። እንቀደስ ዘንድ፥ ከኃጢአት የተለየን እንሆን ዘንድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን እንራመድ ዘንድ፥ በላያችን ያለ ዕዳ ነው። እግዚአብሔር አብ ይህን ያህል ካደረገልን፥ እግዚአብሔር ወልድ ይህን ያህል ከተሠቃየልን፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ቤተ መቅደሱን በውስጣችን ካደረገ፥ በቅድስና እንኖር ዘንድ ዕዳ በእውነት አለብን። ዕዳ አለብን፥ መክፈልም የግዴታ ነው። ዱሮ ልንከፍል አንችልም ነበር፤ ዛሬ ግን፥ እግዚአብሔር ይመስገን፥ እንችላለን።

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሥጋና ከኃጢአት የሚመነጨውን ሁሉ መግደል ያስፈልገናል። ሳናቋርጥ በየሰዓቱና በየቀኑ የምንፈጽመው ግዳጃችን ነው። በመታገልና ራሳችንን ለማስገደድ በመሞከር ሳይሆን (ቈላ.2፡23) መንፈስ ቅዱስ ፈቃዱን ሁሉ በእኛ እንዲፈጽም በመፍቀድ ነው። የሥጋን ሥራ ሁሉ ብልቶቻችንንም (ምኞተ ፍትወትን) መግደል ያስፈልገናል፥ (ቈላ.3፡5-8)። ፈቃዱ ከእኛ ነው፤ ኃይሉ ግን ከመንፈስ ቅዱስ ነው። እውነት ነው፥ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ወገን በሆነው ሁሉ ዘንድ አለ፤ አቀማመጡ ግን የእንግዳ ሳይሆን የባለቤትና የገዥ እንዲሆን ያስፈልጋል። በእኛ ላይ ሙሉ ሥልጣን ከተሰጠው እርሱ የማያቋርጥ ድል ይሰጠናል። መንፈስ ቅዱስን በላያችን በማንገሥ፥ ለእርሱም

ሁልጊዜ በመገዛት፥ በእርሱም በመመራት፥ በዚህ የሰውነታችንን ሥራ እንገድላለን።

«መንፈስ ቅዱስን በላያችን በማንገሥ»? «ለእርሱም በመገዛት»? ይህ ማለት ወደ ባርነት መመለስ ማለት አይደለምን? ለእርሱ ሁልጊዜ መታዘዝ በእርሱም መመራት፥ ባርነት አይደለምን? ከቶ አይደለም! ልጅነት ነው እንጂ ባርነት ከቶ አይደለም። የምንገዛለት እንደ ባሪያዎች በግዴታ ሳይሆን እንደ ልጆች በእሺታ ነው፥ (መዝ.39፡8)። ልጅ ለአባቱ እንደሚታዘዝ ነው እንጂ ባሪያ ለጌታው እንደሚታዘዝ አይደለም። መንፈስ ቅዱስን መከተልና ለእርሱ መታዘዝ ነፃነት ነው እንጂ ከቶ ባርነት አይደለም። ስንከተለውም ነገሩን እናስተውላለን። ስንከተልና ስንታዘዝለት መንፈሳችን የባርነት መንፈስ ሳይሆን የልጅነት መንፈስ ይሆናልና ፍርሃት በጭራሽ ሳይሰማን «አባት» ብለን በፍቅርና በደስታ በእግዚአብሔር ፊት እንቀርባለን።

ባሪያዎች! (6፡19) ሚስቶች! (7፡4-6) ልጆች! (8፡14-16)። የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ (1ኛዮሐ.3፡1) እርሱም ስንኳ አይበቃም፤ ወራሾች ነን እንጂ! (ቊ.17።) የመንግሥት ወራሽ ለመሆን አንዳንዶቻችን በወደድን ነበር፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ወራሾች ሆነን! የክብርም ወራሾች! በእውነት ሙሉ መዳን እነሆ! የሰውነታችንን መዳን ስንመኝ ነበር። ከኃጢአት ኃይልና ደግሞ ከሞት መዳናችንን ከዚህ በፊት አይተናል፥ (ቊ.1-11።) አሁን ግን ከዚያ የሚበልጥ ወራሽነታችንን አይተናል። ሰው አሁን «ከእኛ እንደ አንዱ» ሆኖአል፥ (ዘፍጥ. 1፡26፤ 3፡22)። ሙሉ መዳን ይህ አይደለንም? ይህም ለሰው ሁሉ ነው።

<u>ቊ.18-30</u>፡- በቊ.17 ላይ ከክርስቶስ ጋር አብረን መከራን ብንቀበል አብረን እንከበራለን ተብሎ ነበር። አሁንም፤ በቊ. 18 በዚህ ዘመን የሚደርስብን መከራና ከክርስቶስ ጋር የምንካፈለው ክብር ቢመዛዘን የአሁኑ ሥቃይ አነስተኛ ሆኖ ይታያል ይላል። ስለዚያም ክብር ሲናገር «ይገለጥ ዘንድ አለው» ይላል፤ ለምን ቢባል፥ የማይቀር ነገር ነውና በእርግጥ ይገለጣል።

አሁንም ደግሞ የክብሩን መገለጥ እርግጠኛነት አብዝቶ ለማሳየት የሚጠባበቁት ሦስት ነገሮች እንዳሉ ይነግረናል፤ እነርሱም ፍጥረት (ቊ. 19-22)፥ እኛ ራሳችን (ቊ.23-25)፥ እና መንፈስ ቅዱስ (ቊ. 26-27) ናቸው።

ፍጥረት፥ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆናችንን መገለጥን ይጠባበቃል፤ ስለሆነም፥ በሰው ውድቀት ተካፋይ ሆኖ በእኩል ከንቱነት ተይዞአልና። («ሁሉ ከንቱ ነው፥ አለ ሰባኪው፤ ሁሉ ከንቱ ነው» (መክ.1፡2)። ለከንቱነት ተገዝቶአል፥ ነገር ግን ከዚያ ባርነት ወጥቶ ከእኛ ጋር ወደ ክብር ነፃነት ለመድረስ ተስፋ አድርጎ በመቃተትና በምጥ በተስፋም ይጠባበቃል።

እኛም እንደዚሁ! ጽድቅ ተቈጥሮልናልና ነፍሳችን ድናለች፥ መንፈስ ቅዱስም በውስጣችን በመኖሩ ሰውነታችን ከኃጢአት ኃይል ከሞትም ድኖአል፤ ነገር ግን የተቀበልነው በኩራትን (መጀመሪያን) እንደሆነ እንጂ ያለውን ሁሉ እንደተቀበልን አይመስለንም። እርግጥ፥ ኩነኔ በፍጹም የለብንም፤ ቢሆንም፥ ሥጋችን ገና ከእኛ ጋር አለ፤ እርሱም የኃጢአት መደበቂያ መጣሪያም በመሆኑ ዘወትር ያስቸግረናል። «ሰውነታችን ምነው በዳነ! ቀኑስ ምነው በመጣ! ልጅነታችን ምነው በተገለጠ!» ብለን እንቃትታለን። ፍጥረት በተስፋ እንደሚኖር እንዲሁ እኛ ደግሞ በተስፋ እንኖራለን። እውነት ነው፥ ድነናል፥ ከዚያም በፊት ብዙን ተቀብለናል፤ ነገር ግን ገና ወደ ፊት ሌላ፥ ገና ያላየነው፥ ነገር እንዳለ ይሰማናልና ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ተስፋ መከራን ለመታገሥ ይረዳናል።

እንደዚሁ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ! ያን የመገለጣችንን ቀን ተስፋ እያደረገ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እየቃተተ ይማልድልናል። ለዚያ ለሰውነታችን መዳን ተስፋ እያደረግን «ቀኑ ምነው በመጣ!» እያልን ስንኖር የምንመኘውን ብዙ ጊዜ በእውነት ሳናስተውል ለዚያ መዳን ለዚያም ቀን መጸለይ ስንኳ አናውቅም። ይሁን እንጂ፥ እኛ ባለማስተዋላችንና በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት በመሸነፋችን ስንደክም ያ በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ ገና በማይነገር መቃተት ሲማልድልን ይገኛል።

ደግሞም ሌላ አለ! እግዚአብሔር ራሱ ያን ቀን ይጠባበቃል! ሁላችን የምንመኘውና ተስፋ የምናደርግበት ነገር እግዚአብሔር ራሱ የፈቀደውን ነገር ነው። እርሱ ይህንኑ ነገር ለመፈጸም «በመጀመሪያው» ከተባለ ዘመን (ዘፍጥ.1፡1፤ ዮሐ.1፡1)። ቈርጦአል። እርሱ ልባችንን መርምሮ የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ያውቃል፥ ፈቃዱም ነውና እሺ ይላል።

ያ ቀን እንዲደርስና በዚያ ክብር እንድንገባ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እናውቃለንና እግዚአብሔርን ለሚወዱትና ግሩም እንደ ሆነ አሳቡም ለተጠሩት ማንኛውም ነገር ሁሉ፥ ክፉም ሆኖ ቢታይ በጎም ሆኖ ቢታይ፥ ለዚህ ግብ የሚረዳ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል! ነገር ግን እዚህ ላይ ደግሞ እንጠንቀቅ፤ ለምን ቢሉ፥ ነገር ሁሉ ለበጎ የሚደረግላቸው «እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደ አሳቡ በእርሱ ለተጠሩት» ብቻ እንደሆኑ ማስተዋል ያስፈልገናልና። እነዚህ ተስፋዎች እግዚአብሔርን ለሚወዱትና በእርሱ ለተጠሩት ብቻ ናቸው እንጂ እውነተኞች ክርስቲያኖች ላልሆኑት አይደሉም። እነዚህ እውነተኞች ክርስቲያኖች እርሱን ሳያውቁ በፊት እንኳ እርሱ ዐወቃቸው ዐውቆአቸውም፥ ክርስቶስ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ በመልኩ ይመስሉት ዘንድ ወሰኖአል። አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ጠራ (በክርስቶስ ያመኑበት በዚህ ምክንያት ነው)፤ የጠራቸውንም አጸደቀ ያጸደቃቸውንም አከበረ። መልካም ሥራ የጀመረው ወደ ፍጻሜ አደረሰው፤ ሰውን ከዘላለም ጥፋት ወደ ሙሉ መዳን አሻገረ ማለት ነው። ለስሙ ክብር ይሁን ለዘላለም!

ማስገንዘቢያ

1. በቍ.17 ላይ በመከራና በክብር መካከል ያለውን መተሳሰር እናያለን። «አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» ይላል። እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው በዚህ ዓለም ሳለ መከራን የግድ ይቀበላል። የዓለም ገዥ ሰይጣን ነውና (ዮሐ.14፡30) እኛ ከእርሱ ዘንድ የሸፈትን ስንሆን ገና በግዛቱ ሳለን የግድ ያሳድደናል። እርሱም ብቻ ሳይሆን፥ ወገኖቹ የሆኑቱ ያሳድዱናል፥ (ገላ.4፡29)። መከራ አዲስ ወይም እንግዳ ነገር አይደለም (1ኛጴጥ.4፡12-14)፤ ቅዱስ ጴጥሮስ «የተጠራችሁለት ለዚህ ነው» ይላል፥ (1ኛጴጥ.2፡21)። ቅዱስ ጳውሎስም «ተሰጥቶአችኋል» ይላል፥ (ፊልጵ.1፡28-30)። ሐዋርያትም ደግሞ «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» እያሉ ያስተምሩ ነበር፥ (የሐዋ.14፡21-22)።

በዚህ ዓለም ብንሰደድ ግን በመንግሥተ ሰማያት እንከበራለን፥ (ማቴ.5፡3-12)። ምሳሌያችን ጌታችን ነው (1ኛጴጥ.2፡21፤ ዕብ.2፡9)፥ ነቢያትም ናቸው (ያዕ.5፡10-12)፥ ሐዋርያትም ናቸው (2ኛቆር.11፡23-27)፥ የዱሮ ሽማግሌዎችም ናቸው፥ (ዕብ.11፡33-38)። እንግዲያስ ስድብ ወይም መከራ ወይም ስደት የደረሰብን እንደሆነ ለመሸሽ አናስብ፤ መከራ ወደ ክብር የሚያገባ በር ነውና።

2. የእግዚአብሔር አሳብ በሙሉ ሊያድነን ነበረና ከወደቅንበት ዘንድ፥ እርሱም ማለት ወደ እርሱ መልክና ምሳሌ ነበረና (ዘፍጥ.1፡26-27) ሊመልሰን ቈርጦአል፥ (ቍ.29።) ያ መልክና ምሳሌ የተበላሸብን በኃጢአት ምክንያት ነበርና እግዚአብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት ባዳነን ጊዜ ወደዚያ መልክና ምሳሌ እንድንመለስ አስችሎናል። እግዚአብሔር ልጆቹ አደረገን (ቍ.15-17) ልጆቹም የአንድ አባት ልጆች ናቸውና ወንድማማቾቹ እንዲመሳሰሉ ፈቅዶአል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኵር ሆኖ በእርሱ የዳኑት እንዲመስሉት እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ጀምሮ ወስኖአል። ቍ.29-30:- ወደዚያ መልክና ምሳሌ የሚመልሰን እንደ ጠራቢ ሆኖ በውስጣችን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው። መልካችንና ምሳሌያችን ገና አልተለወጠምና ዛሬ ምን እንደ ሆንን አልተገለጠም፤ ልጅነታችን አይታይምና ዓለም አያውቀንም (1ዮሐ.3፡1-2)። የምንገለጥበት ቀን ግን ይመጣል። የአንድ አገር አርበኛ እስከ መፈጸሙ ድረስ በጨርቅ የተሸፈነውን ሐውልት ከዕለታት አንድ ቀን እንደሚገልጡ እንዲሁ እግዚአብሔር ከዕለታት አንድ ቀን በዚያ ሥጋችን የተሸፈነውንና በመንፈስ ቅዱስ ጠራቢነት የወጣውን አዲስ መልካችንን ይገልጣል፤ ሲገልጥም በልጁ መልክ ሆነን እንታያለን። ልጁም አባቱን እግዚአብሔርን ይመስላልና (ዕብ.1፡2-3) በዚያን ዕለት እኛ እግዚአብሔርን መስለን ወደ ተፈጠርንበት መልክ ተመልሰን እንገኛለንና የኃጢአት ጠንቅ ሁሉ

ይወገዳል። በዚያን ዕለት እግዚአብሔር የክርስቶስን ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፥ (ፊልጵ.3፡21)።

ይህስ መቼ ይሆናል? የምንገለጥበት ቀን የጌታችን ኢየሱስ የዳግም ምጽአት ቀን ነው፥ (1ቆሮ.15፡51-57፤ 1ተሰ.4፡15-17፤ 1ዮሐ.3፡2)። በዚያ ቀን ጌታ ገና ሲመጣ ሳለ በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለንና ይህን የሚያስቸግረንን ሥጋችን ትተን ሁለመናው ንጹሕ የሆነውን የክብር ሥጋችንን እንለብሳለን። በዚያ ቀን ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሥጋ (7፡24) እንድናለን። በዚያ ቀን ሰውነታችን ይድናል፥ (8፡23) በዚያ ቀን ክርስቶስን እንመስላለን፥ (8፡29።) በዚያ ቀን ይገዛን የነበረው ኃጢአትና ሞት ያልፋል። «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ለዘላለም ይሁን! ፍጥረት የሚጠባበቀው ቀን ይህ ነው።

3. ፍጥረት በሰው ውድቀት ተካፋይ መሆኑን በቊ.19-22 ላይ እናያለን። አዳም (ሰው) ኃጢአትን በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር «ምድር ስለ አንተ የተረገመች ትሁን» ብሎ ሲፈርድ (ዘፍጥ.3፡17) ፍጥረት «ስለ ሰው» እንደ ተረገመ እናያለን። ከዚያ ቀን ጀምሮ እሾህ አሜከላም በቅሎአል፥ (ዘፍጥ.3፡18)። ይህም ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት ሞት አልገባም ነበርና በዚያ ቀን ከኃጢአት የተነሣ ሞት በሰው እንዳለፈ፥ እንዲሁ በፍጥረት ሁሉ እንዳለፈ የማይጠረጠር ነገር ነው፥ (ሮሜ 5፡12)። የፍጥረት መሪ የሆነ ሰው ሲረክስ ፍጥረት ሁሉ ረክሶአል። በዚህ ምክንያት ነው በፍጥረተ አራዊት ዘንድ የእርስ በርስ መተዳደን የገባ፤ በዚህም ነው በፍጥረተ ቅጠላ ቅጠል በኩል መጠውለግና መሞት። የፍጥረት ሁሉ ብጥብጥ የተነሣው በሰው ውድቀት ምክንያት ነው። እግዚአብሔር ሲፈጥረው እንደዚህ አልነበረም፤ ወደ ፊትም እንደዚህ እንደማይሆን ፍጥረት ሁሉ ተስፋ ያደርጋል። ተስፋውም የሚፈጸም ነው፤ ለምን ቢሉ፥ ፍጥረት ሁሉ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ይደርሳልና፥ (ሮሜ 8፡19-22፤ መዝ. 95፡11-13፤ 97፡7-9፤ ዕብ.2፡5-9፤ ራእ.5፡13)። ጌታ በሚመጣበትና የእግዚአብሔር ልጆች በሚገለጡበት ቀን ፍጥረት ደግሞ፥ እንደገና ከሰው ጋር ተካፋይ ሆኖ፥ ከባርነት ወደ ነፃነት ይወጣል፤ «ተኵላም ከበግ ጋር ይቀመጣል፥ ነብርም ከፍየል ጋር፥ ጥጃና አንበሳ በግም በአንድ ይሰማራሉ፤ ታናሽ ብላቴናም ይነዳቸዋል፤ አይጐዱም አያጠፉምም በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ» (ኢሳ.11፡6-9፤ 65፡20-25)። እንግዲያስ ፍጥረት ደግሞ ያን ቀን ይጠባበቃል።

4. በቊ.30 ላይ «አከበራቸው» የተባለ ቃል ግሩም የሆነ ቃል ነው። መቼ አከበራቸው? ገና ወደ ፊት አይደለምን? እንግዲያስ ለምን «አከበራቸው» ተባለ? «ያከብራቸዋል» ማለት አይገባም ነበርን?

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ መዳናችን ከእግዚአብሔር ነው፥ (2ቆ.5፡18)። እግዚአብሔር «አስቀድሞ»፥ አንዳች ነገር ሳይሆን በፊት፥ ሊያድነን

ቈርጦአል። ከዚያች አሳቡን ከቈረጠባት ደቂቃ ጀምሮ ነገሩ ተፈጽሞ ነበር። በእግዚአብሔር ዘንድ ማሰብ ማለት መፈጸም ማለት ነው። ለምሳሌ፥ «እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ። ብርሃንም ሆነ፥» (ዘፍጥ.1፡3)። ዓለም ሳይፈጠር በፊት በእግዚአብሔር አሳብ መዳናችን ሁሉ ተፈጽሞአል፥ (1ቆሮ.2፡7፤ 2ጢሞ.1፡9፤ ቲቶ 1፡2) በዚያ ጊዜ መጠራታችን መጽደቃችንም ገና በመጪው ዘመን ነበረ፤ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር እንደተፈጸመ ነገር ቈጠረው። እንደዚሁም መከበራችን ወደ ፊት ነው እንላለን፤ እግዚአብሔር ግን «ሆነ!» ይላል። መከበራችን ይህን ያህል የተቈረጠ ነገር ነውና ከዚህ «አከበራቸው» ከተባለ ቃል ምን ያለ መጽናናት እናገኛለን!

ቍ.31-39፡- እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ሙሉ፥ የተፈጸመ፥ የዘላለምም መዳን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን አደራጅቶልናል። ሁሉ ከእርሱ ነው፤ እርሱም ወደ ክብር ሊያደርሰን ቈርጦአል። እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ለዚህ ግብ ከእኛ ጋር ከሆነ እንዳንደርስ ሊከለክል የሚችል ማን ነው? ለገዛ ልጁ ያልራራለት እንኳ እንድንደርስ የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር ሁሉ ይሰጠን የለምን? በእርግጥ ይሰጣል! አስቀድሞ ዐውቆአቸው መርጦአቸው ያጸደቃቸው እግዚአብሔር ራሱ ሲሆን ማን ይከስሳቸዋል? የሞተላቸው፥ ሊያጸድቃቸውም የተነሣ (4፡25) ዛሬም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ የሚማልድላቸው ክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ወልድ ሲሆን ማን ይኰንናቸዋል? «ኵነኔ የለባቸውም» ተብሎ የለምን? (8፡1)። ወይስ ደግሞ ይህን ያለ የጋለ የክርስቶስን ፍቅር (ክርስቶስ እግዚአብሔር ነውና፤ ቍ.39) የሚያቀዘቅዝ ከቶ ነገር አለን? ሁሉ ቢመጣብን ያን ፍቅሩን ሊያቀዘቅዝ ይችላልን? መከራ፥ ጭንቀት፥ ስደት፥ ራብ፥ ራቁትነት፥ ፍርሃት፥ ሞት ስንኳ፥ ከዚያ ፍቅር ከቶ ይለየን ይሆንን? ከቶ አይለየንም! ምናልባት እንደ ተጻፈ ስንኳ የሆንን እንደሆንሳ? እንደሚታረዱ በጎች ተቈጥረን ቀኑን ሁሉ ብንገደልስ? ይሁን እንጂ፥ ከክርስቶስ ፍቅር አይለየንም! በእንዲህ ያለ ነገር ሁሉ፥ ፍቅሩ ከቶ በማይቀዘቅዝ በወደደን በክርስቶስ ኢየሱስ፥ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ከአሸናፊዎች እንበልጣለን! የለም፥ ሞት ቢሆን ሕይወትም፤ ከላይ የሚመጡ ክፉ መላእክትም ቢሆኑ (ኤፌ.2፡12) የዚህም ዓለም ግዛት ቢሆን፥ አሁን ያለው ቢሆን መጪው ዘመን የሚመጣው ቢሆን፥ ኃይላትም ምንም ቢሆኑ ከዪትም ዘንድ፥ ከከፍታ ወይም ከዝቅታ ቢመጡ፥ ከቶ ያላሰብነውና ያላየነው ነገር ስንኳ ቢነሣ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን (እንደ ወትሮ!) ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን የሚችል ከቶ አንድም ነገር እንደሌለ ሐዋርያው እርግጠኛ ነው። የእኛም ሙሉ መዳን በዚህ በፍቅሩ መሠረት ተመሥርቶአል!

ማስገንዘቢያ፡- በእነዚህ ቍጥሮች ላይ ስለ መዳናችን ጽናት እናነባለን። የመዳናችን መሠረት ከእኛ የሚመነጨው አንዳች ነገር ሳይሆን የእግዚአብሔርና

የክርስቶስ ፍቅር ነው። ጽኑ መሠረት ነው! መሠረቱ ከእኛ የሆነ ነገር ቢሆን ኖሮ ያስፈራ ነበር፤ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ግን ምን ጊዜም አይነቃነቅም! መዳናችን የሚያጠራጥረን የእግዚአብሔር ፍቅር ሲቀዘቅዝ ብቻ ነው! ይህ ከቶ የሚሆን ይመስላልን? (ኤር.31፡35-36፤ 33፡20፤25፤ ማቴ.24፡35)። የመዳናችን ጽናት የእግዚአብሔር የክርስቶስ ፍቅር ጽናት ያህል ነው። ወደዚያ ክብር እንዳንደርስ የሚከለክለን የለም። ለዘለዓለም ዓለም ቦታችን ተይዞልናል!

ልብ እናድርግ! ይህ ሁሉ የሆነልን «በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን» ነው።

* * *

## 4ኛ ክፍል - የእስራኤል አለመውረስ - ሮሜ 9:1 - 11:36

# ምዕራፍ 9

1.2. ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን
እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። 3. በሥጋ ዘመዶቼ
ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና።
4. እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም
ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸው፤ 5. አባቶችም ለእነርሱ ናቸው፤ ከእነርሱም
ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።

6. ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለም። 7. እነዚህ ከእስራኤል የሚወለዱ
ሁሉ እስራኤል አይደሉምና፤ የአብርሃምም ዘር ስለ ሆኑ ሁላቸው ልጆች አይደሉም፥ ነገር
ግን፦ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ተባለ። 8. ይህም፥ የተስፋ ቃል ልጆች የሆኑ የእግዚአብሔር
ልጆች አይደሉም ማለት ነው። 9. ይህ፦ በዚህ ጊዜ እመጣለሁ ለሳራም ልጅ ይሆንላታል
የሚል የተስፋ ቃል ነውና። 10. ይህ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ርብቃ ደግሞ ከአንዱ
ከአባታችን ከይስሐቅ በፀነሰች ጊዜ፥ .11. ልጆቹ ገና ሳይወለዱ፥ በጎ ወይም ክፉ ምንም
ሳያደርጉ፥ ከጠራው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና
ዘንድ፥ 12. ለእርስዋ፦ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት። 13. ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን
ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

14. እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ ዓመፃ አለ ወይ? አይደለም።
15. ለሙሴ፦ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና።
16. እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው
እንጂ። 17. መጽሐፍ ፈርዖንን፦ ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ይነገር
ዘንድ ለዚህ አስነሣሁህ ይላልና። 18. እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል፥ የሚወደውንም
እልከኛ ያደርገዋል።

19. እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል? ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው?
ትለኝ ይሆናልና። 20. ነገር ግን፥ አንተ ሰው ሆይ፥ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ?
ሥራ ሠሪውን፦ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን? 21. ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ
ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?
22.23. ነገር ግን እግዚአብሔር ቍጣውን ሊያሳይ ኃይሉንም ሊገልጥ ወዶ፥ አስቀድሞ
ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ይገልጥ ዘንድ፥ ለጥፋት
የተዘጋጁትን የቍጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግሥት ከቻለ፥ እንዴት ነው? 24. የምሕረቱ
ዕቃዎችም ከአይሁድ ብቻ አይደሉም፥ ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን።
25. እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ፦

> 26. ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብዬ፥ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ
> እጠራለሁ፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለላቸውም ስፍራ በዚያ የሕያው
> እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ

ይላል።

27.28. ኢሳይያስም፦ የእስራኤል ልጆች ቍጥር ምንም እንደ ባሕር አሸዋ ቢሆን ቅሬታው ይድናል፤ ጌታ ነገሩን ፈጽሞና ቈርጦ በምድር ላይ ያደርገዋልና ብሎ ስለ እስራኤል ይጮኻል። 29. ኢሳይያስም እንደዚሁ፦

> ጌታ ፀባዖት ዘር ባላስቀረልን እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን ነበር ብሎ አስቀድሞ ተናገረ።

30. እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከተሉት አሕዛብ ጽድቅን አገኙ፥ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው፤ 31. እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም። ይህስ ስለ ምንድር ነው? 32.33. በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው፤

> እነሆ፥ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም

ተብሎ እንደተጻፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ።

* * *

# ምዕራፍ ዘጠኝ

ይህ ምዕራፍ የእስራኤል አለመውረስ ክፍል መጀመሪያ ምዕራፍ ነው። እስራኤል የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንዳልወረሱ ግልጥ ነበረና የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ መስሎአል። «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ እንደምን ሊጥል ይችላል?» የሚል (11:2) የምዕራፉ ዋና ጥያቄ ነው። በምዕ.9 ስለ እግዚአብሔር ተስፋ ቃል ስናነብ በምዕ.10 እስራኤል ያን የተስፋ ቃል በምን ምክንያት እንዳልወረሱ እናያለን። ከዚያም በኋላ ደግሞ በምዕ.11 ላይ የተስፋ ቃልን ስለ መፈጸሙ እናገኛለን።

ምዕ.9 የእግዚአብሔር ምርጫ ምዕራፍ ነው፤ ምዕ.10 የእስራኤል እምቢታ ምዕራፍ ነው፤ ምዕ.11 የአሕዛብ መከተል ምዕራፍ ነው።

ምዕ.9 የእግዚአብሔር ምርጫ ምዕራፍ ነው። የምዕራፉ አሳብ የተመሠረተበት «የሚወደውን (የሚፈቅደውን) ይምረዋል፥ የሚወደውንም (የሚፈቅደውንም) እልከኛ ያደርገዋል» በሚለው በቍ.18 ላይ ነው። ከዚያ ቍጥር በፊት የተጻፈው ሁሉ ወደ ቍ. 18 ያደርሳል፤ ከቍ.18 በኋላ የተጻፈው ሁሉ ከዚያ ቍጥር መንጭቶአል። «እስራኤል በሞላ ለምን አልዳኑም?» ተብሎ ቢጠየቅ፥ የዚህ ምዕራፍ መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ነው:- «እግዚአብሔር በሞላ ባይመርጣቸው ነዋ!»

<u>ቍ.1-5</u>:- ሐዋርያው አሁን ሌላን ነገር ያነሣል ይኸውም የወገኖቹ የእስራኤል አለመውረስ ነገር ነው። እስራኤል የእግዚአብሔርን ተስፋዎች አልወረሱም። አለመውረሳቸው በምን ምክንያት ይሆን?

በምዕ.8 መጨረሻና በምዕ.9 መጀመሪያ ታላቅ ልዩነት አለ። ምዕ.8:39 ደስታ የመላበት ቍጥር ሲሆን፥ ምዕ.9:1 «ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት አለብኝ» የሚል ነው። በሁለቱ ቍጥሮች መካከል ምን ሆኖ ይሆን? ሐዋርያው አድሮ ደግሞ በማግሥቱ ጀምሮ ይሆንን? ይህም ይቻላል፤ ለምን ቢባል፥ እስከ አሁን ድረስ የጻፈው አውሎት ይሆናልና። ወይም ምናልባት በምዕ.8 በተነገረው ክብርና ደስታ ከመመሰጡ ጥቂት ካረፈ በኋላ ምን ጊዜም ቢሆን ከልቡ ያልራቀውን የገዛ ወገኑን

የእስራኤልን ሁኔታ በድንገት አስቦ ይሆንን? እርግጡን ልናውቅ አንችልም፤ ነገር ግን እስራኤል ያን ሁሉ ሳይወርሱ መቅረታቸውን በማሰብ ልቡ በኀዘን እንደ ተመታ ግልፕ ነው። «እስራኤል!»፥ «የእግዚአብሔር ሕዝብ!»፥ «የእኔ ሕዝብ!» (ዘዳ.7፡6-7፤ ዕብ.11፡25፤ 1ሳሙ.2፡29፤ ኤር.12፡14፤ አሞ.7፡15፤ ሉቃ.2፡32)። እግዚአብሔር መርጦአቸው አልነበረምን? ልጅነትን፥ ክብርን፥ ኪዳንን፥ ሕግን፥ የመቅደስ ሥርዓትን፥ የተስፋውን ቃላትም አስቦላቸው አልነበረምን? አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ክርስቶስ፥ እስራኤላውያን አልነበሩምን? አሁን ግን ልጅነት ክብርም ለአሕዛብ ተሰጠ! (8፡16-19)። ለምን ቢሉ፥ በምዕ.8 ላይ የተናገረውን ሁሉ የወረሱት በተለይ ከአሕዛብ ወገን እንደነበሩ የማይካድ ነገር ነውና።

ጳውሎስ ራሱ እስራኤላዊ ነው፤ ዓይነተኛም ትምህርቱ የእሥራኤል ትምህርት፥ እሪት፥ ሆኖ ነበር። «የእግዚአብሔር ሕዝብ!» እንደምን ይወዳቸው ነበር! የአሕዛብ ወገን ሐዋርያ ቢሆን እንኳ የማይለወጥ አሳቡ የሥጋው ቁራጭ የአጥንቱ ፍላጭ የሆኑትን አቃንቶ እንዲድኑ ለማድረግ ነው፥ (11፡13-14)። ሆኖም፥ አለመዳናቸውን ሲያስተውል «ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት» በልቡ ተሰማው። ሙሴ ስለ ወገኖቹ ሲል ራሱ የተረገመ እንዲሆን እስኪመኝ ድረስ ጭንቀቱ ከባድ እንደሆነበት (ዘፀአ. 32፡32) ለጳውሎስም እንዲሁ ከባድ ሆኖ ተሰማው። ሁሉም የእስራኤል ነበረ፤ እስራኤል ግን አልወረሱም። ምክንያቱ ምን ይሆን? እግዚአብሔር መልሶ ቢጠላቸው ነውን? ቃሉ ሳይፈጸም ቢቀር ነውን? «በዘላለም ፍቅር ወደድሁሽ» ብሎ አልነበረምን? (ኤር.31፡3)። ምን ሆኖአል? ይህ በእውነት በብዙው የሚያሳዝን ጥያቄ ነው!

ቍ. 6-13፡- በእነዚህ ቍጥሮች ላይ ተስፋ የተሰጠበት የእግዚአብሔር ቃል ሳይፈጸም የቀረ እንደሆነ ይመረመራል። በእውነት «ተሽሮአል»? ከቶ አልተሻረም! ምነው፥ እግዚአብሔር ውሸተኛ መሆኑ ነውን? ይህስ አይሁን!

የተስፋው ቃል በእውነት ለአብርሃምና ለዘሩም ተነግሮ ነበር፥ (ዘፍጥ.17፡7፤ ገላ.3፡16)። ቢሆንም፥ እስራኤል የተባሉት ልጆቹ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ እስራኤል ሆነው አልተቈጠሩም። ሁላቸው ምናልባት ከአብርሃም የተወለዱ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ግን በተስፋ ቃል የተወለዱትን ልጆች ዘር አድርጎ ይቈጥራል እንጂ በሥጋ ብቻ የተወለዱትን ልጆች ዘር አድርጎ አይቈጥራቸውም፥ (ገላ.4፡22-23)። እግዚአብሔርም ይህን ያመለከተው «በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል» ባለው ጊዜ ነው። ሌሎቹ ማለት ልጆች ሆነው አይቈጠሩም ነበር። ምንም እንኳ የ14ቱ ዓመት እስማኤል የአብርሃም ልጅ ቢሆንም በዘፍጥ.22፡2 እግዚአብሔር ይስሐቅን «አንዱን ልጅህን» ይለዋል። እንግዲህ፥ የተስፋ ቃል የተሰጣቸው በተስፋ ቃል ለተወለዱት እንጂ ለእስራኤል ሁሉ አልተሰጠም። እስራኤል የተባሉት የአብርሃም የሥጋ ልጆች ብዙ ይሁኑ እንጂ የተስፋ ቃል ግን

አልተሰጣቸውም። የተስፋ ቃል የተሰጣቸው ለመንፈሳዊ ልጆቹ ነው፥ እነርሱም ወይም ከእስራኤል ወይም ከአሕዛብ ወገን ሆነው እንደ አብርሃም ያመኑ ናቸው፥ (ሮሜ 4:12፤ ገላ.3:7)። ለእነዚህም የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አንዳችም ሳይቀር ሁሉ ተፈጽሞላቸዋል።

እንግዲህ የተስፋ ቃል እግዚአብሔር ለመረጣቸው እንጂ ለሁሉም እንዳልሆነ እናያለን። እስማኤልም ይስሐቅም ሁለቱ የአብርሃም ልጆች ነበሩ፥ በኩርነትም ያለው እስማኤል ነበረ። ቢሆንም፥ እግዚአብሔር እርሱንም አስቀርቶ ታናሹን መረጠው። ይህም አንዱ ከሌላው የተሻለ ስለሆነ አይደለም፤ እግዚአብሔር እንዲህ እንዲሆን ስለ መረጠ ነው እንጂ። ይህም አብዝቶ የሚታየው ከኤሳውና ከያዕቆብ ነገር ነው። እነዚህ ሁለቱ የይስሐቅ ልጆች የአንድ አባትና የአንድ እናት ልጆች ሲሆኑ መንታ ሆነው ገና በእናታቸው በርብቃ ማኅፀን ሳሉ፥ ሳይወለዱ፥ በሥራቸው መልካምም ክፉም እንደሆኑ ሳይገለጥ፥ እግዚአብሔር በሌላ በማንኛውም ነገር ሳይሆን በአምላካዊ ምርጫ ብቻ «ታላቁ ለታናሹ ይገዛል» ብሎ ያዕቆብን መረጠ፥ ኤሳውንም ጣለ። ይህም የእግዚአብሔር ምርጫ፥ ጸንቶም በሕይወት ታሪካቸው እንደተፈጸመ፥ ከዚያ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ «ያዕቆብን ወደድሁ፥ ኤሳውን ግን ጠላሁ» ብሎ ጠቅሶ ነቢዩ ሚልክያስ በጻፈው ቃል ተረጋግጦአል (ሚል.1:2-3)። እንግዲህ እግዚአብሔር የተስፋን ቃል የሚወርሱትን እንደሚመርጥ ታይቶአል። መውረስ ከትውልድ፥ ከበኩርነት፥ ከሥራም ሳይሆን ከእግዚአብሔር ምርጫ ብቻ ነው።

ማስገንዘቢያ፡- ለአብርሃም በተሰጠው የተስፋ ቃል ውስጥ ሁለት ክፍል እንዳለ መገንዘብ ቁም ነገር ነው፤ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ ሥጋ ለተወለዱት እስራኤላውያን ምድራዊ የተስፋ ቃል ሲሰጥ፥ የአብርሃም የእምነቱን ፍለጋ ለተከተሉት መንፈሳዊ ልጆቹ መንፈሳዊ የተስፋ ቃል ተሰጥቶአል። ማለት፥ ምድራዊው ከነዓን ለሥጋ ልጆቹ ሲሰጥ፥ መንፈሳዊ ከነዓን (እርሱም መንግሥተ ሰማያት) ለመንፈሳዊ ልጆቹ ብቻ ተሰጥቶአል።

ምድራዊ እስራኤል ለሆኑት የአብርሃም ልጆች ዛሬ «እስራኤል»፥ ዱሮ «ፓለስቲና» (ፍልስጤም)፥ ጥንትም «ከነዓን» የተባለችውን አገር እንደተሰጠቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ በኩል ተጣርቶ ተነግሮአል፥ (ዘፍ.12:6-7፤ 13:14-15፤ 15:18-19፤ ዘ ኍል.24:8-9፤ ዘዳግ.34:1-4)። አገሪቱ «የምታያት ምድር» ተባለች (ዘፍጥ.13:15)፥ ወሰንዋ «ከምስር ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ» ተብሎ በጥንቃቄ ተከልሎ ተሥሎአል፥ (ዘፍጥ.15:18)።

አንዳንዶች ሰዎች «የተስፋ ቃል በሰሎሞን ዘመን ተፈጽሞ ነበርና (1ኛነገ.4:21፤24) ሆኖአል፤ በቃ! ለወደፊት የሚሆን የተስፋ ቃል የላቸውም»

ይላሉ። ሌሎች ግን አገሪቷ የተሰጠቻቸው «ለዘላለም» እንደ ሆነ አይተው (ዘፍጥ.13፡ 15፤ ዘፀአ. 32፡13)፥ በነቢያትም በየበኩሉ የተነገረላቸውን ተስፋዎች ተገንዝበው (ለምሳሌ:- ኢሳ. ምዕ.58 እስከ ምዕ.66 ድረስ፥ ሕዝ. ምዕ.3 እስከ ምዕ.39 ድረስ፥ ዘካ. ምዕ.12 እና ምዕ.13) «በመጪው ዘመን ደግሞ ይወርሱአታል» ይላሉ። ይህም እውነት ይመስላል የሚፈጸመውም ጌታችን ተመልሶ ዓለምን በኢየሩሳሌም ሆኖ ሲገዛ ይሆናል፥ (ኢሳ.2፡1-4፤ ዘካ.14፡1-9፤16)።

ቍ.14-18:- ይህ የእግዚአብሔር አድራጎት፥ አንዱን ሲመርጥ አንዱንም ሲያስቀር ትክክል ነውን? «በእግዚአብሔር ዘንድ ዓመፃ አለ ወይ?» ይህስ ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ምን ይሆን? መልሱ ያ የለመድነው ጽኑ የሆነ «ሎሪ አይሁን!» የተባለው ቃል የግድ ይሆናል! እግዚአብሔር ዓመፀኛ ይሆን ዘንድ እንደምን ይቻላልና? ምክንያቱስ? «የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ፥ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ» ብሎ ለሙሴ ስለነገረ ነው። ማለት፥ «የምፈቅደውን የምመርጠውንም» እንጂ፥ «ሁሉንም አድናለሁ» ብሎ ተናግሮ አያውቅም ማለት ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ ማለት እግዚአብሔር የሚድኑትን መወሰኑን አስታውቆአል። እንግዲህ በአጭሩ፥ ምሕረት ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም። ነገሩን የሚቈርጥ እርሱ (እግዚአብሔር) ነው። በፈርዖን ዘንድ ያደረገውን በዘፀ.6፡6-14 ላይ እይተናል። ለምሕረት ሳይመርጠው ያስነሣበት ምክንያቱ ኃይሉን ያሳይበት ዘንድ፥ ስሙም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ነው። ፈርዖንን ወስዶ ይህን ሁሉ ሠራበት ማለት ነው። የሚወደውን (የሚፈቅደውን) ይምረዋል፥ የሚወደውንም (የሚፈቅደውንም) እልከኛ ያደርገዋል ማለት ነው። ይህም ማለት፥ ሁለቱም ወገኖች፤ እስራኤል በሞላ አልተጣሉም፥ አሕዛብም በሞላ አልተመረጡም፥ ማለት ነው።

ቍ.19-24:- ይህ ከሆነ፥ እንዲያው የተማረው ሰው ተምሮአል፤ እልከኛ የተደረገውም የግድ እልከኛ ሆኖአልና እግዚአብሔር ለምን ይነቅፋል? ይባል ይሆናል። ሰው የሆነውን የግድ፥ ሊቃወመው በማይችለው በእግዚአብሔር ምርጫ ሆኖአል ማለት ነው። ነገር ግን ከፈጣሪያችን ጋር መከራከር እንጀምራለንን? በሥልጣኑ ፈጥሮናል፥ ሠርቶናልም። «ስለምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ?» ልንል ነውን? የሸክላ ሠሪ ያገኘው ጭቃ ነው። ከአንዱ ጉድጓድ ጭብጥ ጭቃ አንሥቶ ለክብር የሚሆን ዕቃ ሊሠራው ከመረጠ፥ እንዲሁም ሌላውን ጭብጥ ደግሞ ለክብር ሳይሆን ለውርደት ቢሠራው፥ ማን ይነቅፈዋል? ሁሉ ጭቃ ነበረ፤ ሠሪውም ባይፈቅድ ኖሮ ሁሉ ጭቃ ሆኖ በቀረ ነበር። በሰው ዘንድም እንደዚሁ ነው። ሰው ሁሉ የአንድ ጉድጓድ ጭቃ፥ የአዳም ልጅ፥ ሲሆን (ኢሳ. 51፡1፤ ኤፌ.2፡3) እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለክብር፥ ማለት ለምሕረትና ለደኅንነት፥ ቢመርጥ ለምን ይነቀፋል? አንዳንዶችን ባይመርጥ ኖሮ ሁሉ በጠፉ ነበር። አንዳንዶችን ለክብር ሌሎችን ለውርደት፥ ማለት እልከኞች ለመሆን፥ ቢጥላቸው ዓመፃ ማድረጉ ነውን?

ከቶ አይደለም! ለመምረጥ እንደምን ይገደዳል? ኃጢአተኛ እንዲፈራና እንዲድን ብሎ ቍጣውን ኃይሉንም ለማሳየት ወድዶ በብዙ ትዕግሥት ለጥፋት የተዘጋጁትን ዕቃዎች ከቻለ (ከታገሠ)፥ የክብሩንም ባለ ጠግነት ይገልጥ ዘንድ ወድዶ የምሕረት ዕቃዎችን ሠርቶ ለደኅንነት ከመረጣቸው፥ ማን ይነቅፈዋል? ለመማርም ለመጨከንም ሥልጣን የለውምን? (11፡22።) አለው! ያልተመረጡትን የነገራቸውን ምሥጢር ጠልቀን ለመመርመር ሳናስብ አንዳንዶች የዳኑበትን የእግዚአብሔርን ጸጋ እንወድስ እናመስግንም። «እነዚያን ለምን አልመረጣቸውም?» ሳንል «እኛን ለምን መረጠን?» እንበል። እኛን መረጠ! የምንገረምበት በዚህ ይሁን! አፍ ሁሉ ተዘግቶ ነበር፥ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ሆነ፥ (3፡19።) ያለ እግዚአብሔር ጸጋ እስራኤል ሆነ ወይም አሕዛብ ተስፋ አልነበራቸውም። እግዚአብሔር እስራኤልም ሆነ አሕዛብም ፊቱን አይቶ ሳያደላ አንዳንዶችን ለደኅንነት መረጠ። ለዚህ ምርጫው ክብር ምስጋናም ለዘላለሙ ይድረሰው!

<u>ቍ.25-33</u>፡- ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር አሳብ እንዲህ እንደ ሆነ ግልጥ ነው። አሳቡን ቃሉንም አልለወጠም። ሆሴዕ በምዕ.2 ቍ.1 እና 25 ላይ የአሕዛብን መመረጥና መዳን፤ ኢሳይያስም በምዕ.10 ቍ.22 እና 23 ላይ የእስራኤልን መጣል እና አለመዳን፥ ከእስራኤል ጥቂቶች ብቻ እንደሚድኑ ስንኳ አመልክተው ነበር። እንግዲህ እንደምናየው ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ እንጂ አልተሻረም፥ (ቍ.6።)

የሆነው ለምን እንዲህ ሆነ? አሕዛብ ኢየሱስን አይተው አመኑበትና ጽድቅም የሚገኘው በእምነት ነውና ጽድቅን አገኙ። እስራኤል ግን ትንቢት ተናግሮባቸው እንደነበረ በኢየሱስ ተሰናከሉ አላመኑበትም። ጽድቅም በእምነት ነውና ጽድቅን አላገኙም። ምክንያቱ ይህ ነው።

ማስገንዘቢያ፡- ይህ ትልቅ ክርክር የተደረገበት ምዕራፍ ነው፤ ምክንያቱም፥ ምዕራፉ «እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለደኅንነት አንዳንዶችንም ለጥፋት አስቀድሞ ይመርጣል» እንደሚል ስለሚመስል ነው። እግዚአብሔር ይስሐቅን መርጠ እስማኤልን እንደ ጠላ፥ ያዕቆብን መርጠ ኤሳውን እንደ ጠላ፤ ይህም «ከጥሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ» እንደሆነ ተነግሮአል። በእግዚአብሔር ዘንድ ዓመፃ ያለ እንደሆነ ስንኳ ጥርጣሬ አለ። እግዚአብሔር «የምምረውን እምረዋለሁ፥ ለሚራራለትም እራራለታለሁ» ሲል በገዛ ፈቃዱ እንደሚሠራ ይመስላል። ከዚህም የባሰ ደግሞ፤ «እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ» ብሎ የፈርዖንን ነገር ጠቅሶ «የሚወደውን (የሚፈቅደውን) ይምረዋል፥ የሚወደውንም (የሚፈቅደውንም) እልከኛ ያደርገዋል» ይላል። ይህን ሁሉ ስናነብ «ታዲያ፥ ሁሉ ከእግዚአብሔር ከሆነ ሰው ምን ሊያደርግ ይችላል? እግዚአብሔር ሊያድነው

ከወደደ ይድናል፤ እግዚአብሔር ግን እልከኛ ክፉ ሊያደርገው ከወደደ (ከመረጠ) ክፉ ሆኖ ይጠፋል» ወደ ማለት እንደርሳለን። «እግዚአብሔር ያለ እንደሆነ እድናለሁ እግዚአብሔር ያለ እንደሆነ እጠፋለሁ፤ እኔ ምን ላደርግ እችላለሁ?» የሚል አሳብ ይፈጥራል።

ነገር ግን ሁለቱን ምዕራፎች፥ ምዕ.9 እና ምዕ.10 ማለት፥ ባንድነት መያዝ ያስፈልገናል። ምዕ.9 የእግዚአብሔርን ምርጫ እንደሚያስተምር እውነት ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ተባለው ሁሉ እንደሚመርጥ የማይካድ ነገር ነው። እግዚአብሔር በእውነት ይመርጣል ነገር ግን ደግሞ ምዕ.10 አለ! በምዕ.10 ላይ ከተነገረው ነገር የሰውን ድርሻ እናያለን፤ በእርሱም «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ተባለ፥ (10፡13።) ነገር ግን ሰው ያን ስም አውቆ፥ ሳይጠራ ቀርቶ ቢጠፋ ጥፋቱ በማን በኩል ነው? እግዚአብሔርን ልንወቅስበት አንችልም። እግዚአብሔርማ « <u>ዓለምን</u> ወድዶአል» (ዮሐ.3፡16)፥ ኢየሱስም «መድኃኔ ዓለም» ነው (ዮሐ.1፡29)፥ ደኅንነትም <u>ለሁሉ</u> ነው፥ (ኢሳ.53፡6)። ሰው ግን እንቢ ቢል እግዚአብሔር ምን ያድርግ? ስለዚህ፥ ለዚህ ለደኅንነት ነገር ሁለት ወገን እንዳለ ማስተዋል ያስፈልገናል፤ ያለ ምዕ.10 ምዕ.9ን አለመያዝ፥ ያለ ምዕ.9 ምዕ.10ን አለመያዝ ነው። ምዕ:9 «እግዚአብሔር ይመርጣልና ሰው ምን ሊያደርግ ይችላል?» ሲል፥ ምዕ.10 ደግሞ ሰው እንቢ ያለ እንደሆነ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ ይችላል?» ይላል። ሁለቱን ምዕራፎች ጎን ለጎን መያዝ ያስፈልገናል።

ይህን ምዕራፍ የሚተረጉሙ አንዳንዶች መምህራን «የእግዚአብሔር ምርጫ ማለት እግዚአብሔር መልካምን እርምጃ በማድረግ የሚድኑትን አስቀድሞ አይቶ ዐውቆ እነዚህን ለደኅንነት ይመርጣል ማለት ነው» ይላሉ። ነገር ግን ምርጫው ይህ ብቻ እንዳልሆነ በምዕ.9፡11፥ ደግሞ በም.8፡29 እና 30 እንረዳለን። ምርጫው ለደኅንነት ነው፥ ደኅንነትም «ከጠሪው እንጂ ከሥራ አይደለም» ተብሎአልና የተመረጡበት ምክንያት መልካምን እርምጃ ስለሚያደርጉ አይደለም። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ «አስቀድሞ» የጠራቸው እግዚአብሔር እንደሆነ እናያለን። (8፡30፤ ዮሐ.15፡16)። አስቀድሞ ዐወቃቸው፥ ወሰናቸው፥ ጠራቸው፥ አጸደቃቸው፥ አከበራቸውም። የሚድኑትን አስቀድሞ እንዳወቀ ብቻ አይደለም።

ሌሎችም መምህራን ደግሞ መመረጡንስ ተመርጠዋል፥የተመረጡት ግን ለዘላለም ደኅንነት ሳይሆን ለዚህ ዓለም መብት ብቻ ነው» ይላሉ። ነገር ግን የዚህ ምዕራፍ ዓይነተኛው አሳብ የመውረስ ወይም የአለመውረስ፥ የመዳን ወይም ያለመዳን፥ አሳብ እንደሆነ በእውነት ግልጥ ነው፥ (ቍ.3፥6፥15፥16፤ ደግሞ ምዕ.10፡1)። ጳውሎስ የተጨነቀበት፥ የሚያዝንበትም እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም መብት ስላልመረጣቸው አይደለም። የተጨነቀበት፥በተለይ በምዕ.8 ላይ ለተጻፈው መዳን ስላልተመረጡ ነው። ይህ የማይካድ ነገር ነው። እግዚአብሔር <u>ለደኅንነት</u> አልመረጣቸውምነበር፤ ፍሬ ነገሩ ይህ ነው።

እግዚአብሔር ለደኅንነትና ለዘላለም ሕይወት እንደሚመርጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ተነግሮአል፡- ሮሜ 8፡29-30፤ ኤፌ.1፡4-5፤ 2ኛተሰ.2፡13፤ 2ኛጢሞ.1፡9፤ 1ኛጴጥ.1፡1-2። የምንድንበት እግዚአብሔር ሊያድነን ስለሚመርጥ ነው። በአምላካዊ ፈቃዱ እርሱ የሚድኑትን ወስኖ ይመርጣል።

እግዚአብሔር ለደኅንነትና ለሕይወት እንደሚመርጥ የተረጋገጠ ነገር ሲሆን፥ ለኩነኔና ለሞት እንደሚመርጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በየትም ክፍል አልተጻፈም። ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም ዝም ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ «ሰው ይኩነን ዘንድ እግዚአብሔር የሰውን ልብ እልከኛ ያደርጋል» አይልም። ስለ ፈርዖን ሲናገር (ቊ.17)፥ «ለዚህ አስነሣሁህ» ይላል እንጂ «ለዚህ ፈጠርሁህ» አይልም። ማለት፥ «ማስተማሪያ ትሆን ዘንድ እንደ ቲያትር ትይንት አድርጌህ በሰው ሁሉ ፊት አስነሣሁህ» ማለት ነው። እግዚአብሔር የኃጢአተኛን ሞት ሳይፈልግ የማይቋረጥ አሳቡ ሰውን ለማዳን ነው፥ (ሕዝቅ.33፡11)። ኃጢአተኞች እንዲሆኑና እንዲኩነኑ ከቶ አልመረጣቸውም፤ ዳሩ ግን ሁላቸው ኃጢአተኞች የተኩነኑም ሆነው አግኝቶአቸው በአምላካዊ ሥልጣኑ ይሠራና አንዳንዶችን ለደኅንነት መርጦ፥ ብዙ አሕዛብን ለማዳን ሲል ሌሎችን በመንገዳቸው ያጸናቸዋል። እግዚአብሔር ፈርዖንን ኃጢአተኛ ሆኖ አግኝቶት ለሌሎች ብዙ ሰዎች መዳኛ እንዲሆን አደረገው። ፈርዖንን እልከኛ ያደረገበት ምክንያቱ ምሕረቱ ለሚበልጡ፥ በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩ እንዲደርስ ትምህርት እንዲሆናቸው ነበረ።

በቊ.22-23 ደግሞ፥ እግዚአብሔር የቊጣ ዕቃዎችን ለጥፋት እንዲያዘጋጃቸው አይልም። እነዚህን ነገሮች በጣም ልብ ማድረግ ይገባናል። ለክብር « አዘጋጃቸው» ይላል፤ ለጥፋት ግን ያዘጋጃቸው ምን እንደሆነ ሳይገልጥ በጥንቃቄ «ለጥፋት ተዘጋጅተዋል» ይላል።

እንደዚሁ ደግሞ በማቴ. ምዕ.25 ላይ ስለ በጎችና ስለ ፍየሎች ሲናገር፥ ንጉሡ በቀኙ ያሉትን «እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» ሲል (ቊ.34)፥ በግራው ያሉትን «እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ» ይላል እንጂ (ቊ.41) « ለእናንተ ወደተዘጋጀ» አይልም። ማለት፥ መንግሥተ ሰማያት ለሰው ሲዘጋጅ ገሃነመ እሳት ለሰው ሳይሆን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ተዘጋጅቶአል። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለደኅንነትና ለሕይወት እንደሚመርጥ (እንደሚያዘጋጅ) በብዙ በኩል ሲነገር ለኩነኔና ለሞት እንደሚመርጥ (እንደሚያዘጋጅ) ተናግሮ አያውቅም።

«ይሁን እንጂ፥ የመረጣቸው እሉ እኮ!» ቢባል፥ ይህስ እውነት ነው። ጉንዳን ደግሞ የሰውን አሳብ፥ ያም ሰው አንድ ነገር የሚያደርግበትን ምክንያት፥ ሳያስተውል ሊቀር እንደሚችል እንዲሁ እኛ የአምላካችንንና የፈጣሪአችንን አሳብና

ሥራ ሁሉ ልናስተውል እንደምንችል አለማሰብ ነው። የማናስተውለው ነገር ይኖር ይሆናል፤ እርሱ አምላክ ነውና ይህስ ባይኖር ያስገርም ነበር። ዳሩ ግን አምላካችን ታማኝ ቸርም እንደ ሆነ፥ ግፍም እንደማያደርግ፥ ሰውን ሁሉ እንደሚወድና የሁላቸውንም መዳን እንደሚመኝ፥ ይህን ሁሉ እናውቃለንና ልናስተውል በማንችልበት ነገር ልንታመን እንችላለን፥ (ዮሐ.3፡16፤ ሮሜ 5፡8፤ ሕዝ. 33፡11)። ሥራው ሁሉ በጥበብና በእውነት በፍቅርም ተመስርቶአልና መጠራጠር አያስፈልገንም።

ይህ ደግሞ፥ እላይ እንዳየነው ሁሉ የሥዕሉ አንደኛው ፊት (ገጽ) ብቻ ነው። በምዕ.10 ላይ ሁለተኛውን ፊት ስናይ ሰው ሁሉ እንደተጠራ፥ ነገር ግን ለጥሪው ብዙዎቹ እንቢ እንዳሉ እናያለን። እግዚአብሔር ይመርጣል፤ እርግጥ! ሰው ግን ያን ጥሪ ለመቀበል ወይም ለመጣል ሙሉ ፈቃድ ተሰጥቶታል።

* * *

# ምዕራፍ 10

1. ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው። 2. በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። 3. የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። 4. የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።

5. ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና። 6. ከእምነት የሆነ ጽድቅ ግን እንዲህ ይላል፦ በልብህ፦ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል? አትበል፤ 7. ይህ ክርስቶስን ለማውረድ ነው፤ ወይም፦ በልብህ፦ ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል? አትበል፤ ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው። 8. ነገር ግን ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። 9. ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ 10. ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። 11. መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ 12. አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤ 13. የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል።

14. እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? 15. መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? 16. ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም። ኢሳይያስ፦ ጌታ ሆይ፥ ምስክርነታችንን ማን አመነ? ብሎአልና። 17. እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

18. ዳሩ ግን፦ ባይሰሙ ነው ወይ? እላለሁ። በእውነት፦

ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።

19. ነገር ግን፦ እስራኤል ባያውቁ ነው ወይ? እላለሁ። ሙሴ አስቀድሞ፦

እኔ ሕዝብ በማይሆነው አስቀናችኋለሁ በማያስተውልም ሕዝብ አስቈጣችኋለሁ

20. ብሎአል። ኢሳይያስም ደፍሮ፦

ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፥ ላልጠየቁኝም ተገለጥሁ

21. አለ። ስለ እስራኤል ግን፦ ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና ወደ ሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ ይላል።

# ምዕራፍ አሥር

ምዕ.10 የእስራኤል እንቢታ ምዕራፍ ነው። ሐዋርያው እስራኤል የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ያልወረሱበትን ምክንያት ሲመረምር፥ የእግዚአብሔር እውነት የተነካ መስሎ ስለታየ በምዕ.9 ላይ የእግዚአብሔርን ወገን የግድ አበረታ። እዚህ ላይ ግን ወደ ሰው ወገን ዞሮ «እስራኤል ያልዳኑበት ምክንያት ስላላመኑ ነው» ይላል። እግዚአብሔር በማይነገር ፍቅር ቆሞ ደጋግሞ ሲጠራቸው እስራኤል በገዛ ፈቃዳቸው «እንቢ! አንሰማም!» አሉ። ጥፋቱ የእግዚአብሔር ሳይሆን የእስራኤል ነው።

ምዕ.9 እና ምዕ.10 እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። በአንዱ ፊት የአንበሳ ገጽ (መልክ) ይታያል፤ ይህም ምዕ.9 ነው። በሁለተኛው ፊት የአገሪቱ የኤኮኖሚ መሠረት የሆነው ግብርና ወይም ገበሬው ከነበሬዎቹ የሚያሳይ ምሥል ይታያል፤ ይህም ምዕ.10 ነው። «ሁለቱ ፊቶች አይስማሙምና አንቀበለውም» ሳንል ገንዘቡን እንዳለ ተቀብለን ብንጠቀምበት ይሻላል! በሮሜ ምዕ.9 እና ም.10 ዘንድ እንደዚሁ ነው። በአንዱ ምዕራፍ ላይ «እግዚአብሔር አልመረጣቸውምና መዳን አልቻሉም» ሲባል፥ በሁለተኛው ላይ «እስራኤል በገዛ ፈቃዳቸው ለሁላቸው ለደረሰ ጥሪ እንቢ አሉ» ተብሎአልና፥ «አይስማማምና የማይቻል ነገር ነው» እግዚአብሔር ከዕለታት አንድ ቀን ይተረጉምልናል» ብለን ሁለቱን ብንቀበል የተሻለ ዘዴ ነው።

በምዕ.10 የእግዚአብሔር ደኅንነት ለሁሉ እንደ ሆነ ተረጋግጦአል። እግዚአብሔር ለሁሉ ሲያዘጋጀው ሁሉንም ሲጠራ ለሰው ፊት አድልቶ አሕዛብን እንደመረጠና እስራኤልን እንደጣለ ሳይሆን፥ ከሁሉ አስቀድመው ተወዳጆቹ እስራኤል እንዲሰሙ አደረገ፥ (ማቴ.10፡5-6፤ የሐዋ.11፡19፤ የሐዋ.13፡42-46)። ደኅንነት በእግዚአብሔር ምርጫ ብቻ ከሆነ እስራኤል ያለ ጥርጥር በዳኑ ነበር፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ምርጫ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊው እስራኤል የእግዚአብሔር ጽድቅ የሆነውን ኢየሱስን ደግሞ እንዲቀበሉ ነበር። ለዚህም እስራኤል በገዛ ፈቃዳቸው እንቢ አሉ። ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቻቸውን ይሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደደ! እነርሱ ግን አልወደዱም፥ (ማቴ.23፡37)። ከፍቅሩ ከናፍቆቱም ብዛት የተነሣ መርጦአቸው ለነበሩት ለተወዳጆች ለእስራኤል ቀላል አደረገላቸው እነርሱ ግን አልፈቀዱም፥ (ዮሐ.5፡40)። «አልመረጣቸውም» ይባላልን? ሉረ! ቀኑን ሁሉ እጆቹን ዘርግቶ ነበር እንጂ! (10፡21።) የለም፥ እስራኤል በገዛ

ፈቃዳቸው እልከኞች ሆነዋል እንጂ እግዚአብሔር የጣላቸው አይደለም። ገናም አልጣላቸውም! (ምዕ.11።) በዘላለም ፍቅር ወድዶአቸዋልና፥ (ኤር.31፡3)።

ቊ.1-4:- ጳውሎስ ወደ አሕዛብ ዘወር ብሎ ስለነበር ብዙዎች እስራኤል ወገኑን አይሁዶችን ፈጽሞ የጣላቸው መሰላቸው፥ (የሐዋ.13፡46፤ 18፡6፤ 21፡21 27-28) ይህ ግን እውነት አለመሆኑን ሐዋርያው እንደገና በዚህ አንቀጽ ይገልጣል። መጥላት ይቅርና የልቡ ፈቃድ የማያቋርጥ ልመናውም ስለ መዳናቸው ነው። በተለይ ያሳዘነው፥ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር እውነተኛ ቅንዓት ሲኖራቸውና ጽድቅን ለማግኘት ሲመኙ፥ መንገዱን ስለተሳሳቱ ነው። በበረሃ ከአጠገባቸው ብዙ ውኃ እያለ በውኃ ጥም እየሞቱ፥ በሌላ መንገድ እንደሚንከራተቱ ሰዎች መስለው የእግዚአብሔር ጽድቅ በአጠገባቸው እያለ የራሳቸውን ሊያቆሙ ይፈልጉ ነበር። በተሳሳተ መንገድ ተንከራትተዋል ማለት ነው። እግዚአብሔር በታላቅ ዋጋ ጽድቅን ገዝቶ በቅርቡ ሲያስቀምጥ እስራኤል የእግዚአብሔርን ጽድቅ ንቀው ራሳቸውን ለማጽደቅ ሲሉ የቀረበውን ትተው ወደ ራቀው ለመድረስ ተጣጣሩ። ይህንም ሲያደርጉ የተገኘባቸው ጥፋት ሁለት ነው:- 1ኛ፥ ጽድቅ የሚገኝበትን መንገድ ተሳሳቱ። 2ኛ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ ለመገዛት አልፈቀዱም። ጽድቅ በእምነት ነውና የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ሕግ (ኦሪት) የኦሪት ግብ የሥዕሉም ፍጻሜ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ መርቶአል፥ (ገላ.3፡24)። እስራኤል ግን በክርስቶስ ተሰናክለው የኦሪት ፍጻሜ እርሱ እንደሆነ ሳይገነዘቡ ቀሩ፤ እግዚአብሔርም ላደራጀላቸው ጽድቅ ተገዝተው እንዲያው በእምነት ለመቀበል ጠልተው ጽድቅን በሥራቸው፥ እንደ ደመወዝ፥ ለማግኘት አሰቡ። አሳባቸው ሳይሳካላቸው ቀረ።

ማስገንዘቢያ:- እነዚያን እስራኤላውያን የሚመስሉአቸው ስንትና ስንት ሰዎች ዛሬ አሉ! ለእግዚአብሔር እውነተኛ ቅንዓት አላቸው፥ ጽድቅንም ለማግኘት ዓይነተኛ የሕይወታቸው ጉዳይ ነው፥ መንገዱን ግን ተሳሳቱ፤ ይህም በውጭ አገር ብቻ ሳይሆን በክርስቲያን አገሮች ውስጥ ነው። ልበ ቅን ሆነው የሃይማኖትን ነገር እጅግ የሚያከብሩ ሲሆኑ ዕውቀት ስለ ጐደላቸው መንገዱን ተሳሳቱ። ጽድቅ በአጠገባቸው ሳለ ወዲያ ያለ ይመስላቸዋልና እላይ እንዳልነው ሁሉ በአጠገባቸው እውነተኛ ውኃ ሳለ የበረሃውን ውኃ እየተከታተሉ ሄደው ከባሰ ወደ ባሰ እንደሚጠፉ ሰዎች መሰሉ። በሥራቸው የሚገኝ እየመሰላቸው እንዲያው በእምነት ሊቀበሉት እንደሚችሉ አልተረዱም።

ቅንዓታቸውሳ? የሃይማኖትን ነገር ማክበራቸውሳ? ያድናቸዋልን? ይህማ ከሆነ እስራኤል በዳኑ ነበር! ጳውሎስ ግን ያዘነበት ባለመዳናቸው አልነበረምን? የለም፥ ለእግዚአብሔር መቅናት ሃይማኖትንም ማክበር፥ ምንም የተመሰገነ ቢሆን፥ ሰው በተሳሳተ መንገድ ከሄደ አይድንም። እነዚያ ውኃ ፈላጊዎች ድነዋልን? አልዳኑም! እውነተኛውን መንገድ አስተውሎ፥ ለተመለከተው ምልክት ታዝዞ፥ መሄድ ብቻ

ያድናል፥ (ዮሐ.14፡6)። ሰው በስሕተቱ ምንም ቢበረታ ወደ እውነት ለመድረስ ከቶ አይችልም።

ቊ.5-13፦ «የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው» ለተባለው ቃል ጳውሎስ አሁን የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት ሊያቀርብ ይፈልጋል። ሙሴ ከሕግ ስለ ሆነው ጽድቅ ሲናገር «የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት ይኖራል» ብሎእንደ ተናገረ እርግጥ ነው። ቢሆንም፥ ከእምነት የሆነ ጽድቅ ደግሞ በሙሴ አፍ ስለ ራሱ መስክሮአል፥ (ዘዳግ.30፡11-14)። ሙሴ የአሪትን አለመፈጸም የእስራኤልንም መበተን ካስታወቀ በኋላ (ዘዳግ.29፡1፤25፤28) በሞአብ ምድር ሳለ ስለ አንድ ተጨማሪ ኪዳን ተናገረ። ቀጥሎም ስለዚያች አዲስ ትእዛዝ ሲናገር የተሰወረች የራቀችም አለመሆንዋን ለማስረዳት ብሎ «በሰማይ አይደለችም፥ ማነው ለእኛ ወደ ሰማይ ወጥቶ እርስዋን የሚያመጣልን፤ ከባሕርም በማዶ አይደለችም፥ ማነው ለእኛ ባሕሩን የሚሻገር እርስዋንስ የሚያመጣልን፤ ትል ዘንድ፥ ነገር ግን ነገሩ ለአንተ እጅግ የቀረበ ነው በአፍህ በልብህም» ብሎ ተናገረ፥ (ዘዳግ.30፡11-14)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አሁን «ይህን የተናገረው ስለ ራሱ የሚመሰክር ከእምነት የሆነው ጽድቅ ነው እንጂ ሙሴ በእውነት ስለ አሪት ሲናገር አይደለም» ይላልና ቃሉን ከዚህ እንደሚከተለው ይተረጒምልናል። «ማን ወደ ሰማይ ይወጣል?» የተባለው፥ «ይህ እኮ፥ ክርስቶስን ለማውረድ ማለት ነውና ስለ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ይናገራል» ይላል፥ (ቊ.6)። «ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል?» የተባለው ደግሞ፥ «ይህስ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ማለት ነውና ስለ ክርስቶስ ከሙታን መነሣቱን ይናገራል» ይላል፥ (ቊ.7)። «በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል» የተባለው፥ «ይህ ደግሞ የምንሰብከው የእምነት (የወንጌል) ቃል ነው» ይላል፥ (ቊ.8)። «በአፍህ በልብህ» የተባለበት፥ ሰው በእምነት የሆነውን ጽድቅ የሚቀበልበት በእነዚህ በሁለቱ ነገሮች ነውና። በአፋችን ለዚያ ለመጀመሪያው ነገር፥ እርሱም ክርስቶስ ጌታ ለመሆን ወደ ዓለም ለመምጣቱ፥ ብንመሰክር፤ በልባችንም በዚያ በሁለተኛው ነገር ደግሞ፥ እርሱም ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ፥ ብናምን እንድናለን። ምክንያቱም፥ ጽድቅ በእምነት ነውና ሰው በአእምሮው ብቻ ሳይሆን በልቡ ቢያምን ይጸድቃል፤ በአፉም ደግሞ ሲመሰክር የመዳንን ሙላት ያገኛል። መመስከርን የሚመሰክርበት፥ በልቡ ያመነ ሰው በአፉ ለመዳኑ መመስከር እንደማያፍር ስለታሰበና ስለተጻፈ ነው። ሰው በእውነት ካመነ ይመሰክራል ማለት ነው። «ሁሉ» የተባለ ቃል የተጨመረበት ምክንያት (ቊ.11) በአይሁድና በግሪክ መካከል ልዩነት ስለሌለ ነው። ከተመረጡት የእግዚአብሔር ሕዝብም ቢሆን ከሌላም ወገን ቢሆኑ፥ ሁለቱም የሚድኑበት በአንድ መንገድ ነው። ኢየሱስ የሁሉ፥ የተመረጡትና ያልተመረጡት፥ ጌታ ነው፤ በእምነትም ለሚጠሩት ሁሉ፥ ከእስራኤልም ቢሆን ከአሕዛብም፥ ባለ ጠጋ ነው። ይህንም የሚያጸና «የጌታ ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» የሚል የነቢዩ የኢዩኤል ቃል ነው፥ (ኢዩ.2፡32)።

እንግዲህ ደኅንነት ለተመረጡት ለጥቂቶች ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሁሉ ነው፤ ሁሉም የሚያገኙት በአንድ መንገድ፥ እርሱም የጌታን ስም በእምነት በመጥራት ነው።

ማስገንዘቢያ:- እላይ ከተጻፈው 3 ነገሮችን እናስተውል:-

1ኛ. በልብ ማመን ያስፈልጋል፥ (ቊ.9)። እምነት ማለት በልብ ማመን ማለት ነው እንጂ የራስና የእምሮ ዕውቀት ብቻ አይደለም። ኢየሱስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፥ ተመላልሶ ተአምራትን እንደሠራ፥ እንደተገረፈና እንደተሰቀለ ማወቅና ነገሩ ሁሉ እውነት እንደሆነ ማመን ብቻ አይደለም። ይህንስ ሁሉ አጋንንት ያምናሉ፥ (ያዕ.2፡19)። ይሁንና እምነታቸው የልብ አይደለምና በማመናቸው አይድኑም። የሚያድን እምነት ነገሩ እውነት እንደሆነ ማመን ብቻ ሳይሆን በአንድ ሰው፥ እርሱም በኢየሱስ፥ ማመን ነው። ኢየሱስ የእኔ መድኃኒት ሆኖ እርሱ እንዳዳነኝ ማመን ነው።

2ኛ. በእምነት መጥራት ያስፈልጋል፥ (ቊ.12-13።) «አቤቱ አቤቱ» ብሎ ስሙን መድገም ብቻ አይደለም። «ኢየሱስ» ማለት «የእግዚአብሔር መድኃኒት» ማለት ነውና በመድኃኒትነቱ አምኖ «አድነኝ!» ብሎ መጥራት ያስፈልጋል። ሰው ይድን ዘንድ በልቡ ማመን በእምነትም መጥራት ያስፈልገዋል።

3ኛ. በአፍ መመስከር ያስፈልጋል፥ (ቊ.10-11)። «ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል» ተብሎ ከተነገረ በኋላ «በአፉም መስክሮ ይድናል» ስለ ተባለ በመጽደቅና በመዳን መካከል ልዩነት ያለ ይመስላል። በአፉ ያልመሰከረ ሰው አልዳነም ማለትነውን? አይደለም! መልእክቱ በሞላ ደኅንነት በእምነት ብቻ እንደሆነ ያስተምራል። ዳሩ ግን የጸደቀ ሰው በአፉ ካልመሰከረ የመዳኑን ጣዕም፥ ደስታውን ኃይሉን አለኝታውንም፥ አያውቅም ማለት ነው። በመዳኑ ላይ አንዳችን ነገር በሥራው እንደሚጨምር ማለት አይደለም፤ ካልመሰከረ ግን የመዳኑን ጽናት አያውቅም ማለት ነው።

<u>ቊ.14-21</u>:- ደኅንነት ለሰው ሁሉ ከሆነ፥ የሚገኝበትም የጌታን ስም በእምነት በመጥራት ከሆነ፥ ሰው ሁሉ ይጠራ ዘንድ ያን ስም እንዲያውቅና እንዲያምንበት ያስፈልጋል። ይህስ ከሆነ፥ ወደ ሰው ሁሉ ዘንድ፥ እርሱም ማለት ወደ እስራኤል ወደ አሕዛብም ደግሞ፥ ሐዋርያት እንዲላኩ የግዴታ ነገር ነው። ጳውሎስ ወደ አሕዛብ ዘንድ ስለሄደ እስራኤል ጠልተውት ነበር፤ የሄደ ግን በግዴታና በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። ይህም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚመሰክር የእስራኤል መጽሐፍ ነው! (ኢሳ.52፡7)። ይድኑ ዘንድ ግን እንዲሰሙና እንዲያምኑ አስፈላጊ ነበረ። መስማትማ እስራኤል ሰምተዋል፤ ለማመን ግን አልፈቀዱም። እግዚአብሔር በእርሱ ወገን በኩል አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ሐዋርያትን ልኮ በማስታወቅ ፈጽሞ ነበር፤ እስራኤል በማመን ግን በእነርሱ ወገን የነበረውን አልፈጸሙም። በቊ.3 ላይ

እስራኤል «አልታዘዙም» ተብሎ እንደነበረ እንዲሁ በቊ.16 ላይ «አልታዘዙም» ተብሎአል፤ ሁለቱም ቃላት እነርሱን የሚመለከቱ እንደሆነ ያመለክታል። ሰምተው ነበር። ሰምተው ሲያበቁ በገዛ ራሳቸው ፈቃድ ቃሉን ተቃወሙ ለመታዘዝም እንቢ አሉ። ከዚህም ደግሞ ነቢዩ ኢሳይያስ አስጠንቅቆአቸው ነበር፥ (ኢሳ.53፡1)። አመካኝተው «አልሰማንም» ይላሉን? መጽሐፋቸው ይመሰክርባቸዋል። እግዚአብሔርን ማወቅ በሰማይ እና በምድር ካሉ ፍጥረቶች ለሰው ሁሉ ተወርቶአል ብሎ ቅዱስ ዳዊት እንደ ተናገረ (መዝ.18፡4)፥ እንዲሁ የጌታን ስም ማወቅ በወንጌል ያለ በሐዋርያት እንደበት በሁሉ ዘንድ ተወርቶ ለሰው ሁሉ ደርሶአል።

አሕዛብ እንደሚተኩ እስራኤል አላወቁምን? ታላቅ መሪአቸው ሙሴ፥ ታላቅም ነቢያቸው ኢሳይያስ፥ ሁለቱም አጣርተው ነግረዋቸው ነበር። ኢሳይያስም ለጌታ ቃል አለመታዘዛቸውንና መቃወማቸውን በግልጥ ነገራቸው። ከፈቀዱ በጸጉ ነበር። አልፈቀዱምና ቀረባቸው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:- በዚህ ምዕራፍ ስለ እስራኤል እንደተነገረው ሁሉ እንደዚሁ በእኛ ዘንድ ነው። እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለሆነ፥ ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርስ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ስለሚወድ (ኤፌ.2፡4፤ 2ኛጴጥ.3፡9) ወንጌል ወደ እኛ ዘንድ እንዲደርስ አድርጎአል። ልንቀበለው እንፈቅዳለንን? በእርሱ በኩል እግዚአብሔር መረጠን እጆቹንም ዘረጋ፤ አሁን በእኛ በኩል በጌታ ስም በእምነት ለመጥራት ዝግጁዎች ነንን? የጌታን ስም መጥራት አለመጥራትም የገዛ ራሳችን ፈቃድ ነገር ነው። ብንጠራ እንድናለን፤ ሳንጠራ ብንቀር ግን ጥፋቱ የእግዚአብሔር ሳይሆን የእኛ ነውና ደማችን በራሳችን ላይ ነው፥ (ሕዝ.33፡4-5፤ የሐዋ.18፡6፤ የሐዋ.20፡26-27)።

ቊ.14 የዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን በጣም መመልከት የሚገባት ቊጥር ነው። በዚህ ቊጥር ሰውን ለመላክ የቤተ ክርስቲያን አላፊነት፥ ለመሄድም የእያንዳንዱ ክርስቲያን አላፊነት፥ እንደሆነ እናያለን።

ሰው የሚድንበት የጌታን ስም በእምነት በመጥራት ከሆነ፥ ለመጥራት እንዲችል ማመን፥ ማመንም እንዲችል መስማት፥ መስማትም እንዲችል ሰባኪዎች እንዲላኩለት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን ባትልክ፥ ክርስቲያንም ባይሄድ፥ የአገሩ ሰዎች እንደምን መዳን ይችላሉ? ሰባኪዎችን መላክ ዓይነተኛ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ነው። ሰባኪዎችን የማትልክ ማንኛዪቱም ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የማትስፋፋ፥ እንዲያውም የምትሞት ቤተ ክርስቲያን ናት።

እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ «መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው ያማሩ ናቸው» ብሎአልና (ኢሳ.52፡7)። መላክ መሄድም የማያምር ወይም የማይገባ ወይም የሚያሳፍር ነገር እንደሆነ ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን ክርስቲያንም ቢሆን አያስቡ። የሄደም ሰው ሳይታክት ሳይደክምም እግዚአብሔር

በእርምጃው ሁሉ ደስ እንደሚሰኝ በማሰብ ይበርታ። ሁሉ እንዲሰሙ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና (ማር.16፡15) ሁሉ ባይታዘዙ እንኳ ምን ጊዜም ሰው እንዲሄድ ያስፈልጋል፥ (ሕዝ.2፤1-8)።

ክርስቲያን ሁሉ በቍ.16 «እንዴት? እንዴት? እንዴት?» በተባሉቱ ቃሎች፥ በተለይ ደግሞ በሐዋ.8፡31 ላይ በተጻፈው ጥያቄ፥ በብርቱ ያስብ። የምሥራችን ለማውራት ተጠርቶ ቻል ወይም እንቢ ለሚለው ሰው ወዮለት! እግዚአብሔር «ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?» ብሎ ላቀረበው ጥያቄ የእያንዳንዱ ክርስቲያን መልስ በኢሳ.6፡8 ላይ እንደ ተባለው «እነሆኝ፥ እኔን ላክ!» የሚል ይሁን።

«ሂድ ንገር!» ለተባለው ትእዛዝ (ሕዝ.3፡1-11) «ከሰማይ የታየኝን ራእይ እንቢ አላልሁም» የሚል የሐዋርያው የጳውሎስ ምስክርነት የራሳችን ደግሞ ይሁን፥ (የሐዋ.26፡16-19)።

* * *

የሐዋ.8፡31፡- «የኢትዮጵያ ንግሥት አሽከር፡-

የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው።

# ምዕራፍ 11

1. እንግዲህ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? እላለሁ። አይደለም፤ እኔ ደግሞ እስራኤላዊና ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና። 2. እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም። መጽሐፍ ስለ ኤልያስ በተጻፈው የሚለውን፥ 3. በእግዚ አብሔር ፊት እስራኤልን እንዴት እንደሚከስ፥ አታውቁምን? ጌታ ሆይ፥ ነቢያትህን እንዴት ገደሉ መሠዊያዎችህንም አፈረሱ እኔም ብቻዬን ቀረሁ ነፍሴንም ይሹአታል። 4. ነገር ግን እምላካዊ መልስ ምን አለው? ለበዓል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ። 5. እንደዚሁም በአሁን ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ። 6. በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል።

7. እንግዲህ ምንድር ነው? እስራኤል የሚፈልጉትን አላገኙትም፤ 8. የተመረጡት ግን አገኙት፤ ሌሎቹም ደነዘዙ፤ እንዲሁም፦ ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው ተብሎ ተጽፎአል።
9. ዳዊትም፦

10. ማዕዳቸው ወጥመድና አሽከላ ማሰናከያም ፍዳም ይሁንባቸው፤ ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፥ ጀርባቸውንም ዘወትር አጕብጥ

ብሎአል።

11. እንግዲህ፦ የተሰናከሉ እስኪወድቁ ድረስ ነውን? እላለሁ። አይደለም፤ ነገር ግን እነርሱን ያስቀናቸው ዘንድ በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ። 12. ዳሩ ግን በደላቸው ለዓለም ባለ ጠግነት፥ መሸነፋቸውም ለአሕዛብ ባለ ጠግነት ከሆነ፥ ይልቁንስ መሙላታቸው እንዴት ይሆን?

13.14. ለእናንተም ለአሕዛብ እናገራለሁ። እኔ የአሕዛብ ሐዋርያ በሆንሁ መጠን ሥጋዬ የሆኑትን አስቀንቼ ምናልባት ከእነርሱ አንዳንዱን አድን እንደ ሆነ አገልግሎቴን አከብራለሁ። 15. የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር መመለሳቸው ምን ይሆን? 16. በኵራቱም ቅዱስ ከሆነ ቡሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው።

17. ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ፥ ከቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤ 18. ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም። 19. እንግዲህ፦ እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል። 20. መል ካም፤ እነርሱ ካለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። 21. ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ። እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና። 22. እንግዲህ የእግዘብሔርን ቸርነትና ጭከና

ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፥ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቈረጣለህ። 23. እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ ሊያገባቸው ይችላልና። 24. አንተ በፍጥረቱ የበረሀ ከነበረ ወይራ ተቈርጠህ እንደ ፍጥረትህ ሳትሆን በመልካም ወይራ ከገባህ፥ ይልቁንስ እነዚያ በፍጥረታቸው ያሉት ቅርንጫፎች በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?

25. ወንድሞች ሆይ፥ ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ ይህን ምሥጢር ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤ እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ 26. እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦

27. መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል።
ኃጢአታቸውንም ስወስድላቸው ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው።

28. በወንጌልስ በኩል ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፥ በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው፤ 29. እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና። 30. እናንተም ቀድሞ ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዛችሁ፥ አሁን ግን ከአለመታዘዛቸው የተነሣ ምሕረት እንዳገኛችሁ፥ 31. እንዲሁ በተማራችሁበት ምሕረት እነርሱ ደግሞ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ እነዚህ ደግሞ አሁን አልታዘዙም። 32. እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ ዘግቶታልና።

33. የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።

34. የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር 35. ወይስ
ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?

36. ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ አንድ።

ምዕ.11 የአሕዛብ መተከል ምዕራፍ ነው። ቢሆንም ደግሞ፥ ለእስራኤልም የተስፋ ምዕራፍ ነው። ሐዋርያው ስለ አለፈው ተናግሮአል፥ አሁን ስለ ወደፊቱ ይናገራል። ያለፈው የእስራኤል ነገር አሳዛኝ ነበር፤ የወደፊቱ ግን ክብር የሞላበት ይሆናል። እስራኤል ለጊዜው በአንዳንድ በኩል እንዳይገቡ ተዘጉ፤ በኋላ ግን በሙሉ ይገባሉ። እግዚአብሔር ሁሉን፥ እስራኤልንም አሕዛብንም፥ ወድዶ ሁሉን ይምር ዘንድ ቈረጠ። የምናመልከው አምላክ ምንኛ ታላቅ ነው!

እግዚአብሔር በእስራኤል ቢጨክን እንኳ በእርሱ ዘንድ ዓመፃ እንደ ሌለ ለማረጋገጥ ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ እንዴት እንደሚቀና መመልከት ነው። ዋና የዚህ ምዕራፍ ቃሎች «አንዳንድ» እና «ሙላት» የተባሉ ናቸው። «እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሞላ (በሙላት) ጣላቸውን?» ለቀረበው ጥያቄ፥ መልሱ ከዚህ እንደሚከተል ነው:- «ሉረ አይሁን! እግዚአብሔር እውነተኛ ነውና ይህስ የማይቻል ነገር ነው። እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትም። ግን አዎን! በሞላ (በሙላት) ሳይሆን አንዳንዱ (ቍ.17)፥ በአንዳንድ በኩል (ቍ.25)፥ ተዘግቶአል፤ ይህም አሕዛብ በሞላ (በሙላት) እስኪገቡ ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እስራኤል በሞላ (በሙላት) ይድናሉ፥» (ቍ.26።)

ቍ.1-6:- እግዚአብሔር ቀኑን ሁሉ እጆቹን ወደ እስራኤል ቢዘረጋ እስራኤል እንቢ ብለው ጥሪውን ተቃውመው ነበር፥ (10:21።) በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን? ከእንግዲህ ወዲህ መዳን ለአሕዛብ ብቻ ነውን? ሉረ አይሁን! ማስረጃው፥ ጳውሎስ ራሱ እስራኤላዊ፥ ከአብርሃም ዘር፥ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ልጅ ከብንያምም ወገን ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን አስቀድሞ ዐወቃቸው። የሚሆነውን ታሪካቸውን ዐወቀ፥ ዐውቆም መረጣቸው። ጥንት ያወቀውን ነገር አሁን አይቶ ይጥላቸዋልን? አይጥላቸውም! ደግሞ፥ እንቢ ያሉ ሕዝብ በሞላ (በሙላት) ሳይሆኑ አንዳንዶች ብቻ ነበሩ። በነቢዩ በኤልያስ ዘመን እንደ ነበረ ነው። በዚያ ዘመን እንደ ጳውሎስ የሚመስል አንድ ሰው ብቻ፥ እርሱም ኤልያስ፥ የቀረ ሲመስል፥ እግዚአብሔር «ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ» ብሎ ተናገረ። እግዚአብሔር መርጦ አስቀራቸው ማለት ነው። እንደዚሁም በጳውሎስ ዘመን በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች (የቀሩ) ነበሩ። ሰው የተመረጠው በእግዚአብሔር ጸጋ ከሆነ ግንም ሰው ከሥራው እንደሚመረጥ አለማሰብ ነው።

ቍ.7-10:- እስራኤል በሞላ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አልተቀበሉም፤ የተመረጡት ቅሬታዎች ግን ተቀበሉት፥ ሌሎችም እልከኞች ተደርገዋል። (9:19።) ለምሳሌ፥ በገዛ ፈቃዱ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወድዶ በጨለማ ቤት

ተቀምጦ ብርሃንን ከመጥላቱ ብዛት የተነሣ የቤትን መስኰት እንኳ ነቅሎ እንደሚያነሣና ከፍቱን እንደሚደፍን ሰው ነገር ነው። ያ ሰው ጨለማን መርጦ በጨለማ ከኖረ በኋላ ወደ ብርሃን ወጥቶ ለማየት ቢወድ ዓይኖቹ እንደማያዩ ይረዳዋል፤ ታውሮም ይቀራል። ማየትም አሁን አይችልም። ጠልቶት ነበርና አሁን በወደደው ጊዜ እንዲያገኘው አልተፈቀደለትም። እንደዚሁ ያለ ነገር እየነገራቸው ኢሳይያስ እስራኤልን አስጠንቅቆአቸው ነበር፥ ቃሉ ግን ተፈጸመባቸው። ወንጌልን ሰሙ፤ ልባቸውን እልከኛ አደረጉ፥ ተቃወሙ፥ ዐመፁ፥ (ማር.3፡22፤ዮሐ.12፡37፤ ሮሜ 10፡21)። እንደዚህ ሲሆን፥ በምዕ.1 እንዳየን ሁሉ፥ ብርሃንን ከበደሉትና እግዚአብሔርን ለማወቅ ካልወደዱ ሰዎች ዘንድ እግዚአብሔር ከሃሊ እጁን ሰብስቦ በገዛ መንገዳቸው ይሄዱ ዘንድ አሳልፎ ይሰጣቸዋል። የመረጡትም መንገድ ወደ ርኵሰት ወደ ጥፋትና ወደ ኩነኔ አደረሳቸው። የእርሱን መንገድ አልወደዱምና በራሳቸው መንገድ ይሄዱ ዘንድ ይተዋቸዋል። በእስራኤል በነበሩ «ሌሎቹ» በተባሉት ዘንድ (ቊ.7) እንዲህ ሆነ። ዳዊት በእግዚአብሔር ቃል ተናግሮ፥ ብርሃንን ጠልተዋልና ለደረሳቸውም ጥሪ እንቢ ብለዋልና፥ «ይሁንባቸው፥ ዓይኖቻቸው ይጨልሙ፥ ወገባቸው ይጐበጥ» አለ፥ (መዝ.68፡22-23)። ይህም ከብርሃን ይልቅ ጨለማን በሚወዱት ላይ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፥ (ዮሐ.3፡17-21)።

ማስገንዘቢያ፡- ይህ ከዚህ በላይ የተጻፈው ነገር ለዛሬው ሰው ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል! ሰው ወንጌልን ከቶ ቢሰማ፥ ወዲያውኑ ያልተቀበለው እንደሆነ ሁለተኛ ሲሰማው ከፊተኛው ይልቅ አሁን ለመቀበል ያስቸግረዋል። ብዙ ጊዜም ሰምቶ ልቡን እልከኛ ያደረገ እንደሆነ፥ በኋላ ምናልባት ለመቀበል ቢወድም አይችልም ይሆናል። በመጀመሪያ ላይ ለማመን አልፈቀደም፤ አሁን ለማመን አይችልም! (ዕብ.12፡16-17)። ይህ የእግዚአብሔር ፍርድ ነውና ሰው ሁሉ ሊያውቀውና ሊጠነቀቅበት ይገባዋል። የምንቀበልበት ቀን አሁን፥ ዛሬ፥ ነው፥ (2ኛቆሮ.6፡1-2)።

ቊ.11-15፡- እንግዲህ የእስራኤል «ሙላት» በዚያ በእንቅፋት ድንጋይ፥ እርሱም ማለት በክርስቶስ (1ኛጴጥ.2፡6-8)፥ ተሰናክሎአል፥ (9፡32-33) መሰናከሉስ ወድቀው እስከማይነሡ ድረስ ነውን? ሉረ አይሁን! ገና በእስራኤል ፊት ክብር የሞላበት ዘመን አለ። እውነት ነው፥ እስራኤል ባለማመንና ባለማታዘዝ ስለ በደሉ «መዳን ለአሕዛብ ሆነ»፤ ማለት፥ ወንጌል ለአሕዛብ ተዛወረ፥ (የሐዋ.13፡44፤48)። ይህ የተደረገው ግን አሕዛብ እስራኤልን አስቀንተው ወደ መዳን ለማድረስ ነው እንጂ ለአሕዛብ ተብሎ ብቻ አይደለም። የእስራኤል በደልና ውድቀት ግን ለዓለም ሁሉና ለአሕዛብ ባለ ጠግነትን ካመጣ፥ ካለማመን የተነሣ የጐደለ ቊጥራቸው ሲሞላ ለዓለም ምን ይመጣ ይሆን?

ጳውሎስ ምንም ስለ እስራኤልና ስለሚመጣላቸው ክብር ቢናገር፥ ለእነርሱም ቢቆና፥ አሕዛብን ባነሰ መጠን ይወዳቸዋል ማለት አይደለም። እርሱ በተለይ የአሕዛብ ሐዋርያ ነው፤ ቢሆንም፥ በዚህ ሐዋርያነት የሚበረታበት ዋና ምክንያቱ ሥጋው የሆኑትን እስራኤልን አስቀንቶ በሙሉ (በሙላት) ሳይሆን አንዳንዶችን ለማዳን ነው። ማለት፥ እስራኤል አሕዛብ ያገኙትን አይተው ንኡተው ለራሳቸው ለማግኘት እንዲቀኑ ነው። ሲሠራም ሳለ የሚመለከተው የሚመጣውን ነገር ነው። ማለት፥ መጣላቸውና መውጣታቸው ለዓለም ደኅንነት ከሆነ፥ ተመልሰው መግባታቸው ለዓለም ሁሉ እንደ ትንሣኤ ሕይወት ይሆናል። ለዚህም መያዣ የሚሆን፥ በብሉይ ኪዳን በዘኍል.15፡17-21 በተጻፈው መሠረት፥ የእግዚአብሔር ፋንታ (በኩራት) አስቀድሞ በቀረበ ዱቄቱ (ቡሆው) ሁሉ የተቀደሰ ነበረ። በኩራት የተባሉ እነአብርሃምን እነይስሐቅንና እነያዕቆብን የሚመስሉ የእስራኤል አባቶች ናቸው፤ ቡሆውም እስራኤላውያን ናቸው። እንደዚሁም ደግሞ በአንዲት ዛፍ ምሳሌ የተነገረው ስለ አባቶችና ስለ እስራኤላውያን ሲናገር ነው። አባቶቹ ለእግዚአብሔር የተቀደሱ መሆናቸው ጥርጥር የሌለበት ነገር ነው፥ (ዕብ.11፡17-21)። ይህም ከሆነ እስራኤላውያን ሁሉ የተቀደሱ ናቸውና ከዕለታት አንድ ቀን ለአባቶች የተናገረው የተስፋ ቃል ለልጆቹ ይፈጸማል።

ማስገንዘቢያ፡- የለም፥ ጨርሰው እንዲወድቁ እስራኤል አልተሰናከሉም፥ እንዲያውም እግዚአብሔር አልጣላቸውም። ከዕለታት አንድ ቀን ለእስራኤል ሕዝብ የሚሆን ታላቅ የደስታ ዘመን ይመጣል፥ እግዚአብሔርም የተስፋ ቃሉን ይፈጽምላቸዋል። «ቡሆው፥ ቅርንጫፎችም» የተባሉት (ቊ.16) የአብርሃም የሥጋ ልጆቹ ናቸውና አሁን የሚናገረው ስለ መንፈሳዊ ልጆቹ አይደለም። ዛሬ ወደ እስራኤል አገር ለተመለሱት፥ የመንግሥታቸውንም ስም ደግሞ «እስራኤል» ላደረጉት ሕዝብ በመጪው ዘመን ታላቅ ተስፋ አለ። ፍጥረት ሁሉ የእኛን፥ በመንፈስ የሆንን የእግዚአብሔርን ሕዝብ (1ኛጴጥ.2፡9)፥ መገለጥ እንደሚጠባበቀው (8፡19) ለእኛም የማይነገር ክብር እንደሚቆይ፥ እንዲሁ እኛ በታላቅ ናፍቆት በማይቋረጥም ጸሎት በእግዚአብሔር ምርጫ የተለዩለት ሕዝብ የሆኑትን የእስራኤልን የክብር መገለጥ መጠባበቅ ይገባናል። ለእስራኤል ሕዝብ የሚሆን ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር አሳብ (ፕላን) አለ። ይህን ሕዝብ በፍቅር በተስፋና በደስታ እንመልከት፥ ለእስራኤልም ሰላም እንጸልይ፥ (መዝ.121፡6)።

ቊ. 17-24፡- በእነዚህ ቊጥሮች ላይ ታላቅ የወይራ ዛፍና የቅርንጫፎችዋ ምሳሌ ይገኛል። ዛፊቱ የተስፋ ቃል ዛፍ ናት። ሥርዋ የተስፋ ቃል የተሰጣቸው አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ የተባሉ የእስራኤል አባቶች ናቸው። ቅርንጫፎችዋ እስራኤላውያን ነበሩ። ዘይቱ የተስፋ ቃል መፈጸምና የበረከት መገኘት ነው። የተስፋ ቃል መፈጸም በእምነት ነውና እምነት የሌላቸው ቅርንጫፎች አይወርሱምና በዛፊቱ ሊኖሩ አይገባቸውም። ስለዚህም የቈረጣሉ። ይህም ሲሆን፥ ከየትም ዘንድ ቢመጡ

አማኞች የሆኑት ቅርንጫፎች ቢኖሩ በተስፋ ቃል ዛፍ ይተከላሉ። እስራኤል መልካም ወይራ ሲባሉ አሕዛብ የበረሃ ወይራ ተባሉ።

ከዚህች ከተስፋ ቃል ዛፍ ከመልካሙ ወይራ ቅርንጫፎች በሙሉ ሳይሆን «አንዳንዱ» ተሰበሩ፥ (ቊ.17።) በእነርሱም ምትክ ከበረሃ ወይራ፥ ከአሕዛብ ማለት፥ ደግሞ በሙሉ ሳይሆን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ተተከሉ። የእስራኤል ቅርንጫፎች የተሰበሩበት ምክንያት ካለማመናቸው የተነሣ ሲሆን፥ የአሕዛብ ቅርንጫፎች የተተከሉበት ከማመናቸው የተነሣ ነው። የተስፋ ቃል አስቀድሞ የተሰጠ ለእስራኤል ነበረና አሕዛብ የእስራኤል ተስፋ ወራሾች ስለ ሆኑ መመካት አይገባቸውም። አሕዛብ ተተከሉ፥ እውነት! የተተከሉበት ግን ከእምነታቸው የተነሣ ነውና እምነታቸውን አጽንተው ይያዙ። «አሁን የእግዚአብሔር ሕዝብ ነን» ሳይሉ (ማቴ.3፥9) በእምነት መቆማቸውን ያጽኑ። አለበለዚያም እስራኤል ባያምኑ ተቈርጠው እንደነበሩ፥ እንዲሁ አሕዛብ ይቈረጣሉ፤ መቈረጣቸውም ከእነዚያ የቀለለ ይሆናል። እንደዚሁ ደግሞ እስራኤል ባለማመን ጸንተው ሳይሆኑ ወደ ማመን ቢመለሱ እግዚአብሔር ደግሞ ወደ ተስፋ ቃል ዛፍ ያገባቸዋል። ይህንም እኮ ያደርጋል!

ማስገንዘቢያ

1. በዘመናችን በእምነታቸው ተመክተው አይሁድን የሚጠሉት አንዳንዶች ሰዎች አሉ። ቢሆንም፥ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን፥ ይህንም በማድረግ እግዚአብሔርን ደስ እንደማናሰኝ፥ እናያለን። ጥቂት ሲቀረው ያለን ሁሉ ከአይሁድ ዘንድ መንጭቶአልና ለእነርሱ ያለብን ዕዳ ከባድ ነው። በእውነት እኛን ይሸከሙናል (ቊ. 18)፤ ልናከብራቸውና ልንወዳቸውም ይገባናል። ከአይሁድ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን ተቀብለናል፥ ከደራሲዎችም የሚበዙት አይሁድ ነበሩ። እንዱን እውነተኛውን አምላክ ለማወቅ እነርሱ አስተምረውናል። ነቢያትና ሐዋርያት ከእነርሱ ዘንድ ናቸው፥ መድኃኒትም ከእነርሱ ነው፥ (ዮሐ.4፥22)። ክርስቶስም ከእነርሱ ነው ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ ይህን ከቶ አይርሳ! ለአይሁድ ያለብን ዕዳ ታላቅ ነው፤ ከእስራኤል የሆኑትን ወደ እምነት መታዘዝ አድርሰን ወደ ዛፊቱ በመመለስ ያን ዕዳ ለመክፈል ክርስቲያኖች የሆንን ሁሉ እንጣጣር።

2. በእስራኤል ከደረሰባቸው ነገር ለራሳችን ማስጠንቀቂያ እናገኛለን። ይህ የተደረገባቸው በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ከሆነ በእኛ ደግሞ እንዳይደርስ እጅግ አድርገን መፍራት ይገናባል። «ፍራ እንጂ፥ የትዕቢትን ነገር አታስብ!» ተብሎአል፥ (ቊ.20።)

3. እግዚአብሔር ልባቸውን እልከኛ በማድረግ በእነርሱ ጨከነ፤ እኛን በመምረጡ ግን ቸርነቱን አሳየ፥ (ቍ.22።) ቸርነቱ እንደምን ታላቅ ነው! በከንቱ አንቀበለው! (2ኛቆሮ.6፡1)።

<u>ቍ.25-32</u>፡- የእግዚአብሔርን ምሥጢር እናስተውል እንጂ በእስራኤል አንታበይ። ያ ከቍ.7 እስከ ቍ.10 ድረስ ያየነው «ድንዛዜ» በእስራኤል ሁሉ ሳይሆን በአንዳንዱ በኩል የሆነ ለጊዜው ብቻ ነው። ለዘላለም ሳይሆን ጊዜው «እስከ» በተባለ ቃል ተወስኖአል። የደነዘዙት የአሕዛብ «ሙላት» እስኪገባ ድረስ ነው፤ ከዚያም በኋላ የእስራኤል «ሙላት» ደግሞ ይድናል! ተጽፎአል! «ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም» እንደ ተባለ ነው፥ (ማቴ.24፡35)። እግዚአብሔር ወላዋይ አምላክ አይደለም። ሰጥቶ በስጦታው፥ ጠርቶ በመጥራቱ፥ አይጸጸትም። (ቍ.29) የተስፋን ቃል ለእስራኤል ሰጥቶ ነበር። እስራኤል እንቢ አሉ። እሺ! ለጊዜው ከተስፋው ቃል መፈጸም በአንድ ዳር ተወግደዋል። እነርሱ ባይገቡ አሕዛብ ይግቡ ተባለ፥ (ሉቃ.14፡16-24)። ይሁን እንጂ፥ የተስፋ ቃል ገና ጸንቶ ይቆያል። «የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? ሉረ ከቶ አይደለም!» ተብሎአል፥ (3፡3።) ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕ.59፡20-21 ደግሞ በምዕ.27፡9 የኪዳኑን መፈጸምና እስራኤል ተመልሰው ወደ ዛፊቱ መግባታቸውን አመልክቶአል። አሕዛብ ይገቡ ዘንድ እስራኤል ኤሳውን መስለው (9፡13) ለጊዜው ጠላቶች ሆነዋል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያዕቆብን ደግሞ እንደ ወደደ እንዲሁ ከመጀመሪያ ጀምሮ ስለ አባቶች ሲል እስራኤልን ወድዶአቸው ነበርና እስራኤል የእግዚአብሔር ተወዳጆች ናቸው። «የአሕዛብ ሙላት»፥ «የእስራኤል ሙላት»! እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላም እኮ! (2፡11።) ፈቃዱ ሁሉን ለማዳን ነው። አሕዛብ ቀድሞ አማልክትን አምልከዋል እንጂ ለእግዚአብሔር አልታዘዙም፥ (ምዕ.1።) እስራኤል ግን ክርስቶስን ወንጌልንም አንቀበልም ብለው በተራቸው የማይታዘዙ ሆኑ፥ (10፡21) እስራኤል ባይታዘዙ የደኅንነት ደጅ ለአሕዛብ ተከፈተ፥ (የሐዋ.14፡27)። አሁንም ደግሞ የአሕዛብን መግባት አይተው እስራኤል ቀንተው ተመልሰው ይገቡ ዘንድ የእግዚአብሔር አሳብ (ፕላን) ሆኖአል።

ማስገንዘቢያ፡- «ቤተ ክርስቲያን (የምእመናን ማኅበር ማለት) ወርሳለችና ለምድራዊ እስራኤል የሚሆን የተስፋ ቃል በፍጹም አልቀረም» የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህን ምዕራፍ ግን ስናነብ ይህ አሳባቸው ስሕተት ሆኖ ይታያል። ለምድራዊ እስራኤል የሚሆኑ ግሩም የሆኑ ተስፋዎች አሉ፥ በፊታቸውም ግሩም የሆኑ ወራት አሉ። በምዕ.9 ላይ እንደተባለ ነው፤ ለእስራኤል የተሰጡ ምድራዊ ተስፋዎች አሉ፥ መንፈሳዊም ተስፋዎች አሉ። ምድራዊ ተስፋዎቹ ለምድራዊ እስራኤል ናቸው፥ መንፈሳዊም ተስፋዎቹ ለመንፈሳዊ እስራኤል፥ እርሱም ማለት ለቤተ ክርስቲያን ነው። ምድራዊ ተስፋዎች እንዳሉ ግን በዚያ በምዕ.9 ላይ አይተናል። ይህም ከሆነ

ሳይፈጸሙ ይቀራሉን? አይቀሩም! «እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ እስት ይናገር ዘንድ፥ የሰውም ልጅ አይደለም አንድ ነገር እንዲጸጸተው። እርሱ ያለውን ማድረግ አይሆንለትምን? የተናገረውንስ መፈጸም አይችልምን?» (ዘኍል.23፡19)።

ታዲያ፥ ይህ መቼ ይሆናል? የሚሆነው «መድኃኒት ከጽዮን ሲወጣ» ነው፥ (ቍ.26፤ ኢሳ.59፡20-21)። እርሱም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም ተመልሶ ሲመጣ ማለት ነው። በዚያን ጊዜ «ዓይን ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፥» (ራዕ.1፡7)። በዚያን ቀን እንቅልፉ ከእስራኤል ዘንድ ይርቃል፥ መታወራቸው መደንዘዛቸውም ይወገዳል፥ ሁሉም ያዩታል ድምፁንም ይሰማሉ፥ (ቍ.8።) በዚያም ቀን የእስራኤል ሕዝብ ያምኑበታልና «ሕዝብ በአንድ ጊዜ ይወለዳል።» (ኢሳ.66፡8)። ክርስቶስን አሳልፈው በመስጠት የሆነባቸው ኃጢአተኛነት ይወገዳል፥ (ቍ.26፤ ማቴ. 27፡25)። አንድ መንጋም ይሆናሉ እረኛውም አንድ፥ (ዮሐ.10፡16)።

ገና ወደ ፊት የእስራኤል ሕዝብ በዓለም ነገዶች መካከል ምስጋና በረከትም ይሆናሉ፥ (መዝ.86፤ ኢሳ.19፡24፤ ኢሳ. ም.35፤ ኢሳ.66፡10-22፤ ሆሴ.14፡4-8፤ ሰፎ.3፡14-20።)

ቍ.33-36፡- «ሁሉን ይምር ዘንድ»! የእግዚአብሔር አሳብ እንደምን ታላቅ ገናናም ነው! የለም፥ ምሥጢሩን ከቶ አላወቅንም፥ አልተረዳንም፥ (ቍ.25።) ያን ወይም ይህን መርጦ እንደከበር መሰለን እንጂ ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ እንደዘጋቸው ከቶ አላሰብንም። በሕዝብ ወይም በሰው ላይ ሲፈርድ ያ ፍርድ ወዴት ዘንድ እንደሚያደርስ ማን ያውቃል? ለደኅንነት ያደርስ ይሆናል እኮ! የእግዚአብሔር አሳብ ሁሉን ለማዳን ነበረ እንጂ አንድ ይጠፉ ዘንድ አልወደደም። 99ኙ ደኅና ሲሆኑ አንዱ ግን ከጠፉ እግዚአብሔር ደስታ ዕረፍትም የለውም። «እስኪያገኘው ድረስ» ሊፈልግ ይሄዳል፥ (ሉቃ.15፡4)። ሰው ግን ዐውቆ ሲበድል፥ እንቢ ብሎም በአለመታዘዝ እና ጥሪውን በመቃወም ሲያጠፉ፥ እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ ማን በመከረው ነበር? ለማዳንም በምን ተገደደ? በእርሱ ዘንድ ብድራትን መመለስ የለም፤ ይህንም ሁሉ ለማድረግ ግዴታ የለበትም፤ ሁሉ ከእርሱ መንጭቶአልና፥ በእርሱ ተደርጎአልና፥ ለእርሱም ይምራልና። ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን። አሜን!

ይህ የመልእክቱ የዶክትርን (የሃይማኖት ትምህርት) ክፍል መጨረሻ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ፥ ከምዕ.12 እስከ ምዕ.16 ድረስ፥ ስለ ክርስቲያን ዕለታዊ ኑሮ እናነባለን።

# ምዕራፍ 12

1. እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው
ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥
እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። 2. የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና
ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ
መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

3. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ
እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው
ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ። 4. በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥
የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ 5. እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ
አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን። 6. እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ
ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ 7. አገልግሎት
ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ 8. የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤
የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤
የሚምር በደስታ ይማር።

9. ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ 10. ከበጎ ነገር ጋር ተባ
በሩ፤ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤
11. ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ 12. ለጌታ ተገዙ፤ በተስፋ
ደስ ይበላችሁ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ፤ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤
እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።

14. የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፥ መርቁ እንጂ አትርገሙ። ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ
ይበላችሁ፥ 15. ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ። 16. እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤
የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ
አይምሰላችሁ። 17. ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም
የሆነውን አስቡ። 18. ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። 19. ተወዳ
ጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን
እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። 20. ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ
አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና። 21. ክፉውን በመልካም
አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ምዕ.12 የክርስቲያን ኑሮ ክፍል መጀመሪያ ምዕራፍ ነው። የክርስቲያን ሃይማኖት የእምነት ነገር ብቻ አይደለም። ደግሞ የአካሄድ ወይም የመመላለስ ነገር ነው። «በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል» ተብሎአልና ክርስቲያን የሆነ ሰው እንዴት መመላለስ እንደሚገባው ማወቅ ያስፈልገዋል፥ (1ኛተሰ.4፡1፤ 1ኛዮሐ.2፡6)። ስለዚህ በእነዚህ በሚከተሉት ሦስት ምዕራፎች ጽድቅን በእምነት የተቀበለ ሰው እንዴት መመላለስ እንደሚገባው እናገኛለን፤ የሰው ኑሮ የእግዚአብሔርን የመንግሥትንና የሌላ ሰውን ነገር ይነካልና፥ በምዕ.12 ስለ ክርስቲያን ኑሮ በእግዚአብሔር ዘንድ፥ በምዕ.13 ስለ ክርስቲያን ኑሮ በመንግሥት ዘንድ፥ በምዕ.14 ደግሞ ስለ ክርስቲያን ኑሮ በወንድሞቹ ዘንድ እናነባለን።

ምዕ.12 ስለ ልብ አኳኋን፥ ምዕ.13 ማድረግ ስለሚገባን ነገር፥ ምዕ.14 ደግሞ ማድረግ ስለማይገባን ነገር በተለይ ይናገራል።

ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ይህን ያህል ካነበብን በኋላ በዚያ ምሕረት መሠረት መልካም ሥራ መሥራት እንደሚገባን ብናነብ አንደነቅም። በአሥራ አንዱ ምዕራፎች ሁሉ የእምነትን ነገር አየን። አሁን የእምነት ተከታይ የሆነውን የመልካምን ሥራ ነገር እናያለን። ትምህርቱን አምኖ መዳን በቂ ነገር አይደለም። የዳነ ሰው አሁን በአዲስ አረማመድ መራመድ ያስፈልገዋል። በዚህ በሮሜ መልእክት ውስጥ እንደተጻፈ ቅደም ተከተሉን ብቻ እናስተውል። መጀመሪያ የሚመጣው፥ ያውም በ11 ምዕራፎች፥ እምነት ነው፤ ከዚያም በኋላ ተከታዩ መልካም ሥራ ነው። መልካምን ሥራ ማስቀደም የከንቱ ከንቱ ነገር ነው። መሠረቱ የእግዚአብሔር ምሕረት ከሆነ ሰው በእምነት ያን ምሕረት አስቀድሞ ካላገኘ በሚሠራው በመልካሙ ሥራ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደምን ይችላል? አይችልም! አስቀድሞ ሰው በእምነቱ ይጸድቃል፥ ቀጥሎም መልካምን ሥራ ይሠራል። ቅደም ተከተሉ ይህ ነው።

ቍ.1-2:- «እንግዲህ» የተባለው ቃል ከምዕ.3፡21 ጀምሮ እስከ ምዕ.11 መጨረሻ ድረስ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ይመለከታል። በዚያ ርኅራኄ

መሠረት፥ «እንግዲህ»፥ ሰውነታችንን እናቀርብ ዘንድ ሐዋርያው ይለምነናል። የምግባር መሠረት የእግዚአብሔር ርኅራኄ ነው። ምግባርን የምንሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ አንዳችን ነገር ለማግኘት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ያን ያህል ርኅራኄ ስላሳየን ነው። ለማግኘት ሳይሆን ወረታውን ለመመለስ ነው። ያን፥ የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ማለት፥ አይተን «እንግዲህ» መልካም ሥራ መሥራት ይገባናል። ያን አይቶ ምግባርን የማይሠራ ሰው እምነቱ የሞተ እምነት ነው፥ (ያዕ.2፡14-26)።

ይህ ነውና ምን ልንመልስለት እንችላለን? በሬን እንስጠውን? በሬን የሚፈልግ አይደለም፥ «ከቤትህ ፍሪዳን አልወስድም» ብሎአልና፥ (መዝ.49፡7-15) የእግዚአብሔር አስተሳሰብ እንደ ምድራዊው ሰው አስተሳሰብ አይደለም። ምድራዊው ሰው እግዚአብሔር የሚፈልገው ትርፍ ጊዜአችንን፥ ወይም ትርፍ ገንዘባችንን፥ ወይም ትርፍ መብላችንን እንደሆነ አርጎ ያስባል። እንዲህ ግን አይደለም! እግዚአብሔር (1ኛ) ታላቅ ንጉሥ ነውና (ሚል.1፡6-14)፥ (2ኛ) ታላቅ ሥራ ሠርቶልናልና፤ ከእኛ ዘንድ የሚፈለገው ሰውነታችንን፥ እርሱም ማለት ሁለመናችንን፥ ነው እንጂ በእንደዚህ ያለ የልጅነት ጨዋታ ደስ ሊሰኝ አይችልም። ከምዕ.3፡21 ጀምሮ እስከ ምዕ.11 መጨረሻ ድረስ የተጻፈው ርኅራኄ ከተደረገልን፥ ከሰውነታችን ያነሰውን ነገር መስጠት ከቶ አይገባንም፤ እግዚአብሔርንም ደስ ልናሰኝ ብንወድ ከዚህ የበለጠ ለመስጠት አንችልም።

«ልጄ ሆይ፥ ልብህን ስጠኝ» እንደ ተባለው (ምሳ.23፡26) እግዚአብሔር ሰውነታችንን ይፈልጋል። ያን ርኅራኄ ተገንዝበን ከዚህ ያነሰውን መስጠት ነውር እንደ ሆነ ሁላችን እንረዳለንና ይህ ከአእምሮአችን ጋር የሚስማማ አገልግሎታችን ነው። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ይህ ነው። የሥጋ ሥርዓት መሥዋዕት ሳይሆን መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው። የሞተ ሳይሆን ሕያው ነው፤ ማለት፥ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርቦ ያለቀ ሳይሆን ዕለት ዕለት የሚታደስ መሥዋዕት ነው። ርኩስም ሳይሆን በክርስቶስ ደም የተቀደሰ ነው።

እላይ እንዳየነው ሁሉ የእግዚአብሔር አሳብና የሰው አሳብ ለየብቻው ነው፥ (ኢሳ.55፡8-9)። ዓለማዊ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ አይችልም። ደስ የሚያሰኘው ይህ ነገር እንደሆነ ሲመስለው በእርግጥ የሚፈልገው ፈጽሞ ሌላ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናውቅ ዘንድ ብንወድ፥ ይህን ዓለም ሳንመስልና ከእርሱ ጋር ሳንስማማ፥ መለወጥ ያስፈልገናል። ይህን ዓለም ሳንመስል ተለውጠን ክርስቶስን እንንድንመስል ማለት ነው። ክርስቶስንም የምንመስልበት በአረማመዳችን ሁሉ፥ ሰውነታችንን መሥዋዕት አድርገን በማቅረብ (ቍ.1)፥ ትሑታን በመሆን (ቍ.3)፥ ፍቅራችን ያለ ግብዝነት በመሆን (ቍ.9)፥ በመንፈሳችን በመቃጠል (ቍ.11)፥ እንደ ተቻለን መጠን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም በመኖር

(ቍ.18)፥ ራሳችን ባለመበቀል (ቍ.19)፥ ክፉን በመልካም በማሸነፍ (ቍ.21) ነው።

ታዲያ፥ እንደምን እንለወጣለን? «በልባችን (በአእምሮአችን) መታደስ» ይላል፥ (ቍ.2።) ይህስ እንደምን ይሆናል? በመንፈስ ቅዱስ ይሆናል፥ (2ኛቆሮ.3፡18)። ያደረብንን መንፈስ ቅዱስ የሰውነታችንን ገዥ አድርገን ለእርሱ በሁሉ ስንታዘዝ እርሱ ልባችንን (አእምሮአችንን) ያድሳል፥ የእግዚአብሔርንም እውነተኛ ፈቃድ እናውቃለን።

ማስገንዘቢያ፦ እኛ ክርስቲያኖች ስለ ምግባር (ስለ መልካም ሥራ) ነገር፥ እግዚአብሔርም ከእኛ ዘንድ ስለሚፈልገው ነገር፥ አእምሮአችንን በእውነት ማስፋፋት ይገባናል። ምግባር፥ እግዚአብሔር የሚፈልገውም፥ አንዳንድ ሳንቲም ለድሆች መጣልን ነውን? ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን በር ደርሰን ቅጥሩን መሳም ነውን? ይህን ያህል ሰዓት በጸሎት፥ ወይም ይህን ያህል ቀን በጦም ማሳለፍ ነውን? ወይም ደግሞ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን መፈጸም፤ ይህ ብቻ ነውን? ይህ ሁሉ መልካም፥ ለክርስቲያን የተገባም ሲሆን፥ እግዚአብሔር የሚፈልገው ከዚህ ሁሉ የበለጠ ነገር አይደለምን? አዎን፤ ከዚህ ሁሉ የበለጠ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው የእኛን ሳይሆን እኛን ራሳችንን ነው፥ ያውም ሁለመናችንን ነው። ይህንም መስጠት እንደሚገባን አይተናል። እርሱ ለእኛ ራሱን ከሰጠ፥ እኛ ከዚህ (ከሰውነታችን) ያነሰውን ልንሰጠው ይገባናልን? ከቶ አይገባንም።

ቍ.3-8፦ ሰውነቱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበ ሰው ከሌሎች ሁሉ ይልቅ ትሑት መሆን ይገባዋል። የነበረውን ለእግዚአብሔር አስረክቦአልና አሁን ያለው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ስጦታ ነው እንጂ የራሱ አይደለም። ያለው ሙያ ሁሉ የተሰጠው ጸጋ ነውና ሊኩራበት አይችልም። አንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉ እንዲሁ እኛ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች ነን። እንደዚሁም ደግሞ የአካል ብልቶች ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁ የእኛ ሥራ (ሙያ፥ ስጦታ) ልዩ ልዩ ነው እንጂ አንድ አይደለም። ከየብልቱ ሁሉ ዘንድ የተፈለገው የሌሎችን ሙያ ወይም ሥራ እንዲመለከት ሳይሆን የራሱን እንዲያሳምርና የአካሉን ስልት (ኅብረት) እንዲጠብቅ ነው፥ (ዮሐ.21፡21-22፤ 2ኛቆሮ.12፡13)። የትንቢት (የስብከት) ስጦታ የተሰጠው ሰው በተሰጠው መጠን (ማቴ.25፡15) በጥበብና በትጋት ይናገር። አገልግሎት፥ ማስተማር፥ መምከር፥ መስጠት፥ መግዛት፥ መማርም የተሰጠው ሰው ሁሉ በተሰጠው ስጦታ ይትጋ። ያ ስጦታ ማንኛውም ቢሆን ያን የእግዚአብሔርን ርኅራኄ አስተውሎ ማሰብ ከሚገባ አልፎ፥ በትዕቢት፥ ማሰብ አይገባውም።

ማስገንዘቢያ፦ ይህ የአካልና የብልቶች ምሳሌ ዓይነተኛ የጳውሎስ ትምህርት ሆኖ ደግሞ በ1ኛቆሮ. 12፡12-27፤ በኤፌ.4፡15-16 እና በቈላ.1፡18 ይገኛል። በኤፌሶንና በቈላስይስ ግን ክርስቶስ አካል ሳይሆን ራስ ነው።

ሐዋርያው በተለይ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥራ እንደሚናገር ይመስላል። ለምሳሌ፥ «ትንቢት» የተባለው (ቍ.6) የወደፊትን ነገር መናገር ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ሁሉ የሚደረገው የወንጌል ስብከት ማለት ነውና (1ኛቆሮ.14፡1-5) የቄስን ሥራ ያመለክታል፥ እንዲሁም ደግሞ «አገልግሎት» የተባለው (ቍ.7) የዲያቆንን ሥራ ያመለክታል። (የሐዋ.6፡1-6)። «ማስተማር» የመምህር ሥራ ነው። «መምከር» ደግሞ (ቍ.8) የነፍስ አባት ሥራ ነው። «መስጠት» የምእመናን ሥራ ቢሆን (1ኛኛቆሮ.9፡11)። «መግዛት» (ማስተዳደር) የአለቃ ሥራ ነው፤ «መማር» ደግሞ በሽተኞችን የሚጠይቀው ሰው ሥራ ነው። እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን (ወይም የክርስቲያኖች ማኅበር) አገልጋዮች እያንዳንዳቸው በተሰጣቸው ሙያ ይትጉ። ይሁን እንጂ፥ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሁሉ አንዳችን ስጦታ ተሰጥቶታል እና (ኤፌ.4፡7) ሁላችን በተሰጠን ስጦታ ሳንኩራ፥ በመጨረሻ ቀን የጌታችንን ምስጋና እንቀበል ዘንድ እያንዳንዳችን እንትጋ፥ (ማቴ.25፡21-23)።

ቍ.9-10፡- በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ «ፍቅርን» የሚያመለክቱ በግሪክ ቋንቋ በአማርኛም ሁለት ቃሎች አሉ፤ አንዱ «ፍቅር» (ቍ.9)፥ አንዱም «መዋደድ» (ቍ.10) ነው። መጀመሪያው ቃል እግዚአብሔር የሚያፈቅርበትን ከፍ ያለውን ዓይነት ፍቅር ያመለክታል፤ ሁለተኛውም ደግሞ ሰው የሚያፈቅርበትን ዓይነት ያመለክታል። እነዚህ ቃሎች በዮሐ.21፡15-17 እየተፈራረቁ የተሠሩባቸው ናቸው። ጌታ «ታፈቅረኛለህን?» ብሎ ጴጥሮስን ቢጠይቀው፥ ጴጥሮስ ያን ቃል ሳይደፍር «እወድሃለሁ» ብሎ መለሰለት። አሁን ግን እዚህ በቍ.9 ላይ «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን» ተባለ፤ ይህም እግዚአብሔርን የምናፈቅርበትን ፍቅር ያመለክታል። ለእግዚአብሔር የሚሆን ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ቢሆን ምልክቱ፥ ክፉን ነገር ትጸየፉላችሁ ከበጎም ነገር ጋር ትተባበራላችሁ፤ «እግዚአብሔርን እናፈቅራለን» የሚሉ ሰዎች ሞልተዋል፤ እነዚህን ሁለት ምልክቶች ግን ባያሳዩ ፍቅራቸው የግብዝነት እንደሆነ ተገልጦአል። እግዚአብሔርን የምናፈቅርበት ፍቅር ያለ ግብዝነት ይሁን፤ እርሱ ክፉን አይወድም እና ክፉን ነገር እንጸየፍ፥ እርሱ በጎን ነገር ይወዳልና ከበጎ ነገር ጋር እንተባበር።

«በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» ይላል ደግሞ። ክርስቲያኖች ሁሉ የአንድ አባት ልጆች ናቸውና ወንድማማችና ቤተሰቦች ናቸው፥ (ዕብ.2፡10-11)። እንግዲህ በወንድማማች መዋደድ ይዋደዱ። ክርስቲያን የሆነ ሰው ሌላን ክርስቲያን ሁሉ እንደ ወንድሙ ይየው።

ሁለተኛ «ተከባበሩ»። ማን ነው ወንድሙን የሚያማ? የወንድሙንስ በደል ወይንም ውርደት የሚያወራ? የወንድሙ ውርደት የራሱ ውርደት ነውና ከቶ አያወራም (1ኛጴጥ.4፡8)። ዳሩ ግን ደግሞ የወንድሙ ክብር የራሱ ክብር ነውና በወንድሙ ክብር የማይሳተፍ ማን ነው? «ወንድሜ ነው እኮ!» እያለ በኩራት

ይናገርና የወንድሙን ክብር ያወራ የለምን? እንዲሁ ክርስቲያኖች ሁሉ እርስ በርሳቸው ይከባበሩ። እያንዳንዱ ክርስቲያን ሁሉ የወንድሙ የክብር ዘበኛ ነው።

ቊ.11፡- የዓለም ነጋዴዎች በሥራቸው የተጉ ናቸው እንጂ ከቶ አይለግሙም። እንዲሁም ክርስቲያን በመንፈሳዊ ተግበሩ የተጋ የጋለም፥ በመንፈሳዊ ቅንዓቱ የተንበገበገ ይሁን እንጂ ልግመኛ አይሁን። መንፈሳዊ ተግባራቸውንና አገልግሎታቸውን በሚፈጽሙ ዓይነት ዓለማዊ ሥራቸውን ለመፈጸም ከቶ የማይወዱ ብዙዎች ክርስቲያኖች አሉ። በዓለማዊ ሥራቸው ትጉዎች ሲሆኑ በመንፈሳዊ ሥራቸው ልግመኞች ናቸው። በዓለማዊ ሥራ በምንተጋበትና በምንቃጠልበት መጠን በዚያ ልክ፥ ሲሆንም በበለጠ ሁኔታ፥ በመንፈሳዊ ሥራችን እንትጋ። ጌታችንን ምሳሌአችን አድርገን «በአባቴ በሚሆነው እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አታውቁምን?» ብሎ የተናገረው ቃል (ሉቃ.2፡49)፥ ደግሞ «የእኔ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው» ብሎ የተናገረው ቃል (ዮሐ.4፡34) የእኛም ስሜት ይሁን።

ቊ.12፡- በኋላ፥ በቊ.13፥ ለማኅበርተኞች (ለክርስቲያኖች) የምናደርጋቸው ሁለት ነገሮች እንደምናገኝ፥ እንዲሁ እዚህ በቊ. 12 ላይ በውጭ ባሉት፥ በዓለም ሰዎችና በጠላቶች፥ መካከል ሳለን የምናደርጋቸው ሦስት ነገሮች እናገኛለን። እነዚህም፡- 1ኛ. በተስፋ ደስ እንዲለን። 2ኛ. በመከራ እንድንታገሥ። 3ኛ. በጸሎት እንድንጸና ናቸው። ተስፋው ምን እንደሆነ በምዕ.8፡16-25 አይተናል፤ ወደዚያም ተስፋ እንዳንደርስ ሊከለክለን የሚችል እንደሌለ ተረድተናል፥ (8፡31-39) የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን ሳለን በዚህ በሰይጣን ግዛት ውስጥ ስንኖር ዓለም እንደሚጠላንና መከራ እንደሚያገኘን የታወቀ ነገር ነው፥ (1ኛዮሐ.4፡4-6፤ ገላ.4፡29፤ 2ኛጢሞ.3፡12፤ ዮሐ.15፡18-21)። ይሁን እንጂ ተስፋውን ተመልክተን ደስ ይበለን፥ በፊታችን ስላለው ደስታ በመከራ እንታገሥ (ዕብ.12፡2)፥ በጸሎትም እንጽና። ጸሎት ተስፋውን ቀስቅሶ ብርታትን ይሰጠናል። መከራ ሲደርስብን እነዚህን ሦስት ነገሮች እናስብ።

ቊ.13፡- አሁንም ደግሞ በማኅበርተኞች (በቤተ ክርስቲያን ሰዎች) ወይም በክርስቲያን ወንድሞቻችን ዘንድ ማድረግ የሚገባንን ሁለት ነገሮች እናገኛለን። 1ኛ. በሚያስፈልጋቸው እንድንረዳቸው፥ 2ኛ. ከአገር ወደ አገር የሚዘዋወሩትን እንድንቀበል፥ («ቅዱሳን» የተባሉት መቸም ክርስቲያኖች፥ የእግዚአብሔር ወገኖች፥ ናቸው፥ ሮሜ 15፡25-26፤ 16፡1፤ 1ኛቆሮ.1፡2፤ 6፡1-2፤ 16፡1፤15)። ወንድሞችንም በችግራቸው ለመርዳት (የሐዋ.11፡27-30) እና የሚዘዋወሩትን ለማስተናገድ (3ኛዮሐ.ቊ.5-8) ለክርስቲያን ሁሉ የተሰጠ አደራ ነው።

ቍ.14፡- ሰው ሲሰድበን ወይም ሲያሳድደን ለእኛ ለክርስቲያኖች የሚሆን መልካም ልማድ እነሆ! (ሉቃ.23፡34 ተመልከት)። በመቈጣት ወይም በመማረር ፈንታ እንመርቅ! ለሚሰድቡን ሁሉ ወዲያውኑ፥ ምንም ሳንቆይ፥ መጸለይ እንልመድ! ይህን ብናደርግ በሕይወታችን ታላቅ ልዩነት ይደረጋል።

ቍ.15፡- እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰው፥ ይልቁንም ለእግዚአብሔር እጅግ የተለየ ሲሆን፥ ከዚህ ዓለም ደስታና ኀዘን ጋር አለመስማማት እንደምን ያለ ቀላል ነገር ነው! ዓለምንና የዓለምን ነገር ከዱአልና አሁን ይንቀዋል። ብቻውን በቅድስናው ይመላለሳልና አንድ ደስ የሚለው ሰው ደስታውን ለማካፈል፥ ወይም ኃዘንተኛ የሆነ ሰው መጽናናትን ለማግኘት፥ ወደ እርሱ ዘንድ፥ አይመጣም። አሳቡ ሁሉ በመንግሥት ሰማያት ነገር ሲሆን ለዚህ ዓለም፥ ለደስታው ወይም ለኀዘኑ፥ ልብ ያለው አይመስልም።

እንደዚህ ያሉ ክርስቲያኖች አሉ፤ ጨካኞች ናቸው፤ ያስፈራሉ እንጂ አያስጠጉም። ጌታ ግን እንደዚህ አልነበረም። ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ ተጻፈ፡- «በመከራቸው ሁሉ ጨነቀው» (ኢሳ.63፡9) በድካማችንም ሊራራልን እንደሚችል እናውቃለን፥ (ዕብ.4፡15)። ሕጻናት ወደ እርሱ ዘንድ ይሮጡ በአጠገቡም ይደሰቱ ነበር፥ ኃጢአተኛ ሴቶችም መጸጸታቸውን በእግሮቹ ላይ አፈሰሱ፥ በሠርግ ቤት ከሠርገኞች ጋር ተቀመጠ፥ የኀዘንተኞችን ኀዘን ተካፈለ፥ (ማር.9፡36፤ ሉቃ.7፡37-38፤ ዮሐ.2፡1-2፤ ዮሐ.11፡33-35)። የክርስቶስ ፍቅር ካደረብን እርሱን መስለን «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይለናል፥ ከሚያለቅሱም ጋር እናለቅሳለን።

ቍ.16፡- በሰው ሁሉ ዘንድ በተወደዱትና በታላላቆች በትዕቢተኞችም ተስቦ መወሰድ እንደምን ያለ ቀላል ነገር ነው! ሐዋርያው በምዕ.1፡16 ላይ «አላፍርም» ብሎ እንደተነገረው ነገር ነው። በአብዛኛው ጊዜ ክርስቲያኖች ሞኞች፥ ደካሞች፥ ምናምንቴዎችም ሆነው ይታያሉና ከእነርሱ ጋር መዛመድ ያሳፍራል፥ (1ኛቆሮ.1፡26-29)። ሰው ሁሉ በተፈጥሮው ዓለም ከሚወዳቸውና ከታላላቆች ከትዕቢተኞችም ጋር ለመሆን ይመርጣል። ይሁን እንጂ፥ ክርስቲያን ጌታውን አስቦ እንዲህ አያድርግ። ጌታ ከድሆች ተወለደ፥ ከተዋረዱትም ጋር ተቀመጠ። መጽሐፍ ቅዱስም በልዩ ልዩ ቦታ የትዕቢትን ነገር እንዳናስብ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት እንድንተጋ ያሳስበናል፡- መዝ.1፡1-6፤ ያዕ.2፡1-9። የጌታ ደቀ መዝሙር በትሑታንና በትሕትና ደስታውን እያየ «ለራስህ ተቀመጥ፥ ወደ እኔ አትቅረብ። እኔ ከአንተ ይልቅ ቅዱስ ነኝና» ከሚል አሳብ ርቆ (ኢሳ.65፡5) ራሱ ልባም የሆነ አይምሰለው። «አገዳው ባዶ ሲሆን ቀጥ ብሎ ይቆማል፤ እሸት ከያዘ ግን ራሱን ይደፋል» የሚል ምሳሌ አለ!

ቍ.17፡- ቅዱስ ጳውሎስ አሁን ቶሎ ቶሎ ስለሚናገር ጸሐፊው ሁሉን ለመጻፍ ተጨንቆአል፥ (ቍ.16-22።) ሐዋርያው የእግዚአብሔርን ርኅራኄ በዓይነ ልቡናው ያያል፥ ያንም አይቶ ክርስቲያን ሁሉ ፍጹም እንዲሆን ይመኛል። ሁለመናው መልካም ይሁን እንጂ ከቶ ክፉ አይገኝበት። የመልካም እንጂ የክፉ ምንጭ አይሁን። ሰውን የሚጎዳ ነገር ከክርስቲያን ዘንድ አይውጣ። ቢበደል እንኳ አይበድል፥ (1ኛቆሮ.6፡7፤ መዝ.68፡4-5)። ወንድሞቻችንን የምናሰናክልበት ብዙ ነገር አለ። ልማዳችን፥ ወይም ጨዋታችን፥ ወይም የገንዘብ አወጣጣችን፥ ሌላም ልዩ ልዩ አድራጎታችን፥ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በእነዚህ ነገሮች እየተጠነቀቅን የምናደርገው ነገር ሁሉ ለሌሎች መልካም እንዲሆን እንጂ ማሰናከያ እንዳይሆንባቸው እናስብ።

ቍ.18 አንዳንዶች ሰዎች መጨቃጨቅና መከራከር ዓይነተኛ የምእመን ምልክት እንደሆነ ያስባሉ። ይህ ግን አይደለም። ሁልጊዜ በግጭት መኖር የዲያብሎስን እንጂ የክርስቶስን መንፈስ አይገልጥም። በሰላም መኖር ተገቢ የሆነ የክርስቲያን አንዋንዋር ነው፥ (ዮሐ.14፡27፤ ገላ.5፡22)። ይሁን እንጂ፥ አንዳንድ ጊዜ የማይቻል ነገር ነውና ሐዋርያው «ቢቻላችሁ» ይላል። እንታረቅ ስትሉ ያ ባላጋራችሁ እንቢ ቢል አይቻላችሁምና። ሐዋርያው ግን «በእናንተ በኩል» ይላል። ይህም ማለት፥ ምን ጊዜም ቢሆን እናንተ በእናንተ በኩል «እንታረቅ» ማለት አለባችሁ ማለት ነው። ክርስቲያን ሰላምን ለማድረግ ሁልጊዜ ዝግጁ ይሁን።

በሰላም ልንኖር የማንችልበት ጊዜ ደግሞ ይነሣ ይሆናል። ሰው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ክፉ ቢናገር፥ ወይም የማይገባ ሥራ ቢሠራ፥ መገሠጽና መቈጣት አስፈላጊና ተገቢ ይሆናል፥ (ማቴ.23፡23-36፤ ዮሐ.2፡14-16)። በሰላም መኖር የማንችልበትና የማይገባን ጊዜ አለ፤ ነገር ግን «ቢቻለን» በሰላም ለመኖር ታዘዝን።

ቍ.19-21፡- እርስ በርሳችን በሰላም እንድንኖር አዝዞን ነበር፥ (ቍ.18።) አሁንም «በዚያ በባላጋራችሁ ራሳችሁ አትበቀሉ» ይላል፤ ምክንያቱም፥ በቀል የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ ጉዳይ ባለመሆኑ ነው። «አትበቀሉ፤ ዳሩ ግን ቍጣን አኑራችሁ (አስቀርታችሁ) ባለጋራችሁን በቸርነት አሸንፉ» ይላል። የቅዱሳን በቀል ባላጋራውን ወንድም ማድረግ ነው።

በቍ.20 ላይ «የእሳት ፍም» ስለሚለው፥ የእሳት ፍምም ክፉ ነገር ስለሚመስል፥ አንዳንድ ሰዎች «መልካም ብታደርጉለት ፍርዱ የባሰ ይሆናልና ይህ እንዲሆን፡- በሉ! መልካም አድርጉለት!» ይላሉ። ይህ ግን ከክርስቶስ መንፈስ የራቀ ነው፥ ከቍ.21ም ጋር ደግሞ አይስማማም። የለም፥ ቍ.21 «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ» ይላል። ቍ.20 ደግሞ ይህን እንዴት ልናደርግ እንደምንችል ያስተምረናል።

ይህን ክፍል የሚፈታ የብረት ምሳሌ ነው። ያ ጠላትህ ጠንካራ ብረትን መስሎ፥ ብርዳም፥ ጨካኝ፥ የማይታጠፍ፥ ይሆን ይሆናል። ብረት ይመስላልና ከዚያ ሰው ጋር መታገልህ ሁሉ ከንቱ ነው። እሺ አይልህም! ምን ይሻላል? ለዚያ ብረት የእሳትን ፍም አቅርበህ በላዩ ላይ መከመር ነዋ! ብረቱ አስቀድሞ ይሞቃል፥ ቀጥሎም ይግላል፥ ቀጥሎም ደግሞ ይላላል፥ እንደ ወደድህም እያጠፍኸው ፈቃድህን ሁሉ ታስፈጽመዋለህ!

እንደዚህም ሁሉ ለጠላትህ መልካምን ቸርነትንም ሁሉ አቅርብ። «አብላው፥ አጠጣው» እንደተባለ (ምሳ.25፡21-22) ልታገለግለው እና ልትጠቅመው ምቹ ጊዜአትን ፈልግ። ይህን በማድረግ ቀጥል እንጂ አትድከም። ቀስ በቀስ ልቡ ይሞቃል፥ ሊወድህም ይጀምራል፥ ፈቃዱ ይለሰልሳል፥ ትምህርትህን ለማዳመጥ ይፈቅዳል፥ በመንገድህ ለመሄድ እሺ ይላል፥ የወንጌልም ጓደኛህ ይሆናል። ይኸውልህ ተበቀልህ! ክፋውን በመልካም አሸንፈሃል።

* * *

# ምዕራፍ 13

1. ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። 2. ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። 3. ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ተወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ 4. ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። 5. ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው። 6. ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፤ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና። 7. ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።

8. እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና። 9. አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል። 10. ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።

11. ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን ዕወቁ፤ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና። 12. ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ። 13. በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ 14. ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

የክርስቲያንን ኑሮ በእግዚአብሔር ዘንድ በምዕ.12 ላይ አይተናል። አሁን ያ ኑሮ ወይም መመላለስ በመንግሥት ዘንድ እንዴት እንደ ሆነ እናያለን። ክርስቲያን ከዓለም አይደለም፥ አገሩም በሰማይ ነው፥ የሚያገለግለውም ንጉሥ ክርስቶስ ነው፥ (ዮሐ.15፡19፤ 17፡14፥16፤ ፊልጵ.3፡20፤ ቈላ.3፡24)። ቢሆንም ቅሉ፥ ደግሞ ምናልባት የኢትዮጵያ ዜጋ የአሁኑን መንግሥትም አገልጋይ ይሆን ይሆናል። የክርስቲያኑ አላፊነት ለመንግሥተ ሰማያትና ለክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ደግሞ ለኢትዮጵያ መንግሥት፥ ለአስተዳዳሪዎችዋና ለሕዝብዋም፥ ነው። መዳን በቂ አይደለም፤ አሁን የአንድ አገር ተወላጆች ስንሆን ታማኝ ዜጋ ምን ማለት እንደሆነ በሕይወታችን ማሳየት ይገባናል።

ቍ.1-7፡- ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነውና የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ክርስቲያን ከሌላ ሰው ሁሉ ይልቅ የመንግሥትና የአስተዳዳሪ የባለ ሥልጣንም አክባሪና ታማኝ አገልጋይ መሆን ይገባዋል፥ (1ኛጴጥ.2፡13-17)፥ ባለ ሥልጣኖች በዚህ ክፍል ላይ ምን እንደተባሉ ልብ እናድርግ። «በእግዚአብሔር የተሾሙ» ናቸው (ቍ.1)፣ ደግሞ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች» ናቸው፥ (ቍ.4 እና 6።) ባለ ሥልጣንን የሚቃወም «የእግዚአብሔርን ሥርዓት» ይቃወማል ተብሎአል፥ (ቍ.2)። ስለዚህ ክርስቲያን ሁሉ ለበላዮቹ ይታዘዝ ዘንድ ተገቢ ነው። አስተዳዳሪው ራሱ የተቃወመ እንደሆነ በራሱ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይቀበላል።

እውነት ነው፥ አንዳንዶች ባለ ሥልጣኖች እግዚአብሔር የወደደውን ሥርዓት አይከተሉምና እንደ አሳቡ አይደሉም። ለመልካም ነገር ለእኛ ቢሾሙ (ቍ.4) ክፉን ነገር ይሠራሉ። ይሁን እንጂ፥ የእነርሱ ክፋት እኛ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ለመቃወም ምክንያት አይሰጠንም። የምንመለከተው ሰውዮን ሳይሆን ወንበሩን ነው። ባለ ሥልጣኑ ሥልጣኑን ምንም ቢያበላሽ ሥልጣኑ ገና የእግዚአብሔር ነውና ልንገዛለት ይገባናል። እርሱ (ባለ ሥልጣኑ) እንደሚገባ ባለመሆኑ ምክንያት እኛ ወንበሩን መናቅ ወይም መቃወም አያስፈልገንም። ጳውሎስ ይህን ትእዛዝ በጻፈበት ዘመን የአገሩ ባለ ሥልጣኖች ማንና ማን እንደ ነበሩ ማሰብ ነው። እነጳንጤናዊው ጲላጦስ፥ እነሄሮድስና እነኔሮን ቄሣር ነበሩ! ቢሆንም፥ ሐዋርያው ልዩነትን ሳያደርግ «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ» ብሎ አዘዘ።

ይሁን እንጂ፥ «ለመልካም ነገር የእግዚአብሔር አገልጋይ» እንዲሆን ተሹሞ ሳለ በክፋት የእግዚአብሔር ባላጋራ ሆኖ ሲገኝ ምን ይሻላል? ሐዋርያው ክርስቲያኖች ለሮማ መንግሥት ተገዝተው ለመንግሥት ጣዖታት ይሠዉ ዘንድ ከቶ አላሰበም (ዳን.3፡14-18)። «የእግዚአብሔር አገልጋይ» ነውና ተገዙለት! «የእግዚአብሔር

አገልጋይ» ነውና እግዚአብሔርን የሚበድል ከሆነ ወንበሩን የእግዚአብሔርንም ሥርዓት በድሎአልና በእግዚአብሔር ነገር ልንገዛለት አልተገደድንም፥ (ማቴ.22፡15-21፤ የሐዋ.4፡18-20፤ 5፡28-29፤ 40-42።) ይሁንና ክርስቲያን በባለ ሥልጣን ወይም በመንግሥት ላይ ሰይፍን ማንሣት ከቶ አያምርም፤ ካለ አንዳንድ ጊዜ በቀር በዓለም ታሪክ ውስጥ በእንደዚህ ያለ ነገር የእግዚአብሔር በረከት አርፎ አያውቅም፥ (ማቴ.26፡52)። ክርስቲያን ለመገዛት ለመታዘዝም ተጠርቶአል። ከባለ ሥልጣን ወይም ከመንግሥት ጋር የተጣላበት ነገር የክርስቲያኑን ሕሊና የሚነካ ነገር ከሆነ፥ ክርስቲያኑ በመንፈሳዊ መሣሪያ ይዋጋ እንጂ የእግዚአብሔርን ሥርዓት እየተቃወመ በሥጋዊ መሣሪያ፥ በጠመንጃና በዓመፅ ቢዋጋ ደግ አይደለም። መንፈሳዊ የሆነ የክርስቲያን መሣሪያ ምንድር ነው? ቢሉ፥ በተለይ ጸሎት፥ ቀጥሎም መታገሥና መቻል፥ ቢያስፈልግም መሞት ነው፥ (2ኛቆሮ.10፡3-5፤ ማቴ.10፡28)።

ስለዚህ የምንገዛ ሥጋዊ ፍርሃት ስለምንፈራቸው ብቻ ሳይሆን በዓይናችን ለእኛ የሚሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለሆኑ ነው። (1ኛሳሙ.24፡3-7፤ 26፡7-16)። ሌላ ሰው የፈቀደውን ይናገር የፈቀደውንም ያድርግ፥ ክርስቲያን ግን በትሕትና በአክብሮትም ሁሉ ይገዛ።

የምንገብርበት ደግሞ ስለዚህ ነው። ከእኛ ዘንድ ግብር ወይም ቀረጥ የሚቀበለውን ሰው፥ እርሱ ምንም የመንግሥታችን ሠራተኛ ቢሆንም ብዙ ጊዜ በመጥፎ ዓይን እናየዋለን ከእጁም ለማምለጥ ልዩ ልዩ ዘዴን እንፈጥራለን። በዚህ ክፍል ላይ ግን በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆነው እንድናያቸውና የተገባውን ሁሉ እንድናስረክባቸው ታዝዞአል። ግብር ከየዓይነቱ ቀረጥም ከየዓይነቱ እንድንከፍል ባለ ሥልጣናችንም እንድንፈራና እንድናከብር ታዝዘናል። ሥርዓቱም ገንዘቡም የእግዚአብሔር ነውና ክርስቲያን፥ የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ገና እያየ፥ የተገባውን ሁሉ፥ ያውም በሙሉ፥ ለመክፈል ይጣደፍ። ክርስቲያን በመክፈል መጀመሪያ መሆን ይገባዋልና እግዚአብሔርን የማያፈቅረው ሰው እንዳይቀድመው ይጠንቀቅ! መክፈል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና አለመክፈል ኃጢአትን መሥራት ነው፥ መንግሥትንም መበደል ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መበደል ነው። የተገባውን ባልከፈለው ሰው ላይ የእግዚአብሔር በረከት አያርፍምና መንገዱ ይቀናለት ዘንድ የሚወድ በቶሎ ይክፈል። እንግዲህ ከመንግሥት ግብርና ቀረጥ ለማምለጥ ከእንግዲህ ወዲህ ዘዴን አንፍጠር፥ ልዩ ልዩን ነገር በመደበቅ ከሚገባ አንዳችን ለማስቀረት አንሞክር፥ ባለ ሥልጣኑን በአእምሮአችን እንድፈር፥ የሚገባውንም ክብር አንርሳ። ይህ ነገር ሁሉ የክርስቲያኑን ሕይወት ይነካል። የክርስቲያን ኑሮ በመንግሥት ዘንድ እንደዚህ ያለ ሁሉ ነው።

ቊ.8-10፡- አስፈላጊውን ለመንግሥት ብቻ ሳንከፍል የተገባንን ለባልንጀራ ደግሞ ብንከፍል እውነተኛ የክርስቲያንን ኑሮ እናሳያለን። ከፍሉ እንጂ ዕዳ አይኑርባችሁ ብሎ ሐዋርያው ይመክረናል።

ዕዳ ክፉ ነገር ነው። ዕዳ ውስጥ መግባት በሰይጣን ወጥመድ መግባት ነው፤ ዕዳ ውስጥም ማስገባት ባልንጀራን በዚያ ወጥመድ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው። ዕዳ ወደ ኃፍረትና ወደ ውርደት፥ ወደ ችግርና ወደ ባርነት፥ ያደርሳል። ዕዳ ወንድም ከወንድሙ ይለያል፥ ወደ መጣላት ወደ መስረቅና ነፍስ ወደ መግደል እንኳ ያደርሳል።

ክፉ ብቻ ሳይሆን ነውርም ነው። ለክርስቲያንም አስፈላጊ አይደለም፤ በሁለተኛ መወለድ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሰው የፈለገውን ለማግኘት ብሎ ወደሚወደው አባት፥ እርሱም ሁሉን ወደሚችል አምላክ ዘንድ በመሄድ ፈንታ፥ እንደዚህ ያለ ዝምድናና ችሎታ ወደሌለው፥ ኃጢአተኛ ወደሆነው ሰው ዘንድ ቢሄድ፥ ደግ ነውን? ደግመይደል! ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልገውም ያገኛል፤ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል»፤ ደግሞ «በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» ብሎ ተስፋ ከሰጠን (ማቴ.7፡7-8፤ ዮሐ.14፡13-14) ለመበደር ወደ ሰው ዘንድ መሮጥ ምን ያሻናል? ከአባታችን ይበልጥ ሊሰጥ የሚችልና ከእርሱም ይልቅ የሚወደን አለን? እንግዳን ከመጠየቅ ይልቅ አባትን መጠየቅ አይገባምን? ከሰው ዘንድ በምንበደርበት ቍጥር አባታችንን እግዚአብሔርን እናሳፍራለን። ከሰው ዘንድ አንበደር፤ ባልንጀራችንንም ብንወድ ለእርሱ በማበደር በወጥመድ አናስገባው። ከማበደር ይልቅ እንዲያው መስጠት እጅግ የተሻለ ነው። ከዚህ ክፉ የሆነ የዕዳ ቀምበር ክርስቲያን ሁሉ ራሱን ይጠብቅ!

ሐዋርያው «ዕዳ አይኑርባችሁ... እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር» ይላል። «ዕዳ» የተባለው የገንዘብ ዕዳ ብቻ አይደለም። ከገንዘብ ዕዳ በስተቀር ሌላ ዕዳ ደግሞ አለ። ጳውሎስ ራሱ «ዕዳ አለብኝ» ብሎአል (1፡10፤ 15)፥ ያን ዕዳ ግን ለመክፈል ችኩሎ ይህን መልእክት ጻፈ። የነበረበት ዕዳ ወንጌልን ለማስተማር ነበረ። ሌላም ዕዳ አለ፥ እርሱም እርስ በርሳችን መዋደድነው፥ (ደግሞ ምዕ.8፡12ን ተመልከት)። ለመንግሥትና ለሰው ሁሉ የሚገባውን ለማስረከብ ዕዳ ሲኖርብን (ቊ.7) እንዲሁ ለሰው ደግሞ የፍቅርን ዕዳ መክፈል አለብን። ለመንግሥት ብንገዛ መንግሥትን አንበድልም፤ እንደዚሁም ባልንጀራችንን እንደ ነፍሳችን ብንወድ ሰውን አንበድልም። ባልንጀራችንን እንወድ እንደሆነ አናመነዝርም፥ አንገድልም፥ አንሰርቅም፥ በውሸት አንመሰክርምና አንመኝም። ፍቅር እንግዲህ ሕግን ሁሉ ያስፈጽማል። ለመንግሥት የሚገባውን ብናስረክብ (ቊ. 7)፥ ለባልንጀራችንም የፍቅርን ዕዳ ብንከፍል (ቊ.8)፥ ታማኝ ዜጋ ምን ማለት እንደሆነ እናሳያለን።

ቍ.11-14፡- ሐዋርያው ይህን ትእዛዝ ሁሉ የሰጠበትን ምክንያት አሁን ይገልጣል። ምክንያቱ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡- መንግሥትንና ባልንጀራችንን ለማታለል ወራቱ ስላይደለ ነው። ሙሉ መዳናችንን የምንቀበልበት ያ የክርስቶስ የመምጣቱ ቀን የቀረበ ነውና ከእንቅልፍ ተነሥተን መታጠቅ ያስፈልገናል፥ (ማቴ.25፡5-6)። ክርስቶስ በዓለም የሌለበት ሰይጣንም የገዛበት ዘመን፥ «ሌሊት» የተባለው፥ አልፎአል፤ ክርስቶስም በደጅ ፊት ቆሞአል፥ (ያዕ.5፡9)። ሌሊት አልፎአል ቀንም ቀርቦአልና ከሌሊት ጋር የተስማማውን ልብስ (ሥራ ማለት) አውልቀን ከቀኑ ብርሃን ጋር የሚስማማውን ልብስ (ሥራ) እንልበስ። የምንለብሰው ልብስ ግን የተራ ሕዝብ ልብስ (ሲቪል) አይደለም፤ ነገር ግን የክርስቶስ ወታደሮች ነንና የምንለብሰው ልብስ ጋሻ ጦር ነው። የክርስቶስ ወታደሮች ሆነን ከቤት እንውጣ፥ እውጭም ስንደርስ መመላለሳችን (ኑሮአችን) በአገባብ ይሁን። ለዘፈንና ለስካር፥ ለዝሙትና ለመዳራት፥ ለክርክርና ለቅናት፥ ወራቱ ዛሬ አይደለም። እንደ ዕቃ ጦር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን እንልበስ፥ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አናስብ።

በሙሉ አእምሮአችን ክርስቶስን ዕቃ ጦራችንን አድርገን እንድንለብሰው ማለት ነው። ለዚህ ክፉ የመጨረሻ ዘመን የሚሆን የሚያድነንም ሌላ መሣሪያ የለም። ሌላው ሁሉ ከንቱ ነው። ክርስቶስ ራሱ ዕቃ ጦራችን ይሁን! አሳቡ መቸም ከምዕ. 6 እስከ ምዕ.8 ድረስ እንዳገኘነው ነው። በክርስቶስ እንታመናለን እንጂ እኛ ራሳችን አንቆጋም። እንዲሁም ክርስቶስን እንልበሰው። ጋሻ ጦራችን እርሱ ነውና።

ነገር ግን በዚህ ክፉ ዘመን ድልን ለማግኘት ይህ ብቻ፥ ማለት ክርስቶስን መልበስ ብቻ፥ አይበቃም። በአንድ ወገን ክርስቶስን መልበስ ሲሆን፥ በሌላ ወገን ደግሞ ምኞቱን እንዲፈጽም ለሥጋ አለማሰብ ነው። (ቍ.14።) እነዚህ ሁለት ነገሮች የተቈራኙ ናቸው። ምኞቱን እንዲፈጽም ለሥጋ ብናስብ ክርስቶስን ዕቃ ጦራችንን ማድረግ ከንቱ ነው። ክርስቶስ በእርሱ ወገን ያለውን ያደርግልናል፤ እኛ ግን በእኛ ወገን ያለውን ደግሞ ማድረግ ያስፈልገናል። ክርስቶስን መልበስ ለሥጋም አለማሰብ ሁለቱን መፈጸም አለብን። በሁለተኛው ያልተጠነቀቀ ሰው በመጀመሪያው እንደሚድን አያስብ። ሁለቱ ነገሮች ያስፈልጋሉ።

ማስገንዘቢያ፡- «ሕይወት ለሕይወት» በተባለው ታሪክ ውስጥ ታላቅ ወንድምዮው ከሞተለት በኋላ ታናሹ ወንድም የታላቁን ልብስ እየለበሰ ሲኖር የቀድሞ ጓደኞቹ መጥተው «እንጫወት» ቢሉት ታናሹ ወንድምዮው «ዛሬ የለበስሁትን ልብስ እንደለበስሁ እንደ ለበስሁ ከእናንተ ጋር መሄድ አስቸጋሪ ነው» ብሎ እንደ መለሰላቸው እንዲሁ የክርስቶስ የሆነ ሰው ክርስቶስን ይልበስ ይህንም ቢያደርግ የጨለማ ሥራዎች ሁለተኛ አያዩትም። ክርስቲያኖች ነን ስንል የመንግሥት ወታደር ከእኛ ልብስና መለዮ በለበሰው የመንግሥቱን ክብር መጠበቅ እንዳለበት እንዲሁ ክርስቶስን ለብሼአለሁ የሚል ሰው ሁሉ የክርስቶስ የክብር ጠባቂ (ዘበኛ) ነው።

እናቱ አለማቋረጥ ትጸልይለት የነበረ ነገር ግን የጉልምስናውን ዘመን ሁሉ በዘፈንና በመዳራት ያሳለፈውን የሂጶ (የሮማ አገር) አውጉስጢኖስ ወደ ክርስትና ሃይማኖት አድርሶ ፈተናን ለማሸነፍና የክርስቶስ ወታደር ለመሆን ያበቃው ይህ ክፍል ነው። በአንድ የአትክልት ሥፍራ ሆኖ ሳለ «አንሥተህ አንብብ!» የሚል ድምጽ ተሰማው። አስቀምጦት የነበረውን መጽሐፍ ቅዱስን ቢያነሣ ዓይኑ «በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፥ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ» በሚሉት ቃሎች ላይ አረፈ። «በዚያን ጊዜ ብርሃን ከሰማይ በራልኝ ጥርጥሬ ሁሉ ቀለጠ፥ ደኅንነትንም አገኘሁ» ብሎ ቅዱስ አውጉሥጥኖስ በኋላ መሰከረ።

በቁ.13 ላይ ስድስት ኃጢአቶች ተዘርዝረዋል። እነዚህ 6 ኃጢአቶች ሁለት ሁለት እየሆኑ በሦስት ዓይነት ኃጢአት ይመደባሉ፡-

1ኛ. «ዘፈንና ስካር» እላይ በቁ.11 እና 12 ላይ ዘመን ብሎ በቁ.13 ላይ የተጻፉት ኃጢአቶች የመጨረሻ ዘመን ኃጢአቶች ናቸው። እነዚህ «ዘፈንና ስካር» የተባሉት የዛሬው ዘመናችን ኃጢአቶች አይደሉም ብሎ በድፍረት የሚናገር ማን ነው? በእኛ ዘመን ያውም እንኳ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ዘፈንና ስካር በዝቶ የለምን? በራዲዮ በየቤታችን ሁሉ የምንሰማው አብዛኛውን ጊዜ ዘፈን አይደለምን? ወጣቶቻችንም የሚያመሹበት በዘፈንና በስካር አይደለምን? ዘመኑን እናስተውል። እነዚህ ራስን ባለመግዛት በግልጥ የሚሠሩ ኃጢአቶች ናቸው።

2ኛ. «ዝሙትና መዳራት» እነዚህ ደግሞ በአሁኑ ዘመናችን በዝተው የለምን? የጋለሞታዎችን ቤቶች ያላየ ማን ነው? እነዚህ እርኩስን ነገር በስውር የሚሰሩ (የግል) ኃጢአቶች ናቸው።

3ኛ. «ክርክርና ቅናት» ክርክር፥ ዓመፅ፥ ለአስተማሪውና ለባለ ሥልጣኑ አለመታዘዝ በዝቶ የለምን? ምቀኝነትስ? ታውቆ የለምን? እነዚህ የጠብ ማኅበራዊ ኃጢአቶች ናቸው።

ዘመኑን እንወቅ! ከእንቅልፋችን እንንቃ የጨለማውን ሥራ (ልብስ) እናውጣ! የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ! በአገባብ እንመላለስ። ይልቁንም ጌታን ኢየሱስ ክርስስቶስን እንልበስ። በደጅ ቆሞ ያንኳኳልና! (ራዕ.3፡20

* * *

# ምዕራፍ 14

1. በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት፥ በአሳቡም ላይ አትፍ ረዱ። 2. ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደተፈቀደለት የሚያምን አለ፥ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። 3. የሚበላ የማይበላውን አይ ናቀው። የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። 4. አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።

5. ይህ ሰው አንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል፥ ያ ግን ቀን ሁሉ አንድ እንደ ሆነ ያስባል፤ እያንዳንዱ በገዛ አእም ሮው አጥብቆ ይረዳ። 6. ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብ ራል የሚበላም እግዚአብሔርን ያመሰግናልና ለጌታ ብሎ ይበላል፤ የማይበላም ለጌታ ብሎ አይበላም እግዚአብሔርንም ያመሰግናል። 7. ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፥ ለራሱም የሚሞት የለም፤ 8. በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይ ወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። 9. ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያ ውም ሆኖአልና።

10. አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለምን ትንቃለህ? ሁላችን በክ ርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና።

11. እኔ ሕያው ነኝ ይላል ጌታ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረ ከካል ምላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

12. ተብሎ ተጽፎአልና። እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።

13. እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በእርሳችን አንፈራረድ፤ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳ ያኖርበት ይህን ቁረጡ። 14. በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደ ሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቼአለሁም ነገር ግን ምንም ርኩስ እንዲሆን ለሚቆጥር ለእርሱ ርኩስ ነው። 15. ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም። ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተ ለትን እርሱን በመብልህ አታጥፋው። 16. እንግዲህ ለእናንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ፤ 17. የእግዚ አብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና። 18. እንደዚህ አድርጎ ለክርስ ቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው። 19. እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በር ሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል። 20. በመብል ምክንያት የእ ግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ። ሁሉ ንጹሕ ነው፥ በመጠራ ጠር የተበላ እንደሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፉ ነው። 21. ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከል በትን አለማድረግ መልካም ነው። 22. ለአ ንተ ያለህ እምነት በእ ግዚአብሔር ፊት ለራስህ ይሁንልህ። ፈተና መልካም እንዲ ሆን

በሚቆጥረው ነገር በራሱ ላይ የሚይፈርድ ብፁዕ ነው። 23. የሚጠራጠረው ግን ቢበላ በእምነት ስላልሆነ ተኰንኖአል፤ በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ አራት

በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ክርስቲያን ኑሮ እናነባለን። በምዕ.12 ስለ ክርስቲያን ኑሮ በእግዚአብሔር ዘንድ በምዕ13 ስለ ክርስቲያን ኑሮ በመንግሥት ዘንድ አንብበናል። አሁን በምዕ.14 ላይ ስለ ክርስቲያን ኑሮ በወንድሞች ዘንድ እናነባለን። ሁሉም በክርስቶስ ሲያምኑ በሃይማኖትም አንድ ሲሆኑ በክርስቲያን ወንድማማቾች መካከል አንዳንድ የልማድ ነገርና የእምነት ልዩነት ይኖር ይሆናል። ይህ ሲሆን የአንድ እውነተኛ ክርስቲያን ኑሮው ወይም አካሄዱ፥ እምነቱ ጥቂት ከሆነው ወንድም ጋር እንዴት መኖር እንደሚገባው ሐዋርያው ያስረዳናል።

መሠረታዊ ስለሆነ ስለ ክርስቶስ ነገር እንዳይደለ መገንዘብ ነው። መሠረታዊ ስለሆነው ነገር ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ «እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መላዕክት ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንገልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» ብሎ ጽፎአል። (ገላ.1፡8) በዚህ በምዕ.14 እና 15 መጀመሪያ ላይ የተናገራቸው ነገሮች ከፍ ያሉ የሃይማኖት ነገሮች ሳይሆኑ ዝቅ ያሉ የልማድ ጥርጥሮች ናቸው። በክርስቶስ በመወለዱና በመሞቱ በመነሣቱም ስለ ማመን ነገር ሳይሆን ሥጋ ስለመብላት በዓላትንም ስለማክበር ነገር ነው። መሠረታዊ በሆኑት በታላላቅ የክርስቶስ ትዕዛዞች ዘንድ ልዩነት ሊኖር የሚይቻል ነው። በትንንሽ የእምነት ነገሮች ግን ልዩነት ይኖር ይሆናል። በዚህ ምዕራፍ የምናነበው በወንድምና በወንድም መካከል ስለሚኖሩ ስለ ትንንሽ የእምነት ወይም የጥርጥር ነገሮች ነው።

ከዚህ በፊት እንዳየን በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይሁድና አሕዛብ ሁሉቱም ተገኙ። አይሁዶቹ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በሕግ(አሪት) ተወሰነው ኖረዋል፤ ሕይወታቸውም ሁሉ ለሕግ ተገዝቶ ነበር። ያደረጉት ሁሉ በውሳኔ እንዲወሰን ለምደዋል ማለት ነው። ለአሕዛብ ግን ሕግ (አሪት) አልተሰጣቸውም ነበርና እነርሱ በነፃነት ኖረዋል። አረማመዳቸው ሕይወታቸውም በሕግና በውሳኔ እንዲወሰን አልለመዱም። ሌላውን ነገር ሁሉ ትተው በክርስቶስ ብቻ ማመን ለአሕዛብ ቀላል ነበረ አይሁድ ግን ያደረጉትን ሁሉ ትተው አሕዛብ በክርስቶስ ብቻ እንዲያምኑ ማድረግ ነበረባቸው። አይሁዶች ያደረጉትን ሁሉ የወሰነውንና ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣላቸውን ሕግ ትተው በአሕዛብ ነፃነት መኖር ቸገራቸው። ይህ ነገር ከዚህ በፊት እንደ ተነሣ ሐዋርያት የመደቡትንም ነገር በሐዋ.15፡23-29 ላይ እናያለን። አይሁድን የሚያስጸይፉአቸውን ነገሮች አሕዛብ እንዲያስቀሩ ያን ጊዜ ደግሞ ታዝዞ ነበር። አይሁድና አሕዛብ በአንድነት በተገኙበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እነዚህ ትንንሽ የልማድ ልዩነቶች እንደሚነሡ ማንም ሰው አይዘነጋውም። የግድ ተነሥተዋል። ሲነሡም በእንደዚህ ያሉ ነገሮች ጥርጥር የሌለባቸው «ኃይለኞች»

ጥርጥር የተሰማቸውን «ደካሞችን» ወደ መናቅ ጥርጥር ያለባቸውም «ደካሞች» የተገባውንም ያልተገባውንም ሳይለዩ ሁሉን እንደ ገዛ ፈቃዳቸው ባደረጉት «ኃይለኞች» ላይ ወደ መፍረድ ተቃርበዋል።

ምዕራፉ በሁለት ክፍል ይከፈላል። ደካሞች በኃይለኞቹ ላይ ይፈርዱ ነበርና መጀመሪያው ክፍል ከቍ.1-12 ድረስ በተለይ ለደካሞች ተጽፎ «አንዱ በአንዱ ላይ አይፍረድበት» ይላል። ከዚያም በኋላ ደግሞ ኃይለኞች ደካሞቹን ይንቁ ነበር፤ ሁለተኛው ክፍል ከቍ.13-23 ድረስ በተለይ ለኃይለኞች ተጽፎአል። «ወንድምን በመናቅ ምክንያት ለወንድሙ እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቍረጡ» ይላል። የክርስቶስን ርኅራኄ አይታችሁ ተፋቀሩ እንጂ አንዱ በአንዱ ላይ አይፍረድ አንዱ አንዱንም አይናቅ ማለት ነው።

<u>ቍ.1-12</u>፡- «በእምነት የደከመው» የተባለው ሰው ሃይማኖት የጎደለበቱ ወይም እውነተኛ ክርስቲያን ያልሆነው ማለት ሳይሆን በልዩ ልዩ የደንብና የልማድ ነገሮች ጥርጥር ያለበት ሰው ማለት ነው። ሥጋን መብላት ይገባው እንደሆነ ወይም የአትክልትን በዓል ቀን ማክበር ይገባው እንደሆነ አያውቅም። ስለዚህ ሁሉ ነገር ሕግን ለማግኘት አልቻለምና ያን ማድረግ ይህንና ያንም መብላት አያውቅምና በጥርጥር ላይ ሆኖና ኃጢአትን ለመሥራት ፈርቶ ይኖራል። ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደተፈቀደለት የሚያምን ሰው ማለት ጥርጥር የሌለበት ሰው «ደካማ» ይባላል። «ደካማነቱ» ምን እንደሆነ በ1ኛቆሮ.8፡7 እናያለን። «ለጣዖት የተሰዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ስለሆነ ይረክሳል» ይላል፤ ማለት ጣዖታትን ዱሮ ስለ ለመዱ ያ ለጣዖታት የተሰዋ ሥጋ ልዩ እንደሆነ ገና ይሰማቸዋል። «ደካማ ሰው» እንደዚህ ነው። (1ኛቆሮ.8፡10፥12)። «ኃይለኛው» ግን ጣዖት ሁሉ ከንቱ እንደሆነ ያውቃልና፤ «ሥጋ ሁሉ ሥጋ ነው» ብሎ ለጣዖት የታረደውን ሥጋ ምንም ሳያስብ ይበላል። በቆሮንቶስ እንደነበረ እንዲሁ በሮሜ ችግሩ ለጣዖት ስለተሰዋ ሥጋ እንደሆነ ወይም በሮሜ ቤተ ክርስቲያን አይሁድና አሕዛብ አብረው ስለ ተገኙ ችግሩ ስለ ንጹሕና ስለ ርኩስ መብል (ዘሌዋ.ምዕ11) ወይም ስለ ሥጋ አስተራረድ ነገር እንደሆነ (የሐዋ.15፡20፥28፥29) ዛሬ አልታወቀም። ይሁን እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ እነዚህ ባሉት ነገሮች ምክንያት ሳይለያዩ እንዲተባበሩ ይመክራቸዋል።

ኃይለኛው ደካማውን አይናቅ፤ ደካማውም በኃይለኛው ላይ አይፍረድ፤ ሁለቱን እግዚአብሔር ተቀብሎአልና፤ እግዚአብሔርም በሎሌ ላይ ለመፍረድ ለሰው ሥልጣን የሰጠው ማን ነው? ቢቆምም ቢወድቅም የጌታው ጉዳይ ነው እንጂ የሌላ ሰው ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን አይወድቅም ጌታው ሊያቆመው ይችላልና፥ (ቍ.1-4)።

የቀን አከባበር ነገር እንደዚሁ ነው። አንድ ሰው አንድን ቀን በልዩ አከባበር ያከብረዋል ሌላው ሰው ግን ቀን ሲባል ሁሉም አንድ ዓይነት እንደሆነ ያስባል።

በእንደዚህም ያለ ነገር የተሰጠን መሪ ቃል «እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ» የሚል ቃል ነው። ማለት እያንዳንዱ ለእርሱ የሚሆነውን የጌታን ፈቃድ ይረዳ ማለት ነው። የሁላችን አሳብ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ነው እንጂ ሰውን ደስ ለማሰኘት የሚኖር ክርስቲያን የለም፥ (ገላ.1፡8)። በእግዚአብሔር ፊት ቆመን «አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር » ብለን (1ሳሙ.3፡9፥10) ስለ እንደዚህ ያለ ነገር ሁሉ ለእኛ ለእያንዳንዳችን የሚሆን የጌታችንን ፈቃድ ለማወቅ አጥብቀን መጣር ያስፈልገናል። ካወቅንም በኋላ ሰው ቢወድም ባይወድም የጌታችንን ፈቃድ መፈጸም አለብን። ሰውን ሳንመለከት እግዚአብሔርን እንመለከታለን። ለሰው ሳንኖር ለእግዚአብሔር እንኖራለን። ወንድማችን ፈጽሞ እኛ እንደወደድነው አይሆን ይሆናል፤ ይህ ግን ምንም አይደለም። ዋና ነገሩ ፈጽሞ እግዚአብሔር እንደ ወደደው እንዲሆን ነው። ለሕይወት ቢሆን ለሞትም የጌታ ነንና ሰው አይፍረድብን አይናቀንም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሙታንና የሕያዋን ጌታ ይሆን ዘንድ ሞቶአል ከሙታንም ተነጽቶ ሕያው ሆኖአል። እንግዲህ ጌታ ለመሆን ተገቢው ነውው። ሰው ግን የወንድሙ ጌታ ይሆን ዘንድ ምን አድርጎአል? ዳኛ ያደረገውስ ማን ነው? በሰው ውንበር ቆመን ለሰው መልስ መስጠት ሳይሆን በክርስቶስ ወንበር ቆመን ለክርስቶስ መልስ እንሰጣለንና ዛሬ ሰው በሰው ላይ አይፍረድ ሰው ሰውንም አይፍራ፥ (ቁ.5-12)።

ማስገንዘቢያ:- «እግዚአብሔር ተቀብሎታል»፥ (ቁ.3) ይህ ምንኛ ግሩም የሆነና የሚያጽናና ቃል ነው! እግዚአብሔር ከተቀበለው ምን ያናውጠዋል? እግዚአብሔርም ከተቀበለው መፍረዳችን ወይም ደግሞ መናቃችን ምን ይጠቅማል? እግዚአብሔር ተቀብሎታልና ዝም እንበል ወይስ ከእግዚአብሔር ጋር እንፋረዳለንን? ይህን «እግዘብሔር ተቀብሎታል» የሚለውን ቃል ልብ ብናደርግ ከማያስፈልግ በወንድማችን ላይ ከመፍረድ ወንድማችንንም ከመናቅ ከብዙ ነገር ራሳችንን እንጠብቃለን።

«እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ» (ቁ.5) አዲስ አማኝ የሆነ ሰው «ይህን ማድረግ እችላለሁን? (ተፈቅዶልኛልን?) ወደዚያ መሄድ እችላለሁን? ያን ማንበብ እችላለሁን? በማለት ብዙ ጊዜ ይጨነቃል። ይጠራጠራል ማለት ነው። እንደዚህ ላለ ጥያቄ ሁሉ መልሱ በዚህ ቁጥር ላይ እንደተጻፈ ነው «እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ።» በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነገሩን ለራሱ ከመረመረ በኋላ «ጌታ ይወደዋል ሳደርገውም ሳለሁ ጌታን ማመስገን እችላለሁ» ለማለት ቢችል እሺ ይችላል። (ተፈቅዶለታል) «የመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ ነው» ወይም «ሳደርገው በመካከላችን ያለው ኅብረት ምንም አይጎዳም» ለማለ ግን ባይችል የለም አይሆንለትም። ሌላን ሰው መመልከት ወይም ሌላን ሰው መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም። ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ብለን (እንደ ሐዋ.9፡6) እያንዳንዳችን ለየራሳችን ያን ነገር እንቈረጥ። በዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ በጣም

ይረዳናል። ነገሩ በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈቅዶ እንደሆነ እናድርገው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ያልተፈቀደ እንደሆነ አናድርገው። ለሰው ሳንኖር ለእግዚአብሔር እንኑር። ዋና አስፈላጊው በሕሊናችን ጥርጥር እንዳይገኝ ነው።

መብላትና አለመብላት ቀንን ማክበርና አለማክበር ዛሬ በክርስቲያኖች መካከል ክርክርና መለያየት ፈጥሯል! ክርስቲያን በክርስቲያን ላይ ይፈርዳል ክርስቲያን ክርስቲያንን ይንቃል። ለሁላችን የሚሆን ሕግ እነሆ! «የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ (ቁ.3)። እያንዳንዱ የክርስቶስ ባሪያ ነው የሚያደርገውም ጌታውን ደስ የሚያሰኝበት ስለሚመስለው ነው። የበላ እንደሆነ መብላቱን ጌታ እንደሚወድለት በመብላቱም ደስ እንደሚሰኝ ስለሚያስብ ነው፤ ያልበላም አለመብላቱን እግዚአብሔር እንደሚወድለትና ባለመብላቱ ደስ እንደሚሰኝ ስለሚያስብ ነው። ቀኑን የሚያከብርናአ የማያከብር እንደዚሁ ነው። ጉዳዩ የሰውዮውና የእግዚአብሔር ብቻ የግል ጉዳይ ነውና ሌላ ሰው በነገሩ ምን አገባው? በአንድ በኩል መፍረድ በሌላውም በቊል መናቅ ለክርስቲያን በፍጹም አገባብ የሌለው ነገር ነው። «ኃይለኛው» (የሚበላው) የማይበላ ወንድሙን አይናቅ አይዘብትበትም፤ « ደካማው» (የማይበላው) «እኔ ከአንተ ይልቅ ቅዱስ ነኝ» ሳይል (ኢሳ.55፡5) በሚበላ ወንድሙ ላይ አይፍረድ። ሰው ሁሉ የገዛ ራሱን ያስብ እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ይሸከማልና፥ (ገላ.6፡4፥5)። በዋናው መሠረታዊ ነገር እንስማማ በትንንሹም ነገር ምክንያት መፍረድንና መናቅን እንተው።

ከቊ.7-9 ድረስ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው አኳኋናችን እናነባለን። «ለራሱ የሚሞት የለም ብንሞት ለጌታ እንሞታለን ብንሞት የጌታ ነን፥ ስለዚህ ነገር ሙታንን ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአል» ተባለ። ማለት በዚህ ዓለም በነበርን ጊዜ ለጌታ እንደሆንን ሁሉ እንዲሁ ከሞትንም በኋላ የጌታ እንሆናለን። ሞት በእኛና በጌታችን መካከል የነበረውን እስራት ኅብረትም አይበጥሰም፥ (1ኛዮሐ.1፡3፥7)። እዚህ በዓለም ላይ ስንሆን እርሱ ጌታችን እንደነበረ እንደዚሁ እዚያ እኛ ከሞትን በኋላ እርሱ ጌታችን ነው። እኛም እዚህ ሎሌዎቹ እንደነበርን እንደዚሁ እዚያ ደግሞ ሎሌዎቹ እንሆናለን። ይህም ስለ ሞት ነገር ጽኑ ተስፋ ይሰጠናል።

ስንሞት የሞትን አይደለንም። «መሞት ሰው የለመደው ንግግር ነው እንጂ ለክርስቲያን ሞት የለበትም፥ (ዮሐ.5፡24፤ 11፡26)። «የሞተ» ክርስቲያን የሞተ አይደለም፥ ለጌታው ገና ሕያው ነው እንደ በፊቱም ያገለግለዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ስለ «ሞቱት» ስለ አብርሃም ስለ ይስሐቅና ስለ ያዕቆብ ሲናገር «ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ስለሆኑ፥ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም» ብሎ ተናግሮአል፥ (ሉቃ.20፡37-38)። ስለዚህ ስለ ሞት ስናስብ በእውነት እንደማንሞት መቊጠር ነው። ሞት የክርስቶስን ደኅንነት ላልተቀበለ ሰው ብቻ ነው። (ራእ.20፡6፤ 21፡8)። ክርስቲያን ሆይ፥ በዚህ ቃል ተጽናና!

በቁ.10 ላይ ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቆም ተነግሮአል። በዚህ በክርስቶስ ፍርድ ወንበርና በራእይ 20፡11 ላይ በተነገረለት «ታላቅና ነጭ ዙፋን» በተባለው መካከል በአሳባችን ልዩነትን ማድረግ ያስፈልገናል። ክርስቲያን ወደዚያው እጅግ ወደ ሚያስፈራው የታላቅና ነጭ ዙፋን ፍርድ እንደማይመጣ እናውቃለን፥ (ዮሐ.5፡24)። በዚያ ዙፋን ጉዳይ የደኅንነትና የዘላለም ኲነኔ ነገር ነው፤ ለክርስቲያን ግን ይህ ነገር ተቈርጦአል፥ (ዮሐ.6፡47፤ 1ኛዮሐ.5፡12-13)። ይሁን እንጂ፥ ሌላ ፍርድ አለ፥ እርሱም በሥራችን የሚፈረድበት ፍርድ፤ ይህም «የክርስቶስ ፍርድ ወንበር» ይባላል። በዚህ ወንበር ክርስቲያን ሁሉ ይቆማል፥ (ሮሜ 14፡10፤ 2ኛቆሮ.5፡10)። እላይ እንዳልን፥ የዚህ ወንበር ጉዳይ የደኅንነትና የኲነኔ ነገር ሳይሆን የሥራችን ነገር ነው። ሰው የክርስቶስ ሎሌ ከሆነ በኋላ የሠራው ሥራ ይመረመራል። የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፥ የሠራውም ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፥ (1ኛቆሮ.3፡11-15፤ 2ኛጢሞ.4፡8፤ ራእ.3፡16)። ጌታ በማቴ.25፡14-30 ድረስ እንደተናገረው ነገር ነው። ጌታችን ተመልሶ ሲመጣ ክርስቲያን ሁሉ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ይቆማል፥ በሥራውም ይቈጣጠራል። በክርስቲያን ላይ የሚሆን ሌላ ፍርድ የለም።

ቊ.13-23፡- አንዱ በአንዱ ላይ አይፍረድ ብሎ ማድረግ የማይገባንን ነገር ከቊ 1 እስከ 12 ድረስ ካስረዳን በኋላ አሁን ከቊ. 13 እስከ ቊ. 23 ድረስ «ይልቁን ግን» ብሎ ማድረግ የሚገባንን ይነግረናል። የምዕራፉ መጀመሪያ ክፍል ደካሞች በኃይለኞቹ ላይ እንዳይፈርዱ እንደሚያዝዝ፥ እንዲሁ ሁለተኛው ክፍል ኃይለኞቹ ደካሞቹን እንዳያሳዝኑ ያዝዛል። «አንዱ በአንዱ ላይ አይፍረድ፤ ይልቁንም ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቊረጡ» ይላል፥ አንዱ በአንዱ ላይ ከመፍረድ ይልቅ መተዛዘን ይሻላል ማለት ነው፥ (ቊ. 13።)

ጳውሎስ ራሱ በጌታ ኢየሱስ ፊት ቆሞ ነገሩን አስቦ መርምሮ በራሱ ርኲስ የሆነ ነገር እንደሌለ ዐወቀ ተረዳም። እርሱ ጥርጥር የሌለበት «ኃይለኛ» ነው። በርኲስና በንጹሕ እንስሳም ቢሆን፥ በሥጋ አስተራረድም ቢሆን፥ ለጣዖት በተሠዋ ሥጋም ቢሆን፥ በራሱ ርኲስ የሆነ እንደሌለ እርግጠኛ ነው፥ (1ኛቆሮ.10፡23-26፤ 1ኛጢሞ.4፡3-5)። ቢሆንም ቅሉ፥ ማንም ርኲስ እንደሆነ ከተሰማው ያ ነገር ለዚያ ሰው ርኲስ ነው ይላል። ነገሩ በራሱ ርኲስ አይደለም፤ ነገር ግን በዩ በጥርጥር ስለሚበላው፥ የበላ እንደሆነ ሕሊናውን ይበድላልና ይረክሰበታል። እንግዲህ ለእርሱ (ለዚያ ሰው) ነገሩ ርኲስ ሆነ ማለት ነው፥ (ቊ. 14።)

ለእኔ መልካም የሆነ ነገር ለወንድሜ ክፉ ቢሆን የራሴን ሳላስብ የወንድሜን ላስብ። በምዕ.12፡10 ላይ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችን ለመዋደድ የተጠራን ስንሆን ወንድሜን ማሳዘን መውደዴ ነውን? አይደለም! ክርስቶስ ፍቅሩን ያስረዳበትና ስፋቱን የገለጠበት ስለ እርሱ በመሞትና ነፍሱንም በማዳን ነበር። እኔ

ፍቅሬን የማስረዳበት ስፋቱንም የምገልጥበት አንድ ሳሕን ሥጋ ለመብላት ስል ነፍሱን በማጥፋት ነውን? (ቊ. 15።)

በእምነት ኃይለኞች ሆነን ጥርጥር የሌለብን ሰዎች ብንሆን መልካም ነው። ይህ መልካም ነገራችን ግን የስድብ ምክንያት ቢሆን መልካም ነገራችን ክፉ ሆነ። ሰዳቢው ማን እንደሆነ እዚህ ላይ አልተጻፈም። ወይም ደካማ ወንድሙ ይሆናል፥ ወይም የውጭ ሰው ይሆናል። ወንድሜን ንቂ የገዛ ራሴን ፈቃድ በፈቱ የፈጸምሁ እንደሆነ መቀያየም መለያየትም ሳይነጣ አይቀርም። ይህስ ሲሆን፥ የእኔ መልካም ነገር ይሰደባል። ወይም ደግሞ የውጭ ሰው መጨቃጨቃችን እና መለያየታችን አይቶ «እይ! ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ይጣላሉ፥ ቤተ ክርስቲያን የተባለው ክፍል ክፍል ብቻ ሆነ!» ብሎ የክርስቲያኖችን ማኅበር ይሰድባል። ከእነዚህ ሁለት ነገሮቸንድም እንዳይሆን እንጠንቀቅ! ቢያስፈልግም ኃይለኛው ፈቃዱን እና መብቱን ባያስጠብቅ (ቢተው) ይሻላል፥(ቊ.16)።

የክርስቲያን ሃይማኖት የጽድቅ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድም ሰላምን የመያዝ፥ በመንፈስ ቅዱስም የሆነ የልብ ደስታ፥ የውስጥ ነገር ነው እንጂ የመብልና የመጠጥ (የሆድ) የሚዳ ሕግ ነገር አይደለም። ጽድቅን፥ ሰላምን፥ ደስታንም የምናገኝበትን ዘዴ ለመመራመር ጊዜአችንንና ጉልበታችንን እንስጥ እንጂ እነዚህን ትንንሾች ነገሮች እንደ ቁም ነገሮች አድርገን በመቊጠር ስለ እነርሱ በመጣላትና አንዱ በአንዱ ላይ በመፍረድ ጊዜአችንን አናሳልፍ፥ (ቊ.17)።

እንደዚህ የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ ተናግሮአል። ማለት፥ በእነዚያ ሌሎች ትንንሾች ነገሮች እየተከራከርን ጊዜአችንን ስናሳልፍ እግዚአብሔርን ደስ አናሰኝም ማለት ነው። ሁለተኛ ደግሞ፥ በእነዚያ ትንንሾች ነገሮች ዘወትር መጨቃጨቅ በሰው ዘንድ ደግሞ ምስጋናን አያስገኝም። ሌላን ሁሉ አስቀርተን እነዚያን የክርስቲያንን ሃይማኖት ታላላቅ ነገሮች በማስተማር በመመራመርም እንወሰን። ይህንም ብናደርግ እግዚአብሔርን ብቻ ደስ ሳናሰኝ በሰው ዘንድ ደግሞ የተወደድን እንሆናለን። ዓለም በታናሽ ነገር ተከራካሪ አይወድም! (ቊ.18።)

በመከራከርና አንዱ አንዱን በመጣል (በማፍረስ) ፈንታ ሰላም የሚቆምበትንና እርስ በርሳችን የምንታነጽበትን እንከተል። በወንድምና በወንድም መካከል እነዚህ ነገሮች እንደሚነሡ የታወቀ ነው፥ (ማቴ.18፡7)። ሰው ሁሉ እርሱ ራሱ ያማረውን ሳይመለከት ሰላምን የሚያጸናውንና ወንድሙ የሚታነጽበትን ይፈልግ፥ (ቊ.19)።

እግዚአብሔር በዚያ ወንድም ልብ ውስጥ ሥራውን ጀምሮአል። ገና እጅግ የበረታ (ኃይለኛ) ክርስቲያን አልሆነም ይሆናልና ጥርጥር ይኖረው ይሆናል። ቢሆንም፥ የክርስቶስን ምሳሌ እናስብ። ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፦ «የተቀጠቀጠውን ሸምበቆ አይሰብርም፥ የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም»፥

(ማቴ.12፡20)። በደካማው አልጨከነም ማለት ነው። «ሁሉ ንጹሕ ነው» ስትል እውነትህ ነው፥ ነገር ግን ያ ለአንተ ንጹሕ የሆነ ነገር ለወንድምህ ርኩስ ለመሆን መቻሉን አትርሳ! ሥጋን መብላት አምሮህ የእግዚአብሔርን ሥራ ብታፈርስ አይፈረድብህምን? ሉረ ይፈርድብሃል! (ቊ.20።)

እግዚአብሔር ሥራውን ሊሠራ የጀመረበትን ወንድም ከማሰናከልና የእግዚአብሔርን ሥራ ከማጥፋት ይልቅ «ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት መልካም ነው (ያምራል)» ተብሎአል። ብዙዎች ክርስቲያኖች ወይንን (ጠጅን) ወይም የሚያሰክር ማናቸውንም ሌላ መጠጥ የማይጠጡበት በዚህ ምክንያት ነው። «አትጠጣ!» የሚል ሕግ በመኖሩ አይደለም። «ምነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ መጠጥ መጠጣትን ይከለክላልን? ኢየሱስ ራሱ ውኃውን ጠጅ አድርጎ የለምን? ቅዱስ ጳውሎስስ በ1ኛጢሞ.5፡23 ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት20የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ ብሎ አዝዞ የለምን?» ብለው ሰዎች ብዙ ጊዜ ይጠይቃሉ። (ይህ የጳውሎስ ቃል መቸም የዱሮ ክርስቲያኖች መጠጥ መጠጣትን እንዳልለመዱ፥ ጳውሎስም ጢሞቴዎስን እንዲጠጣ የመከረው በምን ምክንያት እንደሆነ፥ የሚጠጣውንም ያህል፥ ያስረዳል።) ክርስቲያን ከሕግ በታች አይደለምና፥ እውነት ነው፥ የወደደውን ለማድረግ ሙሉ ነፃነት አለው። ይህ ብቻ ሳይሆን የወደደውን ለማድረግ ይችላል። መጠጥ መጠጣትስ ይችላል! መጽሐፍ ቅዱስ «አትጠጣ» ብሎ አይከለክለውም። ይሁን እንጂ፥ በሌላ አስተያየት ሲታይ ግን ተከልክሎአል። መጽሐፉም ይከለክላል! «እንዴት?» ቢባል፥ በዚህ ቊጥር ላይ እንደ ተጻፈ ወንድሙን ማሰብ ስላለበት ነው! የወይን ጠጅ ሌላም የሚያሰክር ነገር የሰው ልጆችን ለማጥመድ እንደሚችሉ፥ እንደሚያጠምዱአቸውም፥ የማይካድ ነገር ነው። ይህስ ከሆነ፥ እዚህ በሮሜ 14፡21 ላይ የተባለውን ይዞ ክርስቲያን መጠጥን መጠጣት ይችላልን? እርሱ ሲጠጣ አይቶ ወንድሙ ደግሞ ለመጠጣት ይደፋፈራል! በትንሹም ጀምሮ ቢሰክር ግን ጥፋቱ የማን ይሆናል? የዚያ የጠጣው ክርስቲያን አይደለምን? ወንድሙን ያሳሳተው እርሱ ጠጅን መጠጣት ባለመተዉ አይደለምን? ካህናት፥ መኳንንት፥ አስተማሪዎች፥ ሲጠጡ! ሕዝበ ክርስቲያን፥ የአገሩ ሰዎችም፥ ተማሪዎችም፥ ለመጠጣት ይማሩ ይደፋፈሩም የለምን? ይህስ አይጠረጠርም! ይህም ከሆነ ክርስቲያን መጠጥን መጠጣት ቢተው ይሻል የለምን? ከሕግ በታች አይደለንም። «አትጠጣ!» የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝ ይሆናል። ባይገኝሳ? ይህ ቊጥር (ሮሜ 14፡21) ያስተወን የለምን? የግድ ያስተወናል! የሚከለክል የተጻፈ ሕግ አይኖር ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ እኔ ባደረግሁት ነገር ምክንያት ወንድሜ ወደ ገሃነመ እሳት ቢወድቅ ደሙ ከእኔ እጅ ከቶ አይፈለግ ይሆንን? ሉረ ይፈለጋል! እንግዲያስ ለክርስቲያን «ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው (ያምራል)» የሚል በማብላትና መጠጥን በመጠጣት ነገር መሪ ቃል ነው። (ቊ. 21።)

አሁንም በቍ.22 «ኃይለኞች» ለተባሉትና በቍ.23 «ደካሞች» ለተባሉት መጨረሻ ምክሩን ይሰጣል፡-

አንተ ኃይለኛ ክርስቲያን ሆይ፥ ብርቱ እምነትህ ለራስህና ለእግዚአብሔር ደስታ ይሁን እንጂ በእምነትህ ብርታት ሌሎችን አታስቸግር። ሁለተኛ፥ በልብህ በእውነት የማይገባ ሆኖ ሲታይህ «ሉረ መልካም ነው እንጂ!» ብለህ ያን ነገር ደፍረህ ከማድረግ ተጠንቀቅ። ሌሎች ሲያደርጉት አይተህ ይሆናል! በእውነትም የበረቱ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ የሚያደርጉና ለብርቱ ክርስቲያን የሚገባ ነገር ይሆን ይሆናል። ሕሊናህን በድለህ ታደርገው እንደሆነ ግን ትኩነናለህና ከእነርሱ ጋር አንድ በመሆንህና እነርሱን በመምሰልህ ሳትመካ ጥርጥር በልብህ እያለ ብታደርገው ኃጢአት መሆኑን አስበህ ብትተወው የተሻለ ነው፥ (ቍ.22።)

አንተም ጥርጥር ያለብህ ክርስቲያን ሆይ፥ እንዳትበላ ተጠንቀቅ። በእንደነዚህ ያሉ ነገሮች ጥርጥር ካለብህ ከምትጠራጠር ብትተወው ይሻላል። «በእምነት ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው» የሚለው ቃል (ቍ.23) ለአንተ የሚሆን ሕግ ነው። ነገሩን እርግፍ አድርገህ ተወው!

* * *

# ክፍል 6 – ሰላምታ፥ ተግሣጽና ቡራኬ
## ሮሜ 15:1 - 16:27

## ምዕራፍ 15

1. እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል። 2. እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ። 3. ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን:- አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደተጻፈ ሆነበት። 4. በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና። 5.6. በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት፥ ታከብሩ ዘንድ፥ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ።

7. ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ። 8.9. ለአባቶች የተሰጠውን ቃል ያጸና ዘንድ፥ ደግሞም:- ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ ለስምህም እዘምራለሁ ተብሎ እንደተጻፈ፥ አሕዛብ ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ፥ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ። 10. ደግሞም:- አሕዛብ ሆይ፥ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል። 11. ደግሞም:-

እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ፥ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት

12. ይላል። ደግሞም ኢሳይያስ:-

የእሴይ ሥር አሕዛብንም ሊገዛ የሚነሣው ይሆናል፤ በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ፤

ይላል። 13. የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ።

14. እኔም ራሴ ደግሞ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ በበጎነት ራሳችሁ እንደተሞላችሁ፥ ዕውቀትም ሁሉ እንደሞላባችሁ፥ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሥጹ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ። 15.16. ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መሥዋዕት ሊሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፥ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ። 17. እንግዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር በክርስቶስ ኢየሱስ ትምክህት አለኝ። 18.19. አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤ ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ። 20. እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ፤
21. ነገር ግን:-

ስለ እርሱ ያልተወራላቸው ያያሉ፥ ያልሰሙም ያስተውላሉ

ተብሎ እንደተጻፈ ነው።

22. ስለዚህ ደግሞ ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ። 23. አሁን ግን በዚህ አገር ስፍራ ወደ ፊት ስለ ሌለኝ፥ ከብዙ ዓመትም ጀምሬ ወደ እናንተ ልመጣ ናፍቆት ስላለኝ፥ 24. ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ እናንተን እንዳይ፥ አስቀድሜም ጥቂት ብጠግባችሁ ወደዚያ በጕዞዬ እንድትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። 25. አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ። 26. መቄዶንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወድደዋልና። 27. ወድደዋልና፥ የእነርሱም ባለ ዕዳዎች ናቸው፤ አሕዛብ በእነርሱ መንፈሳዊ ነገርን ተካፋዮች ከሆኑ በሥጋዊ ነገር ደግሞ ያገለግሉአቸው ዘንድ ይገባቸዋልና። 28. እንግዲህ ይህን ፈጽሜ ይህን ፍሬ ካተምሁላቸው በኋላ በእናንተ በኩል አልፌ ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ፤ 29. ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት ሙላት እንደምመጣ ዐውቃለሁ።

30. ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፤ 31.32. በእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋር እንዳርፍ፥ በይሁዳ ካሉት ከማይታዘዙ እድን ዘንድ፥ ለኢየሩሳሌምም ያለኝ አገልግሎቴ ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ ጸልዩ። 33. የሰላምም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

ሐዋርያው በምዕ.14 ላይ በሆነ ልማድ ነገር ጥርጥር ስለሌለባቸው «ኃይለኞች»፥ እና «ጥርጥር ስላለባቸውም «ደካሞች» ተናግሮ ነበር። በዚያ ምዕራፍ በቍ. 1 ላይ «በእምነት የደከመውን ተቀበሉት» ብሎ ኃይለኞችን አዝዞ ነበር። አሁንም ደግሞ በምዕ.15 አሳቡን ቀጥሎ ከቍ.1 እስከ 13 ድረስ ኃይለኞቹ የደካሞቹን ድካም እየተሸከሙና ራሳቸውን ደስ ለማሰኘት ሳያስቡ ባልንጀሮቻቸውን ደስ እንዲያሰኙና እርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ ያዝዛቸዋል። ይህ የመልእክቱ ትምህርት መጨረሻ ክፍል ነው። ከዚያ በኋላ በድፍረት የጻፈበትን ምክንያት እያስረዳ በፊቱ ያለውን የሥራውን አሳብ ይገልጣል።

ቍ.1-13፡- በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ ቅርፅ ቅርፃቸው ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት ክፍሎች አሉ፡- 1ኛ. ከቍ.1 እስከ ቍ.6 ድረስ፤ 2ኛ. ከቍ.7 እስከ ቍ.13 ድረስ። በእያንዳንዱ ክፍል 4 4 ነገሮች አሉ፥ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) ኃይለኞችና ደካሞች እየተቀባበሉ በአንድነት እንዲኖሩ የምክር ቃል፥ (ቍ.1 እና 2፥ ደግሞ ቍ.7።)

ለ) ይህን ምክር የሚያጸና የክርስቶስ ምሳሌ፥ (ቍ.3 ደግሞ ቍ.8-9።)

ሐ) ይህን ምክር የሚያጸና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ፥ (ቍ. 4 ደግሞ ቍ.10-12።)

መ) ይህን ምክር ይፈጽሙ ዘንድ የሐዋርያው ጸሎት፥ (ቍ.5-6 ድግሞ ቍ.13።)

በመጀመሪያው ክፍል (ቍ.1-6)፤

ሀ) የምክር ቃል ኃይለኞች የደካሞችን ሸክም እንዲሸከሙ ነው። ማለት፥ ኃይለኞቹ የደካሞችን ድካም እንኪታገሡና እንዲችሉ ነው። ይህም ምክር በሁሉ ዘንድ ተስማሚ ነው፤ ለምን ቢሉ፥ ሸክምን መሸከም የሚችሉ መሸከምም የሚገባቸው ኃይለኞቹ ናቸው እንጂ ከቶ ደካሞቹ አይደሉምና። ስለዚህ፥ ኃይላችንንና ነፃነታችንን አበርትተን ራሳችንን ደስ በማሰኘትና ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን በማኖር ፈንታ ደካማውን ደስ ለማሰኘትና ባልንጀራችንን እንድናንጸው እንመልከት፥ (ፊልጵ.2፡1-5)።

ለ) ይህን ምክር የሚያጸና የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ራሳችንን ደስ ማሰኘት የማይገባበት ምክንያቱ ክርስቶስ ራሱን ደስ ስላላሰኘ ነው። መጀመሪያ ታላቁ የክርስቶስ ምሳሌ እነሆ! ሁለተኛውን ከቍ.8-9 ላይ እናገኛለን። ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘም (ሉቃ.22፡42-45)። ጌታ ራሱን ደስ አላሰኘምና እኛ ባሪያዎቹ ራሳችንን ደስ ለማሰኘት ለምን እንበረታለን? እርሱ ስለ እኛ ምን ያለ ሸክም ተሸከመ! (ኢሳ.53፡4፤ 1ኛጴጥ.2፡24)። እርሱም ስለ እኛ ራሱን እንደምን አዋረደ!

(ፊልጵ.2፡8)። ክርስቶስ ይህን ካደረገ፥ እኛስ የራሳችንን ፈቃድ አስቀርተን የደከሙ ወንድሞቻችንን ጥርጥር በመታገሥ በመቻልም ደስ እናሰኘው ዘንድ እንደምን ይበልጥ ይገባን!

ሐ) አሁን ደግሞ ይህን ምክር የሚያጸና የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አለን። በእንደዚህ ያለ ነገር ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሊረዳን ተሰጥቶናል። እርሱን በማንበብ ትዕግሥትን መጽናናትንም እናገኛለን። ቅዱስ ዳዊት በመዝ.68፡8 ላይ «አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ» ብሎ በመናገሩ እርሱ ደግሞ በማይገባ ነቀፋ እንደተነቀፈ ገልጦአል። በተራውም ክርስቶስ ይህን ነቀፋ ወረሰ። እኛም ይህን ስናይ በእኛ ላይ ደግሞ ያልተገባን ነቀፋ ቢደርስ እንጽናናለን፥ ትዕግሥትንም እናገኛለን እንጂ አንሰናከልበትም። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ሁሉ እኛን ለማስተማር ነውና ራሳችንን ከደካሞች በታች አዋርደን በማይገባ ነቀፋ ምንም ብንነቀፍ ታግሠን በመጽናት፥ መጽሐፍ ቅዱስም በሚሰጠን መጽናናት፥ ያን የሙሉ መዳንን ተስፋ አጥብቀን ይዘን ልንራመድ እንችላለን።

መ) አሁንም ደግሞ የሐዋርያው ጸሎት የጌታው መንፈስ በአገልጋዩ እንደምን አደረ! አንድነት እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው! የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ ነው። ክርስቶስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት ይህ የአንድነት ነገር እንደምን ተጭኖት ነበር! «እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።» (ዮሐ.15፡12)። «ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። ... ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ» ብሎ ክርስቲያኖች ተስማምተው በአንድነት ይኖሩ ዘንድ ጸለየ፥ (ዮሐ.17፡11፤21)። አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ «በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን ታከብሩ ዘንድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ» ብሎ ይጸልያል። እግዚአብሔር የሚከበርበት በክርክርና በመጓደድ በመለያየትም ሳይሆን በትዕግሥትና በመቻቻል በአንድነትም እንደሆነ ልብ እናድርግ። ይህም ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ ነው።

በሁለተኛው ክፍል (ቍ.7-13) ነገሩ ያው ነው፤ ነገር ግን በተለይ ለኃይለኞች ሳይሆን አሁን ለሁለቱም ወገኖች ይናገራል፡-

ሀ) የምክር ቃል ኃይለኞችና ደካሞች እርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ ነው። ይህ የምክር ቃል ግን እንዴት ጽኑ ነው! ምክንያቱም ተነግሮናል። መሠረቱ ክርስቶስ እነርሱን ስለተቀበለ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዲከበር ነው። ክርስቶስ እናንተን ስለተቀበለ እግዚአብሔርም እንዲከበር እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ፤ ከዚህ

የበረታ ከቶ ምክንያት አለን? ተቀባበሉ! (እግዚአብሔር የሚከበርበት በአንድነት እንደ ሆነ ከቍ.5-6 እንዳየን እንዲሁ ደግሞ እዚህ በቍ. 7 እናየዋለን።)

ለ) ይህን ምክር የሚያጸና የክርስቶስ ምሳሌ ደግሞ አለ። እርሱ ኃይለኞችንና ደካሞችን፥ አሕዛብንና አይሁድን፥ አንድ ለማድረግ መጣ። ለይሁድ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ለመፈጸም፥ ስለ እግዚአብሔር እውነት ሲል፥ የመገረዝ አገልጋይ ሆኖ (ገላ.4፡4) ወደ አይሁድ ዘንድ መጣ። ኃይለኛ የነበረው ራሱን አዋርዶ እንደ ደካማ ሆኖ በደካሞች ዘንድ ተቀመጠ። የሁሉ ጌታ የነበረው አገልጋይ ሆነ። ነገር ግን ይህ ብቻ አሳቡ አልነበረም። አሕዛብ ደግሞ እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ፥ ሕግ ወደሌላቸውና ጥርጥር ወደሌለባቸው ኃይለኞች ወደ አሕዛብ ዘንድ ደግሞ መጣ፥ (ኢሳ.49፡6)። በመካከላቸው ልዩነትን ሳያደርግ ለሁለቱም መጣ፥ ሁለቱንም አንድ አደረገ፥ (ኤፌ.2፡13-17)። ይህስ በእርግጥ ለእኛ የሚሆን መልካም ምሳሌ ነው።

ሐ) ይህንም ምክር የሚያጸኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አሉ። ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር አሕዛብንና አይሁድን አንድ ለማድረግ ቈርጦ እንደነበር ብሉይ ኪዳን በሦስቱ ክፍሎች፥ በኦሪት በመዝሙራት በነቢያትም፥ መስክሮአል። እግዚአብሔር እንደዚህ አንድነትን ከወደደ ምነው አንቀባበልም?

መ) በመጨረሻም ላይ ጸሎቱ አለ። «በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ» ሲል ያን ታላቁን ተስፋ እንደገና ያስባል። በምዕ.5፡2፥ ደግሞ በምዕ.8 ላይ፥ በሰፊው የተነገረው ተስፋ ነው። «የተባረከው ተስፋችን እርሱም የታላቁ የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ» ነው። (ቲቶ.2፡12-13)። የፍጹም መዳናችን ቀን ነው። የዚህ ተስፋ አምላክ እግዚአብሔር ነውና ሐዋርያው በተስፋ እንድንበዛ እግዚአብሔር ደስታንና ሰላምን እንዲሞላብን ይጸልያል። አንዱ በአንዱ ላይ በመፍረድና በመናናቅ፥ በመከራከርና በማለያየት ያ ተስፋ እየተጋረደብን ይሄዳል። በመተጋገሥና በመቻቻል፥ በመፋቀርና አንድ በመሆን ግን ተስፋው እየተገለጠ ይሄዳል፤ እየቀረበልንም ይመጣል። በተስፋ መብዛታችን፥ በደስታና በሰላም መሞላታችንም፥ በምን ይፈጸማል? በአንድ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሌላም በኩል በማመናችን ይፈጸማል። በዚህ መልእክት ሁሉ ያገኘነው ነገር ይህ አይደለምን? በእኛ ሥራ ሳይሆን በእኛ እምነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። በዚህ ነው በተስፋ የምንበዛ በደስታና በሰላምም የምንሞላ። ይህ በሮሚ ለነበሩት ክርስቲያኖች የሐዋርያው ጸሎት የእኛ የእያንዳንዳችን ፋንታ ይሁን።

ማስገንዘቢያ፡- ይህን ሁሉ ስናነብና በዘመናችን ክርስቲያን ከክርስቲያን መለያየቱን፥ ያውም ብዙ ጊዜ በትንንሽ ነገር፥ ስናይ ሕሊናችን እንደምን ይወቅሰናል! አንድ እንድንሆን የአንድ ጌታችን ፈቃድ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስን እናነባለን፤ እናምነዋለንም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል አንፈጽምም። እያንዳንዳችን

የገዛ ራሳችንን ፈቃድና አሳብ ለመፈጸም ስለምንወድ በክፍል ክፍል ክፍል ክፍልፍል ብለናል! መቀባበል ይቅርና በመለያየታችን ስንኳ እንጓደዳለን! አንዳንዶቻችን ኃይለኞች አንዳንዶቻችንም ደግሞ ደካሞች ሆነናል። በመካከላችን የመብላትና ያለመብላት፥ የቀንን ማክበርና አለማክበር፥ እንደዚሁም ደግሞ እነዚህን የሚመሳሰሉ ሌሎች ጥርጥሮች ገና አሉ። ሲኖሩም፥ የተሰጠንን ምክር ሳንፈጽም እያንዳንዳችን በገዛ መንገዳችን በረታን። ከእኛ ጋር ስለማይከተሉ ከለከልናቸው እንጂ አልተቀበልናቸውም፥ (ሉቃ.9፡49)። በዙሪያችን አጥር አጥረን ወንድሞቻችንን «አትቅረቡ!» አልናቸው እንጂ መቼ ተቀበልናቸው? ራሳችንን እንድናዋርድ፥ አንዱ በአንዱ ላይ እንዳይፈርድበትና እንዳንናናቅ ታዝዘናል። ይህን ለማድረግ ግን አልፈቀድንም። ኃይለኛው ደካማ ወንድሙን ንቆ በግልጥ ይዘብትበታል ያፌዝባታልም፤ ደካማ በኃይለኛው ላይ ፈርዶ በጭራሽ ክርስቲያን እንዳልሆነ ሰው ይቈጥረዋል። በሮሜ ምዕ.14 እና ምዕ.15 ላይ የተጻፈውን ትምህርት መላልሰን እንደገና እንማረው!

ቍ.14-21፡- ጳውሎስ ሊነግራቸው የወደደውን አሁን ጨርሶአል። በሰው ሁሉ ላይ ስለሚገለጥ ስለ እግዚአብሔር ቍጣ ተናግሮአል። ቍጣ በሰው ሁሉ ላይ ስለሚመጣ ጽድቅ ለሰው ሁሉ አስፈላጊ ሆነ። በወንጌል ስለሚገለጥ ጽድቅ፤ ስለ መገለጡ፥ ስለ መቈጠሩ፥ ስለ መስፋቱም ተናግሮአል። ይህን አድርጎ ሲያበቃ ጽድቅ የነገሩ ሁሉ ፍጻሜ አለመሆኑን ገልጦአል። «ከኃጢአት ይልቅ ጸጋ ከበዛ በኃጢአት ጸንተን ብንኖር ምን አለበት?» ብለው አንዳንዶች ቢጠይቁት ሐዋርያው ስለ ቅድስና፥ ስለ አስፈላጊነቱ፥ ስለ በሩ፥ ስለ ጎዳናውም ተናግሮአል። ይህንም ሲያደርግ ሳለ ስለ መዳን ፍጻሜ፥ እርሱም ስለ መከበራችን፥ ደግሞ ተናግሮአል። ሙሉ ወንጌልን፤ ጽድቅን፥ ቅድስናን፥ ክብርን፥ ሰብኮአል። ስለ እስራኤል አለመውረስና ስለ አሕዛብ መተከል፥ ስለ ክርስቲያን ኑሮና አመላለስ፥ ደግሞ ተናግሮአል። አሁንም ነገሩ አለቀ። ብርዑን አኑሮ ሊያርፍ ነው።

በልቡ ግን ትንሽ ቅሬታ አለ። ወደ ሮሜ ሄዶ አያውቅም ነበር፤ በሮሜም የነበሩ ክርስቲያኖች አላወቁትም። አባታቸው አይደለም፤ ከ12ቱ ሐዋርያት ስንኳ አንዱ አይደለም። የሮሜ ሰዎች ወረቀቱን ተቀብለው «እርስ በርሳችሁ ተስማሙ» ብሎ እስኪያዛቸው ድረስ መድፈሩን አይተው «ሉረ! ይህ እንደዚህ ደፍሮ የጻፈልን ማን ነው?» ብለው ምናልባት ይጠያይቁ ነበር። ቤተ ክርስቲያኑ የጸና ነበረ፥ ያሉበትም ክርስቲያኖች የተማሩና እርስ በርሳቸው ለመገሣሠጽ የቻሉ ነበሩ። እንግዲያስ የጳውሎስን ወረቀት ተቀብለው ምናልባት «ሉረ! ይህን ሁሉ ባናውቅ ነው ወይ?» ይሉ ነበር። ይህን ሁሉ በማሰብ ጳውሎስ አሁን የሚከቱሉትን ቍጥሮች ጽፎአል።

Aረ! በአካሄዳቸው መልካሞች፥ በዕውቀታቸው የተሞሉ፥ እርስ በርሳቸው ሊገሣሥጹ የሚችሉ መሆናቸውን መቼ ዘነጋ? አሳምሮ ዐውቆታል፥ (ቍ.14።) የጻፈበት ምክንያቱ ለማሳሰብ ነበረ እንጂ አዲስን ነገር ለማስተማር ከቶ አልነበረም።

ቢሆንም፥ የእርሱ ልጆች ባይሆኑ እንኳ እግዚአብሔር የአሕዛብ ሐዋርያ ስላደረገውና በሮሜ ካሉ ክርስቲያኖች የሚበዙት ከአሕዛብ ወገን ስለሆኑ እንደዚህ ያለ ወረቀት መጻፍ ተገቢው ነበረ። ጳውሎስ ግን የዋህ ነውና «ሐዋርያ አደረገኝ» ስንኳ ለማለት ሳይደፍር ራሱን «አገልጋይ» ይላል፥ (ቍ.15-16።) እርሱ የጻፈው እነርሱ የእርሱ በመሆናቸው ተመክቶ አይደለም፤ ቢሆንም፥ ትምክህት አለው። ይህ ትምክህት ግን በራሱ ወይም በራሱ ሥራ ሳይሆን «ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር» ነበረ፥ (ቍ.17።) ክርስቶስ በእርሱ አድርጎ ታላቅ ሥራን በእርግጥ ሠርቶ ነበረ። ጌታ ከእርሱ ጋር ሠርቶ በሚከተሉት ምልክቶች ቃሉን ሐዋርያነቱንም አጽንቶ ነበርና ጳውሎስ በክርስቶስ ሥራ ተመክቶአል፥ (ቍ.18-19፤ ማር.16፡20)። እግዚአብሔር አብሮት ያነ ያህል ሠርቶ ስለ ነበርና የጳውሎስም አሳብ ሁልጊዜ ወንጌል ወዳልተሰማበት ስፍራ ለመሄድ ነበረ እንጂ ሌላ ሰው በመሠረተው ላይ ለመቀመጥ አሳብ ከቶ ስላልነበረ ሐዋርያው ወንጌልን ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በግሪክ አገር ጠረፍ ላይ ወደሚገኘው ዛሬ አልባኒያ በዚያ ጊዜ ግን እልዋሪቆን እስከሚባል አገር ድረስ ሰብኮ ነበር፥ (ቍ.20-21።)

ማስገንዘቢያ

ሀ) በቍ.15 እና 16 ላይ ሐዋርያው ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን ማገልገሉን ያስረዳል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ካህን» የተባለው ቃል ስለ ብሉይ ኪዳን ካህናት እንጂ ከዚህ በታ በስተቀር ስለ ክርስቲያን ተናግሮ አያውቅም። በሌላ 3 ቦታዎች በ1ኛጴጥ.2፡5፥ በ1ኛጴጥ.2፡9 እና በራእይ 1፡6፤ ሞላ ሕዝበ ክርስቲያን «ካህናት» ይባላሉ እንጂ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ክርስቲያን ለብቻው «ካህን» ተብሎ አያውቅም። የብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደስ ሠራተኞች «ካህናት» ሲባሉ የአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ወይም «አገልጋዮች» ወይም «ሽማግሌዎች» ይባላሉ። ከአዲስ ኪዳን ደራሲዎች የሚበዙት የቤተ መቅደስንና የመሥዋዕትን የካህናትንም ነገር የለመዱ አይሁዶች ነበሩና በንግግራቸው ውስጥ «ካህን» የተባለው ቃል ብዙ ጊዜ እንደሚገባ በታሰበ ነበር። አለመግባቱ በጣም የሚያሳስብ ነገር ነው።

ለዚህ ሁሉ ነገር ምክንያት አለ። የብሉይ ኪዳን ካህናት የክርስቶስ ምሳሌዎች ሆነው በክርስቶስ ተፈጸሙ፥ (ዕብ.9፡11-14)። እንደዚሁም ደግሞ «ካህን» የተባለው ቃል መሥዋዕት አቅራቢ ማለት ስለሆነ፥ መሥዋዕቶቹም ሁሉ የክርስቶስ የአንዱ መሥዋዕት ምሳሌዎች ሆነው በእርሱ መሥዋዕት ስለተፈጸሙ (ዮሐ.1፡29፤ ዕብ.7፡27፤ 9፡26፤28፤ 10፡11-14)፥ ከክርስቶስ ወዲህ ካህን አላስፈለገም።

ካህናት በክርስቶስ ስለተፈጸሙና ከክርስቶስ መሥዋዕት ወዲህ ሌላ መሥዋዕት ስለሌለ፥ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች «አገልጋዮች» ወይም «ሽማግሌዎች» ናቸው

እንጂ «ካህናት» አይደሉም። ይህን ተገንዝበን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ስንናገር የልማድ ንግግራችንን አርመን «ካህን ካህናትም» በማለት ፈንታ «ቄስ ቀሳውስትም» ብንል የተሻለ ነው።

በዚህ ቍጥር ላይ ጳውሎስ ሁለቱን አሳብ አጣምሮ ራሱን ካህንና አገልጋይ ያደርጋል። ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን ያገለግላል፤ ለአሕዛብም የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ ነው። ለወንጌል «ካህን» ነው፤ ለሰው ግን «አገልጋይ» ነው። ክህነቱስ በምንድር ነው? ሥጋዊ መሥዋዕት የሚያቀርብ የብሉይ ኪዳን ዓይነት ካህን አይደለም። በማስተማርና በማሳመን ግን አሕዛብን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ የወንጌል ዓይነት «ካህን» ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያን «አገልጋይ (የቄስ) ዓይነተኛ ሥራው ነው።

ለ) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስ ስም ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን ለመስበክ እንደተጣጣረ እንመልከት፥ (ቍ.20-21።) ወንጌልን እየሰበከ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ግሪክ አገር የማዶ ወሰን ድረስ ዞሮ ነበር። በእርሱ ያደረው መንፈስ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትም አድሮ ነበር። «ዋዜማ» በተባለ መጽሐፋቸው ላይ በገጽ 104 ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንዲህ ብለው ጻፉ:-

> «አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምንም እንኳ የምንኩስና ማዕረግ ቢቀበሉ፥ እንደ እንጦንስና እንደ መቃርስ ወይም እንደ ሌሎች መነኰሳት የሰይጣንን ፈተና ፈርተው ከሰው ተለይተው ወደ ገዳም ገብተው ዕድሜአቸውን ለመጨረስ አላሰቡምና ወገባቸውን በንጽሕና ዝናር ታጥቀው፥ የብሉይንና የሐዲስን መጻሕፍት እንደ በሬዎች ጠምደው፥ በእርፈ መስቀላቸው ኢትዮጵያን እያረሱ ከማያልቀው ከሰፊው የሕይወት ጎተራ የእግዚአብሔርን ቃል እያወጡ ይዘሩ ነበር። . . . በኢትዮጵያ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የስብከታቸው ብርሃን ያልደረሰበት አገር የለም።»

ይህም ደግሞ የቅዱስ ጳውሎስ የሥራው አሳብ ነበረ። ይህም የልዑል አምላክ ፈቃድ ነው። ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ላይ ተደራርበ ተሠርቶ ቀሳውስት በአንድ ቦታ ከመጠን በላይ በመገኘትና መነኰሳት የወንጌልን ብርሃን ከእንቅብ በታች ተጠንቅቀው ጠብቀው በበረሃ ተከማችተው በመቀመጥ ፈንታ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ አንድም ኃጢአተኛ እንዳይጠፋ ነውና ሁላቸው ተለያይተው ወደየአገሩ ተሠራጭተው የጠፉትን በጎች ቢፈልጉ የተሻለ ነበር፥ (ማቴ.5፡14-15፤ ሕዝ.34፡1-19)። ጌታ «ሑሩ ወመሐሩ» (ሂዱና አስተምሩ) ብሎ የተናገረውን ቃል ቸል ብለን በየአገሩ እስከ አሁን ድረስ የጠፉትን ወንድሞቻችንን ከመፈለግ ይልቅ በማኅበር ተቀምጠን መደሰት ወድደናል። በጳውሎስ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትም ያደረው መንፈስ ቅዱስ ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ እዚያ ከበዙቱ ነቢያትና መምህራን ዘንድ ሐዋርያትን ለወንጌል ሥራ ለይቶ እንዳወጣ

(የሐዋ.13፡1-4) እንዲሁ ዛሬ ወደ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መጥቶ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሚመስሉትን ብዙዎችን ሐዋርያት ለይቶ እንዲያወጣ የየዕለቱ ጸሎታችን ይሁን።

ቊ.22-29፦ የሐዋርያው አሳብ በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳይሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ስለነበረ፥ ሮሜም የሌላ ሰው መሠረት ብቻ ሳይሆን የነበሩበት ክርስቲያኖች የተማሩ በሃይማኖትም የበረቱ ስለነበሩና (ቊ.14) ሮሜ የክርስቶስ ስም በጣም የተጠራበት ስፍራ ስለ ነበረ፥ ወደዚያ ከመምጣት ተከልክሉ ሰንብቶ ነበር፥ (ም.1፡8-11)። አሁን ግን የግድ ሊመጣ ነው። «ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ እልዋሪቆን ድረስ» እየዞረ ወንጌልን ፈጽሞ ሰብኮአልና ቃል በዚያ በኩል አሁን ስፍራ የለውም። አሳቡ ወደ እስጳንያ ለመሄድ ነው፤ ወደዚያም የሚሄድ ከሆነ በሮሜ በኩል የግድ ያልፋል። ነገር ግን የግዴታ ነገር ብቻ አይደለም። ሊያያቸው ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ናፍቆአል። እስከ አሁን ድረስ ያ የሥራው አሳብ (ሕግ) ከልክሎት ነበር፥ አሁን ግን ማለፊያ ምክንያት ተገኘለት። ወደ እስጳንያ ቢሄድ መርከቡ የግድ ወደ ሮሜ ይገባልና የቆየ ናፍቆቱ ይፈጸማል፤ እርሱም ጥቂት ይጠግባቸዋል። በጕዞው ደግሞ እንዲረዱት ተስፋ ያደርጋል።

ሳይመጣ በፊት ግን ከእነርሱ ርቆ፥ ካለበት ከተማ ከቆሮንቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ነው። በሁለቱ የግሪክ አገር ጠቅላይ ግዛቶች የሚገኙ ክርስቲያኖች፥ በሰሜን በኩል ያለው የመቄዶንያና በዱቡብ በኩል ያለው የአካይያ ሰዎች፥ ገንዘብን አዋጥተው በኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች መካከል የነበሩትን ድሆች ለመርዳት አስበዋል፥ በጳውሎስም እጅ ሊልኩት ቈርጠዋል፥ (1ኛቆሮ.16፡1-9፤ 2ኛቆሮ. ም.8 እና ም.9፤ የሐዋ.24፡17፤ ገላ.2፡10)። ይህም ማሰባቸው የተገባ ነበረ፤ ለምን ቢሉ፥ አሕዛብ ከአይሁድ ዘንድ ስንትና ስንት መንፈሳዊ እርዳታ ተቀብለው ነበርና። አሁንም አሕዛብ በሥጋዊ ነገር አይሁድን ቢያገለግሉ ውለታውን መመለስ ብቻ ነው።

እንግዲያስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ ነው። ገንዘቡን አድርሶ በመስጠት የመቄዶንያንና የአካይያን ሰዎች ፍሬ በሰማይ መዝገብ አስጽፎ በስሌታቸው ካተመው በኋላ (ማቴ.6፡19-21፤ ፊልጵ.4፡14-17) ተመልሶ መጥቶ በሮሜ በኩል አልፎ ወደ እስጳንያ ይሄዳል። በመጣም ጊዜ ጥቂት ይጠግባቸዋል (ቊ24)፥ የክርስቶስንም በረከት ሙላትም ያካፍላቸዋል፥ (ቊ.29።)

ማስገንዘቢያ

1. ጳውሎስ ወደ ሮሜ በመጣ ጊዜ አመጣጡ አስቦት እንደነበር ሳይሆን እንደ እስረኛ ሆኖ ነው። ገንዘቡን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም በደኅና ደረሰ፥ እዚያ ሲደርስ ግን

በቤተ መቅደስ ተገኝቶ ተያዘና እንደ ይግባኝ ባይ ሆኖ ወደ ሮሜ ደረሰ፥ (የሐዋ. 21፡15፤17፤26-36፤ 25፡9-12።) ወደ እስጳንያ ይድረስ አይድረስ በእርግጥ አልታወቀም። በመጀመሪያ ቀጠሮው እንደተለቀቀ ታውቆአል፤ (2ኛጢሞ.4፡16-17) የሮሜው ቀሌምንጦስም ሐዋርያው በኋላ «እስከ ምሥራቅ ዳር ድረስ» እንደ ሄደ ጽፎአል። ቢሆንም፥ እርግጡ አልታወቀም።

2. ከዚህ በፊት፥ በምዕ.11 ላይ፥ ለአይሁድ ያለብንን ዕዳ አይተናል። መጽሐፍ ቅዱስን፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ እነዚህን ሁሉ ከአይሁድ ዘንድ አግኝተናል። ጳውሎስ አሕዛብ ያገለግሉአቸው ዘንድ «ይገባቸዋል» ይላል፥ (ቊ.27)። ይህ «ይገባቸዋል» የተባለው ቃል በእኛ ዘንድ ደግሞ ጉዳይ የለውምን? አለው እንጂ! ያለብን ዕዳ በእውነት ከፍ ያለ ነው። በማፍቀር፥ በመጸለይ፥ በመርዳት፥ ያን ዕዳ ለመክፈል እናስብ እንጂ አገራችን እንደ ሌሎች አንዳንድ አገሮች ሆና አይሁድን ከመጥላት ትጠንቀቅ። የአይሁድ ወዳጅ የእግዚአብሔር ተወዳጅ ነው፥ (ዘፍ.12፡3)።

ቊ. 30-33፦ ወደ ሮሜ ስለ መምጣቱ በጋለ መንፈስና አሳብ ሲናገር ቆይቶ ነበር። አሁን ግን አሳቡን ደግሞ ይመልስና በፊቱ ያለውን ነገር ይመለከተዋል። ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ ነው፥ በኢየሩሳሌም ያሉት አይሁዶች ግን ሊገድሉት ይፈልጋሉ! የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ በነበረ ጊዜ አክብረውት ነበር፤ አሁን ግን ዋና ምኞታቸው ሊያጠፉት ነው፥ (የሐዋ.9፡23፤28-29፤ 21፡22፤31፤ 22፡22፤ 23፡12-14 25፡2-3)። አሁንም ወደ መካከላቸው ሊገባ ነው!

ደግሞ ሁለተኛ አሳብ አስጨነቀው። በኢየሩሳሌም የነበሩት አይሁዳዊ ክርስቲያኖች ከአሕዛብ የመጣላቸውን እርዳታ እሺ ብለው ይቀበላሉን? እንጃ! አጠራጣሪ ነበር! ባይቀበሉትሳ? አሕዛብ በብርቱ በተቀየሙ ነበር፤ ክርስቶስ አንድ ያደረገው ደግሞ በተለያየ ነበር (ኤፌ.2፡12-19)፤ ጳውሎስም ሊያገናኛቸው የታገለው ትግል ሁሉ ከንቱ ሆኖ በቀረ ነበር።

ስለዚህ ሁሉ የሮሜ ሰዎች ይጸልዩለት ዘንድ ይለምናቸዋል። መለመኑም ብርቱ ነው። «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» ይለምናቸዋል፤ ማለት፥ የክርስቶስን ነገር እንደሚያከብሩት ያህል። ሐዋርያው ያቀደው አሳብ ሳይፈጸም የቀረ እንደሆነ የጌታ ነገር በተጐዳ ነበርና። ደግሞ «በመንፈስ ፍቅር» ይለምናቸዋል፤ እርሱም ማለት በእርሱና በእነርሱ መካከል በኖረው የፍቅር አንድነት። የሚለምናቸውም ለመጸለይ ብቻ አይደለም፥ እንዲጋደሉም ነው እንጂ። ጸሎትን መድገም ወይም ቃልን መናገር ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን እየተጋደሉ እንዲጸልዩ ነው። የሚጋደሉበት ገድል ነው፥ (ሉቃ.24፡44፤ ቈላ.1፡29፤ 2፡1)። እንግዲያስ ለሦስት ነገሮች ይጸልዩለት ዘንድ ይለምናቸዋል፦

1. በእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ወደ ሮሜ እንዲመጣና ከእነርሱ ጋር ጥቂት እንዲያርፍ፤
2. በይሁዳ ካሉት አይሁዶች ይድን ዘንድ፤
3. አገልግሎቱ ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ፤

በፊቱ ያለውን ትግል አሳምሮ ያውቃል፥ ዐውቆም ይሄዳል። ክርስቶስ በፊቱ የነበረውን እያወቀ ፊቱን እንዳቀናና ጸንቶም ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ወጣ (ሉቃ.9፡51፤ 18፡31-33፤ ማር.10፡32) እንዲሁ ተከታዩ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከመሄድ ሊቀር ይችል ነበር፥ እንደ ጌታው ግን «አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን» ብሎ ሄደ። ለመሄድ ሲል ግን «ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ እለምናችኋለሁ» ይላል። እርሱ ራሱ ወደ ግጭት ወደ ጭቅጭቅና ወደ መከራ ሊገባ ነው። ቢሆንም፥ በሰላም አምላክ እየተጽናና ለእነርሱ ሰላምን ይመኛል፥ (ቊ.33።) በጅረት እንዳለ አዝዋሪት ነው። በዙሪያው ሁሉ ሁከት ይሆናል፥ ከዚያ ከአዝዋሪት መካከለኛ ውኃ ግን የማይነቃነቅ የሰላም ቦታ አለ። በዙሪያችሁ ሁሉ ሁከት ሲሆን በሰላም አምላክ ሁኑ! ይላቸዋል።

ማስገንዘቢያ፡- ሮማውያን ለጸለዩለት ጸሎት መልስ ተገኝቶ ይሆንን? እንደተገኘ ይመስላል። ወደ ሮሜ እንዲመጣና ከእነርሱ ጋር ጥቂት እንዲያርፍ እንዲጸልዩለት ለምኖአቸው ነበር። ጸሎታቸው ተሰማ። ደረሰ፤ የሮሜ ክርስቲያኖችም ሊቀበሉት ሲወጡ ሐዋርያው እንደምን ተደስቶ ይሆን! «ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነና ልቡም ተጽናና» ይላል። ከእነርሱም ጋር ሁለት ዓመት ያህል ተቀመጠ፥ (የሐዋ.28፡15-16፤30-31)።

በይሁዳ ከነበሩት አይሁዶች ይድን ዘንድ እንዲጸልዩለት ለምኖአቸው ነበር። አይሁዶች ሁከት አንሥተው ሊገድሉት ሲፈልጉ፥ የሻለቃው ከተፍ ማለቱን አይተው ጳውሎስን ከመምታት ያስተዋቸው የሮሜ ክርስቲያኖች ጸሎት ይሆን ይሆንን? (የሐዋ.20፡30-32)። ይሆናል! በዐውሎ ነፋስ ተይዞ ይሄድበት የነበረው መርከብ ሲሰባበር፥ ጳውሎስን ያዳነውና ወደ ሮሜ በደኅና እንዲደርስ ያደረገው የሮማውያን ጸሎት ይሆንን? (የሐዋ.27፡20፤41-44)። ይሆናል!

የጸለዩ ሰዎች ባሰቡት ዓይነት አልተፈጸመም ይሆናል እንጂ ጸሎታቸው የኃይል ሥራ እንደሠራና መልስ እንዳገኘ አይጠረጠርም፥ (ኢሳ.42፡16)። እንዲሁም ደግሞ እኛ አንዱ ለአንዱ በጸሎት እንጋደል፤ መልስ ሳይመጣ ከቶ አይቀርምና።

* * *

# ምዕራፍ 16

1. በክንክራኦስ ባለች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የምትሆን እኅታችንን ፊቤንን አደራ ብያችኋለሁ፤ 2. ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሉአት፥ እርስዋ ለብዙዎች ለእኔም ለራሴ ደጋፊ ነበረችና፥ ከእናንተም በምትፈልገው በማናቸውም ነገር እርዱአት።

3. በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ 4. እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም፤ 5. በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእስያ ለክርስቶስ በኵራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ። 6. ስለ እናንተ ብዙ ለደከመች ለማርያ ሰላምታ አቅርቡልኝ። 7. በሐዋርያት መካከል ስመ ጥሩዎች ለሆኑ፥ ደግሞም ክርስቶስን በማመን ለቀደሙኝ አብረውኝም ለታሰሩ ለዘመዶቼ ለአንዲራኒቆን እና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። 8.9. በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ። በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራ ለኢሩባኖን ለምወደውም ለስንጣክን ሰላምታ አቅርቡልኝ። 10. በክርስቶስ መሆኑ ተፈትኖ ለተመሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከአርስጣባሉ ቤተ ሰዎች ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ። 11. ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከንርቀሱ ቤተ ሰዎች በጌታ ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ። 12. በጌታ ሆነው ለሚደከሙ ለፕሮፊሞናና ለጢሮፌሞሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ። በጌታ እጅግ ለደከመች ለተወደደች ለጠርሲዳ ሰላምታ አቅርቡልኝ። 13. በጌታ ሆኖ ለታወቀ ለሩፎን ለእኔና ለእርሱም እናት ሰላምታ አቅርቡልኝ። 14. ለአስቀሪጦንና ለአፍለሶንጳ ለሄርሜንም ለጳጥሮባም ለሄርማንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ። 15. ለፍሌጎንና ለዩልያ ለኔርያና ለእኅቱም ለአልንጦንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። 16. በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ። የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።

17. ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ 18. እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፥ በመልካምና በሚያቈላምጥ ንግግርም ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ። 19. መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአልና፤ እንግዲህ በእናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ። 20. የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

21. አብሮኝ የሚሠራ ጢሞቴዎስ ዘመዶቼም ሉቂዮስና ኢያሶን ሱሲጴጥሮስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።

22. ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ።

23. የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አስተናጋጅ ጋይዮስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። የከተማው መጋቢ ኤርስጦስ ወንድማችንም ቍአስጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 24. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

25.26. እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ፥ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው፥ 27. ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

* * *

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

እንግዲህ ጳውሎስ ሥራውን ፈጽሞአል። ስለ ኃጢአትና ለሁሉም ጽድቅ እንደሚያስፈልግ፥ ስለ ጽድቅ መገኘትና ስለ መቄጠሩ፥ ስለ ቅድስና፥ ስለ እስራኤል መቅረትና ስለ አሕዛብ መተከል፥ ስለ ክርስቲያንም መመላለስ፥ ሙሉ የሆነ ወንጌልን ጽፎአል። አሁንም የቀረው ሰላምታና ፊርማ ብቻ ነው። መልእክቱን ወደ ሮሜ የምታደርስለትን ፊቤን የተባለችውን ሴት እንዲረዱአት አደራ ካላቸው በኋላ (ቁ.1 እና 2) በሮሜ ለሚያውቃቸው ክርስቲያኖች የራሱን ሰላምታ ያቀርባል፥ (ቁ.3-16።) የሐሰትን ትምህርት ከሚያስተምሩ ሰዎች አስጠንቅቆ ሲያበቃ (ቁ.17-20) አብረውት በቆሮንቶስ ያሉትን ክርስቲያኖች ሰላምታቸውን ደግሞ ያቀርብና እምላክን እያመሰገነ መልእክቱን ይጨርሳል፥ (ቁ.21-24።)

<u>ቁ.1-2</u>፦ ከቆሮንቶስ ከተማ 14 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘው የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረች ፊቤን የምትባል ክርስቲያን በጉዳይ ምክንያት ወደ ሮሜ ትሄድ ነበርና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን መልእክት በእርስዋ እጅ ለመላክ አሰቦአል። ስለዚህች ሴት በሌላ ዘንድ አናነብም፥ በምን ጉዳይም እንደተያዘች አናውቅም። የሆነ ሆኖ፥ ከቆሮንቶስ እንሥታ እስከ ሮሜ ድረስ ያለውን ረጅም ጉዞ ለመሄድ ስለ ቻለችና ክርስቲያኖችን ጳውሎስንም ራሱን ለመደገፍ ስለበቃች ጨዋ ሴት መሆንዋን እንረዳለን። ወደ ሮሜ የምትሄድ ነበረችና ሐዋርያው እንደ ማስተዋወቂያ ወረቀት እንዲሆንላት እነዚህን ቍጥሮች ጽፎአል። የሮሜ ክርስቲያኖች ይህች ወደ እነርሱ ዘንድ የመጣችው ሴት መንፈሳዊ እኅትና የከበረች የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደሆነች ይወቁ። አገልጋይነቷ በምን በኩል እንደሆነ አልተጻፈም፤ ነገር ግን በሴቶች መካከል ለሴት የሚሆን መንፈሳዊ ሥራ ምን ጊዜም ቢሆን እንደማይታጣ አንዘነጋውም። የሮሜ ክርስቲያኖች ይህችን ሴት «ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ» ይቀበሉአት ዘንድ ታዝዘዋል። ምእመናን ሁሉ «ቅዱሳን» እንደሆኑ እንጂ «ቅዱሳን» የተባሉት ሌሎች እንዳልሆኑ ከዚህ በፊት በልዩ ልዩ ቦታ አይተናል፥ (ም.12፡13፤ ም.15፡25-26፤31)። ምእመናን ከሁሉ የደከሙ ምንም ቢሆኑ ሁላቸው ቅዱሳን ናቸው። «ለቅዱሳን እንደሚገባ ተቀበሉአት» ሲባል፥ ማለቱ ወይም እነርሱ ቅዱሳን ስለ ሆኑ ቅዱሳንን መስለው ጉዳይዋን እንደ ግል ጉዳያቸው እንዲመለከቱት እንጂ የዚህን ዓለም ሰዎች መስለው ቸል በማለትና ነገሩን በማዘግየት እንዳያጉላሉአት፥ ወይም እርስዋ ክርስቲያን ስለሆነች ከእግዚአብሔር ቅዱሳን አንዲቱ መሆንዋን ተረድተው ጉዳይዋን በትጋት እንዲፈጽሙላት ማለት ነው።

ማስገንዘቢያ ይህ የማስተዋወቂያ ወረቀት አሰጣጥ ጥንት የሆነ የቤተ ክርስቲያን ልምድ ነበረ፥ (2ኛቆሮ.3፡1፤ የሐዋ.28፡27፤ 2ኛቆሮ.8፡18-24፤ 3ኛዮሐ.ቊ.9-10)። ገናም በአንዳንዶች አብያተ ክርስቲያናት ይደረጋል። ሰው ከአንድ አገር ወደ ሌላ ሲዛወር፥ እንዲሁም ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ፥ ከነበረበት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የመታወቂያ ወረቀትን ተቀብሎ ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ይወስደዋል። ይህ መልካምና ጠቃሚ ልምድ ነው። የሰው ልብ እንደማይታወቅ እውነት ነው። ቢሆንም፥ ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለች እንደ ተባለ (ማቴ.7፡15-20) ሰው ከሥራው ይታወቃልና እውነተኛ ክርስቲያን ከሐሰተኛ ይለያል ይታወቃልም። ይህ የድሮ ቤተ ክርስቲያን ልማድ የሆነ የመታወቂያ ወረቀት አሰጣጥ ዛሬ ቢፈጸም ቤተ ክርስቲያን ከብዙ መታለል ከብዙም መጸጸት ትጠበቅ ነበር።

<u>ቊ.3-16</u>፦ ጳውሎስ አሁን በሮሜ ከተማ ወዳሉ ወደ ብዙ ሰዎች ዘንድ ሰላምታውን ያቀርባል። ወደ ሮሜ ከቶ ያልሄደ ሰው እንደምን አድርጎ እነዚህን ያህሉ ሰዎችን ያውቃል? ተብሎ ቢጠየቅ፥ ሮሜ የሮማዊ ግዛት ሁሉ ዋና ከተማ በመሆንዋና ጳውሎስ በዚያ ግዛት ከ20 ዓመታት በላይ እያስተማረ መመላለሱ ሲታሰብ፥ እርሱ በሮሜ 27 የሚያህሉትን ሰዎች ቢያውቅ በእውነት የሚያስደንቅ ነገር አይደለም።

በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከሚገኙት ስሞች ብዙዎች የሴቶች ስሞች ናቸው (ቊ. 3፤6፤12፤13፤15)፥ የቤተ መንግሥት ሰዎች ስሞች አሉ (ቊ.10-11)፥ የባሪያዎችም ስሞች አሉ፥ (ቊ.12።) ሰዎቹ ከልዩ ልዩ ክፍል የመጡ ናቸው፥ ነገር ግን አሁን በክርስቶስ አንድ ናቸው። በእነዚህ 14 ቊጥሮች ውስጥ «በክርስቶስ» ወይም «በጌታ» የተባለው ቃል 9 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል፥ (ቊ. 3፡7፡8፡9፡10፡11፡12፡13)። ወንጌል ለሁላቸው የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ሆኖአል፥ (ም.1፡16)። የሚበዙት ከዝቅተኛ የሰው ወገን የመጡ ናቸው፥ ይህም ከነገሩ ጋር የሚስማማ ነው፥ (1ኛቆሮ.1፡26-29)። በሮሜ ከተማና በሮማውያን ዘንድ ያልታወቁ ይሆናሉ፤ በእግዚአብሔር ግን የታወቁና የተወደዱ የእርሱ ቅዱሳን ናቸው፥ (ሚል.3፡16-17፤ ገላ.4፡9)።

ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ሁሉ በጽኑ ፍቅር ይወዳቸው ነበር። ልጆቹና ወንድሞቹ ባልንጀሮቹም ነበሩ። ሁላቸውን በልቡ ያስታውሳቸው ነበር፥ ለሁላቸው ያለማቋረጥ ይጸልይ ነበር፥ ስለ ሁላቸውም ፍቅር የሞላበትን መልካም ነገር ይናገራል። አንዱ «የምወደው» ነው፥ አንዲቱ «በጌታ የደከመች» ናት፥ አንዱም «ተፈትኖ የተመሰገነ» ነው። ሁላቸው በልቡ ይኖራሉ፥ (ፊል.1፡7)።

ማስገንዘቢያ፦ ክርስቲያን ከክርስቲያን በአስተዳደር በባህልና በአገር ልማድ ይለያይ ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ ሁሉ «በክርስቶስ» ከሆኑ አንድ ናቸው፥

(ገላ.3፡28)። የክርስቲያን አንድነት የውጭ ነገር፥ የአስተዳደር፥ የባህል፥ ወይም የሥርዓት ሳይሆን፤ የውስጥ ነገር፥ የመንፈስ ነገር፥ ነው፥ (ኤፌ.4፡5-6)። ባህልና ልማድ ምንም ቢለያያቸው «በክርስቶስ» የሆኑት አንድ ስለሆኑና ለእኛ ክርስቶስ ራሱ የተመኘው አንድነታችን ስለሆነ (ዮሐ.17፡11፤21-23)፥ «በክርስቶስ» መሆናችንን አረጋግጠን አንድነታችንን እናጠንክር እንጂ ልማድና ባህል እንዳይለያየን እንጠንቀቅ። መተባበር ኃይል ነው፥ (ፊልጵ.1፡27)።

ቍ.3-5፡- ከሮሜ ተሰድደው የነበሩት አቂላና ጵርስቅላ አሁን ወደ ሮሜ እንደተመለሱ እናያለን፥ (የሐዋ.18፡2)። ነፍሳቸውን ለሞት መቼ እንዳቀረቡ አናውቅም። ቢሆንም፥ የጳውሎስን ሕይወት ለማዳን ብለው ከዕለታት አንድ ቀን የራሳቸውን ሕይወት ለሞት አግብተው ነበር፤ ይህንም በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን በሞላ የእነርሱ ባለ ዕዳ አድርገዋት ነበር። ያደረጉትንም ነገር ሐዋርያው ከቶ አልረሳም። አሁን ከብዙ ዓመታት በኋላ ውለታውን ገና ያውቃል ገናም ይናገርበታል።

ቤታቸውን ቤተ ክርስቲያን ማድረግ የአቂላና የጵርስቅላ ልማድ ነበረ። በዚያ ዘመን በብዙ የሚቈጠሩ ክርስቲያኖች በአንድነት እንዳይሰበሰቡ በመንግሥት ተከልክሎ ነበርና በአንድ ቤት በጥቂቱ ብቻ ይሰበሰቡ ነበር። ገና ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን የሚሆን ልዩ ሕንፃዎች አልነበሩአቸውምና በግል ቤታቸው ይሰበሰቡ ነበር። አቂላና ጵርስቅላ በኤፌሶን ሳሉ እንደዚህ ያለ ቤተ ክርስቲያን በቤታቸው ነበራቸው፥ (1ኛቆሮ.16፡8፤19)። ሌሎችም ልዩ ልዩ ሰዎች እንደዚሁ ያደርጉ ነበር፥ (የሐዋ.12፡12፤ ቈላ.4፡15፤ ፊልሞ. ቍ.2)።

ይህ በጥንት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ታላቅ ሥራ የሠራው ልማድ፤ ማለት፥ ክርስቲያኖች የግል ቤታቸውን ቤተ ክርስቲያን ማድረጋቸው፤ በዛሬው ዘመናችን ደግሞ ቢደረግ ምእመናንንም ቤተ ክርስቲያንንም ያበረታ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በሌለበት ቦታ ሁሉ ክርስቲያኖች የሆኑ ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ቤታቸውን ቤተ ክርስቲያን ቢያደርጉ መልካም ነበረ። ሌላ ብዙ ሥራ ለእግዚአብሔር ልትሠራ ላልቻለች ሴት መልካም ሥራ ይኸውላት! ወንጌል እንዲሰማበትና ሰው ወደ ክርስቶስ እንዲሳብ የቤትዋን አዳራሽ ወይም ትልቁን ክፍል እሁድ እሁድ ለይታ (ቀድሳ) ቤተ ክርስቲያን ታድርገው። ሐዋርያት ያመሰገኑት ልማድ ነውና ይህን ልማድ ብንከተል ቤተ ክርስቲያን ትበረታበታለች እንጂ ትጐዳበታለች ብሎ ሊነቅፈን የሚችል የለም።

ቍ.7፡- «አብረውኝ ለታሰሩ»! ከጳውሎስ ጋር አብረው የታሰሩት ስንቶች ይሆኑ ይሆን? (ቈላ.4፡10፤ ፊልሞ. ቍ.23)። ከጳውሎስ ጋር መታሰር የክብር ማዕረግ ስንኳ ሆነ፤ ያፈረበትም ከቶ አልነበረም። ሐዋርያው ስንትና ስንት ጊዜ ታስሮአል! (2ኛቆሮ.11፡23)። እርሱም ራሱ «በእውነት በክርስቶስ ኢየሱስ

እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» ብሎ አስጠንቀቀን። እኛ ግን ለክርስቶስ ስንል መታሰርን ይቅርና መሰደብን መቼ ቻልን? እውነተኞች፥ ማለት ለክርስቶስ የተለየን፥ ክርስቲያኖች ብንሆን እንኳ የዲያብሎስ ግዛት የሆነ የዚህ ዓለም ሰው «ክርስቲያን!» ብሎ ቢሰድበን ጴጥሮስ ክርስቶስን እንደ ካደው እንዲሁ እኛ ከስድብ ለማምለጥ ብለን ባንድ አፍታ እንክደዋለን! ጴጥሮስ መቸም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ከቶ አልካደም። የካደው እርሱ ጴጥሮስ የክርስቶስ ወገን፥ «ክርስቲያን»፥ መሆኑን ነው። (ማቴ.26፡69-75)። እኛም ደግሞ በጴጥሮስ ምሳሌ የክርስቶስ ልዩ ዜጋዎች (ክርስቲያኖች) መሆናችንን ደብቀን ክርስቶስን ስንት ጊዜ ክደናል! ስለ እኛም ደግሞ «ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ደስ እያላቸው ሄዱ» እስኪባል ድረስ እግዚአብሔር አዲስን መንፈስ፥ አዲስን ድፍረት፥ አዲስንም የከብር ግምት ይስጠን፥ (የሐዋ.5፡41)።

(ቊ.13) «ለእኔና ለእርሱም እናት።» የማርቆስ ወንጌል ቃል ፍጻሜ እነሆ! (ማር.10፡29-30)። ይህች ሴት ሐዋርያውን በብዙ ተከባክበዋለችና ሐዋርያው እንደ እናት ያያታል። «ቤቶችን፥ ወንድሞችን፥ እኅቶችን፥ እናቶችን፥ ልጆችንና እርሻንም» የምናገኝ እንደዚህ ነው።

<u>ቊ.17-20</u>፡- ጳውሎስ በእውነት ነገሩን ጨርሶአል፤ ነገር ግን ልቡን የማያሳርፍ ጉና አንድ ነገር አለና ይህን ሳይናገር ለመተው አልወደደም። በእውነት የእርሱ ጉዳይ አይደለም፤ በሮሜ ያሉ ክርስቲያኖች የእርሱ አይደሉም፥ ቤተ ክርስቲያናቸውም የሌላ ሰው መሠረት ነው። ቢሆንም፥ ወሬን ሰምቶአልና እንደ ታማኝ እረኛ ሆኖ በጎቹ የትም ዘንድ ቢገኙ ተኵላ ሲመጣባቸው ቢያይ ሳያስጠነቅቃቸው ቢቀር ሕሊናው ይወቅሰዋል እና የግድ ይናገራል። ድፍረት ግን እንዳይመስልበት ነገሩን በሰላምታና በሰላምታ መካከል አሾልኮ ይጽፈዋል።

የሮሜ ሰዎች የተማሩትን የሐዋርያትን ትምህርት የሚቃወሙ ሰዎች ወደ አገሩ ገብተዋል። የገቡት የመገረዝ ወገን እንደ ሆኑ (ገላ.1፡7፤ 6፡12-13)፥ ወይም ነፃነትን አወድሰው እርከስናን ለመሥራት ያደፋፈሩት እንደሆኑ (ፊልጵ.3፡18-19፤ ቲቶ 1፡10-11፤ 2ኛጢሞ.3፡6፤ 2ኛጴጥ.2፡13-19፤ ይሁዳ ቊ.11-16)፥ ወይም ደግሞ በቈላስይስ እንደገቡ ፈላስፎች እንደ ሆኑ (ቈላ.2፡8)፥ ዛሬ አልታወቀም። የሆነ ሆኖ፥ እነዚህ ሰዎች ከክርክራቸው የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ መለያየትንና ማሰናከያን አድርገው ነበር። ሐዋርያውም «ተመልከቱአቸው!» ይላል እና «ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ!» ይላል። ፈቀቅ እንዲሉ እንጂ እንዳይከራከሩአቸው መምከሩን መገንዘብ ነው። እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የራሳቸውን ክብር ለማላቅ የራሳቸውንም ልዩ ትምህርት ለማጽናት ይፈልጋሉ እንጂ የክርስቶስን ክብር የክርስቶስንም ነገር የሚፈልጉ አይደሉም። በቃል በመከራከርም ንግግራቸውን እያቀላመጡ የዋህንን አታልለው እሺ አሰኝተው ወደ ትምህርታቸው ይማርኩአቸዋል። የሮሜ ሰዎች እምነትና መታዘዝ በዓለም ሁሉ

ተሰምቶ ነበርና (ም.1፡8) እንደ እነዚህ ይሚመስሉት ሰዎች የግድ ይሰግሉና ይቀኑባቸዋል። ወደ አገራቸው መጥተው የእነርሱን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ይመክሩአቸዋል ያባብሉአቸዋልም። ክፉን በመሥራት ግን ክፋትን ማወቅ አስፈላጊ አይደለም። ሰው ለመልካም ነገር ጥበበኛ (ዐዋቂ) ይሁን እንጂ ለክፉ ነገር የዋህ ቢሆን አያሳፍርም። ስለዚህ እነርሱ እንደሚያባብሉት ዓይነት ክፋትን በመፈተን ማወቅ አያስፈልግም። ያነሣሣቸው ሰይጣን ነውና ሰይጣን ሁልጊዜ የሚያነሣውን ክርክርና መለያየት የማይወድ የሰላም አምላክ በዘፍጥ.3፡15 እንደ ተባለው ሁሉ ሰይጣንን በፍጥነት ከእግራችን በታች ቀጥቅጦ ወደ ሰላም ይመልሰናል። እንዲህ ብሎ ሐዋርያው እንደገና ለመጨረስ አስቦ እንደገና የራሱ የሆነውን ሰላምታ ያቀርባል፥ (ቍ.20)።

ማስገንዘቢያ፡- እላይ የተጻፈው ሁሉ ለዛሬዪቱ ኢትዮጵያ እንዴት ምን ምቹ ነው! «እምነታችሁና መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአል» እንደተባለው ሁሉ የኢትዮጵያና የመንግሥትዋ ዝና ዛሬ በመላ ዓለም ተሰምቶአል። ይህም ስለ ሆነ፥ ሰዎች የግድ ይመጣሉና ወደ ኢትዮጵያ ዛሬ ከየበኩሉ ሁሉ ተሰራጭተዋል። ወደ አገሪቱ የገቡ ብዙዎች ናቸው። «እናንተ የተማራችሁትን (የሐዋርያትን) ትምህርት የሚቃወሙ፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉ» አሉ እንደተባለ በመካከላቸውም አልጠፉም። እኩሌቶቹ «ሚሲዮን» ተብለዋል፥ እኩሌቶቹም ደግሞ ሌላ የጥበብን ስም ይዘዋል። ሁሉም ክፉ አይደሉም፥ ሁሉም መልካም አይደሉም። እንደምን እንለያቸዋለን? «ሚሲዮን» የተባለው ሁሉ መቸም ከአንድ ዓይነት አይደለም። ከሚሲዮናች ብዙዎቹ እውነተኛ የሐዋርያትን ትምህርት የሚያስተምሩ ናቸው። ከዚህ ከሐዋርያት ትምህርት የወጣውን ከዚህም ትምህርት ጋር የማይስማማውን ትምህርት የሚያስተምሩ ግን ሌሎች ደግሞ አሉ። ተኵላዎች ወደ አገሩ ገብተዋል። ይህስ ከሆነ ለእኛ የሚሆን የሐዋርያው ምክር ምንድር ነው? «ተመልከቱአቸው! ከእነርሱም ዘንድ ፈቀቅ በሉ!» የሚለው ነው። ምክሩንም ብንከተል ጥበበኞች ነን! ተኵላዎች አሉና እንጠንቀቅ። የበግ ለምድ የሚለብሱ አሉ (ማቴ.7፡15)፥ እነዚህም በሚያቈላምጥ ንግግር የየዋህንን ልብ ያታልላሉ።

እላይ «እንደምን እንለያቸዋለን (እናውቃቸዋለን)?» ተብሎ ተጠይቆ ነበር። ሐዋርያው ራሱ የምንፈትንበትን ፈተና አስረድቶናል። «የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙ፥ መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉ» ብሎአል። በእነዚህ ሁለት ነገሮች ልንፈትናቸው እንችላለን። እነዚህ የገቡት ሰዎች ሐዋርያት ያላወቁትን ወይም ስንኳ ሐዋርያት የጠሉትን ትምህርት ያስተምራሉን? ያስተምሩ እንደሆነ ተኵላዎች ናቸውና ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ! ወይም ደግሞ በክርስቲያናች መካከል መለያየትንና ማሰናከያን ያደርጋሉን? ያደርጉ እንደሆነ ተኵላዎች ናቸውና ፈቀቅ በሉ! ለዚህ ሁሉ ነገር ጠቢባን እንሁን። ከተቀበልነው ከሐዋርያት ትምህርት ጋር የሚስማማ ነገር ሁሉ መልካም ነውና ለመጽናናታችን ልንቀበለው እንችላለን።

ከዚያ ትምህርት የወጣ (ያልተስማማ) ነገር ሁሉ ግን በራእይ 22፡ 18 ላይ ከተጻፈው ፍርድ በታች የወደቀ ነውና ክፉ ነው ልንቀበለውም አንችልም። የሆነ ሆኖ ግን ሐዋርያው «ተመልከቱአቸውና ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ» እንዳለ እንጂ «ከእነርሱ ጋር ተከራከሩ» እንዳላለ ልብ እናድርግ።

የሐዋርያትን ትምህርት ካላወቅን ግን እንደምን እንሆናለን? በዚያን ጊዜ እራታቸው ብቻ እንሆናለን! ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት ምን እንደሆነ ካላወቅን ልንፈትናቸው ልንለያቸውም አንችልም። እኛ ራሳችን ካልተማርን «ይህ መልካም ነው፥ ያም ክፉ ነው» ለማለት እንደምን እንችላለን? ኢትዮጵያዊ ሆይ፥ ከዚህ በአዲሱ ዘመን ሃይማኖትህን ዕወቅ! የሃይማኖት መሠረት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን በመመርመር ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት ለራስህ ለይተህ ተማር ዕወቅም! ይህን ያላደረግህ እንደሆነ ወደ አገርህ የገቡትን ተኩላዎች ለመለየትና ለመካላከል እንደምን ትችላለህ?

ይህን ብለን ስንናገር በሌሎች ላይ ፈርደን ወይም ፍቅር አጥተን አይደለም። የታመነ የቀናም እረኛ በጎችን እንደሚጠብቅ እንዲሁ ከተኩላ ማስጠንቀቃችን ነው፥ (1ኛጴጥ.5፡ 1-4፤ ሕዝ.34፡4-10)። በጎቼ ይጠንቀቁ!

ቍ.21-24፡- ሐዋርያው መልእክቱን ሲጨርስ ሳለ በክፍሉ (በቤቱ) አብረውት ምናልባት የተገኙ ጓደኞቹ ሰላምታቸውን አሁን ለሮሜ ሰዎች ያቀርባሉ። መጀመሪያው እጅግ የተወደደው የጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ ጢሞቴዎስ ነው። እርሱ ምን ጊዜም ቢሆን ከሐዋርያው እጅግ አይርቅም፥ (የሐዋ.16፡1-3፤ ፊልጵ.2፡19-23)። ከእርሱ በኋላ ከጳውሎስ ዘመዶች ሦስት ለጥቆ ጸሐፊው ጤርጥዮስ፤ በመጨረሻውም ከከተማ ከበርቴዎች ሦስት፤ ሰላምታቸውን ያቀርባሉ።

ሥራው አለቀና ጸሐፊው ሐዋርያዊ ሰላምታን ጨምሮ ብርዑን አኖረ። ጳውሎስ ግን ከልቡ ሙላት ገና የሚናገረው አንድ ነገር አለና ብርዑን አንሥቶ በገዛ እጁ የሚከተሉትን ቍጥሮች ጨመረ፥ (ቍ.25-27)።

ማስገንዘቢያ፡- «ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ።» (ቍ.22።) መልእክቱን የጻፈ እኮ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይደለምን? ነው እንጂ! ነገር ግን ከገላትያ መልእክት በስተቀር መልእክቱን ሁሉ ሲጽፍ ለጸሐፊ እየነገረ ነው ያስጻፈው። በየመልእክቱ መጨረሻ ላይ ግን እንደ ፊርማው የሚሆን ሰላምታን በገዛ እጁ ይጽፍ ነበር። (1ኛቆሮ.16፡21፤ ቈላ.4፡ 18፤ 2ኛተሰ.3፡ 17፤ ገላ.6፡ 11)። ጳውሎስ የዓይን በሽታ ያደረበት ይመስላልና ጽሕፈትን መጻፍ ስላስቸገረው ሁልጊዜ በጸሐፊ ያጽፍ ነበር፥ (ገላ. 4፡13-15፤ 6፡11)። የሮሜን መልእክት የጻፈለት የጸሐፊው ስም ጤርጥዮስ ነው።